# ማውጫ



በጥባጭ ካለ ውሀ አይጠራም
ፕ/ር መስፍን ወ/ማሪያም
4


"ድንገቴ ፖለቲከኞች" እና የዳያስፖራ ፖለቲካ
ዘሪሁን ተስፋዬ
6


ኬንያን በድርበቡጇ
አቤ ቶኪቻው
7



ዓለማየሁ ገላጋይ
3
ኢ.ህአዴግ ስንት ቦታ ሊሰነጠቅ ይችላል?

‹‹ሸራተን››ን በፀፀት
5

የኦጋዴን ነገር፦ ድርድሩ ለምን አልተሳካም?
8

የየዋሑ ሰው መልዕክት ለአቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ
17

ለምን አቶ ኃይለማርያም ፖለቲካዊ ለውጥ ማምጣት አይችሉም?
20

ቴዲ አፍሮዎችና ተመስገን ገብሬዎች
24


አኬልዳማው ፍትህ
28

## ርዕሰ አንቀፅ

# ሰንደቃችን ከአንድ ፓርቲ በላይ ነው

ሰንደቅ-አላማ በታሪክ፣ በባህል፣ በቋንቋና በብሔር የተለያዩ ሀገር ህዝቦችን በጋራ የሚያስተሳስር የህብር መገለጫ መሆኑ አጠያየቂ አይደለም። ዜጎች ምንም ያህል የኢኮኖሚና የፖለቲካ ክፍተት በመካከላቸው ቢኖርም በሀገራቸውና በሰንደቃቸው ጉዳይ ግን ተመሳሳይ አመለካከትን ማራመዳቸውም ግልጽ ነው። ከዚህ አንፃር ነው ባንዲራ የአንድ ሀገር ስዕላዊ መልክ ነው የሚባለው። የሉዓላዊነትም መገለጫ ነው። በየትኛውም የአለማችን ክፍል ላይ የሚገኙ ሀገራትም በብሄራዊ በዓላት፣ በስፖርታዊ ውድድሮች፣ በስብሰባዎች፣ በሰልፎች፣ በድርድሮችና በመሳሰሉት ኩነቶች ላይ ሰንደቅ-አላማን ወካይ አድርገው እንደብቸኛ አማራጭ ይጠቀሙበታል። ወደ ኢትዮጵያችን እና ወደሰንደቃችን  ስንመለስ ደግሞ በጉዳዩ ላይ በህዝቦች እንዲሁም በፖለቲካ ቡድኖች መካከል ጉልህ የሚባል ልዩነት እንዳለ መመልከት ይቻላል።

በታሪክ አጋጣሚ ዛሬ የኢትዮጵያ ሰንደቃላማ ተብሎ በአዋጅ የተደነገገው መለያ ቀድሞ ከምናውቀው ላይ ተጨማሪ ምልክት መለጠፉ ያለመግባባቱ መነሻ ሆኗል። ገዢው ፓርቲ ወደ ስልጣን ከወጣና የፌደራል ስርዓቱን ተግባራዊ ካደረገ በኋላ በአረንጓዴ፣ ቢጫና ቀዩ ቀለም መካከል ‹የብሔርና የብሔረሰቦች እኩልነት መገለጫ ነው› በማለት ያለ ብሔርና ብሔረሰቦቹ ፈቃደኛነት የኮከብ ምልክት በማኖሩ መነሻነት ከግራና ከቀኝ ትችቶችን ሲያስተናግድ አመታትን አሳልፏል። በአንድ በኩል ህዝባዊ ድጋፍን ከማግኘትና ፖለቲካዊ ጥቅም ከመሰብሰብ አንፃር ሰንደቁን መለወጥ ለመንግስት ኪሳራ መሆኑን የሚገልፁ ቡድኖች ሲኖሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በባንዲራው ላይ የሰፈረው ምልክት ከብሔራዊ አንድነት ይልቅ ለብሔረሰባዊ ልዩነቶች ቅድሚያ የሚሰጥ አድርገው የሚወስዱት አሉ። ለዚህም እንደምክንያት የሚቀርበው በየትም ሀገር ላይ መንግስታት ቢቀያየሩ እንኳን በሰንደቅ-ዓላማ ላይ ለውጥ እንደማይኖር የሚታወቅ መሆኑ ነው። በእርግጥ በጥቂት ሀገራት በጉልበት ስልጣን ላይ የወጡ መሪዎች ሰንደቁን ወይ ለመቀየር አሊያም የራሳቸውን ርዕዮተ ዓለም የሚያንፀባርቅ ምልክት የለጠፉ ቢኖሩ እንኳን ከስልጣናቸው በተነሱ ጊዜ ሰንደቁም ወደነበረበት እንደሚመለስ የጋዳፊን መንግስት እንደማሳያ አድርገን ልንወስድ እንችላለን።

በመንግስት በኩል ግልፅ በሆነ መንገድ የባንዲራን ክብር በሚነካ መልኩ አስተያየቶች ተሰንዝረው እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝብታችን ነው። ‹‹ባንዲራ ጨርቅ ነው›› የሚለው ሀሳብ ከሀገሪቱ የመጨረሻ ሰው መሰማቱ ብዙዎችን በእርሳቸው ላይ ከመጀመሪያው የነበራቸውን የብሄራዊ ስሜት ጥርጣሬ የበለጠ እንዲሰፋ አድርጎትም ነበር። ለሀገራቸውና ለሰንደቅ-ዓላማዋ ግድ የማይሰጣቸው ግለሰብ በሀገር መሪነት መቀመጣቸው ለብዙዎች አንገት የሚያስደፋ እንደሆነም ሲነገር ቆይቷል። ከቅርብ አመታት ወዲህ ግን ተወርውሮ የነበረው ባንዲራ ክብር አግኝቶ በየዓመቱ ቀን ተቆርጦለት ሲከበር እያየን ነው። መከበሩ በጎ ሆኖ ሳለ ከላይ የጠቀስናቸው ሰንደቅ-ዓላማው ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶች ግን እየተበራከቱ እንጂ ሲቀንሱ አልታየም። ከዚህ ባለፈም የዘንድሮ የባንዲራ ቀንን ‹‹የመለስ ራዕይን ለማሳካት›› በሚል መፈክር ስር መዋሉ ሌሎችን የተቃርኖ ቡድኖችን የሚያገል ለመሆኑ ሌላ ማሳያ ሆኖ አልፏል።

በመሆኑም አዲስ-ታይምስ የእስከዛሬውና ከዚህ በፊት የነበሩትን ትችቶች መንግስት አጢኖ አሳማኝ በሆነ መልኩ ዘለቄታዊ መፍትሔ እንዲያመጣ ስትል ታሳስባለች። ሰንደቅ-ዓላማችን በሌሎች ሳይሆን በገዛ ዜጎቻችን መካከል የሀሳብ ልዩነት ከመፍጠሩም አልፎ የባለቤትነት ስሜት የማይሰማቸው ቡድኖች ትልቅ የመከራከሪያ ሀሳብ እስኪሆን ድረስ እያየን ዝም ማለት አንችልም። ከዚህ በተጨማሪም መንግስትን ከሚወክሉ ግለሰቦችና መሪዎች በማይጠበቅ መልኩ ክብር ለተነሳው ባንዲራ በሀገር አቀፍ ደረጃ፤ መንግስት ህዝብን ይቅርታ ይጠይቅ ዘንድ እናሳስባለን። ባንዲራ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚመለከተውና የሚገባው ሆኖ ሳለ ‹‹በመለስ ራዕይ›› ስም የአንድ ፓርቲ ወኪል መሆኑንም አጥብቀን እንቃወማለን።

# የህዝበ-ሙስሊሙ ጥያቄ በሰላማዊ መንገድ ይፈታ!

ሃይማኖታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ችግሮች ሲከሰቱ ሃይማኖታዊ ወይም መንፈሳዊ የሆኑ መፍትሔ ማፈላለግ ብቸኛው አማራጭ ነው፡፡ በእምነት ተቋማት ውስጥ ለሚነሱ ጥያቄዎች ፖለቲካዊ መልስ መፈለግ ችግሩን ከማስፋፋትና ወደ አላስፈላጊ ውዝግቦች ከመክተት ውጪ የሚፈጥረው በጎ ለውጥ አይኖርም፡፡ የቤተ-ክርስቲያን አለመግባባቶችን ቤተ-መንግስት ለማረቅ ሲሞክር ምን ይፈጠር እንደነበር ታሪክ ደጋግሞ አሳይቶናል። መንግስታዊ ጣልቃ ገብነቶች ከእለት ወደ እለት እየገዘፉና እየጠነከሩ ሲመጡ የችግሮች ስር መስደድም የዚያኑ ያህል እየከፋ ይመጣሉ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በእስልምና እምነት ላይ እየተደረገ ያለው መንግስታዊ ጣልቃ ገብነት በሀገሪቱ ህገ-መንግስት ላይ የተገለፀውን ‹‹መንግስትና ሀይማኖት መለያየታቸውን›› የሚጥስ በመሆኑ አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ ይወሰድ ዘንድ አጥብቀን እንጠይቃለን። በሀይማኖት ጉዳይ መንግስት ጣልቃ መግባቱን አዲስ ታይምስ ህገወጥነት መሆኑንም ታምናለች።

ላለፉት አስር ወራት ሳያቋርጥ እስከዛሬ የቀጠለው የሙስሊም ወገኖቻችን ጥያቄ እልባት አለማግኘቱ ሁላችንንም ያሳስበናል። በአወሊያ መጅሊሱ እንዲወርድ ሲባል የተጀመረው ሰላማዊ አቀራረብ አሁን ከአዲስ አበባም አልፎ ወደሌሎች ክፍለ ሀገራት ደርሶ መሳሪያ አማዟል፡፡ በዚህም ሊያበቃ እንደማይችልም ሁኔታዎችን ተመልክቶ መገመት ይቻላል። ፖለቲካዊ ማንነት ባላቸው ግለሰቦችና ካድሬዎች ቤተ-እምነቶችን መምራት የኋላ ኋላ ይዞ የሚመጣው መዘዝ ሀገራዊ ቀውስ ነው።

ለተቃውሞ የወጣውን ህዝበ ሙስሊም ሰለፊ በሚል ቅፅል መጠሪያ ስም በመስጠት ዓላማቸውንም ከሽብር ጋር በማያያዝ መፈረጅ ሁኔታውን ከማባባስ ውጪ ዘላቂ መፍትሄ ሊያመጣ አይችልም። የዚህ ተራዛሚ ተፅዕኖ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞችን በዓለም አቀፉ የፖለቲካ ስርዓትም ሆነ በአፍሪካ ቀንድ ሰላም ላይ ዋነኛ ተግዳሮት ሆነ ወደመጣው ጽንፈኛ ፖለቲካ እስልምና ሊሰፋ ይችላል። ሙስሊም ወንድሞቻችን ጥያቄያቸውን ህገ-መንግስቱ በፈቀደላቸው በሰላማዊ እና ህጋዊ መንገድ እስካቀረቡ ድረስ መንግስት አግባብ ያለውን መፍትሄ ሊሰጣቸው ይገባል። የሃይማኖቶች ነፃነትን በዚህ አካሄድ እየጨፈለቁ መሄድ ትርፉ ስርዓታዊ ኪሳራ ብቻ ነው። የሃይማኖቱ ተከታዮች ይወክሉናል ብለው የመረጧቸውን የአመራር አባላትንም ሆነ ምዕመኑን ማሰርና ማንገላታት በሀገሪቱ ውስጥ ህገ-መንግስታዊነት እና የህግ የበላይነት ያለመኖሩ ማሳያ ነውና ይኼም በአስቸኳይ ይቆም ዘንድ እንጠይቃለን፡፡ ስለዚህም መጽሔታችን የህዝበ-ሙስሊሙን መሰረታዊ የተቋማዊ ነጻነት ጥያቄ መንግስት በአፋጣኝ ይመልስ ዘንድ ትጠይቃለች።

## አዲስ ታይምስ

*ሃገራዊ፣ ማኅበራዊ፣*
*ኢኮኖሚያዊና*
*ኪነ ጥበባዊ ጉዳዮች ላይ*
*የምታተኩር መጽሔት*

**አሳታሚ:-**
አዱ ህትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር:-**
ተመስገን ደሳለኝ

**ም/ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ሙሉነህ አያሌው

**ስራአስኪያጅ**
ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

**ዋና አዘጋጅ:-**
ዳዊት ታደሰ
አድራሻ አቃ/ቃ/ክ/ከተማ
ወረዳ 8
የቤት ቁጥር 003
E-mail addistimes2005@gmail.com

**ሪፖርተሮች**
ሚካኤል ዲኖ
ሰውአለም ታዬ

**አምደኞች**
ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም
ዶ/ር በድሉ ዋቅጅራ
ዓለማየሁ ገላጋይ
ብርሃኑ ደቦጭ
ኤፍሬም ስዩም
እንዳለጌታ ከበደ
ጌታቸው ታምራት
ዳንኤል ተፈራ
ታዲዮስ ታንቱ
ዘሪሁን ተስፋዬ
አቻምየለህ ታምሩ እውነቱ

**ፀሀፊ**
ቤቴልሄም አመነሸዋ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ:-**
አራዳ ክ/ከተማ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር አዲስ
ስልክ ቁጥር
+251 922 87 19 37
+251 911 55 49 01
E-mail addistimes2005@gmail.com
www.fetehe.com

# ኢህአዴግ
## ስንት ቦታ ሊሰነጠቅ ይችላል?



ተመስገን ደሳለኝ

ብርዱ የጥቅምት ነው፤ አጥንት ድረስ ዘልቆ የሚያንቀጠቅጥ ኃይለኛ ቅዝቃዜ፡፡ አዲስ አበባ ገና ከእንቅልፏ በመንቃት ላይ ነች፡፡ ለስራ የቸኮሉ መንገደኞች ትራንስፖርት ፍለጋ ወዲያ ወዲህ ይካለባሉ፡፡ ማክሰኞ ጥቅምት 7 ቀን 2005 ዓ.ም. ከጠዋቱ 12 ሰዓት ከ50 ደቂቃ ላይ ብስራተ ገብርኤል አደባባይ ‹‹መገናኛ ራዲዮ›› በያዙ የትራፊክ ፖሊስ አባላት በቁጥጥር ስር ዋለ፡፡ የትራፊክ ፖሊሶቹ ስራ የበዛባቸው ይመስላሉ፡፡ 12 ሰዓት ከ55 ደቂቃ ሲል በሁለት የሞተር ብስክሌት በተፈናጠጡ የትራፊክ ፖሊሶች ፊት አውራሪነት አንዲት ሳይረን የተገጠመላት የፖሊስ ታርጋ የለጠፈች መኪና የ‹‹መንገድ ልቀቁልኝ›› ጩኸቷን እያንባረቀች አቋርጣ በማለፍ ወደ ሳር ቤት አቅጣጫ ከነፈች፡፡ ሶስት ‹‹ቪኤት›› መኪና ሰለሱ፡፡ ሌላ ባለሳይረን መኪናም ከኋላ እየተከተለች ነው፡፡ ሁሉም መኪኖች በከባድ ፍጥነት ነው የሚበሩት፡፡ ሳር ቤት ያለው የፑሽኪን አደባባይም ተመሳሳይ ቁጥር ባላቸው የትራፊክ ፖሊሶች ተጨናንቋል፡፡ ሜክሲኮ አደባባይ፣ አምባሳደር፣ ፍልውሃ፣ ገብርኤል መሳለሚያ… ቤተ-መንግስቱ የአጀቡ መድረሻ ቦታ ነው፡፡

አጀቡ አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝን ከመኖሪያ ቤታቸው ወደ ስራ ቦታቸው ለማድረስ ነው፡፡ ይኸው ትዕይንት ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ላይ ይደገማል፡፡ ቅደም ተከተሉ ተገልብጦ፤ ከቤተ-መንግስት… ብስራተ ገብርኤል፤ የአደጋ ማስጠንቀቂያ ድምጽ፡፡

ሀገሪቱ በማን ነው የምትመራው?

ጠቅላይ ሚኒስትር ኃ/ማርያም ደሳለኝ በየትኛውም ሀገር ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ ለሰላሳ አንድ ቀናት ከመኖሪያ ቤታቸው ወደ ቤተ-መንግስት፤ ከቤተ-መንግስት ወደ መኖሪያ ቤታቸው እየተመላለሱ ለመስራት ተገደው መቆየታቸው የሀገር ውስጥንም ሆነ የአለም አቀፉን ሚዲያ ትኩረት የሳበ ጉዳይ ሆኖ አልፏል፡፡ የዓለም አቀፍ የሚዲያ ተቋማት ይህንን ጉዳይ አጀንዳ ከማድረጉም በላይ የናይጄሪያ ቴሌቪዥን ‹‹ቤተ-መንግስቱን ልቀቂ-አለቅም›› በሚለው የሀገራችን ፖለቲካዊ ድራማ ላይ በማፌዝ አንድ ፕሮግራም እስከማስተላለፍ ደርሷል፡፡ አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ለዚህ አይነት እንግልት የተዳረጉት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ባለቤት ወ/ሮ አዜብ መስፍን ቤተ-መንግስቱ ውስጥ የሚገኘውን የጠቅላይ ሚንስትር መኖሪያ ቤት ለመልቀቅ ፍቃደኛ ሆነው ባለመገኘታቸው ነው፡፡ የሴቲቱ መከራከሪያ ሃሳብ ‹‹በቅያሬ ሊሰጠኝ የታሰበው ቤት ለደህንነቴ ያሰጋል›› የሚል ነበር፡፡ በእርግጥ ይህ መከራከሪያ ውሃ አያነሳም፡፡ በየትኛውም መመዘኛ ቢታይም ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ምን አልባት ይህ መከራከሪያ አግባብ ሊሆን ይችል የነበረው ‹‹ለቅያሪ የተሰጠኝ ቤት ለደህንነቴ ስለሚያሰጋ አስተማማኝ ቤት ይፈለግልኝ›› ብለው ለሚመለከተው ክፍል በአቤቱታ መልክ ቢያቀርቡ ነበር፡፡ በተቀረ እንዲህ እንደሰማነው ‹‹ግዛቴን አልለቅም!›› ብሎ ማመፁ የፓርቲያቸው ጤና መታወክን ነው ሊያመላክት የሚችለው፡፡ አሊያም የአዜብን መከራከሪያ ሌሎች የግንባሩ የአመራር አባላቶች ደፍረው ሊነግሩን ያልሞከሩትን በስርዓቱ ላይ የተከሰተውን የ‹‹ማዕከላዊ አስተዳደር›› ድክመት ወይም በሌላ አማርኛ በኢህአዴግ ውስጥ መከፋፈል ስለመፈጠሩ በገደምዳሜ መልዕክት እያስተላለፈ ነው ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡ ምክንያቱም በዚህ ጉዳይ ላይ ሙግት የሚያነሱ ሰዎች የስነ-ሀሳብ ክርክራቸው የሚያርፈው በሁለት ጥያቄዎች ላይ ነውና፡፡ በአሁኑ ወቅት ለሀገሪቱ ወሳኝ የሆነው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ደህንነት ነው? ወይስ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ባለቤት ደህንነት? የእነዚህ ጥያቄዎች መልስም የሀገሪቱን መረጋጋት ወይም የሹመቱን ‹‹ስማዊነት›› ይነግሩናል፡፡

አይበለውና! ጠንካራ ጥበቃ ከሚደረግለት ‹‹የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚንስትር መኖሪያ ቤት›› ውጪ ለተጠቀሱት ቀናት ያህል ለመኖር የተገደዱት ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማሪያም ከቤት ወደ ቢሮ ሲሄዱ፣ አሊያም ከቢሮ ወደ ቤት ሲመለሱ በ1987 ዓ.ም በሆስኒ ሙባረክ ላይ የተሞከረው ግድያ አይነት አደጋ ቢያጋጥማቸው ኖሮ ኃላፊነቱን የሚወስደው ማን ነበር? አደጋውን ተከትሎ የሚፈጠሩ ቀውሶችስ ምን ሊያስከትሉ ይችሉ ነበር? ይህንን ችግር በህግ አግባብ መፍታት የነበረበትስ ማነው? የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ወይስ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀርባ ባለው ወንበር ላይ የተቀመጡ ‹‹ኃያላኑ›› አንጋፋ ታጋዮች?

በእነዛ ሁሉ ቀናት በቤተ-መንግስቱ ለጥበቃ ስራ የተመደበው እስከ አፍንጫው የታጠቀ ሰራዊት ታዛዥነቱ ለማን ነበር? እንደፋብሪካ ወዛደር በሰዓት ገብተው በሰዓት ለሚወጡት ጠቅላይ ሚኒስትር? ወይስ በውሎና በአዳራቸው ከሰራዊቱ ለማይለዩት አዜብ መስፍን?… አሁንም አይበለውና! ሴቲቱ ለሃያ አንድ አመታት የቀኝ እጃቸው ሆኖ የቆየውን ሰራዊት ‹‹በለው በለውና፣ አሳጣው መድረሻ!›› የሚል ቀጭን ትዕዛዝ ቢያስተላልፉለት ኖሮ ምንድር ነበር የሚከተለው? ደህና! ከእነዚህ ሁኔታዎች ተነስቶም ሀገሪቱ የምትመራው በማን ነው? ቃለ-መሀላ ፈፅመው ስልጣን በያዙት ኃይለማርያም ደሳለኝ ወይስ የህወሓት/ኢህአዴግ የአመራር አባልና የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ባለቤት በሆኑት አዜብ መስፍን? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ በእርግጥ የዚህን መልስ ለማግኘት ጥቂት ጊዜ መታገስን ይጠይቃል፡፡

በኢትዮጵያ መንግስት ከወዴት አለ?

የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር በሀገሪቱ ላይ ‹‹ወጥ አምባገነናዊ ስርዓት›› አስፍነው የነበረ ቢሆንም በዘመነ መንግስታቸው ቢያንስ ማዕከላዊ መንግስት እና የስልጣን ተዋረዱን የጠበቁ የተለያዩ ተቋማት (ምንም እንኳን ተጠሪነታቸው ከህገ-መንግስቱ እና ከተቋቋሙበት አዋጆች ይልቅ ለእርሳቸው ቢሆንም) በመኖራቸው ‹‹መንግስት›› ተብሎ ሊጠራ የሚችል አስተዳደር መኖሩ ላይ የሚነሳ ጥያቄ አልነበረም፡፡


ነገር ግን የፓርቲ እና የመንግስትን ስልጣን ጠቅልለው ይዘው የነበሩት የአቶ መለስ ህይወት ማለፍን ተከትሎ ‹‹ማዕከላዊ መንግስት›› እየተዳከመ እንደሆነ ወይም ኢህአዴግ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊሰነጠቅ እንደሚችል ፍንጮች እየታዩ ነው፡፡ የዚህ ምክንያት ደግሞ በራሱ በድርጅቱ ውስጥ የተለያየ ፍላጎት ያላቸው ቡድኖች የተለያየ ሃሳብ ይዘው ማቆጥቆጣቸው ነው፡፡ በእርግጥ በአምባገነናዊ ስርዓት ውስጥ እንዲህ ዓይነት የስልጣን ክፍተት (Power Vacuum) በሚኖርበት ጊዜ የተለያዩ ቡድኖች መፈጠራቸው የሚጠበቅ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የተከሰተውም ይኸው ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ሚዲያውን የያዘው ቡድን ማዕከላዊ መንግስት ጠንካራ ለመሆኑ ምስክር የሚመስሉ እርምጃዎችን ወስዷል (አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር መምረጥ፣ ለከፍተኛ የጦር መኮንኖች ሹመት መስጠት፣ አምባሳደሮችን መመደብ፣ ሽግሽጉን ተከትሎ የተፈጠረውን ክፍተት መሙላት ለምሳሌ፡- ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርን መምረጥ) ይህ ኃይል በዚህ እርምጃው መለስ ቢሞቱም መንግስት በነበረበት የሚቀጥል እንዲመስል ማድረግ ችሎ ነበር፡፡

በአናቱም የአቶ መለስ ህይወት ማለፍ በይፋ ከመነገሩ ጥቂት ቀናት አስቀድሞ የስርዓቱ ‹‹መፈንሳዊ አባት›› እንደሆኑ የሚነገርላቸው አቦይ ስብሓት ነጋ አቶ መለስ አንድ ሰው መሆናቸውን፣ የእሳቸው ማለፍም የሚያመጣው ነገር ያለመኖሩን ለመግለፅ ‹‹መለስ መጣ፣ መለስ ሄደ፤ ፋጡማ መጣች፣ ፋጡማ ሄደች፤ በቀለ መጣ፣ በቀለ ሄደ…›› ሲሉ ለአሜሪካ ድምጽ የሰጡት ቃለ መጠይቅም ይህንኑ የሚያጠናክር ነበረ፡፡ ነገር ግን የአቶ መለስን ማለፍ መንግስት ይፋ ካደረገ በኋላ የተከተሉት ነገሮች መለስ ለኢህአዴግ መራሹ መንግስት እንደ አንድ መሪ (ግለሰብ) ብቻ እንደማይታዩ የሚያረጋግጥ ሆኖ አልፏል፡፡ መለስ ለሀገሪቱ ሁሉም ነገር መሆናቸውን በመንግስት መገናኛ ብዙሃን ለበርካታ ቀናት ደጋግመው የነገሩን ጓዶቻቸው ራሳቸው ናቸው፡፡ በሚቀጥሉት አስር እና ሃያ አመታትም ሀገሪቱ የምትመራው በመለስ ራዕይ እንጂ ከአለም አቀፍ ነባራዊ ጉዳዮች እና ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር እየተገናዘበ በሚቀረፅ ፖሊሲ እና በሚነደፍ እቅድ እንዳልሆነም ጨምረው ነግረውናል፡፡ መቼም ይህ ፕሮፓጋንዳ ሲፋቅ የሚገኘው እውነት ‹‹ለመጪዎቹ አስርና ሃያ ዓመታት ኢህአዴግ በመለስ ራዕይ ሳይበታተን በስልጣኑ ይቀጥላል›› የሚል ሊሆን ይችላል፡፡

በአጠቃላይ ግን በሀገሪቱ ላይ ኃላፊነት የሚወስድ ማዕከላዊ መንግስት ያለመኖሩን የሚያሳየን ወይም ለክርክር የሚጋብዘን፤ አዲስ የተመረጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ‹‹ጥርስ የሌለው አንበሳ›› ተደርገው መሰራታቸው ነው፡፡ በእርግጥም ኃይለማርያም ደሳለኝ ከዚህ ቀደም የደኢህዴን የአመራር አባላትን ያለፓርቲው ውሳኔ ከኃላፊነታቸው ሲያነሱ ‹‹ከበላይ ታዝዤ ነው›› ይሉ በነበረበት መንፈስ ውስጥ ለመሆናቸው ዋነኛ ማሳያ ከሆኑት አጋጣሚዎች አንዱ ወ/ሮ አዜብ ከህግ ይልቅ ፖለቲካዊ ጉልበትን ሲጠቀሙ የፈየዱት ነገር አለመኖሩ ነው፡፡ (በነገራችን ላይ ምክትል ጠ/ሚንስትሩም መወሰን ያለባቸውን ጉዳዮች ከመወሰናቸው በፊት ‹‹አቶ አዲሱን ላማክር›› የሚል ነገር ያበዛሉ ሲሉ በቅርበት የሚያውቋቸው ይተቿቸዋል) በእርግጥ አዜብ ቤተ-መንግስቱን አልለቅም ማለታቸው ያሳጣው መንግስትን ብቻ አይደለም፤

ወደ ገፅ 30 ዞሯል

# በጥባጭ ካለ ውሀ አይጠራም



ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም

> ሽብርተኛነት የሚሆነው አትጫኑብኝ እያለ በሰላማዊ መንገድ የሚጮኸውን ሰው መደብደብ፣ ማሰርና መግደል ነው፤ ሽብርተኛነት የሚሆነው የሰዎችን ቅዱስ ቦታ በጥይትና በደም ማርከስ ነው፤ ሽብርተኛነት የሚገለጠው ሰላሜን ጠብቁልኝ እያለ በሚጮኸው ሰው ሳይሆን በጉልበቱ ብቻ ተማምኖ ሰላምን በሚያደፈርሰው ነው

ዱሮ፣ ዱሮ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የሚባል ከፍተኛ ትምህርት ቤት ነበረ፤ ጥቂት ቆይቶ በክብር ዘበኛ የስዒረ መንግሥት ሙከራ ግርግር የተነሣ ብዙ መኳንንቶች በአጼ ኃይለ ሥላሴ ግቢ ተገደሉና የራስ መኮንን ንብረት የሆነው ግቢ ለአጼ ኃይለ ሥላሴና ቤተሰቦቻቸው መኖሪያ ሊሆን አልቻለም፤ ስለዚህም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ከአባታቸው የወረሱትን ግቢ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ ሰጡ፤ ስለዚህም ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲን ወለደ፤ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የሳይንስ ትምህርት ብቻ የሚሰጥበት ሆነ፤ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅም ሆነ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ የነጻነት ግቢዎች ነበሩ፤ አስተማሪዎቹም ሆኑ ተማሪዎቹ በሙሉ ነፃነት ሀሳባቸውን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ይገልጹ ነበር፤ ዛሬ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅና ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በሞቱ በሠላሳ ስምንት ዓመታቸው ላነሣቸው የፈለግሁበት ምክንያት እሱም የሞተውን የቀድሞ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበርን ለማንሣት ስል ነው።

የቀድሞ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር ጠንካራ ድርጅት ነበር -- እስቲሞት ድረስ፤ አንድ ሰሞን ማኅበሩ በተከታታይ የተለያዩ ታላላቅ ባለሥልጣናትን እየጋበዘ እንዲናገሩ ካደረገ በኋላ በጥያቄዎች ያጣድፋቸው ነበር፤ አንድ ቀን ባለሥልጣኖቹ ተናግረው ሲጨርሱ አንድ በጣም ጎበዝ የሂሳብ አስተማሪ የነበረ የወለጋ ልጅ ተነሥቶ በኢትዮጵያ አሉ የሚላቸውን ችግሮች ከተናገረ በኋላ በአገራችን አንድ አባባል አለ፣ ውሀ ካልተበጠበጠ አይጠራም፤ ይባላል፤ ስለዚህ የኢትዮጵያ ሁኔታ ትንሽ መበጥበጥ ያሻዋል፤ ብሎ ተናገረ፤ (ዛሬ ቢሆን አንጠልጥለው ወስደው በሽብርተኛነት ያስፈርዱበት ነበር!) ሰብሳቢው ደጃዝማች ከበደ ተሰማ እንዲመልሱ ጠየቃቸው፤ ደጃዝማቹ እናንተ የተማራችሁ ናችሁ፤ እኔ መሀይም ነኝ፤ ስለጠየቃችሁኝ አክብሬአችሁ መጣሁ እንጂ እኔ ለእናንተ የምነግረው ነገር የለኝም በማለት ጀመሩና፣ እውነት ነው ውሀ ካልተበጠበጠ አይጠራም ይባላል፤ ግን ሌላም አባባል አለ፤ በጥባጭ ካለ ውሀ አይጠራም ይባላል፤ ሲሉ ቤቱ በሳቅ ተናጋ።

ለእኔ እንደገባኝ እስላሞች የሚሉት አንደኛ የማናውቀውንና የማንፈልገውን ልዩ እምነት አትጫኑብን፤ ሁለተኛ የራሳችንን የእስልምና ካህናት እኛው እንምረጥ፤ ሦስተኛ ምርጫችንን የምናካሂደው በየቀበሌዎች ሳይሆን በመስጊዶቻችን ይሁን የሚል ነው፤ እግዚአብሔር ያሳያችሁ አሁን እነዚህ ጥያቄዎች እንኳን አዋቂዎችንና (ዕድሜያቸው ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን የደረሰ ማለቴ ነው) ልጆችን የሚያጣሉ ናቸው?

ክፉዎች ግን እንደሚንቀሳቀስ ባሕር ናቸው፤ ጸጥ ይል ዘንድ አይችልምና፣ ውሆቹም ጭቃና ጉድፍ ያወጣሉና፤ ለክፉዎች ሰላም የላቸውም፤ ይላል አምላኬ (ኢሳይያስ 57/20-21)።

በእስላሞች ላይ የሚፈጸመውን ስከታተለው በጥባጭ ያለ ይመስለኛል፤ ለዘመናት ተበጣብጦ፣ ተደባልቆ በስምምነትና በሰላም አብሮ የሚኖረውን እስላምና ክርስቲያን ለማበጣበጥ የተጀመረው ዘመቻ ዓላማው ኢትዮጵያንም፣ የኢትዮጵያን ሕዝብም፣ ገዢዎቹንም ቢሆን የሚጠቅም አይሆንም፤ ሃይማኖት ከአንድ አገር ማኅበረሰብ አጥር ይወጣል፤ ወደሰማይ አውጥቶ ከአምላክ ጋር ያገናኛል፤ ከአምላክ ጋር አገናኝቶ የአምላክን ሰማያዊ ኃይል ያጎናጽፋል፤ በዚህም ምክንያት ዓለማዊ ኃይልን ያስንቃል፤ የሥጋን ውሱንነትና ሟችነት አልፎ የነፍስን ሕያውነት ያስይዛል፤ በዚህም ምክንያት ስቃይንና መከራን የመቋቋም ልዩ አቅምን ያስገኛል፤ የክርስቲያንና የእስልምና ሃይማኖቶች ዓለምን በሙሉ ያዳረሱት በመንፈሳዊ ኃይላቸው ነው።

ሃይማኖት ከማኅበረሰብ አጥር ሲወጣ የሚሄደው ወደሰማይ ብቻ አይደለም፤ ወደጎንም ይሄዳል፤ ወደሰማይ ሲሄድ ከአምላክ ጋር የሚያጋጨውን ያህል ወደጎን ሲሄድ ደግሞ ከሌሎች ሰዎች ጋር ያጋጫል፤ ከአምላክ ጋር መጋጨት ትርፉ መዓት ነው፤ ከሰዎች ጋር መጋጨት ትርፉ ጥላቻ ነው።

አሸባሪዎች የሚሆኑት ሁሉ መንፈሳዊ ኃይላቸው ተሟጥጦ ነፍሳቸውን የሰይጣን ማኅደር ማድረግ ሲጀምሩ ነው፤ ይህንንም የሚያደርጉት በጉልበተኞችና በጨቋኞች ገገሮቻቸው እየተገደዱ ነው፤ በገገሮቹ ላይ የሰፈረው የሚያበጣብጥ ሰይጣን በተጨቋኞቹም ላይ ይሰፍራል፤ ስለዚህም ሽብርተኞችን የሚፈለፍሉትና እየኮተኮቱ የሚያሳድጉአቸው ሰይጣን የሰፈረባቸው ጨቋኞች ናቸው።

ሕጋዊ መብትን በግልም ሆነ በኅብረት መጠየቅ ሽብርተኛ አያደርግም፤ ሽብርተኛ የሚያደርገው መብታቸውን የሚጠይቁትን መግደል፣ መደብደብና ማሰር ነው፤ ዓለማዊውን ሥርዓት የማይነካውን፣ ከአምላኬ ጋር ግንኙነት ለመፍጠር የመረጥሁትን መንገድ አክብሩልኝ፤ በሌላ መንገድ ወደአምላኬ እንድሄድ አታስገድዱኝ ማለት ሽብርተኛነት አይደለም፤ ሽብርተኛነት የሚሆነው በሰዎች ላይ ባዕድ የሚሉትን እምነት መጫን ነው፤ ሽብርተኛነት የሚሆነው አትጫኑብኝ እያለ በሰላማዊ መንገድ የሚጮኸውን ሰው መደብደብ፣ ማሰርና መግደል ነው፤ ሽብርተኛነት የሚሆነው የሰዎችን ቅዱስ ቦታ በጥይትና በደም ማርከስ ነው፤ ሽብርተኛነት የሚገለጠው ሰላሜን ጠብቁልኝ እያለ በሚጮኸው ሰው ሳይሆን በጉልበቱ ብቻ ተማምኖ ሰላምን በሚያደፈርሰው ነው፤ ሕዝብ ሰላምን ሲያገኝ ይሠራል፤ ያመርታል፤ ኑሮውን ያሻሽላል፤ ይዝናናል፤ ይህ ሁሉ ጥጋብን ያመጣል፤ ሲጠግብ የሚያስቸግረውን እንዳይጠግብ መበጥበጥ የሚፈልጉ አይጠፉም።

ጮሌነት ዕድሜ አለው፤ የጮሌነት ዕድሜ በጣም አጭር ነው፤ ነገር ግን ጠንቁ ከነኮተቱ በልጅ ላይ ያርፋል፤ የጮሌው ኃጢአት ልጁን አዋርዶ ያቃጥላል፤ ማንም ለማንም የሚመኘው መንገድ አይደለም።



# ‹‹ሸራተን››ን - በፀፀት

ዓለማየሁ ገላጋይ

እንደመነሻ፡-

ወደኋላ ሳንጉዛችሁ…

…ከዚህ በፊት ሰማዕትነትን በወረሰችው ‹‹ፍትህ›› ጋዜጣ ላይ ያቀረብኩት አንድ ፅሁፍ ለዛሬው ወጋችን መነሻ ሆኖኛል፡፡ ‹‹የቂሳሩ ሽክምና የዘመኑ ዘለሰኛ›› በሚል ርዕስ አቅርቤው የነበረው ፅሁፍ በዚያው ሰሞን እኔን ወደመርካቶ መሸኙቱ እዚህ እንድጠቁመው ግድ ብሎኛል፡፡ ያኔ ጫማ ሳስጠርግ አንድ አዛውንት መጥተው ትንሽ ሴንጢ እንድገዛቸው ይጠይቁኛል፡፡ በሴንጢዋ ሰበብ ህይወታቸውን እንድጉበኝ ዕድል ተከፍቶልኝ ነበር፡፡ አዛውንቱን መነሻ በማድረግ የመላው ኢትዮጵያን ጉስቁል ህይወት ገፆዎች ዕጣ-ፋንታ በምናብ ለመፈተሽ እስከመሞከር መዝለቄ ይታወሳል፡፡ የፅሁፉ ማጠቃለያ ላይ አዛውንቱ እዚያው ካሣንችስ አካባቢ የምግብ ቤት ትርፍራፊ (ቡሌ) የሚያገኙበት ሰዓት በማለፉ የዕለት ጉርሳቸውን ለግገር ለማግኘት ወደመርካቶ ማቅናታቸውን ገልጬ ነበር ያቆምኩት፡፡

ታዲያ በዚያው ሰሞን አዛውንቱ የሄዱበትን ዱካ ተከትዬ መርካቶን የማሰስ ፍላጎት ስላደረብኝ ወደዚያው አቀናሁ፡፡ ይሄ ፅሁፍም ተወለደ፡፡

ወደ መርካቶ ያቀናሁት በእግር ነበር፤ እንዲህ እያሰብኩ፤ እያሰላሰልኩ እንዲሁም በምናቤ እያስተዋልኩ…

…እንደ አዛውንቱ ሁሉ ከስንት አቅጣጫ ስንት ጉስቋሎች ወደ መርካቶ ይጉርፉ ይሆን? ደረቅ ወራትን፣ እርጥበት ወዳለበት አካባቢ በመሰደድ እንደሚሸሽ የጉሽ መንጋ ምስኪኖቹ ሰልፍ ይዘው ከያሉበት ወደ መርካቶ ሲተምሙ በአይነ-ህሊናዬ ታየኝ፡፡ እርግጥ መላዋ አዲስ አበባ ለእነዚህ ምስኪኖች የሚፈራረቅ ወቅት የሌላት የ13 ወራት ደረቃማ ባህርይ አስተናጋጅ ከሆነች ሰነባብታለች፡፡ የነዋሪውን ከምግብ ጋር የተያያዘ ልግስና የኑሮ ድቀቱ እየዋጠው ከተማይቱ ለምስኪኖች ፍርፋሪ የማይደማት ከሆነች ሰነባብታለች፡፡ ደግሞም ነዋሪው አይፈረድበትም፡፡ ማጣፊጫው ቀርቶ የዱቄት እህሉ በዋጋ ምን ያህል እንደናረ ማሰብ ነው፡፡ አንድ ኪሎ ጤፍ አሥራ ስምንት ብር በገባበት በዚህ ዘመን ለመጣ ምስኪን ሁሉ እንጀራ ተቆርሶ ይዘለቃል? ስለዚህ ንግሥን መከታ አድርጉ ደጃችን ለሚቆም ምስኪን መገላገያችን ‹‹እግዚአብሔር ይስጥልኝ›› ሆኗል፡፡ በ‹‹እግዚብአሔር ይስጥልኝ›› የማንገላገለው ንግሥን ሳይሆን ‹‹ንጉሥን›› መከታ ያደረገውን የዘመኑን ሹም ብቻ ነው፡፡

መንገዴ በሱፐር ማርኬት በኩል ወደ ፍልውሃ በማሽቆልቆል የጥቁር አንበሳ ሆስፒታልን አጥር እየታከከ ወደ ተክለኃይማኖት ያቀናል፡፡

በእርግጥም አዲስ-አበባ ስለምስኪኖቿ ጩኸት ጆሮዎቿን ደፍናለች፡፡ ሁሉም ስለየራሱ ብቻ እያሰበ በመሮጥ ፊት ለፊቱ የወደቀውን ስለመረጋገጡ ቁርቋሬ አላድርበት ብሏል፡፡ ምግብ ቤቶች እንኳን ከደንበኞቻቸው ፊት የተነሣውን ትርፍራፊ እንደወትሮው ለደሃ በመመፅወት ፈንታ ለተጨማሪ ገቢ ለተኮናታሪ ማስረከብ ከጀመሩ አመታት ተቆጥረዋል፡፡ ይሄ ድርጊት በተዘዋዋሪ ሀብታሞቹ ነጋዴዎች ቡሌውን ሳይፀየፉ እራሳቸው ይበሉታል እንደማለት ነው፡፡

ይሄንን ጉዳይ በተለየ መልኩ ያየው አንድ ወጣት የምግብ ቤት ባለቤት ነው፡፡

‹‹ምክንያቱ ተጨማሪ ገቢ ማግኘት አይደለም›› አለኝ፡፡

‹‹ታዲያ?›› አልኩት፡፡

‹‹ትርፍራፊውን እንደምትመፀውት ከታወቀ ከተለያየ አቅጣጫ የሚመጡ ምስኪኖች ጊዜ ሳይመርጡ በርህን አጥረው ይቀመጣሉ፡፡ ደንበኛ መግቢያ ያጣል፡፡ እየተመገበም እነሱ ሲጓጉ ማየቱ ነፃነት አይሰጠውም፡፡ በዚህ ላይ ትርፍራፊውን በምታድልበት ሰዓት ሌላ መራኮት ይፈጠራል፡፡ ስለዚህ የግድህን ለተኮናታሪዎች ትሰጣለህ፡፡ ወይም ደንበኞች ለውሾቻቸው ይዘውት እንዲሄዱ ታደርጋለህ፡፡››

‹‹ቀደም-ቀርዋ›› አዲስ አበባ ይሄን ሁሉ ችላም ቢሆን ምሥኪኖቿን አብልታ ታሳድር ነበር፡፡

ይሄንንና መሰል ጉዳዮችን እያሰላሰልኩ አንዋር መስኪድ አካባቢ ደረስኩ፡፡ መርካቶ ገና አላንቀላፋችም፡፡ ሱቆቿ ሁሉ አልተዘጋጉም፡፡ የነውር ተግባሯ ጊዜው አልደረሰም፡፡ ሰዓት አየሁ፡፡ ገና አስር ሰዓት ከሃያ ነው፡፡ እንደተነገረኝ ከሆነ መስኪድ አካባቢ የ‹‹ቡሌ›› ገበያው የሚደራው ከአሥራ ሁለት ተኩል በኋላ ነው፡፡ ስለዚህ አካበቢው ላይ ያገኘኋቸውን አንዳንድ ወጣቶች ስለጉዳዩ ጠያየኳቸው፡፡

‹‹ቆይ ተራ አስከባሪውን እናገናኝህ›› አሉኝ፡፡

‹‹የታክሲ….››

‹‹አይ፤ ቡሌም የሚሸጠው በተራ አስከባሪ ነው›› ብለው ልጁን ጠሩት፡፡ ልብሱም ደህና ነው፡፡ ቁመናው እስፖርተኛ ያስመስለዋል፡፡ ተባባሪ መንፈስ ይታይበታል፡፡ መካከል ላይ አንዳንድ የእንግሊዘኛ ቃላትም ጣል-ጣል ያደርጋል፡፡ ሥሜን ነግሬው ተዋወኩት፡፡ ሥሙን ነገረኝ (እንዳልጠቅሰው አሳሰበኝ) የመንገድ ላይ የቡሌ ትርኢት እስኪጀመር ከለላ ይዘው ወደሚሸጡት እንሂድ ብሎኝ ወደዚያው አቀናን፡፡

ቦታው ቆርቆሮ ተራ ነው፡፡ የቆርቆራ ተራ አጫጭር ቤቶች ጣሪያቸው ገጥሞ ቀና ብሎ ለመሄድ ያዳግታል፡፡ በሾሎክላካው መንገድ ውስጥ ልጁ አጉንብሶ መሬት የተሰጡትን ቆርቆሮዎች ላለመርገጥ እየተጠነቀቀ ይመራኛል፡፡ መረጋገጫ ስፍራ ስናጣም ቆርቆሮውን እየረገጥን የተባለው ከለላ ጋ ደረስን፡፡

‹‹ሸራተን ይባላል›› አለኝ፡፡

ሸራተን ውስጥ አራት ሴቶች ጥግ-ጥግ ይዘው ተቀምጠዋል፡፡ በማስታጠቢያ ሰሀን ላይ ከምረው ፊታቸው ያስቀመጡትን ቡሌ በስኒ ማስቀመጫ እየሰፈሩ ለደንበኞቻቸው ይሰጣሉ፡፡ በሩ ሥር አንድ ትልቅ ብረትድስት ተጥዶ ይንተከተካል፡፡ ውስጡ ለቢጫ የሚያደላ መረቅ ይንተከተካል፡፡ መረቁ ከየምግብ ቤቱ በሚገኝ፣ ተግጦ ባለቀ አጥንት የሚዘጋጅ ነው፡፡ አንዳንድ ተንሳፋፊ ቀጫጭን ሥር መሰል ነገሮች ይታያሉ፡፡ ሽርጥ ያደረገችው ሴት ከዚህ ‹‹መረቅ›› ውስጥ በጭልፋ እየጨለፈች በኩባያ ትሰፍራለች፡፡ የመረቅ ደንበኞቿ ከጅማት መሰሉ ሥጋ እንድታደርግላቸው ሴትዮዋን ይማፀናሉ፡፡

‹‹ለምን ሸራተን ተባለ?›› አልኩት አስጎብኚዬን

‹‹ሸራተን ስለሆነ ነዋ›› ፈገግ አለ ‹‹ለእኛ ማለቴ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ‹ቡሌ› የሚሸጠው መንገድ ዳር ስለሆነ ይሄንን ዳስ እንደ ትልቅ ‹‹ኮምፈርት›› (ድሎት) ቆጠሩት፡፡››

ቤቱ የከለላነት እንጂ የተደራጀ ቤትነት አይታይበትም፡፡ ግድግዳው በየምናምኑ የተወታተፈ ነው፡፡ ጣሪያውም እንደዚያው ከለላ እንጂ ዝናብና ፀሐይ ተከላካይ አይደለም፡፡ የ‹‹ሸራተን›› ደንበኞች በየጥጋጥጉ የተበላሸ የመኪና ባትሪ፣ ሞተርና ድንጋይ ላይ ቁጭ ብለው የተሰፈረላቸውን ቡሌ ይበላሉ፡፡

‹‹እንብላ፣ እንብላ፣ እንብላ›› አሉን፡፡

አዲስ አበባ ውስጥ ‹‹እንብላ›› ያልጠፋው እዚህ ብቻ መሆን አለበት ስል አሰብኩ፡፡ ‹‹ሸራተኖች›› እንብላ ባይ ቢያጡም እንብላን አሽቀንጥረው አልወረወሩትም፡፡

ቡሌው መስፈሪያው ሁለት ብር ሆኗል፡፡ ከጥቂት ጊዜ በፊት አንድ ብር ነበር አሉ፡፡ የኑሮ ድቀቱ እላይ ሲያርፍ ‹‹የላይኞቹ›› ችግሩን ለበታቾቹ ‹‹ሸራተኖች›› በማስተላለፋቸው ቡሌ በስኒ ማስቀመጫ ተሰፍሮ ዋጋው የመቶ እጅ እድገት አሳየ፡፡ አንድ ሰው እጅግም ሳይጠግብ፤ በጠኔ ላለመውደቅ ቢያንስ ስምንት ብር ያስፈልገዋል፡፡

አስጎብኚዬ ሁለት የስኒ ማስቀመጫ ቡሌ አስሰፍሮና አንድ ኩባያ መረቅ ይዞ ቁጭ አለ፡፡ ለዚህ ቤት የስድስት ወር ደንበኝነት አለው፡፡ የተሣካለት ዕለት በቀን ሁለት ጊዜ እየመጣ ይመገባል፡፡ ካልተሣካለት በቀን አንዴ በመምጣቱ አይማረርም፡፡ ሲከነክነኝ የቆየውን ጥያቄ ጣል አደረኩለት፡፡

‹‹ተምረሃል?››

‹‹አዎ፣ ከዊንጌት በሙያ ሰልጥኜ ከተመረቅሁ አንድ ዓመት ሊሞላኝ ነው፡፡››

ታዲያ…?

‹‹ሥራ ጠፋ፡፡ በአጋጣሚ መርካቶ መጣሁ ሥራ እስኪገኝ ድረስ በአማራጭ ማጣት ጊዜያዊ ሥራ ላይ ተሰማራሁ፡፡››

‹‹ምን ትሰራለህ?››

‹‹ቆራሌዎች የሰበሰቡትን ብረታ ብረት ሆነ ሌላ ዕቃ ከመኪና ማውረድና መጫን እሰራለሁ፡፡ ማታ ማታ ደግሞ ተራ አስከብራለሁ፡፡››

የቆራሌዎችን ዕቃ የማውረድና የመጫኑም ሆነ የቡሌ ተራ የማስከበሩን ሥራ ያገኘው ስለተማረ ሳይሆን ጉልበት ስላለው እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ መርካቶ ዝቅ ሲሉ ዕውቀት ቦታ የለውም፣ ጉልበት እንጂ፡፡

ሸራተን የቀን የቀን ምግብ ቤት በመሆኑ መስተንግዶው አመሻሽ ላይ ይጠናቀቃል፡፡ ከዚህ በኋላ ቡሌ የሚፈልግ አንዋር መስጊድ አካባቢና ሚኒተሪ ተራ እስከምሽቱ ሦስት ሰዓት መንገድ ዳር መመገብ ይችላል፡፡

ትርፍራፊ ምግቦች የሚሰበሰቡት ከተለያዩ ሆቴሎች ነው፡፡ ተክለኃይማኖት አካባቢ ያሉ ምግብ ቤቶች ከደንበኞቻቸው የተራረፈውን ምግብ በማጠራቀም ለቡሌ ነጋዴዎቹ ይሸጡላቸዋል፡፡ ቡሌው የመርካቶ አካባቢ ብቻ ሳይሆን እስከ ልደታ ድረስ ዘልቆ ‹‹አሹ ሥጋ ቤት››ንም ያጠቃልላል፡፡ አንዳንድ የቡሌ ደንበኞች በቁጭት እንደሚናገሩት ቀደም ሲል ቡሌው ከሒልተን፣ ከግሎባልና ከመሣሠሉት ደረጃቸውን ከጠበቁ ሆቴሎች ይመጣ ነበር፡፡ አሁን ተቋርጧል፡፡ ለምን እንደሆነ እነሱም አያውቁት፡፡

ከዕለት ወደ ዕለት ድህነት ተንሰራፍቶ ያስጨነቃት አዲስ አበባ ከ80 ሺህ በላይ የሆኑ ነዋሪዎቿ ውድቅዳቂ ምግቦችን ከቆሻሻ ገንዳ ላይ ለቅመው የሚመገቡ እንደሆኑ “Ethiopian Review” ድህረ-ገፅ ይገልፃል፡፡ እንግዲህ በአነስተኛ ወጪም ቢሆን ‹‹ሸራተን›› የሚመገቡ እነዚህ ወገኖች ደረጃቸው (ከታች ወደ ላይ ሲቆጠር) ሁለተኞች ናቸው ማለት ነው፡፡ እነዚህ ሁለተኞች ቁጥራቸው ከመቶ ሃምሣ ሺህ በላይ እንደሆነ ድህረ-ገፁ

ወደ ገፅ 32 ዞሯል



ዘሪሁን ተስፋዬ
(የቀድሞ አዲስ ነገር ጋዜጣ ባልደረባ)

# "ድንገቴ ፖለቲከኞች" እና የዳያስፖራ ፖለቲካ

ሚካኤል ብዙዎቹ ኤርትራውያን የቀመሱትን የስደት መራር ሕይወት በብዙው ኖሮታል፡፡ ያሳለፈውን ውጣ ውረድ ሲተርክ በአንድ "አድቬንቸር" ፊልም ላይ ያየውን እንጂ በእውኑ ዓለም የኖረውን አይመስልም፡፡ የኻያ ዘጠኝ ዓመት ወጣት ይህን ያህል ቀምሷል ቢባል የሚያምን የለም፡፡ ሁለት ጊዜ ያህል የሱዳንን ድንበር ሊሻገር ሲሞክር ተይዟል፡፡ ሦስት ዓመታትን በሳህል በረሃ በእስረኝነት አሳልፏል፡፡ ስድስት ወራትን በማይነፌ የቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ብቻውን ታስሯል፡፡ በቀን አንድ ዳቦ ብቻ እየሰጡ የጨው ውሃ እየነሰነሱ ገርፈውታል፡፡

ሞቱን ተመኝቶ ራሱን ለማጥፋት ያልሞከረበት ጊዜ አልነበረም፡፡ ብቸኝነት፣ ርሃብ፣ ግርፋት እና ንዳድ ይሄን ቢያስመኙት አይገርምም፡፡ ሞት አሻፈረኝ ቢለው እንደገና አሰላሰለ፡፡ እናም ለሦስተኛ ጊዜ ከእስር ቤት ጠፍቶ ስደትን ሞከራት፡፡ የሱዳንን ድንበር ማግኘት ግን ቀላል አልሆነለትም፡፡ ያለእንቅልፍ እና እረፍት አምስት ቀናትን ተጉዞ የሱዳንን በረሃ አጋመሰ፡፡ ከዛ በላይ ግን መጓዝ አልቻለም፡፡ ብቻውን በባዶ ሜዳ ተዝለፍልፎ ወደቀ፡፡

ሲነቃ በባዶ ሜዳ ላይ በአገሩ ልጆች ተከቦ አገኘው፡፡ "በድጋሚ ወታደሮች አግኝተው ኤርትራ የወሰዱኝ ያህል ነው የተሰማኝ" ይላል፡፡ እድለኛ ነበር፡፡ እንደርሱ የአስመራ ሕይወት ያንገፈገፋቸው ወጣቶች በረሃ ሲያቋርጡ አግኝተውት ነፍሱን ታደጓት፡፡ ካርቱም ገብቶም ከአገሩ መውጣቱን አላመነም ነበር፡፡ ሦስት ወራት ያህል ይህ ስሜት ከእርሱ ጋር ነበር፡፡ ከእንቅልፉ በባነነ ቁጥር እስር ቤት ያለ ያህል ይሰማው ነበር፡፡ ዛሬ ይህ ዓይነቱ ስሜት ከአዕምሮው ቢወጣም ስለአገሩ እና ስለኢሳያስ አገዛዝ ምንም አይነት ነገር ትንፍሽ ማለትን አይሻም፡፡ ያለፈው ታሪኩ ያስቀመጠው ጠባሳ ብቻ አይደለም ስለፖለቲካ ጉዳዮች እንዳያወራ የሚያደርገው፡፡ "ዛሬም ነፃነት አይሰማኝም" ይላል አንጻራዊ ነፃነት በሰጠው አገር እየኖረ፡፡ የኢሳያስ መንፈስ የትም ሥፍራ አለ፡፡

ሚካኤልን መሠል የኤርትራ ዜጎች በርካታ ናቸው፡፡ ዛሬም ፈርተውት የወጡት ሥርዓት ትልቅ ፍርሃትን በአዕምሯቸው አኑሮ አስሯቸዋል፡፡ ይህ ምስል ግን በኢትዮጵያውያን ዘንድ የግልብጥ ታሪክ አለው፡፡ አፋኙን የኢሕአዴግ ሥርዓት በተለያዩ ምክንያቶች ያመለጡ ዜጎች ፖለቲካን ይበልጥ የሚያጮኂት እንዲሁም አንፃራዊ የነፃነት ስሜት የሚሰማቸው ከለላ ባገኙበት አገር ውስጥ ሆነው ነው፡፡ የመለስ መንፈስ ሲያልፍም አይነካቸው፡፡ ፍርሃቱ የለም፤ ከየት እንደፈለቀ የማይታወቅ ድንገቴ ፖለቲከኝነት እንጂ፡፡

"ድንገቴ ፖለቲከኝነት?"

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አንዱ ጠባይ "ድንገቴ ፖለቲከኛነት" ነው፡፡ ይህ ስሜት በተለይ ዳያስፖራ ለመባል የግድ ተቃዋሚ መሆን መሥፈርት የሚመስላቸው ዜጎችን የሚመለከት ነው፡፡ በአዲሱ ዓለም የፖለቲካ ሥርዓት ተማርከው አገራቸውም የተሻለ ዴሞክራሲ እንዲኖራት በመመኘት የማኅበራዊ ድረ-ገጾችን ድንገት የተቀላቀሉትን አይጨምርም፡፡ ይልቁንም አገር ቤት እያሉ "ኑሮ ተወዷል" ለማለትም የሚፈሩ እና የፖለቲካ ጣጣ "ሲያልፍም አይንካኝ" ይሉ የነበሩትን እና የፖለቲከኛነትን ማዕረግ መድፋትን ትልቁ ግባቸው አድርገው የሚባክኑትን ነው፡፡ እነዚህ ግለሰቦች ድንገት ይለወጣሉ፤ "ፖለቲከኛም" ይሆናሉ፡፡ እያንዳንዷ ዕለት እና እንቅስቃሴያቸው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ጉዳዮች ይያዛል፡፡ ብዙሃኑ የሚደግፉት የፖለቲካ ፓርቲም ሆነ አቋም ላይኖራቸው ይችላል፤ ገዢውን መንግሥት ግን ስለመቃወማቸው እርግጠኞች ናቸው፡፡

በተለይም እንደ "ፓልቶክ" እና "ፌስቡክ" የመሳሰሉ ማኅበራዊ ድረ-ገጾች መበራከታቸው ፖለቲካን በሩቁ ሲሉ ለነበሩ ዜጎቻችን ሁሉ "ዘራፍ" እንዲሉ በሩን ከፍቶላቸዋል፡፡ ለኢትዮጵያዊ ዳያስፖራ የፖለቲካ ጨዋታ ገዢውን መንግስት የመቃወሚያ መድረክ ብቻ አይደለም፡፡ ከዚህም ያልፋል፡፡ የአዲሱ ዓለም የኑሮ ውጣ ውረድ የሚፈጥረው ጫና ማስተንፈሻ ነው፡፡ የቁጣ ማብረጃ አንዱ መሳሪያም ጭምር ነው፡፡ አይዲዮሎጂ ወይም የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ አቋም የሚባል ጉዳይ ላይኖር ይችላል፡፡ ሁሉም ባፈተተው ይጓዛል፡፡ ከሣምንት በፊት የአንድነት አቀንቃኝ የሆነ ግንባርን መለያ አርማ ሲያውለበልብ የነበረ ዳያስፖራ የመገንጠል አቋም ያለውን ፓርቲ አርማ ለማቀንቀን አፍታም አይፈጅበት፡፡ የወቅቱ ነፋስ በነፈሰበት ማዘንበል ብዙ ማሰብን የሚጠይቅ አይደለም- ለድንገቴ ፖለቲከኛው፡፡

በአንድ ወቅት የፖለቲካ ‹‹ሳታየሪስቱ›› አቤ ቶኪቻው ያጫወተኝ ታሪክ የሚረሳ አይደለም፡፡ በስደት በሚኖርበት አካባቢ አንድ ፖለቲካን ፉት አድርጓል ተብሎ የሚወራለት ሰው በቅርብ ርቀት እንደሚኖር ያጫውቱታል፡፡ ለወሬ የፈጠነው አቤ "ፖለቲከኛውን" ለመተዋወቅ ይጓጓል፡፡ እናም ይተዋወቀውና ማውጋት ይጀምራሉ፡፡ ከቆይታ በኋላ አቤ ወደቤቱ ይዞት የመጣው አንድ አረፍተ ነገር ነበር- "መለስ መላጣ ናቸው" የሚል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ቡድን እየተበራከተ መምጣት በዳያስፖራ ፖለቲካ ላይ ዕምነት ለነበራቸው እና ለውጥን በእጅጉ ለሚናፍቁ ዜጎች ተስፋ አስቆራጭ ሆኖ ይታሰባል፡፡ ይሁንና የቡድኑ መበራከት የዳያስፖራውን ፖለቲካ ፍጹም ደካማ እና ተስፋ የማይጣልበት አድርጎ ለመውሰድ በቂ ምክንያት አይሆንም፡፡ ይልቁንም ጠንካራ ፖለቲከኞችን ምን እንደደበቃቸው እና የሚታየውን "ከፍ እና ዝቅ" ዓይነት ትግል እንዲታይ ያደረገውን መንስዔ ለማግኘትና ለመፍትሄውም መንገዱን ያመቻቻል፡፡

## ፖለቲከኞቹን ምን በላቸው?


ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በመርህ የሚገዛ እና ግብ ያለው የፖለቲካ ተዋጽዖ ተስካሩ የወጣ ይመስል የኢትዮጵያ ፖለቲካን የሚያቀነቅኑ የዳያስፖራ ማኅበራዊ ድረ-ገጾች በድንገቴ ፖለቲከኞች እየተሞሉ ናቸው፡፡ ይህንንም ነው ብዙሃኑ "የዳያስፖራ ፖለቲካ" እያሉ የሚሳለቁበት፡፡ ቀድሞ በጠንካራ አመክንዮ በተሞላ ተቃውሟቸው የምናውቃቸው ፖለቲከኞች እና ተንታኞች ቁጥራቸው ከዕለት ወደ ዕለት እየተመናመነ ለድንገቴ ፖለቲከኞች ሥፍራውን ለቀዋል፡፡ ‹‹አሉ›› የሚባሉትም ጥቂት ፖለቲከኞች በየዕለቱ የሚነሱ እና የሚወድቁ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ እና ዘላቂ አገራዊ መፍትሄን የሚጠቁሙ ሃሳቦችን አለማቀንቀናቸው ከትችት እንዳያመልጡ አድርጓቸዋል፡፡ ይህም ‹‹የዳያስፖራ ፖለቲካ ሁሉ ከንቱ ነው›› ብለው ለሚሞግቱት የገዢው ግንባር ደጋፊዎች እና አገር ቤት ሆነው ለሚታገሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች መንደርደሪያ ሰጥቷቸዋል፡፡

የፖለቲካ ተንታኞች ለእንዲህ ዓይነቱ የጠንካራ ፖለቲከኞች መንሸራተት የተለያየ መላምት ያስቀምጣሉ፡፡ የመጀመሪያው መላምት ትግሉን አምነው የተቀላቀሉት ግለሰቦች አዲሱ ዓለም የሚጠይቀውን የኑሮ ግዴታ ለመወጣት በሚያደርጉት ትግል ተውጦ የመቅረት አደጋ ነው፡፡ በተለይም አገር ቤት እያሉ በጠንካራ የትግል አጋርነታቸው የሚታወቁት ግለሰቦች ለንባብ እና ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ያላቸው ቅርበት እየራቀ መሄድ ቀድሞ በነበራቸው አቋማቸው በድፍረት ወደ መድረክ እንዳይመጡ ምክንያት ሆኗል፡፡ እኔም በአጋጣሚ ያገኘኋቸው ጠንካራ ግለሰቦች ቀድሞ የነበራቸውን ጥንካሬ ከዕለት ዕለት ማጣታቸው በራስ መተማመናቸውን እንደበላባቸው ነግረውኛል፡፡

ከእዚሁ ጋር በተያያዘ በአውሮፓ እና በአሜሪካ ዲፕሎማቶች መካከል እንደ ቀልድ የሚወራ አባባል ማንሳቱ ተገቢ ነው፡፡ "ኢትዮጵያዊ ፖለቲከኛ ፓስፖርቱን ጥሎ ጥገኝነት የጠየቀ ዕለት ትግሉን አፈር እንዳለበሰ ይቆጠራል" ይላሉ፡፡ ፋታ የለሹ የካፒታሊዝም የኑሮ ውጣ ውረድ ጠንካራ ፖለቲከኞችን እንደሚበላ ማሳያ ነው፡፡ በተለይም የዕለት ኑሮን ለመደጎም ብዙሃኑ ዳያስፖራ በሚሳተፍባቸው ጉልበት በዝባዥ ሥራዎች ላይ መሳተፋቸው አንገት እያስደፋቸው ፖለቲካውን ዕርም ያሉት ቁጥራቸው በርካታ ነው፡፡

ሌላው ለጠንካራ ፖለቲከኞች ከእለት ወደ ዕለት መጥፋት ምክንያት

ወደ ገፅ 22 ዞሯል



አቤ ቶኪቻው

# ኬንያን በድርበቡ፬

<<ኤርፖርቱ መለስ ኤርፖርት ተባለ እንዴ!?>> <<አልሰማህም እንዴ!?>> <<እሺ ይሁን መስቀል አደባባይ መቼ ነው መለስ አደባባይ የተባለው!?>><<ቆየ እኮ!>> ወደ ስታድየም ሲቃረቡ ግርግር ነገር አየ። <<ምንድነው?>> ብሎ ጠየቀ። "ዛሬ እግር ኳስ ጨዋታ ነበር።" አለው። ሌላ አይነት ጨዋታ መምጣቱ ደስ አለው። <<ይገርምሀል ድሮ ቀንደኛ የስታድየም ታዳሚ ነበርኩ>> ሲል ትዝታው በአይኑ እየመጣ ነገረው። "የማን ደጋፊ ነበርክ?" ብሎ ጠይቆት መልሱንም ሳይጠብቅ "እኔ የመለስ ቡና ደጋፊ ነኝ። ዛሬ መለስ ቡና ከመለስ ጊዮርጊስ ነበር ጨዋታው፤ ስራ ባይኖረኝ አልቀርም ነበር። ይገርምሃል የመለስ ፕሪምየር ሊግ ጨዋታ ገና መጀመሩ ነው!"

አንድ ታክሲ ተኮናትሬ ወደ ጎስቋላዋ ሰፈሬ እየሄድኩ ነው። ኬኒያ ውስጥ ከትላልቅ ችግሮች ውስጥ የሚመደበው የመኪና ትራፊክ መጨናነቅ ነው። በተለይ "ራሽ ሃወር" በሚሉት ወደ ስራ መግቢያ እና ከስራ መውጫ ሰዓት።

ይሄ ችግር ከምን የመጣ እንደሆነ እንኳንስ እኔ አስር ወር የቆየሁት ሰውዬ እና ናይሮቢ ተወልደው ያደጉትም አንድ አይነት ድምዳሜ ላይ መድረስ አልቻሉም። ግማሹ የመኪና ብዛት ስላለ ነው ይላል፤ ሌላው ደግሞ የመንገዱ ጥበት ነው ይላል። እኔ እንደ "አይቲ" ባለሞያነቴ በዚህ አጋጣሚ እንኳ ሙያችንን እንናገር እንጂ...(ሃሃ ብለው መሳቅ ይችላሉ የምር ግን ረስቼው ነበር... ለካስ ባለሞያ ነኝ እኔም ሃሃ... ልበል እንጂ) በአይቲ "Band width" የሚባል አንዳች ነገር አለ። ይህ አንዳች ነገር በውስጡ "data" የተባለውን ነገር እንዲያስተላልፍ የተሰራ ነው። ባንድ ዊድዝ ትንሽ ከሆነ ዳታ ለማስተላለፍ ችግር ይገጥመዋል። ስለዚህ የተቀላጠፈ ፍሰት እንዲኖር፤ ወይ ዳታ መቀነስ አለበት ወይ ደግሞ ባንድ ዊድዝ መጨመር አለበት።

የኬኒያ መንገድም ወይ መንገዱ አልተጨመረ ወይ መኪናው አልተቀነሰ፤ በተለይ በራሽ ሃወር ምን የመሰለውን ሃይሉክስ መኪና አንካሳ ዶሮ ትቀድመዋለች።

መንገዱ ተጨናንቋል። ስለዚህ ከኬኒያዊው የታክሲ ሾፌር ጋር ወግ ተጀመረ።

"ከየት ነህ?" አለኝ

እስቲ ገምት?

ትክ ብሎ አየኝና... "ፍሮም ጋና!" አለኝ አገኘሁሽ! በሚል ስሜት።

አይደለሁም።

"ኦኬ... ናይጄሪያ!?"

ሰውዬው አርቆ ሳይጥለኝ አገሬን ብናገር ይሻላል ብዬ "ከታላቋ ኢትዮጵያ ነኝ።"

"ኦ... ሻሸመኔ!"

ሻሸመኔን ታውቃታለህ?

<<አይ ሬጌ ሙዚቃ አዳምጣለሁ ብዙ ግዜ ሻሸመኔ ትጠራለች።>> አለኝና... ወድያው አንድ ፈታኝ ጥያቄ ጠየቀኝ። "እኔ የምልህ ጠቅላይ ሚኒስትራችሁን እንዴት ብትወዱት ነው ባክህ?"

እንዴት?

"እኔ ነፍስ ካወቅሁ ግዜ ጀምሮ የምሰማው የኢትዮጵያ መሪ ዜናዊ ብቻ ነው። ሃያ አመት፤ ለምን አትቀይሩትም?" አለኝ።

አይ መሬት ያለ ሰው! አልኩ በሆዴ! በአንደበቴ ግን እርሳቸው እምቢ ብለው እንጂ ህዝቡ ሞክሮ ነበር ብዬ የዘጠና ሰባቱን ነገር ነገርኩት። እውነትም በዘጠና ሰባት ኢህአዴግ ስላደረገው ነገር ከእኔ እኩል ጠንቅቆ ያውቃል እና ነገረኝ። ከሰው ሀገር ሰው በደላችንን ስሰማው እንባ ተናነቀኝ! ለካስ ሰው ጉድ ብሎናል!?

ኬኒያ ውስጥ እንደኔ ጠቆርቆር ብለው ካላምታቱ በስተቀር ኢትዮጵያውያንን እና ኤርትራዊያንን የሚለያቸው የለም።

እዝች ጋ የአባተ ኪሾ ጨዋታ ብትመጣ ምን ይለናል!?

በዛን ሰሞን የኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር ከወዳጃቸው እና አለቃቸው የኤርትራው ፕሬዘዳንት ጋር ተቀያየሙ። በአንድ ወቅት "ከኢሳያስ ጋር አንድ ሰዓት መቀመጥ ማለት ዩንቨርስቲ ገብቶ የመመረቅ ያህል ነው" ብለው የተናገሩት ሚቼ መለስ፤ <<ኤርትራዊያን የአይናቸው ከለር ካላማረን ማባረር መብታችን ነው>> ብለው ጠራርገው አስወጡ።

በዚህ ግዜ አቶ አባተ ኪሾም በደቡብ ክልል ያሉትን ኤርትራዊያንን በሙሉ ወደ አዲሳባ ላክ ተብለው ታዘዙ። ይሄኔ የትግራዩንም የአስመራውንም ነጋዴ ቀላቅለው አሳፈሩ። ይሄኔ ትግራይ ነጋዴ ወዳጆቻችን <<ኧረ እኛ ኤርትራዊ አይደለንም>> ብለው አቶ አባተ ኪሾን ተቃወሙ። ይሄኔ አቶ አባተ "እኔ አልለያችሁም እዛው ይለዩዋችሁ!" ብለው ቅኔ የሚመስል ንግግር ተናግረው ነበር አሉ።

እዛ የለዩን ሰዎች እዚህ በኬኒያ ያለንን ፍቅር እና መተሳሰብ ቢያዩ ይገርማሉ።

ከብዙ ጊዜ በኋላ ወደ ሀገሩ መመለሱ ነው። ከቦሌ ኢንተርናሽናል አውሮፕላን ማረፊያ ታክሲ ለመኮናተር አይኑን ቃኘት ቃኘት ሲያደርግ አንዱ ቀልጣፋ ቀልጠፍ ብሎ፤ "ታክሲ ፈልገህ ነው!?" አለው።

አዎ

<<የት ነህ?>>

ስታድየም አካባቢ ካደረስከኝ ይበቃኛል።

<<ሶስት መቶ ብር>>

"አልተወደደም...?" ብሎ እየጠየቀ ለመሳፈር ሳይሆን ለመከራከር የሚገባ ይመስል ወደ ታክሲዋ ገባ። ሹፌሩም ለወጉ ያህል እንጂ ሊከራከረው እንዳልሆነ ገባውና "ባይሆን ፀባዬን አይተህ ትጨምርልኛለህ!" ብሎ ቀልዶ ሊዘውራት ገባ።

ታክሲዋ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን አባላትን እና የሟች መለስ ዜናዊ ፎቶዎች ተለጣጥፈውባታል። እንግዳው ዙሪያ ገባዋን እየቃኘ ሳለ ድንገት "የት ነበርክ!?" ሲል ባለ ታክሲው ጠየቀው። ጨዋታ መጀመሩን እንግዳው አልጠላውም፤

"አውሮፓ ነበርኩ"

"ታድያ ምነው፤ በደህና ተመለስክ?"

"ትምህርት ላይ ነበርኩ ስጨርስ መጣሁ!"

ባለታክሲው በሀሳቡ ባለስልጣኑ፣ ጋዜጠኛው ሁሉ እየወጣ በሚቀርበት በዚህ ዘመን ትምህርት ስለጨረስኩ መጣሁ ብሎ የሚናገር ሰው በመስማቱ ተገረመ። ምናልባትም የመንግስት ታማኝ ሰው ይሆናል! ሲልም አሰበ።

አሁን ደግሞ ተጠያቂ ባለተራው ሹፌሩ ሆነ!

"ስራ እንዴት ነው!?" አለው።

"ጥሩ ነው፤ ይኸው ራዕያቸውን ለማሳካት ቀን ተሌት እየለፋን ነው።" አለ ወደ ተለጠፈው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ፎቶ እየጠቆመ። እንግዳው ግር አለው።

"የእኔ ጥያቄ የታክሲ ስራ እንዴት ነው!? ለማለት ነበር..." ሲል ምናልባት ጥያቄዬን አልተረዳው ይሆን ብሎ አሻሻለለት።

"እኔም የመለስኩልህ የታክሲውን ስራ አስመልክቶ ነው። ለእርሳቸው ራዕይ ስንል በትጋት እየነዳን ነው!" ምን ታመጣለህ! የሚለው መሰለው። ፈገግ ብሎ "አይ ጥሩ ነዋ!" ብሎት ሲያበቃ፤ ማንሰላሰል ጀመረ።

አሁን በቅርቡ በህይወት እያሉ ታላቁ ሩጫ ላይ "ሳንፈልጋቸው ሃያ አመታቸው!" ሲባሉ የነበሩ ሰውዬ ዛሬ ሲሞቱ እንዲህ ወዳጃቸው መብዛቱ አስገረመው። ወደ ውጪ ሲመለከት በየመንገዱ በአጭር አጭር ርቀት ፎቶግራፋቸው ተሰቅሏል። ከተቀበሩ ቆይተዋል። ታድያ ይሄ ነገር እስከመቼ ነው የሚቀጥለው!? ሲል ራሱን ጠየቀ። ልክ ይሄን ጊዜ "ዘላለማዊ ክብር ለመለስ" የሚል አንድ "ፖስተር" ተመለከተ።

ዝምታ መስፈኑን ያልወደደው ባለታክሲ ራዲዮ ከፈተ። ጋዜጠኛው በስልክ አንድ ሰው እያናገረ ነው። እንግዳው ተሳፋሪ ፕሮግራሙ ከግማሽ ስለጀመረ ጫፉን ለመያዝ ትኩረት ሰጠ። ስለ ውበት የሚያወራ የራድዮ ዝግጅት መሆኑን ገመተ።

አዎ በዛኛው መስመር አንዲት የፀጉር ማስተካከል ዲዛይነር ስራዎቿን እያስተዋወቀች ነው።

"እስኪ ለአድማጮቻችን ስለ አሰራሩ አስረጂልን!"

"እንግዲህ እንዳልኩህ አዲስ የወንዶች ፀጉር ስራ ነው... ከፊት ያለው ፀጉር እስከ ግማሽ ድረስ ይላጫል። የተቀረው በአጭሩ ይከረከማል። በጥቅሉ ሰው ሰራሽ በራ በለው!"

"ኦ....ያያ... አሪፍ ፋሽን ነው። ይህ የፀጉር ፋሽን የጠቅላይ ሚኒስትሩን ራዕይ ከማስቀጠል አንፃር የሚኖረውን አስተዋፅኦ እንዴት ትገልጭዋለሽ!? የህዝቡስ አቀባበል እንዴት ነው!?"

እንግዳው ፈገግ አለ።

"ይሄ የፀጉር ፋሽን የተሰራው የእርሳቸውን ራዕይ ለማስቀጠል ታስቦ ነው። ስያሜውንም <ጀግና አይሞትም> ብለነዋል..."

አሁን ሳቁ አመለጠው። ከት ብሎ ሳቀ። ይሄኔ የታክሲ ሹፌሩ እንግዳው እንዳሰበው የመንግስት ቤተዘመድ እንዳልሆነ ገመተ። ቢሆን ኖሮ እንዲህ አይስቅም ነበር ሲልም አሰበ። እናም የራድዮኑን ድምፅ እየቀነሰ "ምን እናድርግ ብለህ ነው፤ አለበለዛ መኖር አልቻልንም እኮ!" አለው።

ይሄን ጊዜ መስቀል አደባባይ ደርሰው ነበር። ባለታክሲው ስልክ ተደወለለት። "ጬኸት" ላይ አድርጎ ማውራት ጀመረ።፡

"አቦ የት ነህ ባክህ!" አለው ደዋዩ፤ የቅርብ ጓደኛው መሆኑ ያስታውቃል።

"ከመለስ ኤርፖርት ተነስቼ አሁን ስታድየም እየሄድኩ ነው። አሁን መለስ አደባባይ ደርሻለሁ። የት ነህ አንተ!"

ወደ ገፅ 27 ዞሯል

ልዩ ዳሰሳ

# የኦጋዴን ነገር፡- ድርድሩ ለምን አልተሳካም?



ሙሉነህ አያሌው
muleayalew@yahoo.com

## መንደርደሪያ

የኢትዮጵያ መንግስት መከላከያ ሚኒስትር በሆኑት አቶ ሲራጅ ፊጌሳ በተወከሉበት የሰላም ስምምነት በአሸባሪነት ከተፈረጀው የኦብነግ አመራር ጋር ዳግም እርቅ ለማድረግ ናይሮቢ መክረሙን ሰምተን ሳንጨርስ ድርድሩ መቋረጡ ወዲያው ተነገረን፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ድርድሩን ለመጀመር የወሰደው ተነሳሽነት የሚበረታታ ቢሆንም ከጅምሩ ሊሳካ እንደማይችል መገመት ግን ከባድ አልነበረም፡፡ ከድርድሩ የሚገኝ ትርፍና ኪሳራን ለመገምገም እንደማንኛውም የፖለቲካ ታዛቢ ቅድሚያ ለድርድር የሚቀርቡ ቡድኖችን ባህሪ እና አላማ መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ አሸባሪ ተብሎ የተፈረጀው ድርጅት በመሰረታዊነት ከመንግስት ጋር ሊያስማማ የሚችል አንዳችም ነገር እንደሌለው ኃላፊዎቹ ጥንትም ተናግረዋል፡፡

ሲጀመር የሁለቱ ተደራዳሪዎች መነሻ አላማ ምን እንደነበር ግልፅ አይደለም፡፡ ከአሸባሪ ድርጅት ጋር ለመደራደር የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን የኢትዮጵያ መንግስት በቅድሚያ ማመቻቸት ነበረበት፡፡ በተጨማሪም የችግሩን ስረ-መሰረት ለመረዳት ውጥረት የነበረባቸው ፖለቲካዊ ዳራዎች አልተዳሰሱም፡፡ የአካባቢው ችግር እውን ታጣቂው ቡድን ነው? ወይንስ ህዝቡ ለመንግስት በጐ አመለካከት ከጅምሩም ስለሌለው ነው? የሚሉት ጥያቄዎችን መመርመር ተገቢ ነው፡፡ በእኔ ምልከታ የኦጋዴን ቀውስ የአሸባሪው ቡድን በአካባቢው መንቀሳቀሱ ብቻ ሳይሆን መንግስት ለማህበረሰቡ ያልፈታቸው ታሪካዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች የመኖራቸውም ሁነት ጭምር ይመስለኛል፡፡

ኦጋዴንን በሚመለከት በመንግስት የሚወሰዱ ወታደራዊ እርምጃዎችም ሆኑ በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ የሚደረጉ የሰላም ስምምነቶች ብዙውን ጊዜ ቀድሞ የታሰበባቸው አለመሆናቸውን የሚያመለክቱት በስተመጨረሻ በሚያስገኙት ውጤት ነው፡፡ አካባቢው ከረጅም አመታት ጀምሮ በተለያዩ አጋጣሚዎች የትጥቅ ትግል ያልተለየው ነው፡፡ ምክንያታቸው የተለያየ ቢሆንም በኦጋዴን/ሶማሌ የሚነሱ ግጭቶች እና ግጭቶቹን በሚመለከት በድጋፍም ይሁን በተቃውሞ የሚሰለፉ ኃይሎች በጥቅሉ ሁለት መልክ አላቸው፡፡ ቀዳሚ ተዋናይ በክልሉ ተወልደው ክልሉን ‹‹እንወክላለን›› የሚሉና በተደጋጋሚ የትጥቅ ትግሉን የመፍትሄ አካል አድርገው የሚወስዱ ኃይሎችን የሚወክለው ሲሆን ሁለተኛው ተዋናይ የአገር ውስጥ ተቃዋሚዎችን በተለያዩ መንገዶች (መሳሪያ በማቀበል፣ ስልጠና በመስጠት፣ መጠለያ በማበጀት) ‹‹ከጐናችሁ ነን›› የሚሉ የውጭ ኃይሎችን የሚወክለው ቡድን ነው፡፡ እነዚህ ቡድኖች በአካባቢው ላይ ያላቸው ፍላጐት የተለያየ ከመሆኑ አንፃር በተናጠል መመልከት ተገቢ ነው፡፡

መሰረታዊው ቀውስ

በሶማሌ ክልል በተለይም በኦጋዴን ለሚነሱ ግጭቶች መፍትሄ ለማበጀት በተደጋጋሚ የተሞከረ ቢሆንም እስከአሁን አንድም ጠብ የሚል ነገር ማግኘት ሳይቻል ቀርቷል፡፡ በአካባቢው ለሚነሳ ግርግር በተደጋጋሚ መፍትሄ ለማበጀት የሞከሩ ግለሰቦችም ይሁኑ የተለያዩ ተቋማት በአማራጭነት የሚያቀርቧቸው አስታራቂ ሃሳቦች ሁለት መልክ አላቸው፡፡ አንዳንዶች ችግሩን ለመፍታት ቀዳሚው አካሄድ ፖለቲካዊ መፍትሄ ማበጀት ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ወታደራዊ እርምጃ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ይሆናል ብለው የሚያምኑ ናቸው፡ ፡‹‹ፖለቲካዊ መፍትሄ ከወታደራዊ እርምጃ ይልቅ ለዘላቂ ሰላም አይነተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት ይችላል›› ከሚሉ ምሁራን መካከል ቶቢያስ ሃግማን ቀዳሚ ናቸው፡፡ እኚህ ስዊዘርላንዳዊ ምሁር የክልሉን ወታደራዊ አጥር ተሻግረው የኦጋዴንን ፖለቲካ በማጥናት ቀዳሚ በመሆናቸው አካባቢውን በሚመለከት የሚያሰፍሯቸው መጣጥፎች ተዓማኒነታቸው ላቅ እንዲል ያደርገዋል፡፡ ዶ/ር ሃግማን ከጅጅጋ እስከ ቆላፎ፣ ከጎዴ እስከ ሀርሺን በመንዝ የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፋቸውን ጨምሮ በጉዳዩ ላይ ወደ አንድ ደርዘን የሚቆጠሩ ጥናታዊ ፅሁፎችን በጆርናሎች እና በአካዳሚያዊ ስብሰባዎች ላይ አቅርበዋል፡፡ ሃግማን ክልሉን በሚመለከት የሚፈጠሩ ተግዳሮቶች ከወታደራዊ እርምጃ ይልቅ ፖለቲካዊ መፍትሄዎችን በማቅረብ ለማረቅ ይቻላል የሚል ፅኑ እምነት አላቸው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት ሁለቱንም አማራጮች ለመጠቀም ሞክሯል፡፡ ፖለቲካዊ መፍትሄውን ለማምጣት ሲባል በመንግስት የሚወሰዱ አማራጮች ውጤታማ ያልሆኑባቸውና ወደፊትም አንዳንድ ማስተካከያዎች ካልተደረገ በስተቀር መፍትሄ ማበጀት አይችሉም የምልበትን አንዳንድ መሰረታዊ ስህተቶችን ለማቅረብ እሞክራለሁ፡፡ የኢህአዴግ ፖለቲካዊ መፍትሄ መሰረታዊውን የክልሉን ችግር በሚገባ የመረመረ ካለመሆኑም በተጨማሪ የክልሉን (በተለይም የኦጋዴን አካባቢን) ችግር አንግቤ ተነስቻለሁ ከሚሉውና አሸባሪ ተብሎ ከተፈረጀው ኦብነግ ጋር የተናጠል ስምምነት ለማድረግ መሞከር ስህተት ይመስለኛል፡፡ የእነዚህን የማይታረቁ ልዩነቶች ምክንያቶች እና መሰረታዊው የክልሉ ችግር ምን መልክ እንዳለው እንይ፡፡ በዛውም በተደጋጋሚ የተደረጉ የሰላም ስምምነቶች ለምን ውጤታማ ሊሆኑ እንዳልቻሉ እናያለን፡፡

## ታላቋ ሶማሊያ

ማሳያ 1፡- በኒለኛው የቅኝ ግዛት ዘመን የአብዛኛው የሶማሊያ ግዛቶች በአንድ ገዢ አገር (እንግሊዝ) ስር መውደቃቸው በሶማሊያውያኑ መካከል የ‹‹አንበታተንም›› አስተሳሰብን (Somalia irredentism) እንዲያቆጠቁጥ በማድረግ አይነተኛ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ ይህንን የአንበታተንም ሀሳብ ተከትሎ የሶማሊያውያኑን የብሔርተኝነት ስሜት የሚያቀነቅን የሶማሊያ ወጣቶች ሊግ ለመጀመሪያ ጊዜ እውን ሆነ፡ ፡ እንግሊዝም ይህንን የብሔርተኝነት ስሜት (በምትቆጣጠራቸው ግዛቶች እና በሞግዚት አስተዳደር በያዘቻቸው አካባቢዎች) እንዲስፋፋ የራሷን አስተዋፅኦ ማበርከት ጀመረች፡፡ እንግሊዝ በጊዜው ታራምድ በነበረው በዚህ የውጭ ግንኙነት እርምጃዋ ሁለት የሚጣረሱ ፖሊሲዎችን ታራግብ ነበር፡፡ አንደኛው ሃሳብ የሶማሊያውያኑ ብሔርተኝነት በሁሉም ሶማሌያውያን በሚኖሩባቸው አካባቢዎች እንዲስፋፋና ወጥ የሆነ አመለካከት እንዲሰርፅ ማድረግ ሲሆን ሁለተኛው ተፃራሪ ምክንያት ኢትዮጵያ በኦጋዴን ላይ ያላትን የግዛት ጥያቄ ሙሉ ለሙሉ እንደምትደግፍ ለወቅቱ ንጉስ ለአፄ ኃ/ስላሴ መግለጿ ነው፡፡

በ1960 ዓ.ም (እ.ኤ.አ.) ሶማሊያ ነፃ አገር ስትሆን የ‹‹ሶማሊያ አንድነት›› መንፈስ በአዲሲቷ አገር ህገ-መንግስት ውስጥ እንዲገባ ከማድረግ ጀምሮ የአገሪቷ ሰንደቅ አላማ ላይ አምስቱን ሉዓላዊ ግዛቶችን የሚያመላክት አምስት ኮከብ በማድረግ እንቅስቃሴውን እውን ወደ ማድረግ እርምጃ ውስጥ ገቡ፡፡ እነዚህ አምስቱ ግዛቶች ብለው ከሚጠቅሷቸው መካከል አንዱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው የኦጋዴን አካባቢ ነው፡፡ አዲሱ ህገ-መንግስት የሶማሊያ ዜጐች (በየትኛውም አገር ውስጥ ያሉ ቢሆንም) ነፃ ህዝቦች መሆናቸውን ያውጃል፡፡

ሶማሊያ ነፃ አገር ሆና በተመሰረተች ገና በመጀመሪያው አመት በምዕራብ ሶማሊያ ነፃ አውጪ ድርጅት አማካኝነት የመጀመሪያውን ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ አወጀች፡፡ የዚህ ጦርነት ዋነኛ አላማ ኦጋዴንን ከኢትዮጵያ መንግስት አስተዳደር ነፃ ማውጣት እና ከሶማሊያ ጋር መቀላቀል ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ንጉስ ነገስት በወቅቱ ተንቀሳቅሶ የነበረውን ሀገራዊ አደጋ አንድም በጦርነት በሌላ ጊዜም በዲፕሎማሲያዊ ጫና (carrot and stick) ችግሩን በቀላሉ ሊያዳፍኑት ችለዋል፡፡ ይህ ማለት ለዘላቂው መፍትሄ ተሰጥቶታል ማለት ግን አልነበረም፡፡

ያልተቋጨው ችግር በኒለኛው ዘመን እየተባባሰ ለመምጣቱ ተንታኞች ሁለት ምክንያት ያቀርባሉ፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት የሶማሊያ መሪ የነበሩት ዚያድባሬ በመፈንቅለ መንግስት ስልጣን ላይ መውጣትን ተከትሎ ያራምዱ የነበረው ተንኳሽ ፖሊሲ ይበልጥ ግጭቱን ለማባባስ መንግስታዊ መደላደል ማግኘቱ ሲሆን በተጨማሪም በኦጋዴን ክልል ነዳጅ የመገኘቱ ነገር እውን መሆኑ ሲረጋገጥ ችግሩ ይበልጥ ተጋጋመ፡፡ የንጉሱን ስልጣን መልቀቅ ተከትሎ የተፈጠረውን የውስጥ ክፍተት በመጠቀም የዚያድባሬ መንግስት በደርግ ላይ የወሰደው ወታደራዊ እርምጃ ለተወሰነ ጊዜ የሰራ ቢመስልም ፍፃሜው ግን ያማረ አልነበረም፡፡ ደርግ ከዚህ ጦርነት በኋላ ሶማሊያን በሚመለከት ሁለት አጣዳፊ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መከተል ጀመረ፡፡ ቀዳሚው እርምጃ ዚያድባሬን ከስልጣን ማባረር የሚለው ሲሆን ሁለተኛው እቅድ ሶማሊያ ውስጥ የሚገኙ ጐሳዎችን እርስ በእርስ በማባላት የብሔርተኝነት ጥያቄያቸውን እንዲረሱት ማድረግ የሚለው ነው፡ ፡ ‹‹ለታላቂቱ ሶማሊያ›› አመለካከት መዳከም ደርግ የተጫወተው የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ አቀጣጫ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገቡን ተንታኞች ይገልፃሉ፡፡

የኢህአዴግ መንግስት ከደርግ የተረከባትን ‹‹የታላቋ ሶማሊያ›› ሀሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጋፈጠው አል-ኢትሃድ አል ኢስላሚያ የሚባለው ቡድን ሃሳቡን ዳግም ካነሳ በኋላ ነው፡፡ ይህ ድርጅት የሶማሊያ ዋነኛ

ግዛቶችን አንድ አድርጐ በእስላማዊ መንግስት ስር የመጠቅለል አላማ ነበረው፡፡ የዚህ ድርጅት አመራሮች ኦጋዴንን በሚመለከት የሚጋሩት አንድ አመለካከት አላቸው፡፡ ድርጅቱ ‹‹ኦጋዴን የሶማሊያ ህጋዊ ክልል መሆኗና የሶማሊያ አንድ አካል መሆኗ የሚያጠያይቅ አይደለም›› ይላል፡፡ አመራሮቹ ለዚህም በአስረጂነት የሚያቀርቡት ሱማሌያውያን ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር ግዛቲቷን ለማስመለስ በተደጋጋሚ ያደረጓቸውን ጦርነቶች እና የከፈሏቸውን መስዋዕትነቶች ነው፡፡

አሁንም ቢሆን በክልሉ የሚንቀሳቀሱና በአሸባሪነት የተፈረጁ ኃይሎች የዚህ ሀሳብ አቀንቃኞች ናቸው፡፡ በተለይ የኢትዮጵያን ህገ-መንግስት በመጥቀስ የክልሉ በተለይም በኦጋዴን አካባቢ ያሉ ጐሳዎች ‹‹የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል›› የሚለው አንቀፅ በህዝበ-ውሳኔ እልባት እንዲሰጠው ተመኝተው ባለመሳካቱ የራሳቸውን የትግል አማራጭ ቀይሰዋል፡፡ አሁንም ሊካሄድ ታስቦ የነበረው የሰላም ስምምነት ይህንን እውነታ ታሳቢ ማድረግ ነበረበት፡፡ በቀጣዩም ከዚህ ማዕቀፍ የሚወጡ ማናቸውም የሰላም ስምምነቶች ይህንን የታሪክ እውነት ትቶ ውጤታማ ይሆናል የሚል እምነት የለኝም፡፡

> <u>የኦብነግን ወደ ስልጣን መምጣት ኦጋዴናውያን ያልሆኑ ሌሎች ጐሳዎችን በፍርሃት ውስጥ እንዲወድቁ አድርጓቸዋል፡፡ ኦብነግ በሶማሊያ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ጎሳዎች መካከል ግማሽ ያህሉን የኦጋዴን ጎሳ አባላትን ይወክላል፡፡ ፍርሃታቸው የተለያየ መሰረት ቢኖረውም በጊዜው የሌሎች ጎሳ አባላት ድርጅቱን በዋናነት እንዲፈሩት ያደረጋቸው የኦብነግ ወቅታዊው አላማ መሆኑን ብዙዎቹ ይስማማሉ፡፡</u>

## የኦጋዴን ጦስ

<u>ማሳያ 2</u>፡- ከታሪካዊ ማንነት በተጨማሪ የአካባቢው ሌላኛው ችግር ሆኖ የወጣው የፌዴራል ሥርዓት አተገባበር ያስከተለው ግርግር ነው፡፡ የብሔር ፌዴራሊዝም በሌሎች ክልሎች የታየውን ዓይነት ቀላል አፈፃፀም በሶማሊያ ክልል ማምጣት አልቻለም፡፡ የብሔር ፖለቲካው እንደ ሌሎች ክልሎች መሰረተ ልማትን፣ መሰረታዊ አገልግሎትን እና አቅርቦትን ከማሟላት ይልቅ በብሔሩ ውስጥ በሚገኙ ቡድኖች መካከል ያለውን ጤናማ ግንኙነት ‹‹በስልጣን ይገባኛል›› ፉክክር ውስጥ እንዲገቡ አስገድዷቸዋል፡፡ ይህ በበኩሉ ብዙኀኑን በተለይ ከከተማ ወጣ ብሎ የሚገኙ ጐሳዎችን እንዲከፉ ከማድረጉም በተጨማሪ በስርዓቱ ላይ ያላቸው እምነት ክፉኛ እንዲላላና ለሌሎች የውጪ ኃይሎች መጠቀሚያ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ የብሔር ፖለቲካው ውዥንብር በዚህ ብቻ የሚያበቃ አይደለም፡፡

ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ከመጣ ወዲህ ከወሰዳቸው እርምጃዎች መካከል የፖለቲካ ፓርቲ መመስረትን ህጋዊ መሆን ይፋ ማድረግ አንዱ ነበር፡፡ የዚህ አዋጅ አንዱ ውጤት በሶማሌ ክልል ጎሳን ማዕከል ያደረጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲፈለፈሉ ምክንያት መሆኑ ነው፡፡

ኦብነግ በክልሉ በተካሄደው የመጀመሪያ ምርጫ በከፍተኛ ውጤት በማሸነፉ በሶማሌ ክልል መንግስት እንዲመሰርት አስችሎት ነበር፡፡ ይህንን ውጤት ተከትሎ የብሔር ፖለቲካው በክልሉ ያለው ትግበራ ፈተናውን ጀመረ፡፡ የኦብነግን ወደ ስልጣን መምጣት ኦጋዴናውያን ያልሆኑ ሌሎች ጐሳዎችን በፍርሃት ውስጥ እንዲወድቁ አድርጓቸዋል፡፡ ኦብነግ በሶማሊያ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ጎሳዎች መካከል ግማሽ ያህሉን የኦጋዴን ጎሳ አባላትን ይወክላል፡፡ ፍርሃታቸው የተለያየ መሰረት ቢኖረውም በጊዜው የሌሎች ጎሳ አባላት ድርጅቱን በዋናነት እንዲፈሩት ያደረጋቸው የኦብነግ ወቅታዊው አላማ መሆኑን ብዙዎቹ ይስማማሉ፡፡ ኦብነግ በጊዜው የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ለኦጋዴን ጎሳ አባላት እና ለክልሉ እንዲሰጥ መጠየቁ ሌሎቹን በሶማሌ ውስጥ ያሉ ጐሳ አባላት አደጋ ውስጥ የመዘፈቃቸውን እውነት እንዲጋፈጡ እንደሚያደርጋቸው መጠርጠራቸው ነው፡፡

ይህንን የኦብነግ አላማ ተከትሎ የኢትዮጵያ መንግስት በክልሉ የወሠደው ተደጋጋሚ ወታደራዊ እርምጃ ጣልቃ ገብነት እንዲሁም የምርጫ ማጭበርበር ተግባራት ድርጅቱን ከሽግግር መንግስቱ ወጥቶ አመፅን አማራጭ እንዲያደርግ ማስገደዱን የተለያዩ ድርሳናት ያወሳሉ፡፡ የኦጋዴን ጎሳ አባላትን የሚወክለው ድርጅት ስልጣኑን ጥሎ መውጣት ተከትሎ የኢትዮጵያ መንግስት ከዚህ ጎሳ አባላት ውጭ ያሉ ልሂቃን ተደራጅተው ክልሉን መምራት እንዲጀምሩ አደረገ፡፡ ለዚህ ፖለቲካዊ ለውጥ አንዱ ማሳያ ለኦጋዴናውያኑ ትቀርብ የነበረችውን የክልሉን ዋና መቀመጫ ጎዴ በመቀየር ወደ ጅጅጋ የተዛወረበት ሁነት አንዱ ነው፡፡ ይህ መገለል በክልሉ ግማሽ የሚሆነውን ህዝብ (ኦጋዴናውያኑን) ያስከፋ ከመሆኑ በተጨማሪ የብሔር ፖለቲካው ሁሉን አሳታፊ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ የሰላም ስምምነቱ ከዘነጋቸው ነጥቦች መሀከል ሌላኛው እውነታ ይህ ነው፡፡ ስለዚህ ድርድሩን ለማድረግ የፖለቲካ ሥልጣን ክፍፍሉን ፍትሃዊ አድርጎ መጀመር ይገባል፡፡

## <u>የ‹ጎሳ› ፖለቲካ</u>

<u>ማሳያ 3</u>፡- የሶማሌን ክልል ለመምራት የሚመረጡ የገዢው ፓርቲ አመራሮች ክልሉን እና ዞኖችን ለማስተዳደር የተሰጣቸውን ህጋዊ ስልጣን በመጠቀም ሌሎች አስተዳዳሪዎችን በየደረጃው እስከታችኛው እርከን ድረስ እንዲመርጡ እድሉን ያገኛሉ፡፡ ለተከታይ የስልጣን እርካብ አገልጋይ ይሆናቸው ዘንድ ቀዳሚ ምርጫ የሚያደርጉት ከራሳቸው ጎሳ የሚወከሉ ግለሰቦችን መመደብ ነው፡፡ ፐ/ር አብዲ ሰማተር “Ethiopia federalism: autonomy versus control in the Somalia region” በሚለው ፅሁፋቸው በክልሉ ያለውን መሰረታዊ ተግዳሮት በተለይ ከጎሳ ፖለቲካ ጋር በተያያዘ ያለውን የተዛባ አተረጓጎም በሚገባ አስቀምጠውታል፡፡

በክልሉ እስከታች ድረስ በሚዘልቀው አስተዳደራዊ መዋቅር ውስጥ ተመሳሳይ ጎሳ ካላቸው ቡድኖች የተውጣጡ ግለሰቦችን ማየት የተለመደ ክስተት ነው፡፡ በዚህ መንገድ ወደ መንበሩ ለሚመጡ ግለሰቦች ስልጣን የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን በማስገኘቱ የሌሎች ጎሳ አባላትን ከማስከፋቱም በላይ በጐሳዎች መካከል ለፖለቲካ ስልጣን የሚደረገውን ፉክክር ይበልጥ አግኖታል፡፡ ይህንን ፉክክር በአሸናፊነት ለመወጣት ሲባል የየጎሳዎቹ ልሂቃን የየራሳቸውን አባላት በተለያየ መንገድ ወደ መደገፍ እና ማጠናከር እንዲገቡ አድርጓቸዋል፡፡

የዚህ አካሄድ አደገኛነቱ በተለይ በክልሉ ጉልቶ የወጣው ልሂቃኑ ጎሳቸውን ለማጠንከር እና ፀጥታ ለማስጠበቅ በሚል የሚያስታጥቁት የጦር መሳሪያ በክልሉ ለተነሱት የጎሳ ግጭቶች ትልቅ ማቀጣጠያ በመሆን አገልግሏል፡፡ በተለይ የ‹‹እኛ ጎሳ በክልሉ የፖለቲካ ስልጣን ክፍፍል የሚገባውን የስልጣን እርካብ አላገኘም›› ወይም ‹‹ከሌሎቹ የጎሳ አባላት አንፃር ሲታይ በፖለቲካ ስልጣን ያለው ውክልና በጣም አነስተኛ ነው›› በሚል ሰበብ የሚያነሱት አምባጓሮ ትልቅ ቁሳዊና ሰብዓዊ ጥፋቶችን አስከትሏል፡፡ አሁንም እያስከተለ ነው፡፡ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ጐሳዎች በነፍስ ወከፍ የታጠቋቸው መሳሪያዎች ከእርስ በርስ ፍጅት በተጨማሪም ለተለያዩ የውጭ ኃይላት መጠቀሚያ መሆናቸው ችግሩን ውጫዊ ይዘት እንዲኖረው አድርጎታል፡፡ ይህ ተደጋጋሚ ውስጣዊ እና ውጫዊ ተግዳሮቶች በክልሉ የሚነሱ የእርስ በርስ ግጭቶችን በአጭሩ ለመቋጨት አስቸጋሪ እንዲሆን አድርጐታል፡፡

የአሁኑም የሰላም ስምምነት ከዘለለው እውነት አንዱ በክልሉ መሰረት ያለውን የጎሳ አመለካከት ቅራኔ ለመፍታት የሚያስችሉ ማዕቀፎቹን ለመዘርጋት አለመቻሉ ነው፡፡ ከአሸባሪ ድርጅት ጋር የሰላም ስምምነቱን ለማድረግ ከመወሰን በፊት ቅድሚያ ሊቀረፍ የሚገባው በጠባብ የጎሳ አመለካከት የታጠረውን የፖለቲካ ከፊፍ አሻሽሎ ሁሉንም አሳታፊ የሆነ የፖለቲካ ስርዓት ማስቀደም ነበር፡፡

## <u>የሸፈተው ልብ</u>

<u>ማሳያ 4</u>፡- ሌላኛው የሰላም ስምምነት ክሽፈት ትልቁ ክፍተት የኢትዮጵያ መንግስት የብዙሃኑን የክልሉ ነዋሪዎች ልብ መማረክ ሳይችል ከአሸባሪው ድርጅት ጋር ለመደራደር መሞከሩ ነው፡፡ በክልሉ በተደጋጋሚ የተከሰቱ ግጭቶች ዳፋ የተረፈው በአካባቢው ለሚኖሩ ዜጐች ነው፡፡ በተለይ ከመስከረሙ የአሜሪካው ጥቃት በኋላ በአለም ላይ የተከፈተው ‹‹ፀረ-ሽብርተኝነት ዘመቻ›› በተዘዋዋሪ በአለም ላይ ያሉ ከደሙ ንጹህ የሆኑ ሙስሊሞችን ያገለለ ነበር፡፡


የኢትዮጵያ መንግስት በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የአሜሪካ የፀረ-ሽብር ዘመቻ ተባባሪ ሆኖ መቅረቡና የዚህ ዘመቻ አንድ አካል የሆነውን የሶማሊያ ጦርነት ለማድረግ ወደ ሶማሊያ መዝለቁ በኢትዮጵያ ያሉ ሶማሌያውያን እንዲከፉ አድርጓቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በተለይ ከመሃል እርቀው በሚገኙ እንደ አፋር፣ ቤኒሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ ሁሉ ሶማሌያውያንም በትላልቅ የመንግስት ተቋማት ላይ በኃላፊነት ያለመመደባቸው እውነታ በአገራዊ ማንነት ጥያቄያቸው ላይ ሌላ ክፍተት በመፍጠር በስርዓቱ ቅር እንዲሰኙ ከማድረጉ በተጨማሪም መንግስት በክልሉ የተሰማራውን አሸባሪ ቡድን ለመቅጣት በወሰዳቸው እርምጃዎች የብዙሃኑን ንፁሃን ዜጎች ደም ያፈሰሰ መሆኑን የተለያዩ ተቋማት ማረጋገጣቸው ማህበረሰቡ ቅራኔያቸው ቀጥታ ከመንግስት ጋር እንዲሆን አድርጎባቸዋል፡፡ የዚህ ድምር ውጤት መንግስት በክልሉ የሚወስዳቸውን ማናቸውም በጎ እርምጃዎች ነዋሪዎች በበጐ አይን እንዳይመለከቱ ዳርጓቸዋል፡፡ መከፋታቸውን ለመግለፅ ከሚጠቀሙባቸው ማሳያዎች አንዱ በክልሉ የሚካሄዱ መሰረተ ልማቶችን ማፈራረሳቸው ተጠቃሽ ነው፡፡

ከላይ ከተገለፁት የክልሉ ፖለቲካዊ ችግሮች መካከል ሌላው ሁሉን አቀፍ የሆኑና የተደራጁ የሲቪል ማህበራት አለመኖራቸው ሲሆን፤ ሰብዓዊ እርዳታ ለመለገስ ወደ ክልሉ የሚመጡ የረድኤት ድርጅቶች በአብዛኛው በክልሉ የሚያቀርቡት ሰብዓዊ እርዳታን አስመልክቶ የሚያቀርቡት ዘገባ የተዛባ ምልከታ አለው፡፡ በክልሉ የተሰማሩ የረድኤት ድርጅቶች በስልጣን ላይ ያሉትን የተወሰኑ ቡድኖች እና የሚወከሉባቸውን ጐሳዎች ከመጥቀም ያለፈ ሁሉን

ወደ ገፅ 32 ዞሯል

## የመፅሐፍት ዳሰሳ

# በጠለፋ ስሌት መቋቋሙን ‹ባለመረዳት/ ለመረዳት ባለመፈለግ› ዕውን የሆነው የአቶ ደረጀ ‹‹460 ቀናት በመንበረ ፓትርያርክ›› ቆይታ



ብርሃኑ ደቦጭ
*(የታሪክ ተመራማሪ)*

ርዕስ፦ 460 ቀናት በመንበረ ፓትሪያርክ
ደራሲ፦ ደረጀ ተክሌ
የታተመበት ዓም፦ መስከረም 2005ዓ.ም
ገጽ፦ 165
አታሚ፦ ኢንተርናሽናል ሊደርሺፕ
የህትመት ሥራ
ዋጋ፦ ብር 35

---

መጽሐፉ ጥንድ ጥንድ ርዕሶች የቀረቡባቸው 23 አጫጭር በጸሐፊው አሰያየም ‹ክፍሎች› ያሉት ሲሆን፤ ይዘቱን ለዚህ አስተያየት በሁለት አንጓዎች ልንከፍላቸው እንችላለን፡፡ አንደኛው ስለአጣሪ ኮሚቴው (አቋቋም፣ አሠራርና ውጤቱ) የሚያትት ሲሆን፤ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ጸሐፊው ለማጣራት በተሠጣቸው ኃላፊነት ጊዜ በመንበረፓትሪያርኩ ያዩትን የሰሙትንና የታዘቡትን እንዲሁም በቅጽሩ ውስጥ የሚካሄደውን በቅጡ ለማናውቀው አንባቢዎች ያደረሱበት ክፍል ነው፡፡ ከፍሬነገሩ ክብደት አንጻር ስለሁለተኛው አንጓላይ ጥቂት ብልም የዚህ አስተያየት ትኩረት የመጀመሪያው አንጓ ይሆናል፡፡ በመጀመሪያው አንጓ አስተያየቴ በመሰረታዊው ውሱንነቱ ላይ ለማተኮር መገደዬን በቅድሚያ መግለጽ እወዳለሁ፡፡ ከውሱንነቶቹ መካከልም ሁለቱ ላይ ብቻ አተኩራለሁ፡፡ እነርሱም ጸሐፊው የቤተክህነት አስተዳደር ችግር የተፈጠረበትን ሁነት ከፖለቲካዊ አውዱ ለይተው ማየታቸውና ኮሚቴው ጥቅም ላይ የዋለበትን የጠለፋ ስሌት ‹ያልተረዳው/ ሊረዳ ያልፈለገ› መሆኑ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጪ ጸሐፊው በእንዲህ ዓይነት ታላቅ ኃላፊነት ለማገልገል ፈቃደኛ መሆናቸውና ብዙ አጣሪ ኮሚቴዎች በተለያዩ ተቋማት ቢዋቀሩም፣ የደረሱበትንና የታዘቡትን እንዲህ በመጽሐፍ መልክ አዘጋጅተው በማቅረብ እኔ በቅርብ ከማስታውሳቸው ምናልባት የመጀመሪያው መሆናቸው የፈጠረብኝን አክብሮት መሸሽግ አልችልም፡፡ አንድ ሰው ብቻውን ይሄን ማድረግ ስለመቻሉ ክርክር ቢነሳም፤ የዚህ መጽሐፍ አቀራረብ ግን ሁለት አንጓ ያለው መሆኑ የሚቻል መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለዚህ አክብሮቴንም የትኛውም አስተያየቴ እንደማይቀንስብኝ የምገልጸው የዛሬ 37/8 ዓመት ስለተካሄደው የአጣሪ ኮሚሽን ሥራና አስተዋጽኦ በአግባቡ ባለመዘገቡ ጭቅጭቁ እስካሁን መቀጠሉ እየታሰበኝ ነው፡፡

### የተፈጠረበትንፖለቲካዊ አውድ የዘነጋው የቤተክህነት አስተዳደር ችግር

በሐምሌ 10 2001 ዓም የተጠራው አጣሪ ኮሚቴ በጥቅምት 14 ቀን የመጀመሪያ ሪፖርቱን በ17 ገጽ አቅርቧል፡፡ መጽሐፉ ጸሐፊው ለአባልነት ከተጠሩበት ጊዜ ጀምሮ የሥራውን ሂደትና ያጋጠሙ ችግሮችን በተለያዩ ርዕሶች እየቋጠሩ አቅርበው የ17 ገፁን ሪፖርት ዋና ፍሬ ሃሳብም አቅርበዋል፡፡ በሪፖርቱም ሆነ (በእጄ ላይ ይገኛል) በመጽሐፉ ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ግን ለአጣሪ ኮሚቴው መቋቋም ምክንያት የሆነውን የቤተክህነት አስተዳዳር ችግር የተፈጠረበትን ፖለቲካዊ አውድ ሳይነኩ አልፈዋል፡፡ ይህ ርዕስ በአጣሪው ኮሚቴ ቅድሚያ ግምት ሊሰጠውና ሊተነተን የሚገባውና የነበረ ጉዳይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን (ከዚህ በኋላ ኢኦተቤ ወይም ቤተክርስቲያኗ) በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ መጠነ ሰፊ ቦታ ያላት ተቋም ናት፡፡ በዚህም ምክንያት በአገሪቱ የሚከሰቱ ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ ተጽዕኖ እንዳላት ሁሉ እርሷም ከተለያዩ አቅጣጫዎች በሚመጡ ኩነቶች ተጽዕኖ ሥር መሆኗ አይቀርም፡፡ በተለይ የመንግሥትና ቤተክህነት ግንኙነት አሉታዊና አዎንታዊ ውጤቱን እያስመዘገበ ለዘመናት ሲሻገር ቆይቶ አሁን ያለንበት ደረጃ ደርሷል፡፡ ከቤተክህነቱ አንጻር ጥቅሙ ኢኮኖሚያዊና ሌሎች ከለላዎች ሲያስገኙለት፤ መንግሥትን የጠላ ሁሉ ቤተክርስቲያኗንም እንዲቃወም አድርጓል፡፡ የኢኦተቤንን ከግብፃውያን ጳጳሳት ነጻ ለማውጣት በተደረገው ትግልም የመንግሥት ሚና በጣም ከፍተኛ ነበር፡፡ ይህ ነጻነት ግን ቤተክርስቲያኗን ከመንግሥት ተጽዕኖ የሚያላቅቃት አልነበረም፡፡ የቤተክህነቱን አስተዳደር የሚያበለፅጉ ሕጎችና አሠራሮች ቢወጡም፤ ሹመት ለመንግሥት/ለንጉሡ ባለ ታማኝነት ላይ የተመሰረተ ሆኖ ዘልቋል፡፡ ይህም የቤተክህነቱን አስተዳደር አቅመቢስና ውሽልሽል እንዳደረገው ጥናቶች ያመለክታሉ (ኃይለማርያም ላሬቦ ‹‹Ethiopian Orthodox Church and Politics in the 20th Century››)፡፡

የንጉሡ አስተዳደር ሲያልፍም ደርግ የሃይማኖትና መንግሥት መለየትን አውጆ የቀደመ ‹ጥቅማ ጥቅሟን› ቢነሳትም፤ የቤተክርስቲያኗን ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት እንደአሴት ለመጠቀም ከመሞከር ወደኋላ አላለም፡፡ የቤተክህነትን አስተዳደርም በቀጥታና በወንጭፍ ሲቆጣጠር ቆይቷል፡፡ ደርግ ወደሥልጣን ሲመጣ ፕትርክናው ላይ የነበሩት አቡነ ቴዎፍሎስ ለሦስት አባቶች የሰጡት ሥልጣነ ጵጵስና ቤተክህነቱ ነጻ ሥልጣኑን የመጠቀም ሙከራ አድርጎ በመውሰድ ፓትርያርኩን ‹ገለል› አድርጓል፡፡ ይህን ተከትሎ በዚህ አገዛዝ የተካሄዱት የአዳዲስ ፓትርያርኮች አመራረጥና ቤተክህነቱ አካባቢ ላሉ ከፍተኛ ሥልጣኖች የሚመደቡ ሰዎች ሹመት ፖለቲካዊ አንድምታው ግልጽ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ እንደውም የሶሻሊዝም አይዲዎሎጂንና የእምነቱን አስተምህሮ በአንድ ለማስኬድ የቃጣቸው እንደነበሩ ተመዝግቧል፡፡ በ1971 ዓም ቀድሞ የነበሩትን ሥራ አስኪያጅ አንስቶ የለወጣቸው የአዲሱ ሥራ አስኪያጅ ፍልስፍናን ለዚህ እንደማሳያ ማቅረብ ይቻላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ፈተና የቤተክርስቲያኗን ክብር በመሪዎቿ ‹አድርባይነት› የሚፈትን መሆኑ አይቀርም፡፡ 3ኛው ፓትርያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ‹‹ታይታንና ብርቅርቅታ››ን በተጸየፈ አኗኗርና ለችግርተኞች በሚያስብ የመንፈሳዊ ስብእና ልእልና በማካካስ ተሳክቶላቸዋል ማለት ይቻላል፡፡

በቀጣዩ በኢህአዴግ አገዛዝም ወደፕትርክናው የመጡት የአዲሱ ፓትርያርክ አቡነ ጳውሎስ አመራረጥም አነጋጋሪ ሆኖ መዝለቁ የሚብራራው ከዚሁ ከፖለቲካው ከባቢ አንጻር መሆኑ ግድ ነው፡፡ በእርግጥ የ1987ቱ ሕገመንግሥት በሃይማኖትና በመንግሥት መካከል ስላለው ልዩነት የበለጠ የሚያስረግጥ ቢሆንም፤ በተግባር እንደሚታየው የሃይማኖት ተቋማትን ለመቆጣጠር የተለያዩ ዘዴዎችን ስለመጠቀሙ መተቸቱ አልቀረም፡፡ በተለይ የዘውጌ ወገንተኝነትና የሙስና/ ዝርፊያ ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ ያደገ እንዲሆን ማድረጉ ዋንኛው ነው፡፡ ይህንን መሰረታዊ ችግርም ተስፋ የተጣለበት የአዲሱ ፓትርያርክ የትምህርት ደረጃ ብቻውን የሚያካክሰው መሆን የቻለ አይመስልም፡፡ ለዚህ ደግሞ የፓትርያርኩ አወዛጋቢ ስብእና ችግሩን የሚያገዝፍ መሆኑ ነው፡፡ ስለአመራረጣቸው ቀድሞ በአንዳንዶች ከሚነሳው በተጨማሪ ለፕትርክና መሰረታዊ ከሚባሉት ከነዚህ ድርጊቶች መራቅ አልቻሉም የሚለውን ወቀሳ የተሸከመው ፕትርክናውን ራሱን በዘመነ ሲመታቸው ጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ምዕመኖች እንዲኖሩና እሳቸውም በተለየ መንገድ የፕትርክናቸውን ተገቢነት እንዲከላከሉ ያስገደዳቸውን ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ለምሳሌ ከ1985ዓ.ም ጀምሮ የወጡት ‹የነጻው ፕሬስ› ህትመቶች በየምክንያቱ ይሄንን ጉዳይ ርዕስ ማድረጋቸው የዘወትር ሁነት ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ በውጪ ይታተም የነበረውና ከአራት አመታት በላይ የዘለቀ ዕድሜ ያልነበረው ‹ኢትዮጵያን ሪቪው› መጽሔት እ.ኤአ በ1992ዓ.ም በጥቅምት፣ ካቲት፣ መጋቢት፣ ሚያዝያ፣ ሰኔ፣ ሐምሌ እና ነሐሴ ወራቶች ያወጣቸው ጽሑፎች ኢኦተቤንን የተመለከተው ዋንኛው ጉዳይም ፕትርክናውን የተመለከተ መሆኑ ሲታሰብ የነገሩ ክብደት ሊሰማን ይችላል፡፡ ተከላካዩ መልሱን በቤተክህነቱ ስር በሚታተመው ‹ዜና ቤተክርስቲያን› ብቻ ሳይሆን በአዲስ ዘመን ጋዜጣም ከማቅረብ አልተገተም፡፡ ልክ እንዲሁ አቡነ መልከጼዴቅ ‹‹የቋሚ ምስክርነት›› በሚል ርዕስ ስለአቡነ መርቆሬዎስ ከአሜሪካ የጻፉትና መምህር ኪዳነማርያም ‹‹የሀሰት ምስክርነት›› በሚል ርዕስ ከኢትጵያ የሰጡት ግብረመልስ የዚህ ክስና ተከላካይነት ሌላ ማሳያ ነው፡፡ በጠቅላይ ቤተክህነቱ ስም የወጣው ‹‹ዜና መዋዕል ወብፁእ ቅዱስ አቡነ ጳውሎስ›› እስከ140ዎቹ ገጾች ድረስ ስለፓትርያርኩ የገድል ያህል የሚተርኩ ‹ታሪኮች› ይዞ መውጣቱም የዚሁ የቅቡልነት ጥያቄ ማሳያ ነው፡፡

ሌላው የፓትርያርኩ አወዛጋቢ ስብዕና መገለጫ ተደርጎ የሚወሰደው የቤተክህነቱን ሥልጣን አጠቃሎ ለመያዝ የመፈለግ አባዜ

ያሳያሉ የሚባለው እና ለመንግሥት አስተሳሰብ ፍቅር አላቸው መባሉ ነው፡፡ ሌሎች ጉዳዮችን ቢያካትትም ዲያቆን በጋሻው ‹የመስቀሉ ስር ቁማርተኞች›› በሚል ርዕስ የጻፈውና ዘሪሁን ሙላቱ የተሰኘ ፀሐፊ‹‹የስድብ አፍ›› (1998ዓም) ብሎ የመለሰው፤ ፍሬ ነገር ከየሚያተኩሩባቸው ጉዳዮች አንዱ ፓትርያርኩ በመንግሥታዊ ተቋማት ላይ ያላቸው መታመን ላይ ጥያቄ የሚያነሱና መልስ የሚሰጡ ናቸው፡፡ የመጀመሪያውን ጉዳይ አስመልክቶ በ1988 ዓም ያለሲኖዶሱ ይሁንታ ህገ ቤተክርስቲያንን ለማሻሻል ባደረጉት ሙከራ ግልጽ አድርገዋል ተብለው ይተቻሉ፡፡ የሲኖዶሱን ሥልጣን የመቀነስ(ፓትርያርኩን የበላይ ለማድረግና የቤተክህነቱን ሁለት ከፍተኛ ስልጣኖች በአንድ ሰው ሥር በማድረግ ተጠሪነታቸውንም ለፓትርያርኩ በማድረግ) ሙከራው ግን ብዙ ውርክብ የፈጠረ ብቻ ሳይሆን በ1990 ዓም በቤተክህነቱ ውስጥ ታየ ስለሚባለው የአድልዎ አሠራር፣ የአስተዳደር በደልና ምዝበራ እንዲያጠና አጣሪ ኮሚሽን እንዲቋቋም አስገድዷል፡፡ የኮሚሽኑ ሪፖርት ከቀረበ በኋላም በ1991 ዓም ሕገ ቤተክርስቲያን ተሸሽሏል፡፡ ተገቢውን ለውጥ ማምጣት ባለመቻሉ ይመስላል በ2001 ግንቦት ዓ.ም ላይ ሲኖዶሱ የሊቃነጳጳሳት ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በማቋቋም የተጓደሉ የቤተክህነት አስተዳደር ጉዳዮችን ‹መልክ› ለማስያዝ እርምጃ መውሰድ ይጀምራል፡፡ ይህን ተከትሎም በወቅቱ እንደተዘገበው በኮሚቴው ውስጥ የተጉት ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ይደርሳል፡፡ የቤተክህነቱ ፖለቲካ በጦዘበት በዚያ ወቅት ፓትርያርኩ ህገ ቤተክርስቲያንን የሚያጠና ኮሚቴ ሰየሙም ተባለ፡፡ ቀጣዩ የሲኖዶሱ ስብሰባ ጉዳዩን ያነሳል ተብሎ ሲጠበቅ፤ ንትርኩና አጀንዳው በአስፈጻሚው ኮሚሽን ውስጥ ትጋት ከነበራቸው አንዱ በሆኑት አቡነ ሳሙኤል ‹በሚመሩት› በአ.አ ሀገረ ስብከት ዙሪያ ስለተፈጠረ የአስተዳደር ችግርና ሕንጻ ግንባታ ወጪ ማጣራት እንዲያነሳ ይደረጋል፡፡

## የፓትሪያሪኩ የጠለፋ ስሌትን ‹ያልተረዳው/ ሊረዳ ያልፈለገው›
## የጋሽ ደረጀ ‹‹460 ቀናት በመንበረ ፓትርያርክ›› ቆይታ

እንግዲህ እዚህ ጋር ነው የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ አባል የሆኑበት የአጣሪ ኮሚቴ የተዋቀረውና ለዛሬው ርዕሰጉዳይ መነሻ የሆነውን ሪፖርት ለማጠናከር የበቁት፡፡ ሁኔታውን የሚተቹ ክስተቱን ‹‹የሊቀ ጳጳሳቱን ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እርምጃ ባኮላሸው ድብደባ የተጠለፈ የሲኖዶስ ውሳኔ›› ይሉታል፡፡ እንደአቶ ደረጀ ግን ይህንን ለመረዳት የሚያስችል ደረጃ ላይ ‹አልነበሩም›፡፡ እንደእኔ እንደእኔ የፈለጉም አልመሰለኝም፡፡ እርሳቸው በመጽሐፉ እንዳስቀመጡት ለኮሚቴ አባልነቱ አጠራራቸው፣ ሥራውን ለመጀመር ስብሰባ አካሂደው ለሊቀመንበርነትና፣ ጸሐፊነት ሲመራረጡም ሆነ ፓትርያርኩ ዘንድ ሄደው መመሪያ ሲቀበሉ ለኮሚቴው መፈጠር ምክንያት የሆነውን የኋላ ታሪክ አያውቁም፡፡ እንደ ጸሐፊው ለአጣሪው ኮሚቴ መፈጠር ‹መንደርደሪያ› ያሉትን የውዝግብ መንስኤ ያወቁት መዝገቦችን አሰባስበው ማጥናት ከጀመሩ በኋላ ነው (ገጽ 16 ወይም በመጽሐፉ አራተኛ ክፍል መጨረሻ ላይ ነው)፡፡ ይህም የኮሚቴው አባሎች የሚጠበቅባቸውንና የኃላፊነቱን ተገቢነት ከወዲሁ ለማገናዘብ መልካም መነሻ የነበራቸው ስለመሆኑ ማረጋገጥን ከባድ ያደርግባቸዋል ማለት ነው፡፡ እንዲህም ሆኖ ለኮሚቴው ከተመለመሉት ሊቀመንበር እንዲሆኑ የተመረጡት ፕ/ር ጥላሁን ተሾመ በመጀመሪያ ቀጥሎም እንዲሁ ለምትክ ሊቀመንበርነቱ የታጩት ኢንጂነር ጌታቸው ማኅተመ ስላሴ በኮሚቴ አባልነት ላለመሥራት በገዛ ፈቃዳቸው ራሳቸውን ማግለላቸው ለቀሩት አባላት የሚያስተላልፈው መልዕክት እንዳለ ይገመታል፡፡ እንደውም ጉዳዩ ከበስተጀርባው ብዙ ችግር እንዳለበት ይገመትና በለቀቁት አባላት ምክንያት ኮሚቴው ተስፋ ቆርጦ መሥራት እንደማይችል ዘርዝሮ ያመለክትና ይሰናበታል፡፡ ይሁን እንጂ ከጥቂት ቀናት በኋላ በስልክ ጥሪ (ምናልባት በአንድምታው ልዩ የስልክ ጥሪ) ብቻ ያለምንም ለውጥ (የአባልም ሆነ ሌላ ነገር ለውጥ አልነበረውም፤ ስለዚህ አንድ የኮሚቴ አባል ተቃውሞታል) ኮሚቴው ‹ሥራውን› ለመቀጠል ይስማማል፡፡


የዚህን ዓይነት ስምምነት ላይ ለመድረስ የተቻለበትን ተጠየቅ ግን ጸሐፊው ሳያብራሩልን ይቀራሉ፡፡ ይህን አለማብራራት ደግሞ ተራ ዝንጋዔ ነው ለማለት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ አንዱ መላምት የኮሚቴው የገለልተኝነት ብሎም የተዓማኒነትን ደረጃ በመፈተሽ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ መጀመሪያ የሚታየው ኮሚቴው ገለልተኝነቱን ለማስረገጥ የሄደባቸው መንገዶች ናቸው፡፡ ከዚህ ውስጥ አንዱ ደግሞ ኮሚቴው ሥራውን ለመሥራት የሚመርጠው ቦታ ለገለልተኝነቱ ወይም በገለልተኝነቱ ላይ የሚኖረው ፋይዳ ታሳቢ ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ የቤተክህነት ውርክብ ምክንያት በ1990ዓ.ም የተቋቋመው የአጣሪ ኮሚሽን ለሥራው ‹አመቺነት› ከመንበረ ፓትርያርኩ ግቢ ውጪ ከአንድም ሁለት ቦታ ቀይሯል፡፡ እንዲህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነውን ይሄን ልምድ ኮሚቴው አለመውሰዱ ለብዙ ነገር ተጋላጭ አድርጎታል፡፡ ከእነዚህ አንዱ ራሳቸው ጸሐፊው ከቢሯቸው ያስቀመጡት ደብዳቤ እንዲጠፋቸው መሆኑ ነው፡፡ ይህም ቢሮው አስተማማኝ እንዳልሆነ ማሳያ ነው፡፡ የተመደበላቸው ተሽከርካሪም በሌላ ቁልፍ መከፈቱን ያወቁት እንዲሁ በአንድ አጋጣሚ ከመሆኑ አኳያ የ‹ማጣራቱ› ሂደትን ምስጢራዊነት ለመጠበቅ የሚያስችል የሥራ ቦታ እንዳልሆነ ይጠቁማል፤ ሰብሳቢው/ጸሐፊው/ኮሚቴው ይህ እንዲሆን ፈቅዶ ካልሆነ በስተቀር፡፡ እንዲህ እንዲህ እያልን ሁኔታውን ከገፋነው ደግሞ የመጽሐፉ ጸሐፊ/ የኮሚቴው ሰብሳቢ አስተዳደራዊ ችግሩን አስመልክቶ የመጀመሪያውን ሪፖርት ጥቅምት 14 ቀን 2002ዓም ከማቅረባቸው በፊት ጥቅምት 9 ቀን 2002 ዓም ለፓትርያርኩ ቤተክህነት ከሚያከራያቸው ቤቶች በአንዱ ተከራይተው እንዲኖሩ ጥያቄ ማቅረባቸው፤ ሪፖርቱ ከቀረበ በኋላም ጥቅምት 18 የተፈቀደላቸው መሆኑን በመጥቀስ ጠቅላይ ጽ/ቤቱ ለሚመለከተው ክፍል እንዲጽፍላቸው መጠየቃቸውና በ24/2/2002ዓም ከየካቲት 1 ቀን 2002 ጀምሮ ተገቢውን ክፍያ እየከፈሉ እንዲኖሩ መፈቀዱ የገለልተኝነቱን ጥያቄ በማስረጃ ያስደግፈዋል፡፡ በነገራችን ላይ ይህንን ሁኔታ መጽሐፉን ለመገምገም የተለያዩ መረጃዎችን በማሰባሰብ ሂደት ያገኘሁ ባልሆንና የመጽሐፉ ጸሐፊ ቀድመው በመጽሐፋቸው ላይ የጠቀሱት ቢሆን ኖሮ በዚህ ረገድ የሚነሳባቸውን ትችት ያለሳልስ ነበር፡፡ በነገራችን ላይ የጸሐፊው ቢሮ በመንበረ ፓትርያርኩ ቅጽር ውስጥ መሆኑ ጥቅም አልነበረውም ለማለት አይደለም፡፡ አንደኛ ስለሚያጣሩት ጉዳይ ባለቤቶቹ ቀንና ማታ የሚያሳዩት ጠባይና አጠቃላይ ስነልቦና ለመረዳት ያስቻላቸውን አጋጣሚ አግኝተውበታል፡፡ ይህም መረዳት በቅጽሩ ውስጥ ስለሚሆነው ሁኔታ በዓይነ ህሊናችን ግድግዳ ስዕል ስሎ የማሳየት ያህል ባቀለሉልን ገለጻቸው ተመስክሯል፡፡ በእርግጥ በዚህ አንድ ዓመት ከሁለት ወር ቆይታቸው ጸሐፊው ቢፈልጉ በግል ካላቸው ከሰው ጋር የመግባባት ችሎታ፣ የትምህርታቸው ዝግጅትና ልምድ እንዲሁም ሰፊ ንባብ (በሌላ የሥራ አጋጣሚ የማውቃቸው መሆኑን መግለጽ ይገባኛል) ተደግፈው የሰፋ ዝርዝር ሊሰጡን ይቻላቸው እንደነበር እመሰክራለሁ፡፡ በአንድ የንጉሱ ዘመን ታዋቂ ኢትዮጵያዊ የሕይወት ታሪክ ዙሪያ ያወጡታል ተብሎ በጉጉት የሚጠበቅ መጽሐፍ አላቸው፡፡

ዞሮ ዞሮ አጣሪ ኮሚቴው ሥራውን ከሠራ ድምዳሜው መታወቅ አለበት፡፡ መጽሐፉም ይሄን ግልጽ አድርጎ ያስቀምጣል፡፡ በደፈናው ውጤቱ የሚያመለክተው እንደጸሐፊው አቀራረብ‹‹የአስተዳደር ሥርዓት እንከንን እንጂ የአባቶችን ችግር አላየንም›› የሚል ነው፡፡ ይህም የቤተክህነቱን አስተዳደር ችግር ከመሰረታዊ ፍልስፍና ይልቅ ቴክኒካል ዝንፈት አድርጎ ያቀርባል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የተለያዩ የቤተክህነት አስተዳዳር መቀየጃ የህግ ምንጮች ያለባቸውን ክፍተቶችንና መጣረሶችን በማስተካከልና በአባቶች ዙሪያ ለግል ጥቅማቸው የሚጎደፍሩትን በማጋለጥ መፍትሔ ሊመጣ እንደሚችል የሚያምኑ ናቸው፡፡ ይህ ድምዳሜ የሃሳብ ግልጽነት የሚጎለው ሊባል ይችላል፡፡ ለምሳሌ የአባቶችን ችግር አላየንም ማለት ምንድን ነው? ግልጽ አይደለም፡፡ የተብራራበት ቦታም የለም፡፡ በእርግጥ ጸሐፊው በግል ተፈጥሯቸው ሰላማዊ፣ ከግጭት መራቅን የሚወዱ ለነገሮች አዎንታዊ እይታ እንዳላቸው ጥቂት ጊዜ አብሯቸው ያሳለፈ ሰው የሚመሰክረው ነው፡፡ መጽሀፉም በተደጋጋሚ በተለይ አባቶችን አስመልክቶ ባላቸው አቋም ይህንኑ ይመሰክራል፡፡ ከማጣራቱ ጎን ፓትርያርኩንና ሊቀጳጳሱን ለማስታረቅ መሞከራቸውም የዚሁ ባህሪያቸው መገለጫ አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡ ያም ሆነ ይህ ድምዳሜያቸው የቀደሙ ግጭቶችን፣ እነርሱን ለመፍታት የተሄደበትን መንገድና ያስገኘውን ወይም ያሳጣውን ነገር ለመመዘን የቻለ ለመሆን አልታደለም፡፡ የ1990/1ዱ የአጣሪ ኮሚሽን የበለጠ ቀጥተኛ፣ ችግሩን በአግባቡ ያየና ላነሳው ጉዳይ ጠንከር ያሉ መፍትሔዎችን የሰጠ መሆኑን ስንታዘብ፤ የ2001ዱ አጣሪ ኮሚቴ እንደ1990/1ዱ ኮሚሽን እንዳይሆን ሲጀመርም የተልወሰወሰ ሚና የተሰጠው መሆኑን እንረዳለን፡፡ ‹ትልቅ› ኃላፊነት ከነበረው ኮሚሽኑ /ሃይጃክ/ መጥለፍ ነበር ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡ የኮሚቴው ሪፖርት የፈየደው ነገር ስለመኖሩ መናገር አይቻልምና፡፡ ለመጽሐፉ የተሰጠው ንዑስ ርዕስ ግን ‹‹… ያልተቋጨው የምርመራ ውጤት›› የሚል እንደመሆኑ፤ በኮሚቴው አሰያየምና ሚና ተገቢነት ላይ ካነሳነው ጥያቄና ሲኖዶሱ ይህንን ካደረገበት አውድ አንጻር በሪፖርቱ ላይ ኮሚቴው እምነት ነበረው እንድንል ያደርገናል፡፡ በነገራችን ላይ ስለቤተክህነቱ ፋይናንስና የሰው ኃይል አስተዳደር እንዲሁም ምዝበራ በምሐባው ዓለሙ ከበደ በ2003 ሐምሌ የታተመው ‹‹የቤተክርስቲያን ፈተናዎች›› በሚለው መጽሐፍ የልደታ ማርያምንና የመድሐኔ ዓለም ቤተክርስቲያንን እንደማሳያ አድርጎ በመውሰድ በጥልቀት ይተነትናል፡፡ የኮሚቴው አባላትም ሆኑ ሰብሳቢያቸው የ460 ቀናት … ጸሐፊ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የለፉበት የኮሚቴ ሥራ ሲጠናቀቅ (ከሐምሌ 10 ቀን 2001 እስከ ጥቅምት 13 ቀን 2003ዓም) በአንድምታ የተሰጠውን የሊቃነጳጳሳቱን የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እንቅስቃሴ በሾኬ መጣሉን በማረጋገጡ፤ ኮሚቴው ‹‹የተቋቋመለትን›› ተልእኮ የፈጸመ የሚያስብለው ሆኗል፡፡

## መጽሐፉ የወጣበት የጊዜ ቀመርና አንድምታው

ያለንበት ወቅት 5ኛው ፓትርያርክ አልፈው ቤተክርስቲያኗ ቀጣዩን

ወደ ገፅ 27 ዞሯል



በአቻምየለህ ታምሩ እውነቱ
(በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ
የኢኮኖሚክስ መምህር)

# በኢትዮጵያ የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ የተደቀነውና ያልታየው ትልቁ ፈተና

**ዘመናዊ የእርሻ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ማቆም( technology disadoption) ባህላዊ የሆነውን እርሻችንን እንዳያድግ ክፉ እንቅፋት እንደሆነበት ነው፡፡ ይህ ችግር ጥናቶች በስፋት የፈተሹት ጉዳይ አይደለም፡**

ባህላዊ እርሻ የዓለም ስልጣኔ አሁ , ካለበት ደረጃ ከመድረሱ ብዙ ሺህ አመታት በፊት የሰው ልጅ ይተዳደርበት የነበረ መሰረታዊ የኢኮኖሚ ተግባር እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ የሰው ልጅ መፈጠሪያና ለአለም ስልጣኔ አጋሪና ተጋሪ የሆነችው ኢትዮጵያም ከጥንት ጀምሮ ህዝቦቿ ተፈጥሮ ለሰው ልጅ መተዳደሪያና መኖሪያ በተለገሰችው መሬት ላይ ባህላዊ እርሻን ዋና የኑሯቸው መሰረት አድርገውት ቆይተዋል፣ ዛሬም ቢሆን ያን ያህል ሳይለወጥ በዳዴ እየሄድን ነው፤ ይህ በግልፅ የሚያሳየው የመጣነው መንገድ በጣም አዝጋሚ መሆኑን ነው፡፡

ከሁለት ሳምንት በፊት፣ ማለትም ቅፅ 1 ቁጥር 6 ጥቅምት 2005 አዲስ ታይምስ መፅሔት ላይ ባሳተምሁት ፅሁፌ ላይ እንዳመለከትሁት፣ ዛሬ ያለው ባህላዊና አነስተኛ አርሶ አደርን ያስቀደመው፣ ከምንጅላቶቻችን በቅብብሎሽ የወረስነው የእርሻ አኮኖሚ ስርዓት ላይ ተንተርሰን የሚጠበቀውን ያህል ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ስርዓት ማስፈን ወደማይቻልበት ደረጃ እየተቃረብን ይመስላል ብዬ ተናግሬ ነበር፡፡ ይህንን በቀላል ማስረጃ ለማሳየትም ከዛሬ 20 ዓመታት በፊት በአነስተኛ እርሻ ህይወቱን ይገፋ የነበረው የህብረተሰብ ክፍል ከጠቅላላው የሃገራችን የህዝብ ቁጥር 85% በላይ ያህሉ ሲሆን ዛሬም ከ20 ዓመታት በኂላ (በነገራችን ላይ 20 ዓመታት እነ ቻይናና ታይዋንን የመሳሰሉ ሃገራት ተሽቀንጥረው በመውጣት፣ በድህነት ላይ መጠነ ሰፊ ጥቃት አድርሰው ታላላቆቹ የእስያ አናብስት ተብለው ለመሞካሸት የበቁበት ጊዜ ነው) የበለጠ ተደላድለን እዚያው 85%ን እየረገጥን መገኘታችን ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር የኢኮኖሚ ስርዓት ማስፈን ወደማይቻልበት ደረጃ እየተቃረብን ይመስላል የሚለውን “ጥንቆላዬን” ፍንትው አድርጎ ሳያሻማ የሚያስረግጥልኝ ይመስለኛል፡፡ ከእርሻ ወደ ኢንዱስትሪ የተደረገ ሽግግር ወይም ሽግሽግ የነበረ ቢሆን ኖሮ ይህ ከላይ የቀረበው አሃዝ ምክንያታዊ ለውጥ ይታይበት ነበር፡፡ ምክንያቱም ከእርሻ ወደ ኢንዱስትሪ በሚደረግ ሽግግር ወቅት የማህበረሰባችን አወቃቀርም ከእርሻና አርሷደርነት ተላቆ ወደ መካከለኛና የሰለጠነ ሰራተኛ ማህበረሰብ መሸጋገር ይኖርበታልና፡፡ ሆኖም ግን ከላይ እንዳልሁት፣ ይህንን አይነት ሽግግር ኮሽታውም አልተሰማም፤ እኔ ወደዚች ምድር በመጣሁበት ባለፉት 20ና በላይ ዓመታት፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት አንድ ወንዝ የሚያሻግር ቁም ነገር ላክል፡፡ ኢትዮጵያን `እያስተዳደረ` የሚገኘው የኢህአዴግ መንግስት ኢትዮጵያን ከረጅም ጊዜ እንቅልፍ አላቅቆ በ2025 እ.ኤ.አ. መካከለኛ ገቢ ያላት አገር ለማድረግ “እንዳቀደ” ይህንን ፅሁፍ በማዘጋጅበት ወቅትና በልዩ ልዩ ጊዜያት ያነበብኂቸው አንዳንድ ወረቀቶች ያትታሉ፡፡ እኔ እንደሚታየኝ ከሆነ አገራችን ኢትዮጵያን በ2025 መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ ለማሰለፍ ከመፈክር ባሻገር በተለይም አሁን ያለውን በአነስተኛ አርሷደር ላይ ያተኮረ ለምንጅላቶቻችን የተገለጠውን “ምሥጢረ የትኩረት አቅጣጫ” መቀየር ይኖርብናል፡፡ ምክንያቱም ከ13 ዓመታት በኂላ(ማለትም በ2025 እ.ኤ.አ.) ኢትዮጵያ አሁን ያለውን 85% አርሷደር ይዛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሃገራት ጎን ልትሰለፍ አትችልም፤ ታምር ካልተፈጠረ በስተቀር፡፡ ስለዚህ ከ13 ዓመታት በኂላ የማህበረሰቡ አወቃቀር፣ ከላይ እንዳስቀመጥሁት፣ አብዛኛው አርሷደር ከአርሷደርነት ተላቆ ወደ መካከለኛና የሰለጠነ የሰራተኛ ማህበረሰብ ሽግግር ማድረግ ይኖርበታል(the huge Ethiopian population must be transformed from peasant to middle class and skilled working class society)፡፡ ዛሬ ባለው ነባራዊ ሁኔታ እንኳን ብንነሳ ከ65 ሚሊዮን በላይ በባህላዊ ግብርና የተሰማራን የማህበረሰባችን ክፍል በ2025 ቢያንስ በግማሽ አውርደን (ሲሰላ ከ33 ሚሊዮን በላይ ይሆናል) ቀሪው ወደ መካከለኛና የሰለጠነ ሰራተኛ ማህበረሰብ መሸጋገር ወይንም graduate ማድረግ አለበት፡፡ ይህንን ያህል ሽግግር ሊፈጥር የሚችል እቅድ እንዳለን እጠራጠራለሁ፤ አላነበብሁምም፡፡ ስለዚህ ዛሬ መታሰብ ያለበት በ2025 መካከለኛ ገቢ ይኖረናል የሚል ህልም ልበለው ቅዠት ብቻ ሳይሆን ከላይ ያስቀመጥሁትን ሽግግር ለማምጣት መሰራት በሚገባቸው መሰረታዊ ተግባሮች(fundamental frameworks) ላይ መሆን ይኖርበታል፡፡

እዚህ ላይ ባለፉት ጥቂት አመታት ፍቃድ እየወሰዱ በተለያዩ የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ መዋለ ንዋይ ለማፍሰስ በመሰማራት ላይ ያሉትን የሃገር ውስጥና የባዕዳን ሃገራት ባለሃብቶችን በማየት ብቻ ከላይ ያስቀመጥሁትን ተገቢ ሽግግር ማምጣት ይቻላል፣ ሽግግሩም ይሳካል የሚል መከራከሪያን የሚያነሳ ካለ፣ ኢትዮጵያ የ80 ሚሊዮንና በላይ ድሃ ህዝቦች ሃገር መሆኗ መዘንጋት የለበትም እላለሁ፡፡ ማለትም እነዚህ ፍቃድ እየወሰዱ ያሉቱና በተጨማሪም መንግስት የሚገባባቸው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ባጠቃላይ ተደምረው የሚፈጠረው የስራ ዕድል መጠን ከላይ የሰፈረውን የሚሊኖች አሃዝ ያህል ሽግግር ለማምጣት የሚያስችል አይደለም በሺዎች የሚቆጠሩ ከሞያና የቴክኒክ ተቋማት፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች የሚያምርቷቸውን ስልጡናንን መሸከም ከቻለም ማለፊያ ነው፡፡ እዚህ ጋ እኔ እያልሁ ያለሁት አላማችንንና ግባችንን እንቀይር ሳይሆን ግባችንን የሚያሳካ እቅድ ይኑረን ነው፤ ተልካሻ አስተሳሰብና አሰራር ይዘን ከባህር ጥልቀት በላይ ጥልቅ ከሆነው ድህነታችን አይደለም ሽጥ አንሻገርም ነው እያልሁ ያለሁት፤ ለምንፈልገው ሽግግር እንድንበቃ የተወሳሰበውን ችግር በቅድሚያ እንፍታ ነው እያልሁ ያለሁት፤ እንዲሁም ቅድሚያ መስጠት ያለብንን ቅድሚያ እንስጥ ነው የምለው፡፡ ባጭሩ፣ ይህንን ወይንም ያን “ማቀድ” የሚጨበጥ ነገር ከሌለው፣ ማቀዱ ከወረቀት ላይ ያለፈ ፋይዳ አይኖረውም፤ የዋኘ ሁሉ አሳ አያወጣምና፡፡

ወደ ዋናው ጉዳይ ከመግባቴ በፊት አንድ ተጨማሪ ጉዳይ ለውይይት ላክል፡፡ ይህም የኢህአዴግ መንግስት ከላይ እንዳልሁት ኢትዮጵያን በ2025 እ.ኤ.አ. መካከለኛ ገቢ ያላት አገር አደርጋታለሁ የሚለው እቅዱ ነው፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ አንድ መንግስት ማቀድ ያለበት በስልጣን ዘመኑ አንድን ሃገር ከየት አንስቼ የት አደርሳታለሁ የሚለውን ብቻ ይመስለኛል፡፡ ለምሳሌ ሰሞኑን በቀጣይ የአሜሪካ ርዕሰ ብሔር ለመሆን የዲሞክራቱ እጩ ፕሬዝደንት ባራክ ኦባማና የማሳቹሴት ክፍለ ሃገር ገዢ የነበሩት ሚት ሮምኒ ትንቅንቅ ላይ ናቸው፡፡ ሁለቱም እጩዎች እቅዶቻቸውን ለመራጮቻቸው እየሸጡ ያሉት ለሚቀጥሉት 4 የዋይት ሃውስ ቆይታ ዓመታት ምን ሊሰሩ እንዳሰቡ በመተንተን ነው፡፡ እኛም አገር ንጉሳዊ ወይንም አሀዳዊ ስርዓት እስካልተዘረጋ ድረስ፣ የስልጣን ምንጭ የመራጭ ድምፅ ነው ተብሎ ህገ መንግስት ተረቆ በህግና በህገ መንግስት እስከተዳደርን ድረስ፣ እንዳሜሪካኑ ሁሉ በኛ ሀገርም መንበረ ስልጣን የሚይዝ አካል ማቀድ ያለበት ለተመረጠበት እንጅ ገና ላልተመረጠበት አይደለም፡፡ ይህ የ2025ቱ እቅድ ለሚቀጥሉት 13ና በላይ አመታትም እኛ ነን ገዥዎች ከሚል እርግጠኝነት የመጣ ይመስላል፡፡ ይህ ደግሞ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ አይደለም፡፡ በዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ፣ ብዙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባሉበት ሃገር፣ የሚታቀደው እቅድ በአንድ የስልጣን ዘመን ሊተገበር የታሰበ እቅድ ብቻ ነው መሆን ያለበት፡፡ ስለዚህ የኢህአዴግ መንግስት ገና ላልተመረጠበት ዘመን እንካችሁ ያለን የ2025ቱ እቅዱ ግራ አጋብቶኛል፡፡ ብመረጥ የማሳካው ነው እንዳይለን፣ ዛሬ እንኳ አቀድሁት ያለውን ከሙሉ በከፊሉ እያሳካው አይደለም፡፡ አይ እስከ 2025 በሚደረጉ ምርጫዎች ቢሸነፍና ቢያቅድ ምን ችግር አለው፣ ሌላ የሚያሸንፍ ፓርቲ ካለ ያ ዳር ያደርሰው የለም ወይ እንዳይባል ያልተሳተፈበትንና ያላረቀቀውን እቅድ አሳካለሁ የሚል የዋህ የፖለቲካ ፓርቲ ያለ አይመስለኝም፤ ከዚህ በተጨማሪ እቅድ ቀላል ነገር አይደለምና፡፡ አንድ እቅድ ሊተገበር እስከሆነ ድረስ የሚታቀደው መሬት ላይ የማይወርድ እቅድ ደግሞ (ኢህአዴግ ቢሸነፍ ማለቴ ነው) እቅድ አይደለም፡፡ ለዚያ ነው ሊተገበር እንደሚችል እርግጠኛ ያልሆኑበትን እቅድ ማቀድ ውሃ ወቀጣ የሚሆነው፡፡ ይህንን ሁሉ የማነሳላችሁ የ2025ቱን እቅድ ብወደውም አንድ መንግስት ያልተመረጠበትን ማቀዱ ተገቢ ስላልመሰለኝና ግራ ስለገባኝ ነው፡፡ ያልተመረጡበትን ማቀድ ሊተገበር መቻሉ፣ አለመቻሉ 50-50% ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሊያጋጥም የሚችለው ቁማር ጨዋታ ላይ ብቻ ነው፡፡ ከዚህስ ባሻገር፣ እጅግ ተለዋዋጭ በሆነ አለም ውስጥ እየኖርን የሃያና ሰላሳ ዓመታት ይቅርና አምስትና አስር አመትስ በርግጠኝነት ማቀድ ይቻላል ወይ? ራዕይ ማስቀመጥ ይቻል ይሆናል፤ ለሃያና ሰላሳ ዓመታት ማቀድ ግን

ወደ ገፅ 23 ዞሯል

ኪነጥበብ



ገጣሚ ኤፍሬም ስዩም

# አንፃር

> የዛሬው ብርሃን የዛሬው አባት ነው። ዕለት ከፀሐይ ማሕፀን ትወለዳለች ስሟም ዛሬ (አሁን) ይባላል። ሁላችንም የአሁን ልጆች ነን ነገር ግን ከጥቂቶች በቀር ብዙዎቻችን አሁንን አናውቃትም፡ ፡ እኔ ግን የብርሃን ፍጥረት ነኝ። ለዚህ ነው ማለዳን የምናፍቀው።

አባቴ ነው።...

...ቀና ብለህ ከግድግዳው ላይ የተሰቀለውን ፎቶዬን ተመልከት አለኝ፡ ፡ አባቴ ከእናቴ ጋር ሲጋቡ የተነሳው ፎቶ ነው። የአባቴ ፀጉር ከብዛቱ ርዝመቱ ጉድ ያሰኛል። የገረጣ ጠይም ፊት። መካከለኛ ቁመና፣ ሥጋ ያልበዛበት አካል ይታያል። አባቴ ከሠላሳ ዓመት በፊት የተነሳው ፎቶ ላይ። ፎቶው ላይ ያለው ምስል የአባቴን ዘመን የአለባበስ ስርዓት ያሳያል፤ ቬሉ የረዘመ ሱሪ፣ ኮሌታው የሰፋ ኮት በነጭ ስፖርት ሸሚዝ ይታያል። አባቴ በኔ ዕድሜ ሳለ በተነሳው ፎቶ...

‹‹አየሕ-አይደል? እኔ በአንተ እድሜ ሳለሁ ነፋሱን እጨብጥ ባህሩን እጨልጥ ነበር። ነገር ግን ነፋሱም ከእጄ የለም፤ ባህሩም ሆዴን አልሞላም። ከንቱ የወጣትነት ምኞት ነበርና። እኔ በአንተ እድሜ ሳለሁ ከአባቴ ምክር ይልቅ የራሴን ስሜት የማዳምጥበት ወቅት ነበር። ከአያትሕ መሬትነት ይልቅ የኔን እሳትነት እመካበት ነበር። እኔ በአንተ እድሜ እያለሁ›› አለኝ አባቴ።

ፀጉሬን እየፈተልኩ አባቴ የደረሰባትን የዘመን እውነት በልቤ እያሽሟጠጥኩባት እሰማ ጀመር...

‹‹ታሪክ ራሱን ይደግማል ማለት እንግዲህ ይህ ነው። የምትመካበት አዲስ ነገር ምንድን ነው? እኔ ያላደረግሁት አንተ የምታደርገው አዲስ ነገር ምን አለ?... ተመልከት ፎቶዬን ‹ፀጉሬ ጎፈሬ ነበር። የአንተም ፀጉር አፍሮ ነው። እኔ ለጎፈሬዬ ከኋላ ኪሴ የእንጨት ሚዶ አይለየኝም ነበር። አንተም እንደኔው ነህ ለአፍሮህ ትጨነቃለህ። አፍሮህ ሲያድግ ደግሞ ትገምደዋለህ። ሲሻህ ደግሞ ትሾርበዋለህ፡ ፡ ይህ ሁሉ ግን ከኔ ከአባትህ የተረፈ ነው። ከኔ ያላገኘሽው ምንም የለም። እኔ በጎፈሬዬ የሀገሬን ጠላት ማጥፋቴን፣ ማንነቴን መጠበቄን መሰከርኩበት። አንተ ግን በሹሩባህ መጀመሪያ ራስህን፣ ቀጥሎ ብዙ ቆነጃጅቶችን ጠለፍክበት። አንተ በፒያሳ እንደምትሆነው ሁሉ እኔም በውቤ በረሃ ዘምቻለሁ። ‹ይሄ ሁሉ የአባቴ ምክር ነበር። አሁንም እጄ ከፀጉሬ ላይ አልተለየም፤ ሶስቱ ጣቶቼ ፀጉሬን ይፈትላሉ አባቴም ያወራል።

‹‹ይሄ ሁሉ ግን ጥላ ነው። እኔ በአንተ እድሜ ሳለሁ የሚዳሰስ አካል ይመስለኝ ነበር። አይደለም። ወጣትነት ፍቺ እንደሌለው ህልም ነው። ታየዋለህ፤ እንደ ነፋስ ሽውታም ያመልጥሃል። ወጣትነት ፊደል ነው፤ ቃል ግን አይደለም። ልጄ ሆይ ምክሬን ስማ ወጣትነትና ህሊና ባዳ ናቸው፡ ፡ ህሊና ፀፀትን እንጂ እርምትን አይወድም፣ ወጣትነትና ሕሊና አንድ ናቸው። ሕሊና ፀፀትን እንጂ እርምትን አይወድም፣ ወጣትነትም እንደዚያው ነው። ብዙ ምኞትና ብዙ ከንቱነት።›› ቀና ብዬ አይኑን አየሁት... አይኔን ወደ መሬት መለስኩት። ቢጨርስና ቤቱን ጥዬው ብወጣ ደስታዬ ነበር። አባቴ የምክር ወሬውን ቀጠለ...

‹‹እስካሁን ከነገርኩህ በላይ የምነግርህ ቢኖር እድሜህ በአንተ ላይ ታዛለች እንጂ፤ አንተ በእድሜህ ላይ መብት የለህም። እስካሁን የነገርኩህን ሁሉ ልትቀበለኝ የምትችልበትም ስልጣን በራስህ የለህም ወጣት ነህና። ወጣትነትህ ደግሞ እርጅናዬን ታስንቅሃለች፤ እርጅናዬ ደግሞ ያንተን ወጣትነት በቅናት ትንቀዋለች።

ምናልባት፡- ዛሬ አንተ ከእኔ ከአባትህ የበለጥክበት ጊዜ እንደሚመስልህ ሁሉ አንተም በተራህ በልጅህ የምትበለጥበት ጊዜ ቅርብ ነው። ልጄ ይበልጠኛል ለማለት አትችልም፣ ልጅህ ከአባቴ እበልጣለሁ ይላል እንጂ። ያን ጊዜ የልጄን ልጅ ሰባት እጥፍ እወደዋለሁ፤ የአያቱ ተበቃይ ነውና። አባቶች የልጆቻቸውን ልጆች የሚወዱበትን ምክንያት ለማወቅ ከፈለግህ ፎቶዬን ተመልከተው፤ አንተን ስወልድ እድሜዬ እንደ አንተ ነበር፡ ፡ አንተ በኔ እድሜ ስትሆን እኔ ወደ አያትህ እየሄድኩ ነው። ህይወት ታሳሳለች፤ አባት ስትሆን ደግሞ ልጅህ እያካለበ ሲያሮጣት ታያለህ ያኔ ለልጅሕ ጠላቱ ልጁ ነውና የልጅህን ልጅ ትናፍቃለህ። የልጅህንም ልጅ ከልጅህ ይልቅ ሰባት እጥፍ ትወደዋለህ። ተበቃይህ ነውና።›› ብሎኝ ሽበት የወረረውን ፀጉሩ ላይ ባርኔጣውን ጥሎ ከመቀመጫው ተነስቶ ወጣ። እኔም አባቴ ከተናገራቸው ብዙ ቁም ነገሮች መካከል ያስገረመችኝና ያስፈገገችኝን እያሰብኩ ወደ ቀጠሮዬ ተነሳሁ...

‹አሁን የነገርኩሕን ሁሉ ልትቀበለኝ የምትችልበት ስልጣን በራስህ የለህም። ወጣት ነህና። ወጣትነት ትሰማለች እንጂ አታስተውልም። ጉብዝናህ እርጅናዬን ታስንቅሃለች፤ እርጅናዬ ደግሞ ያንተን ወጣትነት በቅናት ትንቀዋለች።›

## መዝሙረ ብርሃን

የዛሬው ብርሃን የዛሬው አባት ነው። ዕለት ከፀሐይ ማሕፀን ትወለዳለች ስሟም ዛሬ (አሁን) ይባላል። ሁላችንም የአሁን ልጆች ነን ነገር ግን ከጥቂቶች በቀር ብዙዎቻችን አሁንን አናውቃትም። እኔ ግን የብርሃን ፍጥረት ነኝ። ለዚህ ነው ማለዳን የምናፍቀው። ለዚህ ነው ብርሃን የማፈቅረው። ለብርሃን የማዘነው... የአሁን ልጅ ስለሆንኩ ነው። እኔ አሁን ነኝ አባቴ ዛሬ ነው... አያቴ ደግሞ ብርሃን... ሥሬ በምድር መንፈሴ በሰማያት ነው።

ሳይቆሸሹና መንፈስን ሳያጎድፉ በብርሃን መመላለስ በነጭ ስጋጃ ላይ ህልው መሆን በእግዚአብሔር የተሸለሙ የጥቂት ሰዎች እድል ነው። የፀሐይ ምንጣፍ የብርሃን ወለል የሚቆሽሸው የጨለማ ልጆች በቀን የተራመዱበት መስኳቸው ሲረግጡት ነው።

እውነት ከሀሳዊ አንደበት ሲወለድ፣ ፍቅር በአስመሳዮች አልጋ ላይ ሲሰባበር፣ የተሰባበረው የፍቅር ወጋገን ለሰባሪዎቹ ከፍቅርነቱ ይልቅ ቃጠሎነቱ ሲያመዝን ያኔ... ያኔ... ከብርሃን ጨረር የተገመዱት አሁንን የሰሩ ዕለታዊ ምንጣፎች ይበጣጠሳሉ፤ እሾሃማ እግሮች ቀናቶችን ይሰብራሉና....

ህይወት ያለብርሃን ውበትም ያለ ፀሐይ ፈዛዛ ናቸው። ብርሃን በራሱ ግን ህይወት ነው። ሕይወት ለብቻዋ ብርሃን ልትሆን ግን አትችልም። አሁን የጎሕ ፀዳል ጊዜ ነው። የጋለሞቶችን ጭን ሲሞቁ ያደሩ ከንቱዎች ብርሃን ሲወጣ እንዳይበርዳቸው ፀሐይ ስትገለጥ ላለማፈር በዋሻ ወደሚመስሉ ጎጆዎቻቸው ዛሬን አሁንን ትላንትን ካደረ የአረቄና የድራፍት፣ የቢራና የውስኪ ጠረናቸው ጋር ዛሬን አሁንን ወደኋላቸው እየተንገዳገዷት ነው።...

የብርሃን ልጆች ግን በቀን የፍቅረኞቻቸውን አንገት ለማቀፍ የፀሐይን መገለጥ ይማልዳሉ። ‹የሞት ልምምዱን የሰው ልጅ ፈጽሟል› እያሉ በከተማይቱ የሚበዙት ግራጫ ወፎች መዝሙራቸውን ጀምረዋል። እኔም ዝማሬውን ለመስማት ፀሐይዋ መንገዷን ልትጀምር የምስራቅን መስኮት ለማየት... የነደደ ፊቱ የቀላ ሰማይን ልብ ለማለት በምስራቅ አቅጣጫ በኩል የሚገኘው የቤቴን መስኮት እከፍታለሁ...

ከእንቅልፍ ንቃት በኋላ የሚከተለውን የዕለት ውሎዬን የሚሰራው የማለዳው የፀሐይ ምንጣፍ ነውና፤ ከፀሐይ ጨረር ያልተጠለፈ ቀሚስ ያጠለቀች ዕለት ልኬና ምርጫዬ ስላልሆነች


የዛሬው ብርሃን የዛሬው አባት ነውና።

ይህንን እያሰብኩ ከተኛሁበት ተነስቼ መስኮቴን ከፈትኩ። በቤቴ መስኮት ስር በሚገኘው ጎዳና የሚመላለሱት ሰዎች ዘወትር እንደሚያደርጉት ዛሬም እንደዛው ናቸው። ፈዛዛና ችኩሎች ናቸው። የዛሬ አባት ግን የማለዳ ብርሃን አልነበረም።

ደስ አይልም በደመና የተሸፈነ ዕለት ነው። ዝናባማ ጠዋት። ማለዳ በጉም ሲሸፈን የእኔም ማንነት ወደ ክረምትነት ይለወጣል። ይህ ምንም ዓይነት የስነ ልቦና ችግር አይደለም። በቃ ያን እፈልጋለሁ፣ ይህን አልፈልግም የምርጫ ጉዳይ ነው። የዛሬው አባት ግን የዛሬው ጭጋግ ነው። አያቱ ደግሞ ትናንት ልጅየውም ዝናብ... ቢሆንም ግን የሁሉም የሕልውና ምክንያት መፀነሻ ዘራቸው ቅድመ አያታቸው ብርሃን ነበር...

በዚህ ጨቅጫቃና አስቀያሚ ዕለት ውስጥ የምወደው ብርሃን በሆነ ምክንያትነት አለና በማልፈልጋቸው ዕለታቶች ውስጥ የምፈልገውን አገኛለሁና፡ ፡ የማልወደውን ለመውደድ ምክንያቴን እያሰላሰልኩ በመስታወት መስኮት ማዶ ማዶውን እየተመለከትኩ ቆሜያለሁ። እኔ፡ ፡...

የዛሬው ዕለት ዝናባማ ቢሆንም የዝናብነት ምክንያቱ አያቱ ብርሃን ነውና ደስተኛ ነኝ። አንዳንዴ በማንፈልጋቸው ሰዎች (ሁኔታዎች) ውስጥ የምንፈልጋቸው በሕቡዕ አሉ። አስቀያሚ ባልናት ሴት ውስጥ ብሩህ ዓይኖች አልያም የወተት ፍርፋሪ የመሰሉ ጥርሶች እንደማይጠፉት ሁሉ...



በድሉ ዋቅጅራ (ዶ/ር)

# ዘፍጥረት - 83

እነዚህኞቹ ክፉኛ ያዘኑት የገዛ ራሳቸው ልሳን ስላልነበራቸው ነውን? በርግጥም ጥቂቶቹ ተራራ አቋርጠው፣ ወንዝ ተሻግረው መጥተዋልና የአያቶቻቸውን ቋንቋ አይናገሩም ነበር። በፋንታው የአዲሱን መንደራቸውን ቋንቋ ልሳናቸው አድርገው ይጠቀሙበት ነበርና የራሳችሁ ቋንቋ የሚነገርበት ቀዬ ሂዱ ተባሉ። እነሱ ግን አባቶቻቸውም ሆኑ አያቶቻቸው ከወደየት እንደሆኑ አያውቁም ነበርና ይሄዱበት ገደዳቸው። ቋንቋውንም የሚናገሩት መጤዎች ቢሆኑ ምንጫቸው ከሴላ ነውና አዲሱ የኢህአዴግ በረከት ራቃቸው

> ኢህአዴግም ከመንበሩ ከአራት ኪሎ ሆኖ፣ በመዲናይቱ አደባባዮችና ካፌዎች የሚሆነውን ያስተውል ነበር፡ ፡ ፈጣሪያቸው የፈቀደላቸውን ሃሳብን በነጻነት የመግለፅ እድል የእሱ ፈቃድ ይሞላ ዘንድ የተጠቀሙበት እጅግ ጥቂቶች ነበሩ። አብዛኞቹ ፈቃዱን ከእርሱ ከፈጣሪያቸው መሻት ውጪ ተጠቀሙበት። ከሁሉም በላቀ ግን ልቡ የተሰበረው በመከራው ዘመን አብረውት ሲታገሉ ከኖሩት አጋሮቹ መካከል አንዳንዶቹ፣ ጠብ-መንጃቸውን አሽቀንጥረው በነጻ ፕሬስ ስም በብዕር ይሸነቁጡት በገቡ ጊዜ ነበር።

የክርስትና ሃይማኖትንና ስነ-ጽሁፍን አቆራኝተው፣ ፍልስፍናን ትራስ አድርገው የተነተኑ ሊቃውንት ‹‹እግዚአብሔር በቅዱስ መጽሀፍ እንደተባው መፍጠሩን በስድስት ቀን አልጨረሰም›› ብለው ይከራከራሉ። ለክርክራቸው መነሻ የሚያደርጉትም ራሱን መጽሐፍ ቅዱስን ነው። መጽሐፉ “እግዚአብሔር በሰባተኛ ቀን ከስራው ስራ ሁሉ አረፈ።” ማለቱን ጠቅሰው “አረፈ” የሚለው ቃል ላይ በማስመር፣ አረፈ ማለቱ ስራው ቀጣይ መሆኑን ይናገራል ብለው ተጠየቃቸውን ይደረድራሉ፡፡ በተለይ በዚህ ረገድ በዋናነት ከሚነሱት ፍልስፍናዊ የስነጽሁፍ ስራዎች አንዱና ዋናው የጆን ሚልተን “Paradise Lost” (1667) ነው።

ዘፍጥረት በስድስት ቀን የተጠናቀቀ አለመሆኑን የሚናገሩት ፈላስፎች፣ ዘፍጥረት ቀጣይና ዛሬም ድረስ እየተከናወነ ያለ ነው ይላሉ። ለምሳሌ የእየሱስ ክርስቶስ መወለድና በዚህ አለም መመላለስ፣ የእግዚአብሔር አለምን በወደደው መልክ የመፍጠር አንድ አካል ነው ብለው ይከራከራሉ። ዝቅ ሲልም አንድ ፀሐፊ የሚጽፈው ልቦለድ ወይም ግጥም የነበረን አለም መገልበጥ ሳይሆን አዲስ ጽንፍ (dimension) መፍጠሩ ነውና የእግዚአብሔር አለምን የማበጀት /የዘፍጥረት/ አካል ነው ብለው ይሟገታሉ። በነሱ አያያዝ በመንደሮች፣ በከተሞች፣ በሀገራት፣ በአህጉሮች… በዩኒቨርስ ውስጥ ዘፍጥረት እንደቀጠለ ነው።

ዘፍጥረት - 83

እየሱስን ወደ መሬት ከላከ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ አመት አልፎ ከስልሳ ስድስተኛው አመት ጀምሮ በኢትዮጵያ ላይ በሆነው እግዚአብሔር በእጅጉ አዘነ። በእጁ ከፈጠራቸው አራት ወንዞች አንዱ በሆነው በግዮን ወንዝ የከበባት ኢትዮጵያ በልጆችዋ ደም ተከባ ተመለከተ። ለአህዛብ መጠለያ አድርጎ የፈጠራት ምድር፣ ይሄዱበት የጨነቃቸው ህዝቦች ተከማችተውባት ባየ ጊዜ፣ ያለ እሱ ፈቃድ አንድም የሆነ እንደሌለ ያውቃልና ስለመፍቀዱ አዘነ። የኢትዮጵያ እናቶችን እንባ ሊያብስ፣ ወጣቶቹንም ከየተደበቁበት ወጥተው በሀገራቸው አደባባይ ላይ ይራመዱ ዘንድ ወደደ።

በፍቃዱ በተፀፀተ በዚያኑ ቀን ከአስራ ሰባት አመት በፊት በኢትዮጵያና በህዝቦችዋ ላይ የጀመረውን ዘፍጥረት ይቀጥሉ ዘንድ ፍቃድ የሰጣቸውን ወታደሮች እንዲህ አላቸው። “ስለምን ወጣቶችን ታስራላችሁ? ስለምንስ ትገድሏቸዋላችሁ? ግዮንን የመሰለ ኸረት የሰጠሁዋችሁስ ህዝቤን በረሀብ ትፈጁት ዘንድ ነውን? ከአፈር አንስቼ አንግሼያችዋለሁና ህዝቤን ከአፈር ያነሱታል ብዬ አይኔን ከእናንተ ላይ ለጥቂት አመታት ባነሳ ህዝቤን አፈር ከተታችሁት። ከእንግዲህ በሰፈራችሁበት ትሰፈራላችሁ። እስር ቤት መታጎሪያችሁ ይሁን፤ ሀገር ይናፍቃችሁ።” አላቸው፡፡ ፈቃዱንም ነሳቸው። እነሱ ግን ሀጢያታቸው ተጭኗቸው ነበርና ቀና ብለው ሊያዩት አልደፈሩም።

ይህ ከሆነ ከሰአታት በኋላ እግዚአብሔር ምንጩ ከሰሜን ተራሮች የሆነ ድምጽ ሰማ። ድምጹ እጅግ አስገምጋሚ፣ ኳኳታም የበዛበት ነበር። ለእሱ ግን ያዳምጠው ዘንድ አላወከውም። ድምጹም ይህ ነበር፡- “አቤቱ ጌታችን ሆይ አበርትተህ እዚህ አድርሰኸናልና በኢትዮጵያና በህዝቦችዋ ላይ ዘፍጥረትህን እንቀጥል ዘንድ ፈቃድህ ይሁን።” እሱም አላቸው፣ “እናንተ እነማን ናችሁ? በእጄ በፈጠርኩት ግዮን ከብቤ ባሰፈርኩት ህዝቤ ላይ ዘፍጥረቴን ልትቀጥሉስ ስለምን ወደዳችሁ?››

“ጌታ ሆይ እኛ ኢህአዴግ እንባላለን፡፡ የዘፍጥረት ፈቃድህን የሻትነውም ህዝቦችህ ላይ የደረሰውን የመከራ ቀንበር እናወልቅ ዘንድ ነው፡፡ የሚፈሰው ደም ይቆም ዘንድ፣ ህዝቦችህ በቀን ሶስቴ በልተው ያድሩ ዘንድ፤ ለአስራ ሰባት አመት ደከምን። እነሆ ዛሬ በአንተ ፈቃድ እዚህ ደርሰናልና ጌታ ሆይ እባክህ የዘፍጥረት ፈቃድህን ስጠን።”

እግዚአብሔር ልመናቸውን በሰማ ጊዜ ራራ። እውነትም ከኢህአዴግ በላቀ በህዝቡ ላይ ለወረደው መቅሰፍት አምርሮ የተቃወመ አልነበረም። እንዲህም አላቸው፡- “እናንተ በህዝቦቼ ላይ የደረሰው መቅሰፍት ያበቃ ዘንድ ሞታችኋል፤ አካላችሁንም አጉድላችኋል። እናም እላችኋለሁ። ከእናንተ በቀር የዘፍጥረት ፈቃድ የሚገባው አሁን በዚህች ምድር የለም። ፈቃዴን ባርኬ ሰጥቻችኋለሁ።” ስለፈቃዱም እጁን ጭኖ ባረካቸው። እየባረካቸው እያለም አላቸው፣ “ህዝቦቼ ለአስራ ሰባት አመት መቅሰፍት ወርዶባቸዋል። ታርደዋል፣ ታርዘዋል፣ ተርበዋልም። ፈቃዴ ለናንተ መሆኑ ደማቸው ይደርቅ ዘንድ ነው። ታለብሱዋቸውና ታበልዋቸውም ዘንድ ነው። ከአመታት በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ስመለከት እንደፈቃዴ ሳይሆን ቀርቶ ህዝቤ አንገቱን ደፍቶ፣ በመቅሰፍቱ ላይ መቅሰፍት ጨምራችሁበት ባይ ይቅር አልላችሁም።” ይህንን ተናግሮ ከፊታቸው ተሰወረ።

ዘፍጥረት 83-1 የተበታተነችውን ሀገር እንደገና ፈጠራት

የዘፍጥረትን ፈቃድ ከእግዚአብሔር ተቀብሎ በመንበሩ በተቀመጠ እለት፣ ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ተበታትና ተመለከታት። አንድ አድርጎ ይመራት ዘንድም ወረደ። ይሁን እንጂ ሀገሪቱን አንድ አድርጎ ዳግም መፍጠሩ በአንዲት ጀምበር እንደማይሆን አወቀ።

በመጀመሪያ ኢህአዴግ የሽግግር ዘመን ፈጠረ። የፈጠረውንም ዘመን ህግና ደንብ አበጀለት። “ ”

“የሽግግር ቻርተር” ብሎም ሰየመው። የሀገሪቱንም ህዝቦች በሽግግር ቻርተሩ ስር እንዲሰበሰቡ ጠራቸው። ይህንንም አብዝቶ በሬዲዮና በቲቪ ሰበከ። የዘፍጥረትን ፈቃድ ከሰጠው ከፈጣሪ ቤተ-አምልኮዎች በስተቀር፣ መስሪያ ቤቶች፣ ት/ቤቶችና ዩኒቨርሲቲዎች፣ ቀበሌዎችና ወረዳዎች የሽግግር ቻርተሩ ይሰበክባቸው ገቡ። የሰበካው ድምጽ ወሰን አልነበረውም። ተራሮችን አልፎ፣ ጫካ ገብቷልና የሸፈቱ ነፍጣቸውን ጥለው ወጡ፡፡ ባህር አቋርጦ ባዕድ ሀገር ድረስ ተሰምቷልና የተሰደዱትም አልቀሩም።

ጥቂቶች ግን የሽግግር ዘመኑን እንጂ ቻርተሩን ተጠራጠሩት፡ ➩

፡ በዚህም የተነሳ አልተቀበሉትም፡፡ አብዝተውም ይሞግቱት ገቡ፡፡ ኢህአዴግ ይህንን ባየ ጊዜ “መጀመሪያ ቃል ነበር” እንዲል ወንጌሉ “ፀረ-ቻርተር” የሚል ቃል ፈጠረ፡፡ የሽግግር ቻርተሩን ቅድስና ተጠራጥረዋልና እነዚህን ሰዎች በፈጠረው ቃል ስር አስቀመጣቸው፡፡ ቃሉ እርኩስነትን የሚገልፅ “ፀረ” የሚል ቅጥያ አለውና አህዛብ ከሚመላለሱበት ቅዱስ መድረክ ሁሉ ይወገዱ ዘንድ ኢህአዴግ አዘዘ፡፡ ፀረ-ቻርተር የሚለው ቃል ከዩኒቨርሲቲ፣ ከትምህርት ቤት፣ ከመስሪያ ቤት… ተወገደ፡፡ በቃሉ ስር የተፈረጁ ሰዎችም አብረው ይወገዱ ዘንድ ሆነ፡፡

ከዚያም በኋላ ኢህአዴግ በዘፍጥረት መንበሩ በተሰየመ በሰላሳ አራተኛው ቀን የሽግግር ዘመኑ ይጀመር ዘንድ “የሽግግር ጉባኤ ይሁን” አለ፡፡ ጉባኤም ሆነ፡፡ በሀገሪቱ ጉዳይ ልሳን አለን እንናገራለን፤ ጉልበት አለን እንሰራለን ያሉ ሁሉ በጉባኤው ታደሙ፡፡ ይሁንና ከስደት የተመለሱት እንጂ፣ ከጫካ የወጡት ብዙዎች በጉባኤው ይሳተፉ ዘንድ የኢህአዴግ ፈቃድ አልነበረም፡፡ “ቀኝህን ለመታህ ግራህን ስጠው” የሚለውን የፈጣሪውን ቃል አላስታወሰም፡፡ ቀኙን መትተውት ነበርና በፈጣሪ ሚዛን ሳይሆን በራሱ ሚዛን ላይ አስቀምጦ ፈረደባቸው፤ እስር ቤትም ከተታቸው፡፡ ቢሆንም አብዝቶ መልካም ነገር ሰርቷልና ስለዚች ኢምንት በደል “አቤት” ያለ አልነበረም፡፡

ባህር አቋርጠው ከስደት ከተመለሱትም መካከል በፈጣሪያቸው ኢህአዴግ ዘንድ ሞገስን ያላገኙ ነበሩ፡፡ እነዚህኞቹም ያልደሙለትን፣ መስዋዕትነት ያልከፈሉለትን የዘፍጥረት ፈቃድ ይመኙ ነበርና በእግዚአብሔር ፊት ይፈጥር ዘንድ ከተቀባው ፈጣሪ ከኢህአዴግ ጋር የሚገዳደሩበት ግርማ አልነበራቸውም፡፡ ይህ በተገለጠላቸው ጊዜም የሽግግሩን መቅደስ ረግጠው ወጡ፡፡ የአዲሲቷን ኢትዮጵያ ፍሬ ሊቋደሱ ፍላጎትም አልነበራቸውም፡፡ ወደ መጡበት ስደታቸው ይመለሱ ዘንድ ፍቃዳቸው ሆነ፡፡ ሙሴ ቀይ ባህርን በበትሩ ሰንጥቆ አህዛብን እንዳሻገረ ሁሉ፣ ኢህአዴግም ዳመናውን በጢያራ ሰንጥቆ ወደማይመለሱበት ሸኛቸው፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ ኢህአዴግ በሽግግሩ መቅደስ የታደሙትን ሁሉ፣ በአምሳሉ በቀረጸው የሽግግር ቻርተር ባረካቸው፡፡ “ለሽግግር ቻርተሩ ታማኞቹ ሁኑ፡፡ የፈራረሰች ሀገራችንን በብሔር ብሔረሰቦች ያሸበረቀች፤ በዲሞክራሲ የገሞራች ሀገር አድርጌ እፈጥራት ዘንድ ፈቃዳችሁ ይሁን” አላቸው፡፡ እንዳለውም ሆነ፡፡ ታዳሚዎቹ ለሽግግሩ ቻርተር ታማኞች ሆኑ፡፡ እንዲህም አለ፡- “የሽግግሩ ዘመን ሁለት አመት ይሁን፡፡” እንዳለውም ሆነ፡፡ ጉባኤተኞቹም ጭብጨባና ዝማሬ አሰሙ፡፡ ኢህአዴግ ጭብጨባና ዝማሬውን በሰማ ጊዜ የፈጠረው የሽግግር ዘመን መልካም እንደሆነ አወቀ፡፡

ኢህአዴግ የአዲሲቷ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ መሰረት ይሆን ዘንድ የሽግግር ጉባኤው ተሳታፊዎች ፍላጎት ይሁን ባለው መሰረት ቃሉ ተፈጽሞ ባየ ጊዜ ደስታው አጽናፍ አልነበረውም፡፡ ይህንንም ተከትሎ የምድሪቷ ደም ደረቀ፡፡ የአህዛብ ልጆች እንደገና በግዮን ለምለም ምድር ይመላለሱ ጀመር፡፡ ለአስራ ሰባት አመታት የወረደውን መቅሰፍት ከህዝቡ ልብ ውስጥ ይነቀል ዘንድ ኢህአዴግም አለ፡- “እነሆ ያለፈው ዘመን አለፈ፡፡ ያንን ዘመን የሚያስታውሱ ድርሳናት ይቃጠሉ፤ ሀውልቶች ይፍረሱ፤ ግፈኞችም ቢሆኑ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ አደባባዮች አይመላለሱ” እንደቃሉም ሆነ፡፡ የግፍ ኮሮጆ የነበሩ ቤተ-መዛግብት የገሞራ እጣ ወረደባቸው፡፡ ሀውልቶች ተነቃቀሉ፡፡ ያለፈውን መከራ ያወረዱ ግፈኞችም በአህዛብ መሀል አይራመዱ ዘንድ እስር ቤቶች ተበጁላቸው፡፡ ያስራ ሰባት አመቱ መቅሰፍት ከኢህአዴግ ልብ በቀር ከምድሪቱ የተወገደ መሰለ፡፡

ኢህአዴግ የሚፈጥራት አዲሲቷ ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ከነበሩት የነገስታት ኢትዮጵያ የተለየች ትሆን ዘንድ ተመኘ፡፡ እንደ ደርግ የዘፍጥረት ዘመንም ጦርነትና ረሃብ የነገሰባት እንዳትሆን ወደደ፡፡ አዲሲቷ ኢትዮጵያ ህዝቦች በጋራ የሚገነቧት፣ በፍቅር ተደጋግፈው የሚኖሩባት ትሆን ዘንድ ኢህአዴግ የዘፍጥረትን ፈቃድ ወደሰጠው ወደ እግዚአብሔር አብዝቶ ፀለየ፡፡ እግዚአብሔርም “ዴሞክራሲ” ሲል ምስጢሩን ገለጸለት፡፡ ኢህአዴግም ዴሞክራሲ በምድሪቱ ይሁን አለ፡፡ የዲሞክራሲ መገለጫ ከሆኑት መካከል የግል ጋዜጦችና መጽሔቶች ጎዳናውን ሞሉት፡፡ አህዛብ የተሰማውን ይናገር ገባ፡፡ በየሻይ ቤቱና ቡና ቤቱ ጠረጴዛ ላይ የቡና ቁርስ ይቀርብባቸው የነበሩ የዛጉ ሳህኖች ተሰበሰቡ፡፡ በፈንታቸው መጽሔቶችና ጋዜጦች የቡና ቁርስ ሆኑ፡፡ በምድሪቱ እንዲህ ሆኖ አያውቅም ነበርና ከግዮን ባሻገር በሱዳንና በኬንያ የሚኖሩ ህዝቦች በዚህች ሀገር ስለሆነው የቅንአት መንፈስ አደረባቸው፡፡ በእግዚአብሔር ፈቃድ ቀድመው ዲሞክራሲ ያስፈኑት ታላላቆቹ የምዕራብ ሀገራትም ስለሆነው ፈጣሪውን ኢህአዴግን አንቆለጳጰሱት፡፡

ኢህአዴግም ከመንበሩ ከአራት ኪሎ ሆኖ፣ በመዲናይቱ አደባባዮችና ካፌዎች የሚሆነውን ያስተውል ነበር፡፡ ፈጣሪያቸው የፈቀደላቸውን ሃሳብን በነጻነት የመግለፅ እድል የእሱ ፈቃድ ይሞላ ዘንድ የተጠቀሙበት እጅግ ጥቂቶች ነበሩ፡፡ አብዛኞቹ ፈቃዱን ከእርሱ ከፈጣሪያቸው መሻት ውጪ ተጠቀሙበት፡፡ ከሁሉም በላቀ ግን ልቡ የተሰበረው በመከራው ዘመን አብረውት ሲታገሉ ከኖሩት አጋሮቹ መካከል አንዳንዶቹ፣ ጠብ-መንጃቸውን አሽቀንጥረው በነጻ ፕሬስ ስም በብዕር ይሸነቁጡት በገቡ ጊዜ ነበር፡፡ አንዳንዶቹ ቀንድና ጭራ አበጅተው ሰይጣን ያደርጉት ገቡ፡፡ ገሚሶቹ የፈጣሪነቱን ድርሳን አጉድፈው ጻፉ፡፡ በተባረከችው ሀገራችን ላይ የመጣ የምፅአት ምልክት ነው ያሉም ነበሩ፡፡

ኢህአዴግ የዚህ ክህደት ምንጩ ከወዴት እንደሆነ አልተገለጸለትም፡፡ ማዘኑ ግን አልቀረም፡፡ በሀዘኑም መሀል እንዲህ ሲል አሰበ፡፡ እግዚአብሔር መስኮትን ለሣራ ከፈተላት፡፡ ሣራ ያቺ የመስኮት ክፍተት አነሰኝ አላለችም፡፡ ይልቁንም እንዲህ ብላ መስኮትን ለፈቀደላት ፈጣሪዋ ፀለየች፡- “አቤቱ አንተ ፈጣሪዬ ብሩክ ነህ፡፡ ቅዱስና ክቡር ስምህም ለዘለአለም ይመስገን፤ ስራህም ሁሉ ለዘለአለሙ ክቡር ነው”፡፡ እኔ ግን ለህዝቤ መስኮትን ሳይሆን ሀገሩን ሰጠሁት፡፡ በየአደባባይ የረጋ ደሙን አድርቄ ይናፈስበት ዘንድ ክፍት አደረኩለት፡፡ ይሁን እንጂ የግል ጋዜጦች ስለዚህ በጎ ስራ ሊያመሰግኑኝ አልወደዱም፡፡ እነሆ አብዛኛው የመሬትን ከርስ ቆፍሮ አዳሪ ገበሬ በየወንዝና በየሸንተረሩ እያመሰገነኝ ‹‹እነዚህ የግል ጋዜጦች ስለምን ያብጠለጥሉኛል?›› ሲል አሰበ ይህን ባሰበ ጊዜ ኢህአዴግ በፈጠረው ነፃ ጋዜጣ እጅግ አድርጎ ተፀፀተ፡፡ ተፀጽቶም አልቀረ “መጀመሪያ ቃል ነበር” እንዲል ወንጌሉ፣ “የደርግ ኢሠፓ ቅሪቶች፣ ትምክህተኞች፣ ነፍጠኛ አማሮች” የሚሉ ቃላት ፈጠረ፡፡ የግል ጋዜጦችንም እንደፈቀደው በቃላቱ ስር መደባቸው፤ ገሚሶቹንም ወደ እስር ቤት ላካቸው፡፡

ኢህአዴግ የሚፈጥራት አዲሲቷ ኢትዮጵያ በቋንቋ የተነሳ ትደርስ ዘንድ አልወደደምና አህዛብ በየልሳናቸው ይነጋገሩ ዘንድ ፈቀደ፡፡ መኖራቸው እንኳ የማይታወቅ ልሳኖች በቅድስቲቷ ምድር ይሰሙ ጀመር፡፡ ስለፈቃዱም አህዛብ በልሳናቸው ኢህአዴግን አመሰገኑት፤ መስዋዕትም አቀረቡ፡፡ ከሚያመሰግኑትና መስዋዕት ከሚያቀርቡት መካከልም ክፉኛ ያዘኑና የተጎዱም ነበሩበት፡፡ እነዚህኞቹ ክፉኛ ያዘኑት የገዛ ራሳቸው ልሳን ስላልነበራቸው ነውን? በርግጥም ጥቂቶቹ ተራራ አቋርጠው፣ ወንዝ ተሻግረው መጥተዋልና የአያቶቻቸውን ቋንቋ አይናገሩም ነበር፡፡ በፋንታው የአዲሱን መንደራቸውን ቋንቋ ልሳናቸው አድርገው ይጠቀሙበት ነበርና የራሳችሁ ቋንቋ የሚነገርበት ቀዬ ሂዱ ተባሉ፡፡ እነሱ ግን አባቶቻቸውም ሆኑ አያቶቻቸው ከወደየት እንደሆኑ አያውቁም ነበርና ይሄዱበት ገደዳቸው፡፡ ቋንቋውንም የሚናገሩት መጤዎች ቢሆኑ ምንጫቸው ከሌላ ነውና አዲሱ የኢህአዴግ በረከት ራቃቸው፡፡ ቢሆንም ቅሉ አብዛኛው ህዝብ የሚገባውን ተሰጥቶታልና የሚገባቸውን ስላላገኙት የማዶው ጎጥ ሰዎች የተጨነቀ አልነበረም፡፡

እድሮች በየጎጡ በየቋንቋው ይቆሙ ዘንድ፤ አህዛብ በየልሳናቸው ሸንጎ ይሰይሙ ዘንድ የዘፍጥረት ፈቃዱ የኢህአዴግ ሆነ፡፡ ብዙዎች በእድሮቻቸው ተራዱበት፤ በቆሙበት ሸንጎ ፍትህን አገኙ፡፡ በቋንቋቸው የተነሳ ይቀበሩበት እድር፣ ፍትህን ያገኙበት ሸንጎ የቸገራቸው በቁጥር አልገቡም እንጂ ጥቂት አልነበሩም፡፡

እነሆ ኢህአዴግ በእግዚአብሔር ፈቃድ በዘፍጥረት - 83 መንበሩ ላይ ከተሰየመ አንድ አመት ሆነ፡፡ በዚህም ጊዜ የግፍና የበደል ስር ይደርቅ ዘንድ፣ ዴሞክራሲያዊት ሀገር ትገነባ ዘንድ የጣለውን መሰረት ይገመግመው ዘንድ ወደደ፡፡ ሀገሪቱ በአዲስ መንገድ ላይ ናት፡፡ የሽግግር ዘመኑ፣ በሽግግሩ ቻርተር እየተመራ እንደፈቃዱ እየተከወነ ነው፡፡ ያሳለፋትን አንድ አመት ዞር ብሎ ቃኛት፡፡

ህዝቦች በየቋንቋቸው ይግባቡ ጀምረዋል፡፡ የተከለላቸውን መሬት በየባንዲራቸው አድምቀውታል፡፡ በመቅሰፍት ዘመን ምድሪቷን ተጭኗት የትምክህተኞችና የነፍጠኞች ስርዓት እየተወገደ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ኢህአዴግ ይህ መልካም ጅምር ስሩ እንደተነካ የበጋ ችግኝ ይጠወልግ ዘንድ አልወደደም፡፡ ይህንን ጅምር ይጠብቁለት ዘንድ ከፈጠረው ጠንካራ የመከላከያና የፖሊስ ሀይል ውስጥ የተመረጡትን የዘፍጥረት መቀመጫውንና ዋና ዋና አደባባዮችን ይጠብቁለት ዘንድ ለያቸው፤ ፖሊሶቹን ፌደራል፤ ጦር ሰራዊቶቹን ‹‹አግአዚ›› ሲልም ጠራቸው፡፡

ኢህአዴግ በአህዛብ ላይ መቅሰፍት ካከማቸው ከደርግ መንግስት እግዚአብሔር የነጠቀውን የዘፍጥረትን ፈቃድ ያገኘባት ‹‹ግንቦት ሃያን›› ከሌሎች ቀናቶች አስበልጦ ባረካት፡፡ “እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን ከሰራው ስራ ሁሉ አረፈ፡፡ እግዚአብሔር ሰባተኛዋን ቀን ባረካት፤ ቀደሳትም፤ ሊፈጥር ከጀመረው ስራ ሁሉ በእርሷ አርፏልና፡፡” እንዲል መጽሐፉ፣ የዘፍጥረት- 83 ፈጣሪ ኢህአዴግም እንዲሁ አደረገ፡፡ አስራ ሰባት አመት ካደረገው ተጋድሎ በዚህች ቀን አርፏልና ግንቦት ሃያን ባረካት፣ ቀደሳትም፡፡ “በዚህች ቀን የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ህዝቦች በሙሉ ከስራ ይረፉ፤ ፈጣሪያቸው ከአመታት መስዋዕትነት በኋላ በዚህች ቀን አርፏልና፡፡ ወደ አዘቦት ስራው በዚህች ቀን የሚገባ ቢኖር ይቀሰፋል፡፡ ይልቁንም ወደ አደባባይ ይውጣ፡፡ በዚያም ደስታውን ይግለጽ” አለ፡፡ እንዳለውም ሆነ፡፡

(ይቀጥላል)

## የህግ ዓምድ

በዚህ ዓምድ የአገራችንን ህጎች ፣ ዓለም አቀፍ ህግጋት ፣ በሀገራት መካከል የተደረጉ ስምምነቶችን እንዲሁም ለንፅፅር እና ለማገናዘቢያ ይረዳን ዘንድ ሌሎች ሀገሮችን ህጎች መሰረት በማድረግ ከማንኛውም አይነት የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መልኩ ትንታኔ ይሰጣል።

# ጃሚኒግ ሌላው የመረጃ አፈና ዘዴ

ጌታቸው ታምራት (LLB)

የእስያ ፓስፊክ ብሮድካስቲንግ ዩኒየን (ABU) የሊባኖስ ቴሌኮምንኬሽን ሚኒስትር የሆኑትን ኒኮላስ ሳህናዊን ጠቅሶ አንድ መረጃ እንካችሁ አለ። የመረጃው ይዘት ለኢትዮጵያ መንግስት የሚመች አልነበረም። ሚኒስትር ሳህናዊ እንደሚሉት በአካባቢው የሚገኘውን የአረብ-ሳት ስርጭት የሚጠልፈውና የሚገድበው የኢትዮጵያ መንግስት መሆኑን ገልፀው አረብሳትን ከሚያሰራጨው አካል ለኢትዮጵያ መንግስት የተላከው አቤቱታ ቅጂ በእጃቸው እንደሚገኝ ይፋ አደረጉ። በእርግጥ የሊባኖሱ ሚኒስትር በአደባባይ ቢያወሩትም ስርጭቶቹ በቴሌቪዥን መስኮቶች ላይ “No Signal” የማለታቸው ሚስጢር አንድም የኢትዮጵያ መንግስት አልያም ደግሞ የኤርትራ መንግስት መሆናቸውን ጉዳዩ የሚመለከታቸው አሰራጮችና አንዳንድ ሀገራት ኢ-መደበኛ የሆነ ምልከታ ሰጥተውበት ነበር። ድንበር የለሹ የጋዜጠኞች ቡድን እ.ኤአ መስከረም 6/2012ዓም ባወጣው መግለጫ የኤርትራ መንግስት ራዲዮ ኤሪና የሚባለውን ስርጭት ማገዱን ገልጿል። የቴሌቪዥንና የራዲዮን ስርጭቶችን ማገድ /Jamming/ በእነኚህ ሁለት የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት እንደቀላል ቅጥፈት የሚታይ ቢሆንም በዓለም አቀፍ ደረጃ ግን ከፍተኛ ውግዘት የሚያስከትል ሕገ-ወጥ ተግባር ነው። ለወራትና ለዓመታት የሚደረጉ ዕግዶች ቀርቶ ለሰዓታት እንኳ ስርጭቶች እንዲስተጓጎሉ ማድረግ በአንዳንድ ሀገራት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጠዋል። ለምሳሌ በሀምሌ 17/2011ዓ.ም (እ.ኤ.አ.) መሰረቱን ለንደን ያደረገውና ስለ ባህሬይን የውስጥ ጉዳይ ዘገባ የሚያቀርበው ሉዋሉዋ /Lualua TV/ ቴሌቪዥን ለአራት ሰዓታት ያህል ጃም መደረጉ የዓለም የቴሌቪዥን ቀን በሚከበርበት ወቅት ትልቅ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ ነበር። አፋኝ መንግስታት የስርጭቶችን ዱካ እየተከተሉ ‹‹ጃም›› የሚያደርጉት ‹‹ሃይ የሚላቸው ሕግ ወይም ስምምነት አለመኖሩ ነው ወይስ ህጉን የሚያስከብር አካል ጠፍቶ ነው?›› የሚል ጥያቄ ያስነሳል።

ጠለፋና ጃም ማድረግን አስመልክቶ ከሰው ልጅ መብትና መረጃን ከማዳረስ አንፃር የሚያስከትሉትን ችግር መሰረት በማድረግ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተለያዩ ሕግጋትና ስምምነቶች ተደርገዋል። ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃልኪዳን (ICCPR)፣ እ.ኤ.አ. በ1950ዓ.ም ከስምምነት ላይ የተደረሰበት የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ቁጥር 424(V)፣ በ1986 ዩኔስኮ ይፋ ያደረገው የትምህርት ስርጭትን፣ የባህል ልውውጥና ነፃ የሆነ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር የሚጠይቀው ዲክላሬሽንን እንደ አብነት ማንሳት ይቻላል። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ አንዳንድ ስምምነቶችን ከተለያዩ ሀገራዊ ጥቅሞች አንፃር አለመፈረም፣ ለመፈረም ማንገራገር አንዳንዴም ከፊርማ በፊት አንዳንድ ቅድመ ሁኔታዎችን ማስቀመጥ የተለመዱ ተግባራት ናቸው። ይሁንና እነኚህ ማንገራገሮች ስምምነቱ ለሀገር ከሚያመጣው ፋይዳ አንፃር እንጂ መንግስታት ላይ ከሚያስከትለው አደጋ በመነሳት አይደለም። ሆኖም አንዳንድ ስምምነቶች ደግሞ ለየትኛውም ሀገር ህዝቦች ከሚሰጡት ጠቀሜታ አንፃር እነሱን ላለመፈረም ማንገራገር የዚያን ሀገር መንግስት ከህዝቦቹ ጋር ያለውን ቀረቤታ ያሳብቁበታል። ስለዚህ ሁሉም ሀገራት በሚባል ደረጃ የዚህ ዓይነት ስምምነቶችን ይፈርማሉ። ይህን ስል የሰሜን ኮሪያን መንግስት የመሳሰሉ ከዓለም አቀፍ የህግ ማዕቀፍ ራሳቸውን ያራቁ መንግስታትን አይመለከትም። አብዛኛዎቹ ሀገራት ከሚፈርሟቸውና ለህዝቦች ትልቅ ጠቀሜታ አላቸው ከሚባሉ ስምምነቶች ውስጥ የዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን ይገኙበታል። ይህ ቃልኪዳን በአንቀፅ 19 ላይ የህዝቦች መብትንና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብቶችን በሚያስቀምጥበት ርዕስ ስር ግለሰቦች ማንኛውንም ዓይነት መረጃ የማግኘት እንዲሁም የማዳረስ መብት እንዳላቸው ደንግጓል። አንቀፅ 19 እንደሚገልፀው ሆን ተብለው የሚደረጉ የጃሚንግ ተግባራት በግልፅ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ናቸው ይላል። ህዝቦች በነፃነት መረጃን እንዳያገኙና እንዳያሰራጩ መከልከል ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን መገደብ ስለሚሆን ትልቅ የሰብዓዊ መብት ጥሰት አድርጐ ይህ ቃልኪዳን ይቆጥረዋል። ከዚህ በተጨማሪ ይህ አንቀፅ በየትኛውም ሀገር ያሉ መንግስታት ከዚህ መሰል ተግባር እንዲታቀቡና በእንዲህ ዓይነቱ ተግባራት ውስጥ የሚሳተፉ በሀገራቸው የሚገኙ ተቋማት ላይ እርምጃ እንዲወስዱ ይጠይቃል። የ‹‹ሳተላይት እቀባ›› ተብለው በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተቀመጡት ተግባራቶች መካከል ከሌሎች ሳተላይቶች ላይ ጠንካራ ሲግናል መልቀቅ፣ የስርጭት ሳተላይቶች ላይ ሌላ ሲግናል መልቀቅ እንዲሁም ከመሬት ላይ በሚደረግ የሲግናል ስርጭት ፕሮግራሞቹ የታቀደላቸውን ዓላማ እንዳይጫወቱ ማድረግ ይገኙበታል። በእንዲህ ዓይነት ተግባራት ተሳታፊ ናቸው ተብለው በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ፣ ኤርትራ፣ ኢራን፣ ባህሬንና ሰሜን ኮርያ ይገኙበታል።

ስርጭቶችን ጃም በማድረግ የሚከሰሱ ሁሉም ሀገራት በሀገር ውስጥ ነፃ ሚዲያን የሚያፍኑ፣ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ሚዲያዎችን ሳንሱር የሚያደርጉና መረጃ የማግኘትን ነፃነትን የሚጋፉ ሀገራት ናቸው። ሁሉም ሀገራት ስርጭቶችን ለመጥለፋቸውና ተጠቃሚ ጋር እንዳይደርሱ ለማድረጋቸው እንደ ምክንያት የሚገልፁት ሀገራዊ ደህንነትና አንዳንድ የውጭ ሀገር ፕሮፓጋንዳዎች በሀገር ውስጥ እንዳይሰራጩ በማሰብ እንደሆነ ይከራከራሉ። በአንቀጽ 19 የተቀመጠው መረጃን የማግኘት መብት በሀገራት ውስጥ ራሱን በድንበር አይከልልም። አንቀፅ ዜጐች ያለገደብ ከየትም አካባቢ የሚለቀቅ መረጃን የማግኘትም ሆነ የማዳረስ መብት በስምምነቱ መሰረት አስቀምጦላቸዋል። ይሁንና በአንዳንድ ምክንያቶች መነሻነት ሊከሰቱ በሚችሉ ህገ-ወጥ ተግባራት የሀገራትን ደህንነትና የህዝቦችን መብት በበቂ ሁኔታ ለመጠበቅ ሲባል የዚሁ ቃልኪዳን አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 3 ሶስት መንገዶችን አስቀምጧል። እነኚህ መንገዶች ‹‹The three-part test›› እየተባሉ ይጠራሉ። ህገ-ወጥ ያልሆነ ጃሚንግ ለማድረግ በመጀመሪያ ለምን ዓይነት ሁኔታዎች ጃም እንደሚደረግ መገለፅ አለበት። ሁለተኛ ሁኔታዎቹም በህግ መገለፅ አለባቸው። ይሁን እንጂ ጃም ለማድረግ የተገለፁት ሁኔታዎች በምንም ዓይነት መንገድ እንደ ክፍተት ተወስደው የተለየ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸውን አካላት፣ ነፃ ሚዲያዎችና መሰል ተቋማትን ለማጥቃት የተሰሉ መሆን የለባቸውም። ይህ ከሆነ በአንቀጽ 19 በመርህ ደረጃ የተቀመጠውን ሀሳብን በነፃነት የመግለፅና መረጃን የማግኘት መብትን ይጋፋል። በተጨማሪም የስልጣን ግድፈትን ለመከላከል ህጉ የሚቆጣጠርበት መንገድ ሊኖረው ይገባል። ሦስተኛ ተብሎ የሚጠቀሰው፤ ጃም የማድረግ ስራው በትክክል ለታሰበለት አላማ ብቻ እንደተከወነ መረጋገጥ ይገባዋል የሚል ነው። በተጨማሪም ጃም ከማድረግ ሌላ አማራጭ እንደሌላቸውም ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል።

እነዚህ ጃም ለማድረግ የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች ቢኖሩም አብዛኞቹ በጃሚንግ ተግባራት ላይ የተሳተፉ ሀገራት ከላይ ከተቀመጡት ህጋዊ መንገዶች አንዳቸውንም አይከተሉም። በዚህም የተነሳ ለተሳተፉበት ህገ ወጥ የስርጭት እቀባ ስራ አንድም ማስረጃ ማቅረብ አይችሉም በማለት የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችና የስርጭቶቹ ባለቤቶች ይከሷቸዋል። የኢትዮጵያ መንግስትም ላደረጋቸው የስርጭት እገዳዎች የሚሰጠው ምክንያት ከኢራንና ከኤርትራ የተለየ አይደለም። አረብ-ሳትን የሚያስተዳድረው አካል የኢትዮጵያ መንግስት አድርጐብኛል ለሚለው የጃሚንግ ተግባር በመንግስት የተሰጠውን የማስተባበያ ምክንያት አልተቀበለውም። በሀገር ውስጥ የተደነገጉ ሕጐችን እንደምክንያት ቢያነሳም እነዚህ ህጐች በራሳቸው ከዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር የሚጋጩ ከሆነ ችግሩ ያለው ሕጐቹን ካወጣው አካል ጋር እንጂ ከስምምነቶቹ ስላልሆነ ሕጐቹን እንደገና ማጤን ይገባዋል። በሀገር ደህንነት ሰበብ የዜጐችን ሰብዓዊ መብት መጋፋት ለየትኛውም ሀገር በምንም መልኩ መከራከሪያ ምክንያት ተደርጐ ሊቀርብ አይችልም። ሀገራት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚሰጣቸው ተቀባይነት ሊጨምርም ሊቀንስም የሚችለው ለፖለቲካዊና ሰብዓዊ መብቶች በሚሰጡት ትኩረት ሲሆን፤ ከሀገራት ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት፣ ታዳጊ ሀገራት ከበለፀጉ አገራት የሚያገኙት እርዳታና ለሌሎች ጉዳዮች የመብት አያያዛቸው ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል። የኢትዮጵያ መንግስት ደግሞ በተለየ መልኩ ከሌሎች የዓለም ሀገራት ተገልሎ ብቻውን የሚቆም መንግስት ስላልሆነ በከፍተኛ ሁኔታ የዜጐችን መብት ማክበር ይጠበቅበታል። ከመረጃ ጋር በተያያዘ በሀገር ውስጥ ከሚደረገው ሳንሱርና እጅ አዙር እገዳ በተጓዳኝ የህዝብን ሀብት የፖለቲካ አጀንዳ ለማስፈፀሚያ እንዲውል ማድረግ ሌላ ሕገ-ወጥነት ነው። ሕዝቡ መረጃ የማግኘትና የማስተላለፍ መብቱን ከመገደብ አልፎ በራሱ ሀብት ራሱን ለማፈን መሞከር በወንጀል ላይ ሌላ ወንጀል ነው። ለጃሚንግ (ለአፈና) ተግባር የሚውለው ገንዘብ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ እንደ ኢትዮጵያ ባለ ሀገር ላይ የሚያደርሰው ኪሳራ መጠነ ሰፊ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ህዝቡ ከውጭ ያሉ የመረጃ ምንጮችን ለማግኘት የሲግናል መቀበያ ሳህኑን ከወዲያ ወዲህ እንደ ቁና የሚያገላብጠው ኢቲቪን ለማግኘት ነው ብሎ የሚከራከር ያለ አይመስለኝም። የኢትዮጵያ መንግስት የጃሚንግ ስራ በአረብ-ሳት ላይ አጥፍተህ ጥፋ ሆኗል። ሌሎችንም አጥፍቷል ራሱንም ከሳተላይቱ አስወጥቷል። የአረብ-ሳት ጃሚንግን በቋሚነት ለመከላከል መፍትሄ እያፈላለገ ይገኛል። የኢትዮጵያ መንግስትስ በቋሚነት ጃም ለማድረግ እየጣረ ይሆን?… ማን ያውቃል?

ቸር እንሰንብት።

ስርጭቶችን ጃም በማድረግ የሚከሰሱ ሁሉም ሀገራት በሀገር ውስጥ ነፃ ሚዲያን የሚያፍኑ፣ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንገድ ሚዲያዎችን ሳንሱር የሚያደርጉና መረጃ የማግኘትን ነፃነትን የሚጋፉ ሀገራት ናቸው።

# የየዋሑ ሰው መልዕክት ለአቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ



ዳዊት ታደሰ

በቅዱስ መጽሐፉ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች ሰማያዊ የሆነውን ፀጋና ሰላም እንዲበዛላቸው ከተመኘ በኋላ እንዲህ የሚነበብ መልዕክት ልኮላቸው ነበር።- ‹‹በአንድ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢያተኞች እንደ ሆኑ÷ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ፃድቃን ይሆናሉ።›› (ወደ ሮሜ ሰዎች ም.5 ቁ.19)

ሀገር መምራትን ያህል ሽክም እንደሌለ ይሰማኛል። በተለይ እንደኛይቱ ኢትዮጵያ በታሪክና በባህል ምች ተመትታ ለምትዳክር ሀገር፣ ድህነትና ጦርነት እንደ ቅፅል ማዕረግ ሆኖ ለሚነገርላት ሀገር፣ የዜጎቿ እንባ እንደጅረት ሲፈስ እየታየ ለማይታበስባት ሀገር። እንዲህ ባለው ሀገር መሪ ሲሾም የመምራት ብቻ ሳይሆን ሀገርን ከሞት የማትረፍ ጥሪና ተልዕኮ አብሮ ይቀበል ዘንድ ይገደዳል። ይሄ ደግሞ ፀጋም እዳም ነው። እርስዎ ብቸኛዋን ወንበር ለመያዝ የታጬበት ወቅት ሀገርዎ በምትፈልግዎ ሰዓት በመሆኑ የቁርጥ ቀን ልጃችን እንድንልዎ ሆነናል። የሀገሪቱ የመጨረሻ ሰው እንደመሆንዎ ዛሬን ጨምሮ ከዚህ በኋላ ለሚሆነው ሁሉ ኃላፊነቱ በእጅዎ ነው። ስኬት ወይም ውድቀት፤ ድል አሊያም ሽንፈት ከሰፊ ቢሮዎ ጠረጴዛ በላይ የተቀመጡ ወሳኝና ልዩነት ፈጣሪ ምርጫዎች መሆናቸው ነው። ከዚህ በመነሳት ቀሪ ህይወትዎ የሚኮሩበት ወይም የሚያፍሩበት መሆኑን መገመት ይችላሉ። ይህን ስልዎ ግን አያውቁትም በሚል ድፍረት እንዳይመስልዎ፤ ቀልብዎን ለመሳብ እየሞከርኩም አይደለም፤ ይልቁኑ በፍፁም ትህትናና ጥልቅ በሆነ አክብሮት መሆኑን ከወዲሁ ይረዱልኝ።

የማስተርስ ዲግሪዎን በስራ አመራር (Organizational Leadership) በሰሩባት አሜሪካ በመዲናዋ ዋሽንግተን ዲሲ ለእንግዳም ቢሆን በግልፅ የሚታዩ ሁለት ምልክቶች አሉ። አንደኛው የዋሽንግተን ሀውልት ነው። ጆርጅ ዋሽንግተን ሀገሩን አንድ አድርጎ ለመምራት ስለከፈለው መስዋዕትነት ሲባል ሀገሬው ያስቀመጠለት ‹‹ትንሹ›› ማስታወሻ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የሊንከልን መታሰቢያ ይባላል። ይሄኛው ዋሽንግተን አንድ ያደረጋት ውድ ሀገሩን አንድነቷን ጠብቆ ላቆያት ለአብርሃም ሊንከልን የተገባው መሆኑ ነው። እኚህ ሁለት መታሰቢያዎች መሪዎቹ ሀገር ለማቆም እና ለማቆየት ሲሉ ላሳዩት ፅናት ክብር ለመስጠትና ህያውነታቸውን ለመዘከር የተገነቡ ቋሚ ምስክሮች ናቸው። የሀገርን ዕጣ ፈንታ ለመወሰን ብዙዎች ቢደክሙም ታሪክ የሚያስታውሰው እንዲህ ያሉትን ነው። እርስዎም ቢሆኑ ከእነዚህ ጥቂቶች መካከል አንዱ ለመሆን ተግተው ከመፀለይም ባለፈ ተግተው እንዲሰሩ እማፀንዎታለሁ። ዝንተ-ዓለም ለመታወስ እንዲሁም ስምና ክብርዎ እንደ አለት እንዲፀና አቅላችንን ያሳተንን ግራ ፖለቲካውን ወደ ጎን ትተው ለዘመናት የተጫነንን የአገዛዝ ቀንበር ለመስበር ይደፍሩ ዘንድ የፈጣሪያችን ኃይል ከቀኝዎ እንዲሆን እለምናለሁ።

ሀገሬ በመልካም ስነ-ምግባር የታነፀ፤ አይኖቹን ወደ ፈጣሪ እጆቹንም ወደ አምላኩ የሚቀስር መሪ በማግኘቷ ደስታዬ እስካሁን አልበረደም። ሌሎቹ ይቅሩና ከእርስዎ በፊት የነበሩት አቻዎ ሃይማኖት እንደነበራቸው ያወቅነውስ በቀብር ስርዓታቸው ወቅት አልነበር እንዴ? ስለቤተ-መንግስታቸው ሲሉ ቤተ-መቅደሳችንን አርክሰውትስ አልነበር? በቀደመው ዘመን ከሃይማኖት አፈንጋጭ ገዢዎቻችን የአምላክ ህላዌነትን በመካድ የእምነት እሴቶቻችን ከተሸሸጉበት ቤተ-መቅደስ ጓዳ ድረስ በመግባት ሲያራብሹን ቢከርሙም። ከእምነት ተቋማቱ በራፎች ላይ የፈሰሰው የምዕመኑ እንባ ፈጣሪንም አስለቅሶታል መሰለኝ ይኸው ለአምላኩ ቀናኢ የሆነን ሰው ከመካከላቸው አስነስቷል። ስለእውነት ለመናገር የእስከዛሬው ቆይታችን ሶቅራጠስ ጥበብ የተጠማውን ወጣት ባደረገው ቢመስል ለመረዳት ይቀላል። ጎረምሳው ጥበብ ከወዴት እንደምትገኝ እንዲነግረው ፈላስፋውን ይጨቀጭቀዋል። ጠቢቡም በፍጥነት በአቅራቢያቸው ወደሚገኝ አነስተኛ ኩሬ በመሄድ የወጣቱን አንገት ይዞ ውሃ ውስጥ ይዘፍቀዋል። ከጥቂት ማፍጨርጨር በኋላ ቀና በማድረግ ‹‹ውሃ ውስጥ በነበርክ ሰዓት ከምንም በላይ የፈለግከው ምን ነበር?›› በማለት ሶቅራጠስ ጠየቀ። ወጣቱ ‹‹አየር›› እንደሆነ ሲናገር ጥበብ የሚገኘው በዚህን ያህል ናፍቆት ሲፈለግ እንደሆነ ጠቢቡ ተናግሮ አለፈ። ለነብሳችን ያደርንባቸው ቤተ-አምልኮዎችም ልክ እንዳየነው ወጣት ትንፋሽ እስኪያጥራቸው ድረስ በፖለቲካው ታፍነዋል። ከአፈናው ሲያቀናቸው ነፃነትን ምን ያህል ይመኟት እንደነበረ ይመሰክሩልዎታል። እናም እባክዎን! ስለእምነትዎ ሲሉ ቤተ-እምነቶችን ከመንግስት ሰፊ መዳፎች ይታደጓቸው። ስለሃይማኖትዎ ሲሉም የየትኛውም ሃይማኖት ተከታዮች በነፃነት እንዲያመልኩ ነፃ ያውጧቸው።

መቼም የኋላ ታሪካችን እንደሚነግረን ከሆነ እኛ ኢትዮጵያዊያን ለሎሌነት አንመችም። እንጀራ አጉርሰው በባርነት ሰንሰለት ሊጠፍሩን የከጀሉ ሁሉ ሞክረው ወድቀዋል። በጊዜያችንም ጥቅመኛ ሆኖ ለስጋ ከመኖር የስርዓቱን አስከፊነትና መንግስታዊ ስህተቶችን ነቅፈው እንዲታረም ደፋ ቀና ሲሉ የነበሩ የሞያ ጓደኞቼ ምስክር ይሆናሉ። ዳሩ ምንያደርጋል! በቃሊቲው እስር ቤት ውስጥ እንደቀማኛ ተወረወሩ እንጂ። በሰባራ ምክንያት የታሰሩት እነኚህ ወጣቶች ለቤተሰብና ለወዳጆቻቸው ብቻም ሳይሆን ለሀገሬና ለፓርቲዎ እጅጉን ይጠቅሙ ነበር። የእርስዎ ሰዎች ያላዩትን ህፀፅ በመጠቆም ላሳዩት ተጋድሎ መመስገን በተገባቸውም ያሰኛል። መሪዎን እንዳጣች መርከብ ወዲህና ወዲያ ለምትለው ሀገር፤ አንዱ ወደ ግራ ሌላኛው ወደ ቀኝ እያለ የሚያዋክብ ተሳፋሪ በሞላበት ታንኳ ውስጥ እንዲህ አይነት ልጆችን ማግኘት እንዴት መታደል ነበር!? እውነት እውነት እልዎታለሁ ለህዝብና ለሀገር ጥቅም ከታሰበ እነኚህን ‹ፀሐዮች›› ማሯቸው ስል እጠይቆታለሁ። እባክዎን! የስሟ ትርጓሜ ‹የእግዚአብሔር ስጦታ› ስለሆነው ልጅዎ ስለዮሀና ሲሉ የናፍቆትን አባት እስክንድርን ይፍቱልን። ስለባለቤትዎ ስለ ሮማን ሲሉ የአቶ አለሙን ልጅ ርዕዮትን ይልቀቁልን። ስለወላይታ ወጣቶች ሲሉ የኦሮሚያ ወጣቶችን ይማሩልን። ስለደቡብ ክልል ሲሉ የሁላችንም የሆነችውን ኢትዮጵያን ነፃ ያድርጉልን።

በቅርቡ በመካከለኛው አውሮፓ ነዋሪ ነኝ ያሉ የቀድሞ ወዳጅዎ ከእርስዎ ጋ ስለነበራቸው የአስር አመታት ጓደኝነትና ስለባህሪዎ የገለፁበትን ፅሁፍ ከድረ-ገፅ ላይ ተመልክቼ ነበር። በወርቃማው ጊዜያት የነበራችሁ ፍቅርና መተሳሰብ እንዴት ያስቀና እንደነበር በቅናት ተርከዋል። ከዚህ ባለፈም የአርባ ምንጭ ውሃ ቴክኖሎጂ ተቋም ኃላፊዎችን በመምህራን ማህበር ስብሰባዎች ላይ በጠንካራ ተቃውሞ ሲጋፈጧቸውና ሌሎች ጓደኞችዎም የተሰማቸውን በድፍረት እንዲያወጡት ያበረታቱ እንደነበር ወዳጅዎ በፅሁፋቸው አትተዋል። ከአቶ መለስ የአርባ ምንጭ ጉብኝትና ከእርስዎ ዲን ሆኖ መሾም በኋላ ያ መልካም ባህሪዎ ፈተና ላይ መውደቁ እንዳሳዘናቸውም ገልፀዋል። ይሄ ግን ለእኔ ብዙም የሚዋጥ አልሆነም። የአመራር ቁርጠኝነትን ለማሳየት ሲሞክር ብዙ ወዳጆች ሊከፉ ይችላሉ። የኚህ ሰው መከፋት የመነጨውም ከዚህ በመነሳት ሊሆን ይችላል። በጉብዝናዎ ወራት እንዴት ባለ ጥንካሬ አለቃዎችዎን እንደሚጋፉ የተነገረውን ግን ከሌሎችም ስለሰማው ግለሰቡ ዋሽተዋል ለማለት ከበደኝ። ይሄ ነብርነት አሁንም ከእርስዎ ጋር እንዳለ አምናለሁ። በዙሪያዎ የከበቡት ከውይይት ይልቅ በብረት የሚያምኑ ባልደረቦችዎ እርስዎን ለመቆጣጠር እንደማይመቻቸው የተረዱት ይመስለኛል። ነገር ግን ያ የወጣትነት ባህሪዎ እኔው ጋም ስላለ ስህተትዎን ስነቅፍ ብዕሬን እንዲነጥቁኝ ያማክሩዎ ይሆናል። ስለወጣትነት ጊዜዎ ይገፄዎታለሁ አያዳምጧቸው፣ የወጣትነቴንም ኃይል አያምክኑብኝ። ስለሚያደፋፍሯቸው የቀድሞ ጓደኞችዎ ሲሉ ጓደኞቼንም ይተዋቸው።

ሌላም የምነግርዎ አለኝ። ዴሞክራሲን እንደ አባት ስሙ ስለደረበው አብዮታዊ አስተሳሰብ። በሰብዓዊ መብት አፈናና በአምባ-ገነናዊ አገዛዝ ልማታዊነትን ለማግነን የሚሞክረው ይሄ ኃልዮት ኢትዮጵያዊ ስብዕናችንን እያረከሰው መሆኑን ይገንዘቡልኝ። እንዲህ እንድል ያስገደደኝ አብዮታዊ ዴሞክራሲ አባቶቻችን የኖሩበትና እኛም ያደግንበት ‹ቅድሚያ ለሰው ልጅ ህይወት ክብር› የሚሰጠውን ማህበራዊ ህጎቻችንን በአፍጢሙ ደፍቶ ግለኝነትና ራስ-ወዳድነትን ለመተካት እየጣረ እንደሆነ ስለገባኝ ነው። እዚህች ጋር የዶስቶቪስኪ ስራ ከሆነው ‘Brother Karamazov’s’ አንድ ዘለላ ልጥቀስልዎ። አይቫን የተባለው ገፀ-ባህሪ ለታናሽ ወንድሙ ‹‹ለሰው ልጆች ሰላምንና እፎይታን በስተመጨረሻ በሚያስገኝ የህንፃ ግንባታ ስራ ተጠምደሀል እንበል። ይህ ይሆን ዘንድ ግን አንድ ህፃን አሰቃይቶ መግደል የግድና የማታመልጠው ቢሆን የህንፃው ሙያተኛ ለመሆን ትስማማለህ ወይ?›› ብሎ ይጠይቀዋል። ታናሽ አልዩሻም ጥያቄውን በጥያቄ መልሶ ‹‹እነኛ ህንፃውን የምታንፅላቸውስ በአንድ ህፃን የደም ክፍያ የሚመጣን ደስታ ለመቀበል ይስማማሉ?

ወደ ገፅ 21 ዞሯል

# የኃይለማርያም የርዕዮተ-ዓለም ዕዳ



*ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ*

በቀደመው ወር መጨረሻ የጠቅላይ ሚኒስትርነት ሲመታቸውን ያገኙት ኃይለማርያም ደሳለኝ ሹመቱን ተከትሎ የተከተላቸው የመጀመሪያው የስራ ኃላፊነት በኒውዮርክ ከተማ በተዘጋጀው የተባበሩት መንግስታት ስብሰባ ላይ ንግግር ማድረግ ነበር። በወቅቱ ሰውዬውን ለቃለ-መጠይቅ ያገኛቸው የአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ የአፍሪካ ቀንድ ፕሮግራም አዘጋጅ ፒተር ኃይንላይን ከሀገር ውስጥ ፖለቲካ እስከ የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ድረስ ባሉ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ሲጠይቃቸው እርሳቸውም አጫጭር መልሶችን ሲሰጡ የቆዩት አቶ ኃይለማርያም የፓርቲያቸውን ርዕዮተ-ዓለም ምንነት ሲያስረዱ ኢህአዴግ ‹‹ተራማጅ ግራ-ዘመም›› ፓርቲ መሆኑን ባልተለመደ ድፍረት ተናገሩ። እርሳቸውን ጨምሮ አሁን በስልጣን ላይ ያሉትም ሆኑ የቀድሞ ጠ/ሚኒስትር አቶ መለስ ከምዕራባውያን ጋዜጠኞች ጋር ሲገናኙ ለመግለፅ የማይደፍሩትን አቶ ኃይለማርያም መናገራቸው ፓርቲያቸው አሁንም ድረስ ከግራ-ዘመምነቱ እንዳልተላቀቀ ጥቁምታ መስጠቱን የፖለቲካው ተከታታዮች ይናገራሉ።

ከዚህ የአደባባይ የሰውዬው ኑዛዜ በዘለለ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ኢትዮጵያን ወዴት ሊወስዷት እንዳሰቡ ለማወቅ ለሚሹ፤ ስራቸው ‹‹የመለስን ራዕይ››ን ከማስፈፀም የዘለለ እንዳልሆነ በተደጋጋሚ እየተናገሩ ነው። ይህ የሚቹ ሰው ‹‹ራዕይ›› ዋነኛ አዕማድ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮተ-ዓለም ስለመሆኑ የሀገሪቱን ፖለቲካ ያጠኑ ሁሉ ይስማማሉ። የረጅም ጊዜ የኢትዮጵያ ወዳጅና አጥኚ የሆኑት ዶ/ር ሳራ ቫግሆን እንደሚሉት ‹‹ስለ ርዕዮተ-ዓለሙ በበቂ ሁኔታ ለመናገር አስቸጋሪ ነው›› ይላሉ፡ ፡ ለዚህም ሁለት ተዛማጅ ምክንያቶች ይቀርባሉ። የመጀመሪያው ባለፉት ሃያ አንድ ዓመታት ሲበረዝና ሲከላለስ የከረመው አብዮታዊ ዴሞክራሲ በተለያዩ ወቅቶች ማህበረሰቡን ወደተለያዩ እና እርስ በርስ ወደሚጣረሱ ግቦች እንደሚያደርስ በተደጋጋሚ ስርዓቱን በሚተቹ ሰዎች ሲወሳ መቆየቱ ነው። በመጀመሪያ ወደ ሶሻሊስት ስርዓት ያደርሳል የተባለው ርዕዮተ-ዓለም ከ1980ዎቹ መጨረሻ ወዲህ ወደ ሊበራሊዝም እንደሚያደርስ ተሰበከ። ከ1990ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ደግሞ ልማታዊ መንግስት የማይቀለበስ የፓርቲው ግብ እንደሆነ እየተወሳ ነው። እነዚህ ተለዋዋጭ ትንታኔዎች ርዕዮተ-ዓለሙን ለማጥናት አስቸጋሪ እንዳደረገው የሚጠቅሱት የኤዲንበርግ ዩኒቨርስቲው መምህር ሁለተኛው ምክንያት አድርገው የሚያቀርቡት ፅንሰ-ሀሳቡን በሚገባ የሚያውቁት የፓርቲው ጥቂት ልሂቃን ብቻ መሆናቸው ነው። እነዚህ ልሂቃን ደግሞ ለአጥኚዎች የማይደረስባቸው ሆነው መራቃቸው ስለጉዳዩ ለመናገር ምሁራኑን እንዲከብዳቸው ማድረጉን ሴትዮይቱ ይጠቅሳሉ። ኢህአዴግ በሊቀመንበሩ አንደበት ‹‹ግራ-ዘመም›› ፓርቲ ስለመሆኑ መታወጁ እና የሚቹ ሰው ‹‹ራዕይ›› በግራ-ገብነት የተበረዘ በሚባለው ርዕዮተ-ዓለም ላይ የቆመ መሆኑ ስለሃሳቡ ጥቂት ነገሮችን ማንሳት የአዲሱ አመራርን ቀጣይ እርምጃዎች ለማንፀር ሳይጠቀም አይቀርም።

## ሀያ ዓመታት ወደኋላ

ሰኔ 1985 ዓ.ም. ኢህአዴግ ሀገሪቷን ወዴት ሊወስዳት እንዳሰበ ለአባላቶቹ የሚያስረዳበት አንድ ሰነድ አሳተመ። ‹‹የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ግቦችና ቀጣይ እርምጃዎች›› በሚል ርዕስ በጥብቅ ሚስጥር የተበተነው ይህ ባለ 68 ገፅ ዶክመንት የፓርቲውን ያለፉትን የሃያ አንድ ዓመታት አስተዳደር ባህሪያት በሚገባ ይናገራል። በአለም አቀፍ የፖለቲካ መድረክ የቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት እና የሊበራሊዝም ፖለቲካዊ አስተምህሮ የበላይነት አውድ ላይ ወደ ስልጣን የመጡት የፓርቲው ሰዎች ግራ-ዘመምነታቸውን ሙሉ ለሙሉ ሳይተው ‹‹አደናጋሪ›› በሚባለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ስር ለመጠለል መሞከራቸውን ጉዳዩን ያጠኑ ምሁራን ይናገራሉ። ሰነዱን በጥልቀት የተነተኑት ፕ/ር ቴድሮ ቬስታል የሰነዱ ተቀዳሚ ግብ ‹‹የርዕዮተ-ዓለሙ ዋነኛ ማጠንጠኛ፣ የፓርቲው መሪዎች ሁሉንም የማህበረሰቡን የህይወት ገፅ ‹‹አለን›› በሚሉት ላዕላይ እውቀት ለመምራት መወሰናቸውን›› የሚያሳይ ነው ይላሉ።

ይህ በፓርቲው ታሪክ የመጀመሪያው የሚባለው ሰነድ ዋነኛ ግቦቹን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ በማለት በሁለት ይከፍላል። ቀዳሚው ፖለቲካዊ ግብ ‹‹የህዝቦችን ፖለቲካዊና ሰብዓዊ መብቶች ማክበር›› ሲሆን፤ ርዕዮተ-ዓለሙ የሚተገበረው በአገሪቱ ውስጥ ሁለት ፅንፈኛ ማህበረሰባዊ ቡድኖች ባሉበት ነባራዊ ሁኔታ እንደሆነ ይናገራል። ፓርቲው ‹‹ህዝቦች›› የሚለውን ‹‹የተጨቆኑት ብዙሃን›› ብሎ ሲፈታው፤ ሁለተኛውን ‹‹ፅንፈኛ ቡድን›› ደግሞ ‹‹ጨቋኞች›› ይላቸዋል፡ ፡ ጨቋኞች የሚባሉት ቡድኖች በቀደሙት ሁለት ስርዓቶች በገዢነት የተሳተፉትን እንደሚመለከት ቢያወሳም፤ ‹‹ፓርቲውን የሚቃወሙትን ሁሉ ያካትታል›› ይላሉ ቬስታል ‹‹Ethiopia; a post-cold war African state›› በሚለው ስራቸው። ‹‹ተጨቋኞች›› የተባሉት ከመደራጀት እስከ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብቶች ድረስ ተሰጥቷቸዋል። የርዕዮት አለሙ መከራከሪያ ግራ-ገብነትን የሚፈጥረው እነዚህ መብቶች ለ‹‹ጨቋኞች›› መሰጠታቸውን አስመልክቶ ያለው አቀራረብ ነው። እንደ ፓርቲው ሙግት፤ የ‹‹ተጨቋኞቹ›› መብቶች አተገባበር ከ‹‹ጨቋኞቹ›› መብቶች ጋር የሚቃረንበት ዕድል ከተፈጠረ፣ ገዢው ፓርቲ ለህዝቦቹ መሰረታዊ ጥቅሞች ሲል የ‹‹ጨቋኞቹ›› መብቶች መጨፍለቅ ይኖርባቸዋል። ሰነዱ እነዚህን መብቶች የፓርቲውን አቋም ለሚፃረሩ ኃይሎች የመስጠቱን መግፍኤ ከሁለት ጫፍ ለመተንተን ሞክሯል።

የመጀመሪያው ምዕራባውያን ለጉዳዩ የሚሰጡትን ዋጋ እና በእነርሱ አይን ሊገኝ የሚገባውን ተዓማኒነት በመንተራስ የሚቀርብ ነው። የዓለም አቀፉ የፖለቲካ አሰላለፍ በ‹‹ኢምፔሪያሊስቶች›› የሚመራ መሆኑ፤ እንደቀደሙት ዓመታት ኢህአዴግ ከአንዱ ዓለም አቀፍ ስብስብ ወደሌላኛው በቀላሉ መገለባበጥ አይችልም። ፓርቲው እንደሚያምነው፤ የተጠቀሱትን ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶች በህግ-ማዕቀፍ እርሱ ላነወራቸው ማህበረሰባዊ ቡድኖች ባይሰጥ፣ ‹‹አሜሪካ ኢምፔሪያሊስት ኃይሎችን በማስተባበር የሀገሪቱ እርዳታ እንዲቋረጥ ልታደርግ ትችላለች››። የሚለው አንዱ ምክንያት ነው።

ሁለተኛው መከራከሪያ የፓርቲውን ጥንካሬና የተቃዋሚዎችንም ሆነ የ‹‹ጨቋኝ ገዢ መደቦችን›› አቅም አልባነት በማነፃፀር ለማቅረብ የተሞከረበት አካሄድ ነው። እንደ ሰነዱ አቀራረብ ከሆነ እነዚህ ‹‹ፊውዳልና ፀረ-ህዝቦች›› ስርዓቱ ላይ ለመነሳት ያላቸው አቅም እጅግ ደካማ ነው። በተፃራሪው ፓርቲው ከገበሬው የሚያገኘውን ድጋፍ ጨምሮ መንግስታዊ ስልጣኑን የመጠቀም እድል ስላለው ተገዳዳሪ ኃይሎቹ በራሳቸው አያስጉም፡ ፡ እነዚህ ሃይሎች ስጋት ሊሆኑ የሚችሉት በፓርቲው የተከፉ ‹‹ኢምፔሪያሊስቶች›› ሲረዷቸው ከሞከሩ ብቻ ነው። በመጀመሪያው መከራከሪያ መሰረት ይህ የሚከሰትበት እድል ጠባብ ቢሆንም፤ የመተግበር እድል ካለው ግን ‹‹መጨፍለቅ›› እንደሚገባ ፓርቲው ያምናል። ይህን ጭፍለቃ ለመከወን ሁለት ተመጋጋቢ መንገዶች አሉ። የመጀመሪያው ህገ-መንግስቱ እና ከህገ-መንግስቱ በታች ያሉ የትኞቹም ህጎች ሲሆኑ፤ እነዚህ ህጎች ይህን ጭፍለቃ በማሰብ መቀረፅ ይኖርባቸዋል፡ ፡ ሌላኛው አማራጭ መንግስታዊ ተቋማት ናቸው። እንደ ልሂቃኑ ሀሳብ ‹‹የተጨቋኞችን መብቶች የሚያደናቅፉ ክስተቶች ከተስተዋሉ ሁለቱም መንገዶች ለጭፍለቃው›› ይውላሉ። ይህን የመብት ረገጣ ለመተግበር ደግሞ ወታደራዊ ኃይሉ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጋር በጥብቅ መተሳሰር ይኖርበታል። ወታደራዊ ሃይሉ በቅርፅ ነፃ እንዲመስል ቢደረግም ‹‹ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ከኢህአዴግ ጋር በመተሳሰር አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግዴታዎችን እንደሚወጣ›› ሰነዱ ያብራራል፡ ፡ እንደ ኦክላሆማ ዩኒቨርስቲው መምህር አነጋገር፤ ‹‹መብቶችን የሚያደናቅፉ›› የተባሉት ድርጊቶች ምን እንደሆኑ በግልፅ ባይቀመጥም፤ የስርዓቱ ተግባሮት ግን ተቃዋሚ ፓርቲዎችንም ሆነ ተገዳዳሪ ድምፆችን ጭምር ይጠቀልላል።

ባለፉት ሃያ ዓመታት ኢህአዴግ ይህን መንገድ ስለመጠቀሙ በእርግጠኝነት የሚከራከሩት አደም አባተ የተባሉ ፀሐፊ፤ የድህረ ምርጫ 97ን አፈና ጨምሮ ሌሎች ፓርቲው የፈፀማቸው የመብት ረገጣ ድርጊቶች፤ ፓርቲው ለድርጊቱ ማስተባበያ ህጎችን ለመጠቀም ምን ያህል እንደማያመነታ ማስረገጡን ይናገራሉ። ፀሐፊው “Rule by law in Ethiopia: rendering constitutional limits on government power nonsensical” በሚለው ጥናታዊ ፅሁፋቸው፤ ይህን ዶክመንት በመጥቀስ ኢህአዴግ በሲቪል ማህበረሰቡ፣ በሚዲያው እና በፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ ያወጣቸው ህግጋቶች ከሃያ ዓመት በፊት ካስቀመጠው ፖለቲካዊ ግብ ጋር ከፍተኛ ትስስሮሽ እንዳለው ያብራራሉ። በተቀራራቢ ጊዜ ከወጡት ህጎች ዋነኛ አከራካሪ ይዘት ሆኖ የወጣው የተጠቀሱት ሶስት ተቋማት የገንዘብ ምንጫቸውን ሙሉ ለሙሉ ከሀገር ውስጥ መሰብሰብ እንዳለባቸው የሚያስገድደው የአዋጆቹ ክፍል ነው፡ ፡ ፒተር ጊል “Ethiopia: famine

and foreigners" በሚለው መድብሉ እንደሚያስረዳው፤ ኢህአዴግ ሲቪል ማህበረሰቡን የኒዮ-ሊበራል ኃይሎች ‹‹የትሮይ ፈረሶች›› እና ‹‹እግረኛ ወታደሮች›› አድርጎ ይቆጥራቸዋል፡፡ ዶክመንቱ እንደሚለው ደግሞ ‹‹ኢምፔሪያሊስቶች በሀገር ውስጥ ካሉ ጠላቶች›› ጋር የሚያብሩበት ገመድ መበጠስ ይኖርበታል፡፡ በካምብሪጅ ዩኒቨርስቲ የአስተዳደርና ሰብዓዊ መብቶች ማዕከል የፒኤች ዲ ተማሪ ለሆኑት አቶ አደም የእነዚህ ‹‹አፋኝ›› ተብለው የሚወገዙት ሶስት አዋጆች ፖለቲካዊ ግብ ይህን በሰነዱ የሰፈረውን ማሳካት ነው፡፡

## ካለስልጣን የበላይነት…

ኢህአዴግ ባወጣቸው ሰነዶችም ሆነ በፓርቲው መሪዎች አንደበት ፍፁማዊ የስልጣን የበላይነትን እንደሚፈልጉ የሚያስረዱ ሐረጎች ብዙ ጊዜ አይስተዋሉም፡፡ ገና በሽግግር መንግስትነት ተሰይሞ ሳለ ባወጣው በዚህ ሰነድ ላይ ግን ይህን ፍላጎቱን በማያሻሙ ቃላት አስቀምጧል፡፡ ‹‹አላማዎቻችንና ግቦቻችን ማሳካት የምንችለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚኖር ብቸኛው ገዢ አመለካከት መሆን ሲችል ነው›› የሚለው ይህ ሰነድ፤ ይህን ለማሳካት ‹‹ተከታታይ ምርጫዎችን ማሸነፍ እና ለአንድም ጊዜ ቢሆን ‹‹ስልጣን መልቀቅ›› እንደማያስፈልግ ይሰብካል፡፡ በተከታታይ የሚደረጉትን ምርጫዎች ለማሸነፍ መፈፀም ያለበት ቅድመ-ሁኔታ የ1987 ዓ.ም. ምርጫን ማሸነፍና ከዚያም ‹‹ፍፁማዊ የስልጣን የበላይነት››ን የሚያስጠብቁ ሁኔታዎችን በሚገባ ማመቻቸት እንደሆነ ያወሳል፡፡

ሟቹ አቶ መለስም በ1993 ዓ.ም. በፓርቲያቸው ውስጥ የተከሰተውን የሃይል መተናነቅ ተከትሎ ባቀረቧቸው ፅሁፎች ይህንኑ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ምንነት በቀጥተኛ ቋንቋ አብራርተዋል፡፡ ‹‹የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብን የበላይነት ማረጋገጥ ማለት በጣም የሚበዛውን የህብረተሰብ ክፍል ስለማንኛውም ዓይነት ጥያቄ ብቻውን ሆኖ በነፃነት ሲያስብ በውስጡ ያሉት መሰረታዊ እምነቶች የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስለሆኑ ዞሮ ዞሮ ወደ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አቋም መድረስ የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡›› የሚሉት አቶ መለስ፤ ‹‹የዴሞክራሲ መሰረታዊ ጥያቄዎች በኢትዮጵያ›› በሚል ርዕስ ባቀረቡት ፅሁፍ የሀሳቡ የበላይነት መገለጫ የሚሆነው ‹‹አንድ ሰው ከሀሳቡ ጋር ሙሉ በሙሉ በመዋሃዱ ሰውዬው ብቻውን ሲያስብም ቢሆን›› ከርዕዮተ-ዓለሙ አፀድ ውጪ እንደማይወጣ ያወሳሉ፡፡ ‹‹የአንድ ሀሳብ የበላይነት መፍጠር ማለት ይህን ያህል በጥልቀት እንዲሰርፅ ማድረግ ማለት ነው›› ሲሉም ይደመድማሉ፡፡

ፓርቲው የበላይነት ጥማቱን ሊገዳደሩ የሚችሉ የተቃውሞ ስብስቦችን ከማናናቅ እና ከማጠልሸት በዘለለ አቅማቸው ቢፈረጥም ከላይ በተጠቀሱት ህጋዊና ተቋማዊ መንገዶች ‹‹መጨፍለቅ›› ስለሚቻል

**ራሱን እንደ አብዮተኛ ፓርቲ የሚያየው ኢህአዴግ፤ ማህበረሰባዊ ስርዓቱን በሁለት የቅራኔ ኃይሎች ይከፍላል፡፡ ‹‹ከኔ ውጪ ያሉትን ቡድኖች ይረዳሉ፤ በዚህም ፍፁማዊ የስልጣን የበላይነቴን ይነካሉ›› የሚላቸውን ሃይማኖታዊ ተቋማት እንደ ምሁራኑ ሁሉ በጥርጣሬ እንደሚያያቸው ሰነዱ ያብራራል፡፡**

ከነርሱ ውጪ ስላሉት የምሁራን ስብስቦችና የሃይማኖት ተቋማትም ፓርቲው የሚወስዳቸውን እርምጃዎች አስቀምጧል፡፡

እንደ ፓርቲው ትንታኔ፤ በሀገሪቱ ያሉ የማንኛውንም የሙያ ዘርፍ ምሁራንን የሚወክሉ ማህበራት የመወያያ መድረኮችን እንዲያቋቁሙና ግለሰቦች በነርሱ እንዲወከሉ መበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡ እንደ ‹‹ንዑስ ከበርቴዎች›› ሁሉ እኒህ የልሂቃኑ ተቋማትም ‹‹ጨቋኞችን›› መስመር ሊያስቷቸው የሚችሉበት አቅም ስላላቸው ከዚህ አደጋ ለመጠበቅ ማህበራቱ ‹‹በሰርጎ ገብ›› የፓርቲው ሰዎች መሞላት አለባቸው፡፡ የ‹‹ሰርጎ ገቦቹ›› ዋነኛ ተልዕኮ ማህበራቱን ‹‹ወደ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ካምፕ መቀላቀል›› ሲሆን፤ ይህ የማይቻል ከሆነ ፓርቲው በተለዋጭ ሌላ አማራጭ አስቀምጧል፡፡ እነዚህ ምሁራን የሚሰሩባቸው መንግስታዊ ተቋማት አልያም የገቢ ምንጭ የሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ህልውና በማዕከላዊ መንግስቱ ፖሊሲዎች ስለሚወሰን ‹‹መንግስታዊዎቹን እና የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የኢኮኖሚ ተቋማትን በመጠቀም ድጋፋቸውን ለማግኘት መሞከር ወይም የመቃወም አቅማቸውን ማኮሰስ›› ይቻላል፡፡ እንደ ዶክመንቱ አቀራረብ፤ ከኢህአዴግ ጋር ሊሰሩ የማይሹቱን ‹‹ኪሳቸውንና ሆዳቸውን ባዶ ማድረግ›› እንደሚገባ በግልፅ ይናገራል፡፡

ራሱን እንደ አብዮተኛ ፓርቲ የሚያየው ኢህአዴግ፤ ማህበረሰባዊ ስርዓቱን በሁለት የቅራኔ ኃይሎች ይከፍላል፡፡ ‹‹ከኔ ውጪ ያሉትን ቡድኖች ይረዳሉ፤ በዚህም ፍፁማዊ የስልጣን የበላይነቴን ይነካሉ›› የሚላቸውን ሃይማኖታዊ ተቋማት እንደ ምሁራኑ ሁሉ በጥርጣሬ እንደሚያያቸው ሰነዱ ያብራራል፡፡ እነዚህ የሃይማኖት ተቋማት ፓርቲው ወደ ማይፈልገው የተቃውሞ አልያም የመገዳደር አዝማሚያ የሚያጋድሉ ከሆነ ሁለት መንገዶችን ለመጠቀም እንደሚገደድ ይናገራል፡፡ ቀዳሚው አካሄድ በየእምነት ተቋማት ውስጥ ያሉ አማኞቹን ወደ ፓርቲው ማካተት ነው፡፡ እነዚህን ዜጎች በአብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተምህሮ በማጥመቅና በኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች በመደለል የ‹‹አብዮታዊ ዴሞክራሲ ኃይሎች›› ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህን መከወን የማይቻል ከሆነ የሃይማኖቶቹ አመራሮች ላይ ማተኮር ሌላኛው ይሆናል፡፡ እንደፓርቲው አገላለፅ ‹‹የተለያዩ ኃይማኖቶችን የሚወክሉ መሪዎች መሀከል ያለውን ቅራኔ በማባባስ የጋራ ግንባር ፈጥረው ወደ ኢህአዴግ እንዳይዞሩ ማድረግ ያስፈልጋል››፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ሁለት አካሄዶችም የሃይማኖት ተቋማቱን ‹‹አብዮታዊ ዴሞክራሲ›› ወደሚሰበክባቸው መድረኮች መቀየር እንደሚገባ ሰነዱ በግልፅ ቋንቋ ይናገራል፡፡

## ስለአብዮታዊ ኢኮኖሚ

አብዮታዊ ዲሞክራሲን በተጣራሽ ግቦች ለመበየን የማይቸገረው ኢህአዴግ፤ ስልጣን በያዘ ማግስት ኢኮኖሚውን ለመምራት ያሰበበበት መንገድ እና ከ1990ዎቹ ወዲህ ያስቀመጣቸው የኢኮኖሚ ግቦች እጅግ ተፃራሪ ናቸው፡፡ ከላይ የተጠቀሰው ሰነድ ይህን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ የሀገር ውስጥ እና የውጪ ባለሀብቶችን አስመልክቶ የርዕዮተ-ዓለሙ ሚና ምን እንደሆነ በማያሻሙ አንቀፆች ገልጿል፡፡ ከውጪ ለሚመጣ ካፒታል በቂ ዕድሎችን ማመቻቸት እንደሚገባ የሚናገረው ሰነዱ፤ በምንም ዓይነት ምክንያት በውጭ ባለሀብቶች መያዝ የሌለባቸውን የኢኮኖሚ ተቋማት ይዘረዝራል፡፡ ከፋይናንሺያል ተቋማት እስከ ቴሌ ኮሚኒኬሽን ያሉ መንግስታዊ ድርጅቶችን ለእነዚህ ባለሀብቶች ክፍት ከተደረጉ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ህልውና አደጋ ውስጥ እንደሚገባ ይጠቅሳል፡፡ ከዚህ ውጪ ባሉት ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥም የሚሳተፉ ባለሀብቶችን ለመቆጣጠር የሀገሪቱን የፊስካል ፖሊሲዎች ፓርቲው ለመጠቀም እንደሚገደድ ይናገራል፡፡ በተለይም ከፊስካል መሳሪያዎች መሀከል የታክስ ስርዓቱን ለአብዮታዊ ዴሞክራሲ ብቸኛ የበላይነት እንዴት ማዋል እንደሚቻል ሲያወሳ፤ ‹‹ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ግቦች ውጪ በሚሄዱ ድርጅቶች ላይ ከፍተኛ ታክስ በመጫን ማውደም›› እንደሚያስፈልግ ከመናገር በዘለለ፤ ከፓርቲው መስመር ጋር የሚስማሙ የኢኮኖሚ ተቋማትን ከታክስ ነፃ በማድረግ እንደሚያግዝ ይናገራል፡፡

ይህን መሰሉን የፓርቲውን የኢኮኖሚ ስትራቴጂዎች ያጠኑት ቶብያስ ሃግማን እና ጆን አቢቢኒክ፤ ፓርቲው በአንድ በኩል ነፃ ገበያን ለመመስረት ለአለም አቀፍ ተቋማት ቃል እየገባ በሌላ ጫፍ በራሱ በፓርቲው በእጅ አዙር የሚመሩ የንግድ ተቋማትን ያስፋፋል፡፡ የሀገሪቱ ህግ የፖለቲካ ፓርቲዎች በንግድ እንቅስቃሴ ላይ መሳተፍ እንደማይችሉ ቢደነግግም፤ የስርዓቱ ቁንጮ ሰዎች በተለያየ መንገድ በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ በመሳተፍ የፓርቲውን የርዕዮተ-ዓለም የበላይነት ለማስጠበቅ እንደሚሰሩ አጥኚዎቹ "Twenty years of revolutionary democratic Ethiopia, 1991, to 2011" በሚለው ፅሁፋቸው ያወሳሉ፡፡ ‹‹በሁሉም የሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ውስጥ ያሉት የፓርቲው ኢኮኖሚ ተቋማት ኢኮኖሚውን ይመሩታል›› የሚሉት እነ ሀግማን፤ የዚህ ሁሉ ተቋማዊ ጥንካሬ መነሻ የህወሓት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ፕ/ር ቬስታል በበኩላቸው ህወሓት በትጥቅ ትግሉ ወቅት ‹‹የዘረፈው›› ገንዘብ ለፓርቲው ንግድ እንቅስቃሴ መነሻ ምክንያት ስለመሆኑ ይከራከራሉ፡፡ ፕ/ሩ ከላይ በተጠቀሰ ስራቸው እንደሚጠቅሱት፤ ሆስፒታሎችን፣ መንግስታዊ ባንኮችን እና እንደ ቀይ መስቀል ያሉ የእርዳታ ድርጅቶችን በመዝረፍ ያልተገታው ህወሓት፣ በ1983 ዓ.ም. ስልጣን በያዙ ማግስት የነበረውን መንግስታዊ የገንዘብ ክምችት በቀጥታ ወደ ኢህአዴግ አዛውሯል፡፡

ስለዚህም ጉዳይ የፃፉት ጂያን ኒኮላስ ባች የተባሉ ፀሐፊም ፓርቲው ይህን እቅዱን ስለመተግበሩ በግልፅ ይከራከራሉ፡፡ ይህን መሰል ሰነዶች ላይ የፓርቲው አቋም በግልፅ እንደተቀመጠው፤ የገበያ ስርዓቱ ለሁሉም ክፍት እንዲሆን ቢደረግም፤ ስርዓቱ ከላይ ወደታች በሚያስተላልፋቸው ጥብቅ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ብቻ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው እንደሚዘወር የሚናገሩት ዶ/ር ኒኮላስ ‹‹የግል ክፍለ ኢኮኖሚው እንዲሰራ የሚፈቀድለት ፓርቲው ባስቀመጠው ክበብ ሲንቀሳቀስ ብቻ ነው›› ሲሉ የሰነዱ ሀሳብ መተርጎሙን ይናገራሉ፡፡ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ፓርቲው እየሄደበት ያለውን የምስራቅ እስያ ሀገራትን የፖለቲካ-ኢኮኖሚ ሞዴል የመኮረጅ አካሄድ ይህን በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ሀሳባዊ ማዕቀፍ ስር ኢኮኖሚውን የመምራት አባዜ ምሁራዊ መሰል አመክንዮ ለማቅረብ መሻቱን የሚያሳይ እንደሆነ ፀሐፊዋ "Abyotawi democracy: neither revolutionary nor democratic, a critical review of EPRDF's conception of revolutionary democracy in post 1991 Ethiopia" በሚለው ጥናታዊ ስራቸው ያወሳሉ፡፡ ይህ የልማታዊ መንግስትነት መስመር ፓርቲው ስልጣን ሲይዝ ‹‹እከውነዋለሁ ያለውን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የመገንባት ግብ ለመቀልበስ ነው›› የሚሉት ፈረንሳዊቷ አጥኚ፣ ለማሳያነትም በ1998 ዓ.ም. ፓርቲው ባደረገው ኮንግረስ ያወጣውን

ወደ ገፅ 20 ዞሯል



ዳንኤል ተፈራ

# ለምን አቶ ኃይለማርያም ፖለቲካዊ ለውጥ ማምጣት አይችሉም?

**አቶ ኃይለማርያም ምንም ያህል ጊዜ ቢሰጣቸው የኢህአዴግን መስመር ከማስፈፀም በስተቀር ጠብ የሚያደርጉት አዲስ ለውጥ የላቸውም:: ይሄ ማለት ግን ዕድሉ በእጃቸው የለም ማለት አይደለም:: አዲሱ ጠ/ሚኒስትር የኢህአዴግን አብዮታዊ ዴሞክራሲና የልማታዊ መንግስት እሳቤ ለማስፈፀም ያመኑ እንጅ በተለምዶ የፖለቲካ አሻንጉሊት እንደሚባሉት አይነት መሪ አይደሉም ለማለት እደፍራለሁ:**

## እንደ መነሻ

የባለፈው የኢትዮጵያውያን ዓመት ወደማገባደጃው በድንገተኛ ግዙፍ ክስተቶች የተሞላ ነበር:: እነሆ ያልተገመተው ግዙፍ ክስተት የጠቅላዩ መታመምና ብዙም ሳይቆይ ዜና ዕረፍታቸው መነገሩ ነው:: የጠቅላይ ሚኒስትሩን ሞት ተከትሎ እንደተለመደው የቀንዱ ፖለቲካ መጋል ጀመረ፤ ንዝረቱ ከምዕራብ እስከ ምስራቅ ድረስ ተስተጋባ::

በዚሁ ድንገተኛ ዜና የተነሳም የተለያዩ ክስተቶችንና መላምቶችን ለማዳመጥ በቃን:: ከዚህ አንፃርም ኢትዮጵያውያንን በሁለት ክፍሎ ማየት ይቻላል:: አንደኛው የኢህአዴግን ስርዓት ተከትሎ የብልፅግና ማማ ላይ የተንሳፈፉት፤ ከስርዓቱ ስር በመሆንና በማጐብደድ ፍርፋሪውን እንደ ጤዛ የሚልሱት፤ ከታጋይነት በፍጥነት ወደ ኢንቨስተርነት የተለወጡት ድንገቴው የፖለቲካ አየር ሌላ ነገር ሳይረብሽ ስርዓቱ እንዲቀጥል ወይም በነበረበት መንገድ ላይ እንዲጓዝ የሚፈልጉት ናቸው:: በሁለተኛ ጎራ የሚመደቡት ደግሞ በነፃነት እጦት በሀገራቸው ላይ እንደ መፃተኛ የሚታዩት፤ የኢኮኖሚው ትሩፋት መሶባቸውን ያልጎበኘው፤ ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ የሚፈልጉ የጠ/ሚኒስትር መለስን ሞት ተከትሎ ከምር ለውጥ እንዲመጣ መሻታቸውን ተመልክተናል::

እጀ ረጃጅሞቹ ምዕራባዊያን በተለይ አሜሪካና እንግሊዝም በምስራቅ አፍሪካ ከፍተኛ የፖለቲካ ጠቀሜታ አላት የሚሏት ኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁናቴ የነሱን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ እንዲቀጥል እንቅልፍ አጥተው እንደሰነበቱ አስተውለናል:: በኢትዮጵያ የሚገኙ የፖለቲካ አታሼዎቻቸውም ያችኑ የማታልቅ የአንገት በላይ ፈገግታቸውን ብልጭ እያደረጉ ጉዳዩን ፈር ለማስያዝ ባጅተዋል:: በረጅም ማንኪያቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የሚችሉትን ያህል አማስለዋል::

እንዲህም ሆነ:: በፊትም ግምት የተሰጣቸው አቶ ኃ/ማርያም ጠ/ሚኒስትር፤ በርካቶች ከገመቱት ውጭ ድምቡሽቡሽ ያለ መልክ ያላቸውን አቶ ደመቀ መኮንን ም/ጠ/ሚኒስትር በማድረግ ተጠናቀቀ::

ከዚያ በኋላስ? ከዚያ በኋላማ ስርዓቱ እንደነበር ቀጠለ ማለት ነው:: የኢትዮጵያን ፖለቲካ አይናቸው ስር አድርገው የሚከታተሉ በውጭ የሚኖሩና ሀገር ውስጥ ያሉ ልሂቃን እንዲሁም የፖለቲካ ተቿዎች አሁንም ትንታኔያቸውን ቀጠሉ:: ‹‹ሌጋሲ›› የሚለውን ቃል ደጋግመው በመጥራታቸው እንደ ተጨማሪ መገለጫ እየተወሰደባቸው ያለው አቶ ኃ/ማርያም በዓለ-ሲመታቸው ላይ ባሰሙት ንግግር ሳይጨምሩና ሳይከልሱ የመለስን ሌጋሲ እንደሚያስቀጥሉ ተናገሩ:: ንግግሩን ትንሽ ስናፍታታው የኢህአዴጋውያኑን የተንጠለጠለ ልብ ‹‹እፎይ›› ለማሰኘት የታሰበ ይመስላል:: በተጨማሪም የቀድሞዋ ቀዳማዊ እመቤት ወ/ሮ አዜብ መስፍን በባለቤታቸው የቀብር ሽኝት ላይ ‹‹የባለቤቴን ራዕይ ሳይበረዝ ሳይከለስ ከሚቀጥሉት ጐን እቆማለሁ›› ባሉት መሰረትም የተቃኘ ነበር::

አቶ ኃ/ማርያም ዙሪያቸውን ያሰፈሰፉት በተለይ የህወሓትን ሹማምንት ቀልብ ለመግዛትና የኢህአዴጋውያኑን ይሁኝታ በማግኘት ስልጣናቸውን ለማስቀጠል እንደዚያ መናገር ነበረባቸው የሚሉ ወገኖች ‹‹ሃይማኖተኛና ትሁት›› ናቸው የሚባሉትን ጠ/ሚኒስትር ከመተቸት ይልቅ ‹‹ጊዜ እንስጣቸው›› የሚል ሀሳብ ሲያንሸራሽሩ አይተናል::

እነዚህ ወገኖች ለአቶ ኃይለማርያም ‹‹ጊዜ ከሰጠናቸው ለውጥ ሊያመጡ ይችላሉ›› በማለት ጭልጭል የምትል ተስፋ ይዘው መቀጠሉን ይመርጣሉ:: ምክንያታቸው ደግሞ ከኢህአዴግ መሰረታዊ ባህሪ የሚመነጭ ነው:: ኢህአዴግ ጥላውን የማያምን ተጠራጣሪ ድርጅት ነው:: በዚህም የተነሳ ጠንካራ የደህንነትና የስለላ (በህወሓት የበላይነት የሚመራ) ተቋም አለው:: በተጨማሪም ‹‹የታገልንለት›› የሚል አሮጌ አስተሳሰብ ያላቸውና ‹‹ደም›› እያሰሉ የሚኖሩ ታጋይ ግለሰቦች ጠቅላይ ሚኒስትሩን በቅርብ ርቀት ይከታተላሉ:: ስለዚህ አቶ ኃይለማርያም ይሄን የሚያለዝቡበትና የሚያርቁበት ጊዜ ይሻሉ በማለት ይከራከሩላቸዋል::

ሌሎች በርከት ያሉ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ተከታታዮችና ፀሐፊዎች ደግሞ ‹‹ትሁቱን›› ሰውዬ ‹‹ምንም ለውጥ ማምጣት የማይችሉ፣ አድርግ የተባሉት ከማድረግ በስተቀር አዲስ ውሳኔና አዲስ ለውጥ የማያመጡ›› በማለት የትችት ምታቸውን በቁና ያወርዱባቸዋል:: ከረር ያሉት ተቿዎች ደግሞ ‹‹አሻንጉሊት›› የሚለውን ቃል ለመጠቀም ጥቂት እንኳን አያቅማሙም::

የዚህ ፅሁፍ አቅራቢ ግን ከላይ በቀረቡት ሁለት ግምቶች አይስማማም:: አቶ ኃይለማርያም ምንም ያህል ጊዜ ቢሰጣቸው የኢህአዴግን መስመር ከማስፈፀም በስተቀር ጠብ የሚያደርጉት አዲስ ለውጥ የላቸውም:: ይሄ ማለት ግን ዕድሉ በእጃቸው የለም ማለት አይደለም:: አዲሱ ጠ/ሚኒስትር የኢህአዴግን አብዮታዊ ዴሞክራሲና የልማታዊ መንግስት እሳቤ ለማስፈፀም ያመኑ እንጅ በተለምዶ የፖለቲካ አሻንጉሊት እንደሚባሉት አይነት መሪ አይደሉም ለማለት እደፍራለሁ:: በእኔ እይታ ‹‹አሻንጉሊት›› የሚለው ቃል የራሱ ነገር የሌለው እና በሌሎች የተጫነውን የሚያስፈፅም የሚል ትርጉምን ያዘለ ቃል ነው:: እሳቸው ግን አቶ መለስ የተከሉትን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ለማስፈፀም ያመኑ ናቸው:: ለዚህ ነው ጉዳዩ የኃይለማርያም ወይም የወልደማርያም መቀየር አይደለም ብዬ ለመሞገት የምደፍረው:: ጉዳዩ ያለው የተበላሸውን ገዥ ፓርቲ መቀየር ላይ ነው:: ለውጥ የሚመጣውም እንደዚያ ነው:: ለዚህ መከራከሪያ ጥቂት ነጥቦችን እየቆነጠርኩ ማሳየት ይኖርብኛል:: እነሆ 11 ዓመታት ወደ ኋላ ላንሸራታችሁ::

### 1992 ዓ.ም. ክረምት

በ1992 ዓ.ም. መገባደጃው ላይ የኢትዮጵያ አየር ቀዝቅዟል:: ሰማዩ በሚንቀዋለል ደመና ተሞልቷል:: ቅዝቃዜው የፈጠረው ብርድም የዚያኑ ያህል ጨምሯል:: ኃይለኛ ሙቀትና ግለት ያለው ህወሓት መንደር ብቻ ነበር:: በርግጥም የግለቱ ወላፈን ወደ ሌሎች አጋር ድርጅቶች፤ ኦህዴድ፣ ብአዴንና ደኢህዴን ዘንድም ደርሶ ነበር::

ህወሓትን የለበለበው ግለት ግን ልዩ ነበር:: ነብሳቸውን ይማርና አቶ መለስ ‹‹ቦናፓርቲዝም›› የምትል ጦስ አምጥተው ወደረኛ፣ ወደረኛ የህወሃት ሰዎችን በስራ ባይጠምዱ ኖሮ ህወሓት ፀሐይ እንደነካው በረዶ ሟሙታ ታልቅ ነበር:: ነገር ግን ነገሩ ወዲህ ሆነና፤ ችግራችን ቦናፓርቲዝም ነው? አይ ተንበርካኪነት ነው? በሚል ክርክር ተጠምዱ አቶ መለስም ስራቸውን በፍጥነት በመስራት ‹‹ጋንግሪን ካልተቆረጠ በስተቀር አይድንም›› በሚል የቆየ ብሂላቸው ተጠቅመው አንጋፋ ታጋዮችን አስወገዱ:: የህወሓት ነገርም ለሁለት በመሰንጠቅ ተደመደመ::

በ1992 ዓ.ም. ክረምት ግን ግለቱ አልበረደም:: ኢህአዴግ በከፍተኛ ግምገማ ተጠመደ:: ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ስለዚህ ጉዳይ ጠይቂያቸው እንዳጫወቱኝ ‹‹ግምገማው ሃይለኛ ነበር:: ከዚህ በፊትም ተደርጐ አይታወቅም›› ብለውኛል:: እንዴት? የምትል አፍታች ጥያቄም አንስቼ ነበር:: እንዲህ ነው:-

ግምገማው አቶ መለስን ጨምሮ በፌደራል መንግስት ውስጥ ያሉ ከፍተኛ ካድሬዎችን እና የመንግስት ሰራተኞችን ያካተተ ነበር:: ዓላማውም በአሸናፊነት የወጣውን የህወሓት ክንፍ የበላይነት ማጠናከር ነበር:: በዚያን ወቅት የኢህአዴግና የሻዕቢያ ግንኙነት እንዲሁም ጦርነቱ እንዴት እንደተካሄደም ተገምግሟል::

የአቶ መለስ አቋም የነበረው ‹‹የወደፊት አቅጣጫችንን አስቀምጠን እንገምግም›› የሚል ሲሆን ከህወሓት የተለዩት ስዬ አብርሃ፣ ገብሩ አስራት፣ አለምሰገድና አባይ ፀሐዬ (አሁንም ቀንደኛ የህወሓት ሰው ናቸው) ‹‹ሀገራችን ላይ ያንዣበበው አደጋ ምንድን ነው?›› የሚል እሳት ጥያቄ አንስተው ነበር አሉኝ ዶ/ር ነጋሶ::

ከህወሓት መሰንጠቅ በኋላ ብአዴን ባህርዳር ላይ በአቶ በረከት ስምኦን፣ አዲሱ ለገሰና አቶ ተፈራ ዋልዋ አማካኝነት የተቀመጠ ሲሆን ህወሓት ‹‹ትምክተኛ›› የሚል ስም ይሰጣቸዋል:: ታዲያ ‹‹ቅቤ አልቀቡኝ ለምን ዝም



addistimes2005@gmail.com

እላለሁ?›› ያለው ብአዴን ‹‹ዝግ በረኞች!›› በማለት መልሱን ሰጥቷል፡፡ በዚህም ህወሓትና ብአዴን ፍጥጫ ላይ ይወድቃሉ፡፡ የኃይል ሚዛኑ እንደሳሳ ያወቀው ብአዴንም የውሸት ሳቀና የፖለቲካ ፕሪሚየር ሊጉን ተቀላቀለ፡፡ የፖለቲካ ተንታኞች በዚያ ቀውጢ ‹‹ህወሓትን ያተረፈው ተመስግኖ የማያውቀው ኦህዴድ ነው›› ይላሉ፡፡ የተጠረገው ተጠረገና ጉዞው ቀጠለ፡፡ ክረምቱም አለፈ፡፡ ‹‹አቶ ኃይለማርያም የፖለቲካ ለውጥ አያመጡም›› ብዬ የምከራከርበት ታሪክ የሚጀምረውም ከዚህ በኋላ ነው፡፡ እነሆኝ፡፡

1993 ዓ.ም. ተሃድሶ

በ1992 በህወሓት መንደር የተፈጠረው ግለት የተለየ አመለካከትና ጥያቄ ያላቸውን ግለሰቦች በመጠራረግ አላበቃም፡፡ ወላፈኑ ወደ 1993 ዓ.ም. ተሸጋግሮ ኢህአዴግና አጋሮቹ በስብሰባና ግምገማ ተወጥረዋል፡፡ አቶ መለስን ጨምሮ ኦህዴድና ደኢህዴን ገምጋሚዎች ሁነዋል፡፡ ከወርሃ ግንቦት ጀምሮም አሁንም ድረስ ‹‹የሁሉ ነገር መሀንዲስ›› እየተባሉ በኢህአዴጋዊያኑ ዘንዳ የሚንቆለጳጰሱት አቶ መለስ ቦናፓርቲዝምን በነካካ እጃቸው ‹‹ተሃድሶ›› የሚል አዲስ መንገድ ይዘው ከተፍ ብለዋል፡፡ ተሃድሶው ማጥመቅና አዳዲስ ውልዶችን መፈልፈል ዋነኛ ዓላማው ሆነ፡፡

የተሃድሶው መሰረታዊ ነጥብ ‹‹ኢትዮጵያን ከ20-30 ዓመት ድረስ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች እንመድባታለን›› የሚል ቀና የሚመስል ሃሳብ የያዘ ሲሆን በውስጡ የኢህአዴግን ተቀናቃኞች በመመንጠር ዘላለማዊ መንግስት ማቋቋም ዋነኛ ዓላማው ነበር፡፡

ኢህአዴግ ‹‹ተሃድሶ ውስጥ ነኝ›› ሲል እና የመሰረታዊ ባህሪ ወይም የቅርፅ ለውጥ ለማድረግ ሲሰናዳ፣ ዴሞክራሲን ገለመሌን መሳቢያ ውስጥ ሲከትና ‹‹መጀመሪያ ዳቦ›› የሚል አዲስ ዜማ ሲያሰናዳ ‹‹ሞዴሎቼ›› ያላቸው ሀገራትም ነበሩ፡፡ እነዚህ ልምዳቸውን እንቀስማለን የተባሉት ሀገሮች ደቡብ ኮሪያ፣ ቻይና፣ ማሌዥያና ታይላንድ የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ታዲያ በተሃድሶ ሰበብ አዲስ ዜማ ይዞ ብቅ ያለው ኢህአዴግ /ህወሓት/ ሀገራችን የኢኮኖሚ ለውጥ እንድታመጣ ሰብዓዊ መብትና ነፃነት መቀማት እንዳለባቸው ያወጀው በአደባባይ ነበር፡፡ ለስለስ ባለቋንቋ ‹‹ተግዳሮት›› ተብለው የተቀመጡትን በማስወገድ የልማት ኃይሎችን መሰብሰብ የምትል ቅኔም ተዘርፋለች፡፡ ልማታዊ ባለሀብት፣ ልማታዊ አርሶ አደር፣ ልማታዊ አርቲስት፣ ልማታዊ ሯጭ፣ ልማታዊ ወታደር፣ ልማታዊ ሊስትሮ..... እያሉ ማደራጀትና የማይበረዝና የማይከለስ ነጭ ካፒታሊዝም መከተል የሚል ዓላማም እንዳለው ከህወሓት/ኢህአዴግ መንደር የቃረምነው መረጃ ያመለክታል፡፡

አሁን ጥያቄው ‹‹ይሄን የሚቃወሙትስ?›› የሚለው ነው፡፡ ለዚህም የእነ አቶ መለስ ተሃድሶ መልስ ነበረው፡፡ ‹‹እነዚህማ ፀረ-ልማት፣ ላባቸውን ሳያንጠፈጥፉ ባለሀብት ለመሆን የሚጥሩ ኪራይ ሰብሳቢዎችና ጥገኞች ናቸው›› የሚል፡፡ እነዚህን መሰረታቸውን እንዲያጡ ማድረግ እንደሚገባም ተወስኗል፡፡ ለባለፉት 10 አመታትም የፀረ-ሽብርተኝነት ህጉን የመሰለ የማስፈፀሚያ ገመድና ሌላ ሰበብ ተበጅቶላቸው ‹‹ስርዓቱ በአጉል ጐዳና እየሄደ ነው›› ብለው የተቃወሙት ወደ ወህኒ ወርደዋል፡፡

የልማት ኃይሎች መሪዎችና ‹‹የፀረ-ልማት ኃይሎች መሪዎች›› የሚል ሁለት መደብም ተፈጥሮም ኢህአዴግ ራሱን የልማታዊ ኃይሎች መሪ አድርጐ ሲያስቀምጥ የፀረ-ልማት ኃይሎች የሚለው ምድብ ደግሞ ለሀቀኛ ተቃዋሚዎች ተሰጠ፡ በዚህ መሰረትም ከዚህ በፊት የጐሪጥ ያዩዋቸው የነበሩና ‹‹ስኳር አላሽ›› በሚል ይጠየፏቸው ከነበሩ ባለሀብቶች ጋር ሽርክ ሆኑ፡፡ ለነዚህ ባለሃብቶችም ልማታዊ የሚል ሜዳሊያ ጠለቀላቸው፡፡

‹‹ፀረ-ልማት ኃይሎችን ይመራሉ›› የተባሉ ተቃዋሚዎች ላይ ‹‹እናጠፋቸዋለን!›› የሚል ክፉ አዋጅ የታወጀውም በ1993 የኢህአዴግ ተሃድሶ ወቅት ነው፡፡ ይሄው ዕቅድ ታቅዶና ቡራኬ ተሰጥቶ፣ ጠመቃውም ተካሄዶ፣ ጉዞውም ተጀመረ፡፡ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝም ተሃድሶ ከወለዳቸውና ግራና ቀኝ የዓይን መከለያ እንደተገጠመለት ፈረስ የኢህአዴግን መስመር ተከትለው ከሚፈሱት መካከል ናቸው፡፡ ከዚህ መሰረት በመነሳትም ነው ‹‹ጊዜ ቢሰጣቸውም ለውጥ ሊያመጡ አይችሉም›› የምለው፡፡

አቶ መለስ ዜናዊም ከ1993 እስከ 2004 (በሞት እስከተለዩበት) ‹‹ቆሻሻውን ሁሉ አስወግዶ እሰይ እሰይ ህዳር ታጠነ›› የሚል የተሃድሶ ዜማቸውን እያቀነቀኑ መርተዋል፡፡ ሰብዓዊ መብት፣ ዴሞክራሲ እና መድብለ ፓርቲ የመሳሰሉት ውድ ቃላት ከኢህአዴግ መዝገበ ቃላት ከተፋቁም ከ10 ዓመት በላይ ሆኗቸዋል፡፡

ድንገተኛውን የአቶ መለስን ሞት ተከትሎ ወደ ስልጣን የመጡት አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ‹‹ምንም ለውጥ አይደረግም›› ያሉት እንዲሁ ከመሬት ተነስተው አልነበረም፡፡ በተሃድሶ ሰበብ የተነጠቁ መሰረታዊ መብቶችን ወደ ህዝቡ እንዳይመለሱ ለማድረግና የኢህአዴግን አቅጣጫ ለማስቀጠል ትክክለኛ ሰው ሆነዋል ማለት ነው፡፡ ፓርላማ ቀርበው ባሰሙት ንግግርም ይሄንን አረጋግጠዋል፡፡ ያውም የንግግር ለዛ ሳይቀር ለመኮረጅ ችለዋል፡፡ የአቶ መለስን ‹‹ፊንጅ ወረዳ›› አቶ ኃይለማርያም ‹‹እሳት መንካት›‹ በመለወጥ አቅርበዋል፡፡ የጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ተግባር ቢኖር አምባገነንነቱን (እሳቸው የመለስ ሌጋሲ ይሉታል) ማስቀጠል ነው፡፡ ስለዚህ ምንም አይነት ጊዜ ቢሰጣቸው፣ ምንም ‹‹ቀና›› ብንላቸው አቶ ኃይለማርያም ፖለቲካዊ ለውጥ ሊያመጡ አይችሉም፡፡ ይሄን ለውጥ ማምጣት የማይችሉት ደግሞ ‹‹አሻንጉሊት›› ስለሆኑ ሳይሆን የስርዓቱ መስመር ከተሃድሶው በኋላ እንደዚያ ስለቀጠለ ነው፡፡

አንዲት ምሳሌ ብቻ ላንሳ፡፡ በ1993 ዓ.ም. አቶ መለስ ከ20-30 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች እንመደባለን አሉ፡፡ አቶ ኃይለማርያምስ? አቶ ኃይለማርያም ስልጣን ሲይዙ 10 ዓመታት አልፈው ነበርና ይሄን በመቀነስ ‹‹በ10 ዓመት ውስጥ መካከለኛ ገቢ ያላቸውን ሀገሮች እንቀላቀላለን›› አሉ፡፡ የአቶ ኃይለማርያም ስርዓቱን እንዳለ የማስቀጠል ማረጋገጫም ይሄው ነው፡፡ አቶ ኃይለማርያም የተበላሸውን የኢህአዴግ መስመር ለማስቀጠል ባያምኑ ኖሮ ስልጣኑን እሺ ብለው አይቀበሉም ነበር፡፡ ምክንያቱም ምርጫው ወይ ማስቀጠል አሊያም መልቀቅ ነውና፡፡

የተሃድሶው ውልድ-ኃይለማርያም

ከላይ ለመግለፅ እንደሞከርኩት ወይም ለመከራከር እንደከጀልኩት አምባገነንነትን ለማስቀጠል ቃል የገቡት ጠ/ሚ ኃይለማርያም ደሳለኝ አቶ መለስ ያረቀቁት የ1993 ተሃድሶ ፍሬ ናቸው፡፡ እሳቸው አስቀጣይ እንጂ ጊዜ ስለተሰጣቸው ፖለቲካዊ ለውጥ የሚያመጡም፣ አሻንጉሊትም አይደሉም፡፡ እንደውም ለመጀመሪያ ጊዜ የመንግስትን አቋም ለማብራራት ፓርላማ በቀረቡበት ወቅት መለስን መስለው ከመቅረባቸውም ባለፈ ለመብለጥ ተጣጥረዋል፡፡ ይሄ ማለት ግን አቶ ኃይለማርያም ደፈር ካሉ ለውጥ ማምጣት የሚችሉበትና ታሪክ የሚሰሩበት ዕድል ተጠርቅሞ የተዘጋ ነው ማለት አይደለም፡፡

የኢትዮጵያ ህዝብ የለውጡ ባለቤት ይሆን ዘንድ ሁለት መንገዶች አሉ፡፡ አንደኛው በአቶ ኃይለማርያም እጅ ያለና ምናልባት ከተጠቀሙበት የነፃነት መንገድ ሊሆን የሚችል ሲሆን፣ ይሄም ከኢህአዴግ መዋቅር የሚመነጭ ነው፡፡

ከ1993 ዓ.ም. በፊት የኢህአዴግ ማዕከል ሆኖ የሚያገለግለውና የቀን ተቀን ስራ የሚከውነው የፖሊት ቢሮ ይመራ የነበረው በጣም ጠንካራ በሚባሉ ሰዎች ነበር፡፡ በዓለምሰገድ ገ/አምላክ፣ በረከት ስምኦንና ተወልደ፡፡ እነዚህ ሰዎች የፖሊት ቢሮው የሚያረቀውን አጀንዳ ተጠሪ ለሆነበት ጠ/ሚኒስትርና ም/ጠ/ሚኒስትር በማቅረብ ይሁንታ እንዲያገኝ ያደረጉ ነበር፡፡ ታዲያ ከ1993 ዓ.ም. በፊት የቀድሞው ጠ/ሚ መለስ ገዝፈው እንዳይወጡ ያደረጋቸው ይሄው የፖሊት ቢሮ ጠንካራ መሆን ነበር፡፡ በ1993 ዓ.ም. ዓለምሰገድና ተወልደ ከድርጅቱ ሲወጡ መለስ የፖሊት ቢሮውን በመቆጣጠር ብቸኛ ሆነው የመውጣት እድል አገኙ፡፡

የአቶ ኃይለማርያምም ለውጥ የማምጣት ዕድል የሚመነጨው ከዚህ ነው፡፡ በፖሊት ቢሮው በኩል ያሉ ሰዎች ጥንካሬ እንደበፊቶቹ እንዳልሆነ ይነገራል፡፡ ስለዚህ ፖለቲካዊ ለውጦችን ለማምጣት የፖሊት ቢሮውንና የፖሊት ቢሮው የሚገመግማቸውን አጋር ድርጅቶች መቆጣጠር፣ ከላይ ደግሞ የስራ አስፈፃሚው ላይ ጉልበት በማሳየት ከ1993 ጀምሮ የተበላሸውን የፖለቲካ ጉዳና ማቅናት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እነዚህም ተሃድሶው ባመጣው ህግ ሰለባ የሆኑትን ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች መፍታት እንዲሁም ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር ሊሰሩባቸው የሚችሉበትን መንገድ ክፍት ማድረግ ናቸው፡፡

ይሄ መሆን ካልቻለ ሁለተኛው መንገድ ግልፅ ነው፡፡ እሱም ስርዓቱን ከናካቴው መለወጥና ስልጣኑን ለህዝብ ማስረከብ፡፡ ይሄ በተቃዋሚ ጐራ የተሰለፉት ኃላፊነት ይሆናል፡፡ ወይም የቤት ስራ፡፡

# የየዋሑ ሰው መልዕክት...

ከገፅ 17 የዞረ

በዚህስ ዘላለማዊ ሀሴትን ያገኛሉ ብለህ ታስባለህ?›› በማለት አስጨናቂ መልስ ጠየቀው፡፡ ጥያቄው እንግዲህ ለአይቫን ብቻም ሳይሆን ለእኔም ነው፡፡ እውነት ነው! በግፍና በግድያ፣ በማስገደድና በማፈናቀል ከሚመጣ ልማት እንድካፈል ያሳደገኝ ባህልና ሰብአዊነቴ አያበረታታኝም፡፡ በኃይል ከተገፉ ደሀ ገበሬዎች መሬት የተገኘ ምርት እንዴት ይበላልኛል? ልክ እንደኔው ሁሉ በዚሁ መልክ ተከሽኖ ከቀረበ ሌማት እጃቸውን የማይሰዱ ብዙሃን ናቸው፡፡ እናም አቶ ኃይለማርያም! ይሄ ገራገር ምክንያቴን በሚገባ ያጢኑልኝ፡፡ በህዝብ እንባና ደም የሚገነቡ ስራዎች የእኔም የሌሎችም ስላልሆኑ ስለሰው ልጆች ሁሉ ሲሉ ያስቁሙልን፡፡

በሲቪል ምህንድስና የተመረቁበትን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን አስተውለውታል? የተስፈኞቹ ግቢ ‹ተስፋ የለንም› በሚሉና የፓርቲዎን መታወቂያ መያዝ ከዲግሪያቸው በላይ ዋጋ እንዳለው በሚያስቡ ወጣቶች መጥለቅለቁን የግዛቱ የጎበዝ አለቃ ዶ/ር አድማሱ የማይናገሩት እውነታ ሆኗል፡፡ የብሔር ፖለቲካውም ጠንካራ መሰረት በሌለው የፌዴራል ስርዓት ላይ በመንጠልጠሉ ከዛሬ ነገ ክሩ ተበጥሶ ወደ ሞኝ ፀብ እንዳያስገባን እፈራለሁ፡፡ በአረቡ ዓለማት የሚባክኑ ሴቶቻችን እንቅልፍ አሳጥተውናልና ያስቧቸው፡፡ ስለ ሰላም ሲሉም የሙስሊም ወገኖችዎን ጥያቄ በውይይት ይፍቱልን፡፡ ህግ ከአለቆች በላይ መሆኑን አምነው ያሳምኑልን፡፡ የተሰደደው ፖለቲካችንንም /ዲያስፖራውን/ ለሀገሩ ያበቁት፡፡ የኤርትራንም ጉዳይ ከዚህ በኋላ የስጋታችን ምንጭ እንዳይሆን አድርገው መቋጫ ያብጁለት፡፡ ገበሬውን ለረሃብ ከሚዳርገው የዘልማድ አሰራር እንዲላቀቅ እርዳታዎ አይለየው፡፡ እንደሚያዩት የአቶ መለስ ራዕይ ውጤት መንገዶቻችንን እንዲህ በእሾህ ሞልተውታል፡፡ ራዕያቸውን የማስቀጠል ሀሳብም መለኮታዊነታቸውን የማስቀጠል ዕቅድ አንዱ አካል ነው፡፡ እርሶ ግን የዚህ ሰለባ መሆን የለብዎትም፡፡ ሀገርዎ የፈለገችዎ የሌላን ሳይሆን የራስዋን ራዕይ ቀርፀው እነዚህንና መሰል ሽክሞችዋን እንዲያቀሉላት ነው፡፡ በመልዕክቱ መግቢያ ላይ እንደሰፈርው የእስከዛሬው አበሳችን በአንድ ሰው እንደመጣብን ሁሉ በአንድ ሰው መነሳቱ የማይታበለው ቅዱስ ቃል ምስክር ነው፡፡

አሁንስ ሳይበቃኝ አይቀርም! እንደ አባት አስቤዎ እነኚህን ሁሉ ጥያቄዎች በቅንነት ጠይቄያለሁ፡፡ መቼም እኔም ቅን መልሶች ብጠብቅ እርስዎም አይፈርዱብኝም፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ የዋህነቴ ወደ ቁጣ፣ ገርነቴም ወደ ብስጭት፣ ጭምትነቴም ወደ ጩኸት ከተለወጠ ጥፋቱ የእርስዎ ስለሚሆን እንዳያዝኑብኝ፡፡

# የኃይለማርያም . . .

ከ ገፅ 19 የዞረ

ሪፖርት ይጠቅሳሉ፡፡ እንደ ኢህአዴግ ሙግት ‹‹ብዙዎቹ ልማታዊ መንግስታት ፀረ-ዴሞክራሲ ስለነበሩ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ከመገንባት ይልቅ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን እንዴት ማምጣት እንደሚቻል ከእነርሱ ልምድ መቅሰም›› ይቻላል፡፡ እነ አቢቢኒክ በበኩላቸው፤ ከዓመታት በፊት የተከሰተውን የምዕራባውያኑን የፋይናንሽያል ቀውስ አስመልክቶ ፓርቲው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ የኢኮኖሚ መስመሩ ትክክል እንደሆነ ቢታበይም፤ ሀገሪቱን ከምግብ ዕጥረት፣ የዋጋ ንረትና ከፍተኛ ስራ አጥነት ማውጣት እንዳልቻለ በመጥቀስ ስርዓቱን አጥብቀው ይተቻሉ፡፡

‹‹አሳታፊ ዴሞክራሲ›› ድንቁም¡

በፓርቲው የሚዘጋጁትና ሀሳቡን የሚያብራሩ ሰነዶች እንደሚያወሱት አብዮታዊ ዴሞክራሲን ከሊበራሊዝም አስተምህሮት የተሻለ ያደርገዋል ብለው የሚያነሱት ዋነኛ ጭብጥ፣ እንደ ሊበራሊዝም ‹‹ህዝቦች›› በውክልና ከሚመሩበት ስርዓት ይልቅ በቀጥተኛ ተሳታፊነት ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበትን ሁኔታ ይፈቅዳል›› የሚል ነው፡፡ ይህንንም ለመተግበር ህገ-መንግስት፣ የመድብለ-ፓርቲ ስርዓት እና የፖለቲካ ምርጫን የመሰሉ በሊበራሊዝም ዕሴቶች ስር የሚበየኑ ተቋማት መኖራቸውን ይጠቅሳሉ፡፡ ይህን የፓርቲውን መከራከሪያ የሚያብጠለጥሉ ምሁራን በበኩላቸው ተፃራሪ ድምዳሜያቸውን ያስነብባሉ፡፡ እነዚህ በቅርፅ ነፃ የሚመስሉ ተቋማትን በመጠቀም ሊመጣ የሚችለውን ፖለቲካዊ ብዙህነትን ገዝቸው ፓርቲ ከላይ የተዘረዘሩትን ማፈኛ መንገዶች በመጠቀም የነገሩን ህልው መሆን እንደሚከላከል የሚናገሩት እኒህ ምሁራን፤ የፓርቲውን መከራከሪያ ‹‹ማጭበርበሪያ›› ይሉታል፡፡ ከነዚህ ፀሐፊዎች አንዷ ኒኮላስ ባች፤ ኢህአዴግ ለማስመሰል ያዋቀራቸውን እነዚህን ተቋማት የአብዮታዊ ዴሞክራሲን የበላይነት ብቻ ለማስረገጥ ይጠቀምባቸዋል ሲሉ ይከሳሉ፡፡

ሌላኛው ለአሳታፊ ዴሞክራሲ ማሳያ ተደርጎ በፓርቲው የሚጠቀሰው የታችኞቹን መንግስታዊ መዋቅሮች ታሳቢ የሚያደርገው ነው፡፡ ከ1997ቱ ምርጫ ወዲህ ኢህአዴግ የወረዳና የቀበሌ መዋቅሮችን በማስፋፋት ተጠምዶ ቆይቷል፡፡ ሎቪስ አለንና ኬጅቴል ቶርኖቬል እንደሚያወሱት የሰፊውን ህዝብ የውሳኔ ሰጭነትና ተሳታፊነት ለማረጋገጥ በሚል የቀበሌ መማክርቶች ሲቋቋሙ፤ በእያንዳንዱ ቀበሌ ያሉት የጉባኤው አባላት ቀድሞ ከነበረው አስራ አምስት አባላት ወደ ሶስት መቶ እስከማሳደግ ሄዷል፡፡ በዚህ ስሌት በእያንዳንዱ ቀበሌ ውስጥ ከሚገኙ ሦስት ነዋሪዎች በአማካይ አንዳቸው ፓርቲው በሚመራቸው እነዚህ ተቋማት ውስጥ እንዲደራጁ ተገድደዋል፡፡ ሁኔታው የጥንቷን የሶቬየት ህብረት ኮሚኒስታዊ አተገባበርን ያስታውሳል የሚሉት እነ ቶርኖቬል፤ የዚህ ሁሉ ውጤት የታችኛውን ማህበረሰብ ጠርንፎ መያዝ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ሌላኛው የኢትዮጵያ ፖለቲካ አጥኚ ሳራ ቫግሆን፤ በአሳታፊነት ስም ኢህአዴግ ‹‹መሰረታዊ ድርጅት›› ብሎ በሚጠራቸው አወቃቀሮች በኩል በየቀበሌው ውስጥ ያሉ አምስት ቤቶችን በአንድ ሴል በማዋቀር የፓርቲውን ማኒፌስቶ እንዲያነቡ እንደሚያስገድድ ይጠቅሳሉ፡፡ አጥኚዋ "Revolutionary democratic state building: party state and people in the EPRDF's Ethiopia" በሚል ርዕስ ከ6 ወራት በፊት ባስነበቡት ጥናት ለመሰረታዊ አገልግሎቶች (PBS) በሚል ከምዕራባውያን ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣውን እርዳታ ፓርቲው በወረዳና በቀበሌ ደረጃ ላሉት አባላቱ ለደሞዝ ክፍያ እንዳዋለው፣ ይህም የነዚህን መዋቅሮች ባጀት በየዓመቱ በ10% እየናረ እንደሆነ የገንዘብ ሚኒስቴርን ዘገባ በመጥቀስ የፓርቲው ግብ ከአሳታፊነት ይልቅ ማህበረሰቡን በስሩ በመሰብሰብ ላይ የተጠመደ እንደሆነ ያወሳሉ፡፡ ይህ መዋቅራዊ አፈና የድህረ-ደርግ ኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ሽግግር ተደርጎባታል ማለት እንደማያስችል የሚናገሩት እነቶርኖቬል ፖለቲካዊ አምባገነንነት ስለመገንገኑ በማያሻማ ቋንቋ ያስረግጣሉ፡፡ "The end of democracy? Curtailing political and civil rights in Ethiopia" ብለው በሰየሙት ስራቸው ‹‹ኢትዮጵያ ያልተሟላ ዴሞክራሲ ያለባት ሀገር ሳትሆን ዴሞክራሲያዊ አስመሳይነት የሰፈነባት ወጥ አምባገነን ሀገር ነች›› ሲሉ ጠንከር ባሉ ቃላት ይደመድማሉ፡፡

## የኃይለማርያም ዕዳ

እጅግ በከፋና እርስ በርስ በሚጣረሱ መንፈሶች የተበከለው አብዮታዊ ሰነድ ከታተመ ከሃያ ዓመታት በኋላ ፓርቲው ለስልጣን መቆያ ሌላ መከራከሪያ ማቅረብ ጀምሯል፡፡ የቀደሙት የሀገሪቱ ተከታታይ መንግስታት መሰረታዊ ግድፈት ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ያለመገንባት ከዚህም የተነሳ የብሄሮች ጭቆና እና ድህነት መንሰራፋት መሆኑን ሲናገር የነበረው ኢህአዴግ፤ ከጥቂት ጊዜያት ወዲህ ስርዓታዊ መረጋጋትን መጠበቅ ቀዳሚ አጀንዳው አድርጎ ማቅረብ ጀምሯል፡፡ እነ ዶ/ር ቶብያስ ሀግማን እንደሚከራከሩት ይህ የፓርቲው የሙግት ሽግግር ‹‹ስልጣኑን በጠንካራ ድልዳል ላይ ለማጠናከር›› የሚቀርብ ነው፡፡ ሽብርተኝነትን እና ጽንፈኛ ፖለቲካዊ እስልምናን በሀገር ውስጥ እና በአፍሪቃ ቀንድ ዙሪያ ያሉ ነባራዊ ፈታኝ ጉዳዮች አድርጎ ማቅርቡ፤ በዚህ ሰበብም ከሶማሊያ ጣልቃ ገብነት ጀምሮ ጋዜጠኞችንና ፖለቲከኞችን ካለመታከት እየሰበሰበ ማሰሩ ይህን መከራከሪያውን ለማስረገጥ እንደሆነ የሚናገሩት አጥኚዎቹ፤ ፓርቲው ‹‹መቼም እና እንዴትም ስልጣን ለመልቀቅ አይፈቅድም›› ሲሉ ይደመድማሉ፡፡ ከዚህ ከባድ ድምዳሜ በመለስም የአቶ መለስ ‹‹ራዕይ›› ኢትዮጵያን የት እንዳደረሳት ለመረዳት የተቋማትን የቅርብ ጊዜ መንግስታዊ ፍረጃ ማየት እንደሚገባ ያስታውሳሉ፡፡ በቀደመው ዓመት መጨረሻ የወጣው የፍሪደም ሃውስ የነፃነት መጠቆሚያ ሪፖርት ለመጀመሪያ ጊዜ ሀገሪቱን ‹‹ነፃነት አልባ›› በሚለው ምድብ ውስጥ ከቷታል፡፡ የኢኮኖሚስት መጽሔት አጋር ተቋም የሆነው ኢኮኖሚክ ኢንተለጀንስ ዩኒት የዴሞክራሲ መጠቆሚያን በሚመለከት የሚያወጣው አመታዊ ዘገባም የኢትዮጵያን መንግስት ‹‹አምባገነን መንግስት›› ለማለት ብዙ አላመነታም፡፡ ከነዚህ ሁለት ሪፖርቶች በከፋ ሁኔታ የሞአብራሂም አፍሪካን ገቨርናንርስ ኢንዴክስ፤ የህግ የበላይነትን በማስከበር፣ ፖለቲካዊ ተሳታፊነትን በማበረታታት እና ሰብዓዊ መብቶችን ከመጠበቅ አንፃር ኢትዮጵያን ከአፍሪካ ሀገራት በ38ኛ ደረጃ ላይ መድቧታል፡፡ እኒህ ሁሉ ከባባድ ነባራዊ ድምዳሜዎች የመለስ መንገድ መዳረሻ ከመሆናቸው አኳያ የኃይለማርያም ዕዳ ይህን ተግዳሮት መሻገር ይሆናል፡፡

# "ድንገቴ ፖለቲከኞች"...

ከ ገፅ 6 የዞረ

ተደርጎ የሚወሰደው በገንዘብ ከፍተኛ ድጋፍ የሚያደርገው ዳያስፖራ ፖለቲካውን እንዳሻው ለመምራት የሚያደርገው ተጽዕኖ ኃያል መሆን ነው፡፡ ዳያስፖራው በለገሰው ዶላር መጠን ድምጹ እንዲሰማ ይፈልጋል፡፡ "አንዲት ሳንቲም ስትቀበል ተጨማሪ አጀንዳ መቀበልህን አትርሳ" ብለውኛል ለአንድ ፖለቲካ ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ስራ የሚሰሩ የአመራር አካል፡፡ ዳያስፖራው ከማይፈልገው የፖለቲካ ቡድን ጋር የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት ወይም ውይይት ድጋፍን ሊያሳጣ ይችላል፡፡ አንድ ዳያስፖራ ገንዘቡን ሲያካፍል በዛው ልክ ተደማጭነት እንዲኖረው በእጅጉ ይሻል፡፡ ይህም አንዳንድ ፖለቲከኞችን አስኮርፎ ከትግሉ እንዲሸሹ ምክንያት ሆኗል፡፡

የኢሕአዴግ አፋኝ ሥርዓት በውጭ ያሉ ተቃዋሚ ኃይሎች በአገር ቤት ካለው የተቃውሞ ቡድን ጋር ግንኙነት እንዳይፈጥሩ ማድረጉም ሌላው ተጨማሪ ምክንያት ነው፡፡ አሁን በግልጽ እንደሚታየው በውጭ ያሉ ተቃዋሚ ኃይሎች በአገር ቤት ያላቸው እንቅስቃሴ እጅጉን ደካማ እና ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡ አገር ቤት ያሉ ዜጎች እና ፓርቲዎቹ በአግድሞሽ የሚተላለፉ ዓይነት ሆነዋል፡፡ ይህም እውነታ ተስፋ ያስቆረጣቸው ፖለቲከኞች ማፈግፈግን አንዱ አማራጭ አድርገዋል፡፡

## "በወጡበት በር . . ."

የዳያስፖራው "በድንገቴ ፖለቲከኞች" ፈረስ መጋለብ እና የጠንካራ ፖለቲከኞች ከትግሉ ጎራ ማፈግፈግ የነጻነት ጥያቄውን የሚያዳፍን እና ተስፋ የሚያስቆርጥ ግን አይደለም፡፡ ይልቁንም የተሻለ ቅርጽ ያለው የትግል ስልት ይዘው በአዲስ ኃይል እንዲነሳሱ የሚያደርግ ነው፡፡ ‹‹የኢሕአዴግ ጥንካሬ የተቃዋሚዎች ድክመት ነው›› ብለው የሚሞግቱትን ሰዎች ሃሳብ ተቀብሎ በአዲስ መንፈስ መነሳት የግድ ነው፡፡

ብዙዎች አገር ቤት ካለው ተቃዋሚ ፓርቲ ጋር ጥንቃቄ የተሞላበት ግንኙነት መመስረትን እንደ ቀዳሚ አማራጭ አድርገው ይወስዳሉ፡፡ አገር ቤት ያሉት ኃይሎች ሕዝቡን ለማደራጀት እና ወደሚፈለገው አቅጣጫ ለመውሰድ ብቸኛ መንገድ ናቸው፡፡ ከሰው ኃይል፣ ከፋይናንስ እና ከስትራቴጂ አኳያ ያለባቸውን የአቅም ውስንነት የውጭው ኃይል መሸፈን ከቻለ ለውጥን ለሚናፍቀው ሕዝብ ትልቅ ተስፋ ነው፡፡ ይህንንም ለማድረግ የገዢው አካል አካሔድ ሥራ ፈታኝ ቢሆንም የተሻለ ብልሃት በመንደፍ ተግዳሮቶቹን መወጣት ይቻላል፡፡

በተጨማሪም ተበጣጥሶ የሚገኘውን የትግል ስልት ወደ አንድ መስመር ማምጣት አማራጭ ነው፡፡ አዲሱ የማኅበራዊ ድረ-ገጽ መድረክም ይሄንን ተግባር በማቀላጠፍ ረገድ አስተዋጽዖው ከፍተኛ ነው፡፡ መረጃዎች በተቀላጠፈ መልኩ እና በሚጠበቀው የጊዜ ሠሌዳ ለሚመለከተው አካል እንዲደርስ በማድረግ ትግሉን ያግዛል፡፡ ለዚህም እንደምሳሌ በዚህ ወቅት የሙስሊሙን ማኅበረሰብ ተቃውሞ እየመሩ ከሚገኙ አካላት ብዙ መማር ይቻላል፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ለአሥር ወራት ሲዘልቅ በሙስሊም ወንድሞች የሚመሩት የማኅበራዊ ድረ-ገጾች መረጃን በማቀባባል ሰላማዊ እንቅስቃሴው ከዓላማው እንዳያፈነግጥ አስተዋጽዖ አድርገዋል፡፡

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ እንደ ኤርትራዊው ሚካኤል ባህር ሲሻገር "ፖለቲካን በሩቁ" ብሎ የሚንገፈገፍ አይደለም፡፡ ሁሌም እንደ ጋለ ብረት ነው፡፡ መልካም እና አስተዋይ አንጥረኛ ይፈልጋል፡፡ በጥናት የተደገፈ ሥራ መሥራት ከተቻለ ይህንን ኃይል ወደ ተፈለገው አቅጣጫ መውሰድ ይቻላል፡፡ ይህም ቢሆን ግን አገር ቤት ያለው ዜጋ የአንበሳውን ድርሻ እንደሚወስድ ተዘንግቶ መሆን የለበትም፡፡

# በኢትዮጵያ የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ...

ከገፅ 13 የዞረ

አዋጪ (feasible) አይመስለኝም፣ በአስተሳሰብ ደረጃም ቢሆን፡ ፡ ምክንያቱም ሃያና ሰላሳ አመታት ይቅርና ነገ ምን ጣጣ ይዞ ሊመጣ እንደሚችል የምናውቀው ጉዳይ የለም፡፡ ለምሳሌ እኔ ባላምንበትም፣ አለም ከ20 ዓመታት በኋላ ትጠፋለች የሚሉ አሉ፡፡ ይህ ሁሉ በዋናነት ስለ ነገ እርግጠኛ ካለመሆን የመጣ ነው፡፡ስለዚህ በዚህ ሁሉ ሁኔታ ለ20ና 30 ዓመታት "ማቀድ"፣ ትርጉም የሚሰጥና መሬት ላይ የሚወርድ ስሌት አይደለም፡፡ በመጨረሻም፣ ከላይ ላነሳኋቸው መከራከሪያዎች መከራከሪያ አንስቶ እንዴት ሊሆን እንደሚችል ሊያስረዳኝና የበረበረው ምስጢር/ምክንያት አለኝ የሚል ካለ ቢያካፍለኝ በሬ ክፍት መሆኑን እገልጣለሁ ፡፡

ወደ ዋናው ርዕሰ ጉዳይ ስመለስ፣ ባህላዊ የሆነውን የኢትዮጵያን የእርሻውን ክፍለ-ኢኮኖሚ ከነ ትንሽነቱ እግር ተወርች አስረው እንዳይሻሻልና የኢንዱስሪ ሽግግር በሃገራችን እንዳያስከትል ያደረጉትን ችግሮች በሚመለከት ባለፉት 20 አመታት በተለየ መልክ፣ ፖሊሲ አውጪዎችን አከራክሯል፣ በተለያዩ የትምህርት መስኮች የማስትሬትና የዶክትሬት የጥናት ፅሁፎችን አፅፏል፣ እንዲሁም ለሌላ ፍጆታ የሚውሉ የታተሙና ያልታተሙ ጥናታዊ ወረቀቶችን አበርክቷል፡ ፡ ከተዳሰሱት ችግሮች መካከል የመሬት ስሪት ፖሊሲው ደካማነት፣ ክፍለ ኢኮኖሚው በተፈጥሮ ቁጥጥር ስር የወደቀ መሆኑ፤ ተልካሻ የእርሻ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መስፈናቸው፣ ያልተጠኑ ስትራቴጂዎችና ፓኬጆች ለገበሬው መቅረባቸው፣ እርሻን ማዕከል ያደረገ የመድን ዋስትና አለመኖር ወዘተ... ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተወሰኑ ጥናታዊ ፅሁፎች እንደሚጠቁሙት(የእኔን ጨምሮ) የኢትዮጵያ የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ እንዳይለማና ተራውን ለኢንዱስትሪው እንዳይለቅ የተጋረጠበት፣ በብዛት በጥናቶች ያልተዳሰሰው ፈተና፣ የቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ማቋረጥ( Disadoption of Agricultural Technologies)፤ ማለትም አርሷደሮች በስራ ላይ ያውሏቸው የነበሩ የእርሻ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን ከተወሰነ ጊዜ መጠቀም በኋላ( አንድ ወይንም ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ ካዋሉ በኋላ) ላለመጠቀም መወሰን ወይንም መጠቀማቸውን ማቋረጥ ነው ( a situation when farmers discontinue the use of already adopted technology):: አንድ ጥቅም ላይ የዋለ የእርሻ የቴክኖሎጂ ግብዓት እርሻን ሊያሳድገው ብሎም ወደ ኢንዱስትሪው የሚደረገውን ሽግግር ሊያግዝ የሚችለው በስራ ላይ የዋለው የቴክኖሎጂ አይነት( ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘር፣ ልዩ ልዩ የአሰራርና የአስተራረስ ዘዴዎች፣ የተባይና የአረም ማጥፊያ መድሃኒቶች፣ ልዩ ልዩ ዘመናዊ የግብርና ግብዓቶች፣ ወዘተ....) ሳይቋረጥ ለረጅም ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆን ነው፡፡ በሃገራችን የተደረጉ ጥቂት ጥናቶች የሚያረጋግጡት ግን ከፍተኛ የሆነ የቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ማቋረጥ (technology disadoption) እንዳለ ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል በእርሻው ዘርፍ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን መጠቀም የእርሻውን ክፍለ ኢኮኖሚ ያላሳደገውና ገፋ ሲልም ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረግ ሽግግር የማይታየው፡፡

እንደሚታወቀው የእርሻ ዘርፉ እንዲዘምን፣ ምርታማነት እንዲጨምርና ከእርሻ ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገው ሽግግር (structural transformation) እንዲቀላጠፍ፣ የግብርናው ዘርፉ ማደግ ይኖርበታል፡ ፡ የእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚ እንዲያድግ ደግሞ፣ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን መጠቀም ግድ ይላል፡፡ የቴክኖሎጂው ጥቅም ላይ መዋል ደግሞ ለአፍታ ሳይሆን ለተከታታይና ረዘም ላለ ጊዜ ተግባር ላይ መዋል ይኖርበታል፡፡ ከዚህ የምንረዳው ምንድን ነው ያልን እንደሆን፣ አርሷደሩን የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን በግድም በውድም ስራ ላይ እንዲያውል ማድረግ ብቻ በራሱ በቂ እንዳልሆነ ነው፤ ይልቁንም በቀጣይነት ጥቅም ላይ ካልዋለና ያዝ ለቀቅ ከሆነ ቅሉ፣ የቴክኖሎጂ መጠቀም እርሻ እንዲያድግና ከማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ጋር ትስስሩ እንዲጠብቅ የሚጫወተው ሚና እዚህ ግባ የሚባል አይሆንም፡፡ ዛሬ እንደምናየውም ከአንዱ አርሷደር (በልዩ ልዩ ምክንያት "ስኬታማ" ከሆነ አርሷደር) የተገኘን ልምድ ወደ ሌላው አርሷደር እንዲጠቀም መዘርገፍ(dumping)እንዲሁ የ technology disadoption እንዲኖር ምክንያት ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ ከአገራዊ የፖሊሲ አቅጣጫ ያልተቀዱና በዘፈቀደ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚደረጉ አሰራሮችም እንዲሁ ሌላኛው ምክንያት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ለአርሷደሩ "የቴክኖሎጂ ግብዓት" ከራሱ ከአርሷደሩ ነጥቀን ወይንም ከባዕዳን ሽምተን፣ ባርሷደሮች መካከል ያለው ልዩነት ሳይጤን፣ ቴክኖሎጂው ካርሷደሩ አስተሳሰብ፣ ንቃተ ህሊናና ባህሪ ጋር እንደሚሄድና እንደማይሄድ ግንዛቤ ሳይወሰዱ፣ አርሷደሩ ያለበት የአየር ንብረትና የሚኖርበት መልክዓ ምድራዊ ጠባይ ሳይተነተን፣ ወዘተ.... በውዴታ ወይም በግዴታ በማሳው ላይ ጥቅም ላይ እንዲያውል ማድረግ እርሻ በቴክኖሎጂ ታግዞ እንዲያድግ በራሱ በቂ አይደለም፡፡ ጥቅም ላይ የዋለው የቴክኖሎጂ ግብዓት ሳይቋረጥ ለረጅም ጊዜ የዋለ እንደሆነ ነው በእርሻ እድገት ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ ማምጣት የሚችለው፡፡ ወረድ ብለን እንደምናየው፣ ከላይ ያስቀመጥኳቸው መላምቶች፣ ጥናቶች ያስረገጧቸው እውነታዎች እንደሆኑ ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ያልተጤነን የእርሻ ቴክኖሎጂ አርሷደሩ እንዲጠቀም ስናቀብለው፣ ሌላ ጊዜም እንዲሁ ሌላ አይነት አሰራርና ግብዓት በማቀበል ላይ ተጠምደን "ስናላግጥ" በቀጣይነት አርሷደሩ የተቀበለውን መጠቀሙን ሳናረጋግጥ፣ እርሻ ወደ ግብርና እንዳያድግ፣ ይልቁንም ባለበት እንዲረግጥ አሊያም የኋሊት እንዲሄድ፣ አልፎም ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገው ሽግግር እንዳይሰፍን ደንቃራ እየሆነበት ነው፡፡

በሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ አርሷደሩ አንድ ይጠቀመው የነበረን የእርሻ ቴክኖሎጂ እንዲያቋርጥ ከሚያደርጉት ምክንያቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፣ ያለፍላጎት(በግዴታ) እንዲጠቀሙ መደረግ (forced adoption)፣ ዘላቂነትና ወጥነት ያለው የእርሻ ፖሊሲ አለመተግበሩ፣ ከላይ ወደ ታች የሚወርዱ ደንቃራ "አሰራሮችና መፍትሄዎች"፣ የተቀየጡ(hybrid) ምርጥ ዘሮች በበቂ መጠን አለመኖር፣ እንደ በሬ የመሳሰሉ መሰረታዊ የሆኑ የእርሻ ግብዓቶች(key farm assets) በአርሷደሩ ዘንድ አለመኖር፣ አመች የሆነ የብድር አቅርቦት(functioning credit market) አለመኖር፣ የሞያተኛ እጥረት በዋናነት ጥናቶች የለየዋቸው ምክንያቶች ናቸው፡፡ የተወሰኑትን በአስረጂ ለማስቀመጥ ልሞክር፡፡

አርሷደሮች የእርሻ ቴክኖሎጂ ተገፋፍተው እንዲጠቀሙ መደረጉ ከጊዜ በኋላ ያንን ይጠቀሙት የነበረውን ቴክኖሎጂ እንዲያቋርጡ ምክንያት ሆኗል ሲባል ምን ማለት ነው፤ አርሷደሩ ሳያምንበት በልዩ ልዩ ሰንካላ ምክንያቶች( መሬትህን ትነጠቃለህ፣ ማዳበሪያ አታገኝም፣ ቅጣት ይጣልብሃል፣ ወዘተ... በሚሉ ማደናገሪያዎች) ጥቅም ላይ እንዲያውሉ ማስገደድ በአጭሩ እርሻ በቴክኖሎጂ ታግዞ እንዳያድግ ትልቅ በር የሚከፍት ነው፡፡ ምክንያቱም በግፊት እንዲጠቀሙ መደረጉ ቴክኖሎጂውን እንዲያቋርጡ ምክንያት እንደሆነ ከላይ አይተናልና፤ ይህ ተጠቅሞ ማቋረጥ ደግሞ እርሻ እንዳያድግ ተግዳሮት እንደሆነበት ጥናቶች በርብረው፤ እንዳሳዩንም ከላይ አይተናል፡፡ ስለዚህ እርሻ እንዲጎለብት ይህ አካሄድ መሰረታዊ "ተሃድሶ" ያሸዋል፡፡

ሌላኛውን ምክንያትንም ያየን እንደሆን፣ በስራ ላይ እየዋለ ያለ ወጥነት ያለው የእርሻ "ፖሊሲ" አለመኖሩን ከላይ ያየነው ነው፡፡ ከአመታት በፊት እናራግበው የነበረው የእርሻ እድገት ለኢንዱስትሪ ልማት( Agricultural Development Led Industrialization) ደብዛው ጠፍቶ ዛሬ፣ ከላይ እንዳልሁት፣ ከአንድ "ምርጥ" ገበሬ የተገኘን ልምድ ወደሌላ ገበሬ እንዲጠቀም በማቀበል ላይ ተጠምደናል፡፡ ይሄ ከአንዱ ነጥቀን ወደ ሌላኛው አርሷደር እንዲጠቀም በማቀበል ላይ መዋላችን በአገር አቀፍ ደረጃ እየተመራንበት ያለ የእርሻ "ፖሊሲ" እንደሌለ ያሳብቃል፡ ፡ ቢኖርማ ከአንድ በልዩ ልዩ ምክንያቶች "ስኬታማ" ከሆነ አርሷደር ወደ ሌላኛው አርሷደር በማቀበል ላይ አንጠመድም ነበር፡፡ ቢኖርማ መሸለጥ አድርገን አገራዊ የሆነውንና ወጥነት ያለውን አሰራር ለአርሷደሩ እንሰጥ ነበር፡፡ የዚህ አሰራር መሰረታዊ ድክመቱ፣ እንበልና ባይሰራ፣ በጥናት የተደረሰበት ፈውስ ባለመሆኑ የመፍትሔ ሃሳቦች የሉትም፡፡ የቀሩትን ምክንያቶችም በተመሳሳይ አኳኋን ማብራራት ይችላል፡፡ እዚህ ላይ ማስረገጥ የምፈልገው ዋናው ቁም ነገር፣ የኛ እርሻ በቴክኖሎጂ ሊዘምን ያልቻለው፣ እኔ እንደሚመስለኝ፣ ይህ ዘመናዊ የእርሻ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ማቆም (technology disadoption) በመኖሩ ይመስለኛል፡፡ ይህ ባይኖርማ ኖሮ እንዳግበሰበስነው "ዘመናዊ" የእርሻ ቴክኖሎጂዎች ብዛትና ያካሄድናቸው ያላቋረጡ "ተሃድሶዎች" አንፃር፣ ዛሬ ድህነትን ነጥርቀን ጥለነው፣ እርሻችንም ጎልብቶና መሪነቱን ለአምራች ኢንዱስትሪው አቀብሎ፣ ከባቢ አየሩን ከኢንዱስትሪዎቻችን በሚወጣ ጭስ በክለነው ወደ ከባቢ አየር የምትለቁትን ጭስ ቀንሱ የሚል ጫና ይበዛብን ነበር፡፡

ባጠቃላይ ሲታይ፣ ዘመናዊ የእርሻ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ማቆም( technology disadoption) ባህላዊ የሆነውን እርሻችንን እንዳያድግ ክፉ እንቅፋት እንደሆነበት ነው፡፡ ይህ ችግር ጥናቶች በስፋት የፈተሹት ጉዳይ አይደለም፡፡ መንግስትም የባነነበት አይመስለኝም፡፡ ስለዚህ ባህላዊ እርሻችን ፋይዳ ያለው እመርታው እንዲያሳይና እንዲጎለብት፣ ከእርሻ ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገው መዋቅራዊ ሽግግር እውን እንዲሆን(የ2025ቱን "አገራዊ ግብ" ጭምር) ከላይ የተተነተነው ደንቃራ ሳይውል ሳያድር እስከ ግሳንግሱ ማስወገድ አማራጭ የሌለው መፍትሄ መሆኑ ሊታመንበት ይገባል፡፡ አለበለዚያ ግን የእርሻ እድገትና ወደ ኢንዱስትሪ የሚደረገው ሽግግር(ይህ ሊሆን የሚችለው እርሻ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በግብዓት መልክ በመጠቀሙ እንደሆን ልብ ይሏል) ይቅርና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ በራሱ ሊታሰብ የሚችል ጉዳይ አይደለም፡፡ ትንሽም ብትሆን ይህቺ ጠቃሚ ምክሬ ናትና የሚመለከተው አካል "በነፃ" ቢጠቀምባት ወንዝ ታሻግረናለች የሚል ፅኑ ዕምነት አለኝ፡፡ አበቃሁ! በሌላ ምጣኔ ሃብት ነክ ጉዳዮች እስክመለስ ድረስ ጤና ይስጥልኝ፡፡

# ቴዲ አፍሮዎችና ተመስገን ገብሬዎች



እንዳለጌታ ከበደ

## መ. ቴዲ አፍሮዎች

ሁላችንም እንደምናውቀው፣ ቴዲ አፍሮ (ቴዎድሮስ ካሣሁን)፣ ከ1990ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ፣ የኢትዮጵያውያንን አየር ተቆጣጥሮ ይዞታል፣ መገናኛ ብዙሃን ውሎ እና አዳሩ ግድ ይሰጣቸዋል፣ ከኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ግርማ ወልደጊዮርጊስ አንስቶ፣ ታች በጥቃቅን እና አነስተኛ እስከተደራጁት ጉብሎች ድረስ፣ ቴዲ ተደናቂ ነው፣ ብዙ መጽሔቶች እና ጋዜጦች የቴዲ አፍሮ ስም መተዳደሪያቸው ነው፣ እድሜያቸውን የሚያራዝሙት ምስሉን የያዘ ዕትም ይዞ በመውጣት ነው፡፡

ለአንዳንዶች ደግሞ፣ ቴዲ አፍሮ ብልጥ ነው፣ ልቡ የወለደውን የፈጠራ ሥራ ከማቅረብ ይልቅ፣ በሕዝብ ልብ የሚመላለሰውን ነገር አስቦ የሚሰራ ሙያተኛ ነው፣ የተለየ ሃሳብ ለማንሳት ብሎ የተለየ ስህተት በስራዎቹ ውስጥ የሚከት ድምፃዊ ነው፣ ስሙ ከሚዲያ እንዲጠፋ ስለማይፈልግ፣ አቡዋራ የሚያስነሳ ዜና በየጊዜው እየለቀቀ፣ ጭር ሲል የማይወድ መሆኑን በተግባር የሚያሳይ፣ ለግልብ ትውልድ የተፈጠረ፣ የጆብድ ጌታ ነው፡፡

ቴዲ አፍሮ ዕድለኛ ነው፣ ከምርጫ 97 በኋላ ደግሞ፣ በ‹ጃ ያስተሰርያል› ዘፈኑ ምክንያት፣ ሕዝቡ ‹ንጉስ› አድርጐ፣ ዘውድ ደፍቶ፣ በልቡ ውስጥ ዙፋን አመቻችቶለታል፡፡ ነጋዴዎች፣ የነገስታትን ምስል የያዘ ፖስተር አትመው ሲሸጡ፣ ፖስተሩ ላይ አፄ ቴዎድሮስ ጀምረው ምኒልክ ተከትለው፣ ኃይለሥላሴ ቦታቸውን ይዘው፣ መንግስቱ ኃይለማርያም ለጥቀው፣ መለስ ዜናዊ መስፈር ሲገባቸው፣ በቦታቸው ቴዲ አፍሮ ፈገግ ብሎ ሰፍሯል፡ ፡ ይህንንም ምስል በየታክሲው ተለጥፎ አየነው፣ ይህ የሚያሳየው ቴዲ አፍሮ፣ በአንዳንድ አድናቂዎቹ ልብ ውስጥ፣ ቤተመንግስት መገንባቱን ነው፣ እሱ የገነባው ቤተመንግስት ሌላ አርቲስት መጥቶ፣ ግዛቱን አስፋፍቶ፣ እስኪቆጣጠረው ድረስ፣ ቴዲ አፍሮ፣ ኢህአዴግን የሚቃወሙ ሰዎች ድምፅ ሆኗል፣ ነኝ አላለም፣ ሕዝቡ ግን ነህ ብሎታል፣ በግጥሞቹ ውስጥ የሌለ መልእክት እየፈለጉ፣ ያልተነገራቸውን ምስጢር እየተነተኑ፣ ‹የት አባታቸውንና! ለእነዚህ ሀወሓቶች-አይገባቸውም እንጂ-በቅኔ ልክ ልካቸውን አስታጠቃቸው› እየተባለ፡፡ ‹‹አንድ ላይ ብንሆንም ተለያይተናል››-ያለውቀ መንግስት ከሕዝብ ጋር ተራርቆ ተኳራፎ መኖሩን ለማመላከት ነው፣ ልጅማ ድምፃዊ፣ የነፃነት ታጋይ፣ የታሪክ ተመራማሪ ብቻ አይደለም ትንቢት ተናጋሪ ጭምር ነው፣ጥቁር ሰው ብሎ ሙሾ ቀላቅሎ አወጣ፣ ይኼው ጠ/ሚሩ እና ፓትሪያሪኩ ተያይዘው ሄዱ እነሱ ግን አልገባቸውም›› ተባለ፡፡

ለእኔ ቴዲ አፍሮ አሁንም ‹እስረኛ› ነው፣ ‹ደጉ ይበልጣል የተባለ አንድ ጐዳና ተዳዳሪ ገጭተሃል› ተብሎ ወህኒ ቤት ወርዶ ቢወጣም፣ አስቀድሞ በገነባው ስም ምክንያት ራሱን ሆኖ ለመኖር የተቸገረ ይመስለኛል፣ ይመስለኛል ነው ያልኩት፣ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፣ ቴዲ ከእስር ከተለቀቀ በኋላ፣ ኢህአዴግን የሚደግፉም ሆኑ የሚቃወሙ ሰዎች፣ ምን ገጥሞ፣ ምን ዘፍኖ እንዳደረ ብቻ ሳይሆን ምን አልሞ እንዳደረ ግድ ይሰጣቸው ያዘ፣ ቂጭ ብለው፣ ቀይ እስኪርብቶ ይዘው፣ እንዲህ ያለው እንዲህ ለማለት ፈልጐ ነው፣ እንዲህ ያደረገው እንዲህ እንዲያደርግ ስለተገደደ ነው እያሉ፣ በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሞት ምክንያት ቤተሰቦቹ ዘንድ ሄዶ፣ ማፅናናት ይገባዋል ወይስ አይገባውም እያሉ፣ ‹ራይት› እና ‹ሌክስ› የሚሰጡ ‹የሞራል መምህራን› እና ‹የፖለቲካ ተንታኞች› ማፍራት ችሏል፡፡

በቅርቡ ያወጣውን ‹ጥቁር ሰው› አልበም መጀመሪያ ስሰማ፣ ምኒልክን እና አርበኞቹን የሚያወድስ ግጥም ፅፎ፣ በኦሮሚኛ የሙዚቃ ስልት መጫወቱ፣ እጅጉን አስደስቶኝ ነበር፣ ምንም እንኳን በዘፈኑ ውስጥ ከተጠቀሱት አርበኞች ይልቅ በአድዋ ዘመቻ፣ አስተዋፅኦ አድራጊዎች እና ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ሌሎች ናቸው ተብሎ ትችት ቢሰነዘርበትም፣ ምንም እንኳን የባልቻ አባት ሳፎ እንጂ ነፍሶ አይደለም፣ የፈረስ ስሙን እንደ አባት አድርገህ ተጠቅመህ ጠርተህ ተሳስተህ አሳስተሃል ቢባልም፣ ምንም እንኳን በአንድ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ቀርቦ ስለዚህ ጉዳይ ሲጠየቅ፣ ‹ሆነ ብዬ፣ ለግጥሙ ውበት ብዬ…› ዓይነት መልስ ሰጥቶ፣ የባልቻ አባት ሳፎ አለመሆኑን እንኳንስ እኔ ማንም የአራተኛ ክፍል ኢትዮጵያዊ አያጣውም ብሎ መልስ መስጠቱ፣ ይኼ ‹ብላቴና› ወዴት እየሄደ ነው ቢያስብለውም፣ ለእኔ ‹ጥቁር ሰው›፣ በአፄ ምኒልክ ላይ ቂርሾ አለን ለሚሉ ኦሮሞዎች የተላከ የዕርቅ ደብዳቤ ነው፣ በራሳቸው ቋንቋ፣ በራሳቸው ተወዳጅ ዜማ፣ ከአብራኮቻቸው የተከፈሉ አርበኞችን ስም እያንቀለቀለ፣ የዓድዋ ድል፣ የሰሜኖች ጀብዱ ብቻ አይደለም እናንተም አላችሁበት፣ ምኒልክ ከጉያዎቻችሁ የወጡ ጦረኞችን ነው ይዘው የተዋጉት ለማለት የፈለገ ነው የመሰለኝ፣ እንዲህ ካለ በኋላ ነው ‹ስለፍቅር›ን ያስከተለው…

የሆነው ሆኖ፣ ብዙ ገፅ ሊወስድ የሚችለውን ቴዲ አፍሮን እዚህ ላይ እንግታና፣ መነሻችን ‹አብዛኛው የኢትዮጵያን ሕዝብ በአንዳንድ ከያኒ ስመስለው› ነውና፣ ከላይ የተጠቀሰውን የድምፃዊውን ባህርይ ከባህርያችን ጋር ማመሳሰሌን ልቀጥል

…አንዳንዶቻችን እንደ ቴዲ አፍሮ ነን፣ የሕዝቡን የመንፈስ ግለት ተከትለን፣ የምንሰራው ስራ የብዙ ሜዳሊያዎች ባለቤት ያደርገናል፣ ቁጣችን ከሕዝቡ ቁጣ እኩል ሲሆን፣ ተቃውሞአችን ከአብዛኛው ተቃዋሚ ስምም ሲሆን፣ ህዝቡ ወደምንሄድበት ይሄዳል፣ በቆምንበት ይቆማል፣ የሚያመኘን ነው ያከምከኝ፣ የበላኝን ቦታ ነው ያከክልኝ ይለናል፣ ያፀደቅነው መተዳደሪያ ደንብ ሳይኖር፣ የተፈራረምነው ሰነድ ሳይኖር፣ በሥራችን ብቻ፣ ‹የፓርቲህ አባል ነኝ› ይለናል…

እኛ ቴዲ አፍሮዎች፣ የስህተት ድጥ አዳልጦን ብንወድቅ እንኳን በውድቀታችን የሚሳለቁ እና የሚሳሳቁ ልቦችና ጥርሶች ጥቂቶች ናቸው፣ ጥቂቶቹም በዕውቀት የተሞሉ፣ በሙያቸው አንቱ የተሰኙ ይሆኑ ይሆናል፣ ግን እነዚህን ማን ያደምጣል ብለን፣ ሚዲያ ላይ ብንቀርብ እንኳን ‹ሆን ብዬ ነው፣ ለዜማው ስምረት፣ ለግጥሙ ጥምረት እንዲጠቀመኝ ብዬ ነው› እንላለን እንጂ፣ ተሳስቻለሁ የሚለው ቃል ከአንደበታችን አይፈልቅም፡፡

‹አቡጊዳ› ላይ ፊደላቱን በትክክል አልጠራችሁም፣ ብንባል፣ ባልደራሱ ዘፈንህ ላይ፣ ‹…በቀን በአራተኛው በዕለተ ሐሙስ ብለሃል፣ ግን እሁድ ብለን፣ ሐሙስ 5ኛ ቀን ነው እንጂ አራተኛ አይደለም› ብንባል፣ አንድ ዘፈንህ ላይ ‹ከአፈር የሰራሃት ነፍሴ ብለሃል፣ ነፍስኮ ከአፈር አትሰራም› ብንባል፣ ሌላም ሌላም ነገር ብንባል፣ እየተባለ ያለውን ነገር አሜን ብለን ማረሚያ አንሰጥም፣ ለምንድነው የምንሰጠው አንደኛ ከሰው ስህተት ክብረት ዝገት አይጠፋም የሚል ማህበረሰብ ነው አምጦ የወለደን፣ ሁለተኛ ደግሞ ለህዝቡ እንኳንስ እንደዚህ አይነት ግጥም ሰጥተነው፣ ባዶ አልበም፣ ግጥምም ዜማም ሙዚቃም የሌለው ነገር አትመን፣ ስማችንን ለጥፈን ብናሳትም፣ ‹የኢህአዴግ ነገር ዝም ነው› ለማለት ፈልጐ ነው ይለናል እንጂ ነገር አያጠብቅም፣ አቀንቃኞች ነንና ለቅን ሕዝብ እንጂ ለቅንቅን አቃቂረኞች ቦታ ሊኖረን አይገባም እንላለን፡፡

እኛ ቴዲ አፍሮዎች፣ መጀመሪያ ተኩሰን አለመሳታችንን እስካሳየን ድረስ፣ ቀጥለን የሆነ ነገር ብንል የሆነ ነገር ተብሎ ይተረጉምልናል፣ ለሚወዱን ሰዎች አነጋገራችን ብቻ ሳይሆን አቀማመጣችንም ትርጉም አለው፣ ልክ ባለፈው ቴዲ አፍሮ በጠቀስኩላችሁ ፕሮግራም ላይ ቀርቦ እግሩን እግሩ ላይ ሰቅሎ፣ ቃለ ምልልስ ሲሰጥ ያዩ አንድ የማውቃቸው እናት፣ ‹…ኧይ ቴዲ አፍሮ! እነዚህን ኢህአዴጎች በቃላት አልገባቸው ሲል፣ በምልክት ይሰድባቸው ጀመር፣ አያችሁ፣ አልፈራችሁም! ሲል› ብለው አቀማመጡን ትርጉም እንደሰጡት፡፡

እኛ ቴዲ አፍሮዎች፣ መሬቱም ንፋሱም ጐንበስ እንዲሉልን የሚያደርጉ በቂ ‹የሚዲያ ሰዎች› አሉን፣ እነዚያ ሚዲያዎች ደረጃችንን ከፍ ለማድረግ፣ ባልዋልንበት ቦታ የዝና አክሊል ያቀዳጁናል፣ በተመሳሳይ ጊዜ ብዙ ወንበሮች ላይ የመቀመጥ መለኮታዊ ኃይል ያላብሱናል፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረብን፣ አምላክ በአንደበታችን አድሮ የሚናገርብን፣ ‹ፍትሕ ተነፍጌያለሁ፣ ዴሞክራሲ ተርቤያለሁ› የሚለውን ሕዝብ እየመራን፣ ከድህነት አረንቋ፣ ከዘር አድልዎ ሸለቆ ይዘን፣ በፍርሃት የተሞላውን ባህር የምናሻገር ‹የዘመናችን ሙሴ› አድርጐ ይቆጥረናል፡፡

☞

**ተመስገን ገብሬዎች መንገዳቸው የጨዋ ነው፤ አነጋገራቸው የጭምት ነው፤ በገድላት እና በድርሣናት ውስጥ እንደምናገኛቸው ሰማዕታት፤ ራሳቸውን ለተከበረ ነገር ያጩ ናቸው፤ ለተከታዮቻቸው ግድ አላቸው፤ የሆነ ሰው፤ የሆነ ቦታ ሆኖ፤ ለአርአያነት ሲመርጣቸው እንደሚችል ግምት አላቸው፤ ተከታዮቼ ወዴት ናችሁ ብለው ግን አይፈልጉም፤ የሚታመኑት ለሃሳባቸው ነው፡፡**

አብዛኛው ሕዝብ ፍቅሩን ለመግለፅ ብሎ፤ እኛን የመሰለበት ቋንቋ፤ ‹አይገልፀንም፤ አይወክለንም!› የማለት አቅም የለንም፤ ልክ ነውም አይደለምም ሳንል መንገዳችንን እንቀጥላለን፤ የሚወደውን እየወደድን፤ ‹አትንካብኝ› የሚለውን እያከበርን፤ ‹ሕይወቴም መንገዴም ሕዝብ ነው› እያልን፤ ጊዜ እና ዕድል አድልተውልን በብዙሃኑ እጅ እንድንቀመጥ ያደረገን እንቁላሎች መሆናችንን አምነን፤ ከእጃቸው ተፈትልከን የምንወድቅበት እና አስኳላችን የሚፈርጥበት ዘመን መቼውንም እንዳይመጣ እየፀለይን፤ ኑሮአችንን የምንቀጥል እንሆናለን-

ሠ. ተመስገን ገብሬዎች

እነሆ! ስለተመስገን ገብሬ አሁንም ልተርክ ነው፤ ከዚህ ቀደም ‹ከማደንቃቸው ሰዎች አንዱ› ስለመሆኑ በሌላ አጋጣሚ፤ ለአድማጮች አውርቼ ነበር፤ ተመስገን ገብሬ፤ ብዙ ያልተባለለት፤ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ዘመናዊ አጭር ልቦለድ ደራሲ፤ የመጀመሪያው ያሰኘውን ብቸኛ እና ነጠላ አጭር ልቦለዱን ‹የጉለሌው ሠካራም›ን ለማየት ሁለት ሦስት ወራት ሲቀሩት ሞት የቀደመው፤ ከ63 ዓመት በፊት ግብዓተ ሕይወቱ የተፈፀመ፡፡

ከአምስት አመት በፊት፤ የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበር፤ አጫጭር ልቦለዶች ብቻ የሚነበቡበት አንድ ጉባዔ፤ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር አሠናዳ፤ መታሰቢያነቱም ለተመስገን አደረገው፤ ‹የጉለሌው ሠካራምም› ተተረከ፤ ስለ የሕይወት ታሪኩም ብዙ የሚታወቅ ነገር እንደሌለ ተነገረ፤ መድረክ ላይ የሆነው ሁሉ፤ በኢቲቪ ተላለፈ፤ ይህን ያዩ የደራሲው ቤተሰቦች፤ አባታችንን እናንተ በምትሉት ልክ አናውቀውም፤ ሳናውቀው ነው ሞት የቀደመው አሉና፤ እናታችን አደራ በማለት የሰጠችን፤ በእርሳስ የተፃፈ፤ ያልተጠናቀቀ፤ ከመቶ ገፅ የበለጠ፤ 60 ዓመት ያስቆጠረ ረቂቅ ድርሰት ይዘን መጥተናልና እዩት እስኪ አሉንና፤ ሳይሸጥ የቀረ፤ ቤት ውስጥ የተቀመጠ ‹የጉለሌው ሠካራም› አለና ማኅበሩ ይረከበን ብለው ይዘው መጡ፡፡

ከዚያ በኋላ፤ በእርሳስ የተፃፈችዋ፤ ‹ሕይወቴ› ታተመች፤ ተመስገንን ብቻ ሳይሆን፤ የዘመኑን መንፈስ ቃኘንበት፤ የአተራረክ ብቃቱን ብቻ ሳይሆን፤ እሱና ሌሎች አርበኞች፤ በየካቲት 12/1929 ዓ.ም.፤ ስለተጐነጩት የመስዋዕትነት ፅዋ አወቅንበት፤ በጣሊያን ወረራ ጊዜ የዚያን ዘመን ትውልድ አባላት፤ ሀገር እና ባንዲራ የሚባል መስቀል ተሸክመው፤ ምን ያህል ጊዜ እንደተገረፉ፤ ምን ያህል ጊዜ እንደተወገዙ፤ ምን ያህል ጊዜ ቀራኒዮ ተራራ ላይ ወጥተው ለነፃነት ብለው በፋሽስት ምስማር እንደተቸነከሩ አየንበት፡፡

‹የጉለሌው ሠካራም› ውስጥ ተበጀ የተባለውን ገፀባህርይ የሚገልፅበት አንድ ዐረፍተ ነገር፤ ራሡ ተመስገን ገብሬን ይገልፀዋል ብዬ አምናለሁ፤ ‹የሕይወቱ ታሪክ ፍፁም ገድል ነው›

ተመስገን ገብሬ፤ በአክብሮት እንደሚያነሳው፤ የልጅነት መምህሩ፤ እንደ ኑሬ ነው ‹…ኑሬ እውር ነው፤ ግን ለተማሪዎች ሁሉ የሚያስደንቅ ብርሃን ነበር፡፡ እኛ ጭቃማ በሆነው በጠባቡ መንገድ መራነው፡፡ እርሱ ግን በተሻለው በእውቀት መንገድ መራን፡፡ ምሽት የለውም፤ ግን የሁላችን አባት ነበር፡፡ ወላጆቻችን ገንዘብ ስላልከፈሉት ይርበው ነበር፤ እና ግን ብዙ በሆነ ጊዜ ረሃብን ይረሣው ነበር….(ገፅ 21-ሕይወቴ)

ተመስገን ስለራሱ ሲፅፍ አፅድቶ እና አንፅቶ አይደለም፤ በ15 ዓመቱ ኮከብ እየቆጠረ፤ የጥንቆላ መጻሕፍት እያነበበ፤ ጉቦ እየተቀበለ፤ ራሱን ያስተዳድር እንደነበር ሲፅፍ፤ ግልፅነቱ እንጂ ችሎታው አይመስጠንም፡፡ ‹…ምንም እንኳን አሁን ድሆችን በጉቦ በማስጨነቅ ብጨክን፤ ምን መሆኑን ለማላውቀው አንድ ታላቅ ነገር ሰማዕት ለመሆን ከልጅነቴ አብሮኝ ምኞት አድጐአል› ይለናል-ራሱ፡፡

ይህቺ ከልጅነቱ ጀምሮ አብራው ያደገችው ምኞት ብዙ ዋጋ አስከፍላዋለች፤ ‹…ለታላቅ ተጋድሎ ይልቁንም ሌሎችን ለመታደግ ራሳቸውን ለመስዋዕትነት አሳልፈው ለመስጠት ታላቁን የእሳት ነበልባልና የተሳለውን ሰይፍ ለመገናኘት በመድፈር ባደረጉት ሌሎችን በማሰማው በሰማዕታት ታሪክ ደስ ብሎኝ ከእነርሱ እንደ አንዱ ለመሆን ተመኝቼ ነበር (ገፅ 41)› ብሎ የተጓዘበት መንገድ አሁን ስሙን እንዳነሳው ምክንያት ሆኖኛል፡፡

ተመስገን ተናጋሪ ነው፤ እሱና ወዳጆቹ ባቋቋሙት ማሕበር፤ በየቤተክርስቲያን ቅፅር ግቢ እየተገኘ፤ ስለሰማያዊ ሕይወት በሚነገርበት መድረክ፤ ስለምድራዊ ኑሮ በመተረክ፤ ብዙ አድናቂዎችን ቢያተርፍም፤ የእንግሊዝ ሰላይ ነው ተብሎ፤ በሚከተለው ሃይማኖት ሰበብ መወገዝ ሆኖ ነበር ዕጣ ፈንታው፤ ያደነቁት አናናቁት፤ ያከበሩት አዋረዱት፤ እሱና ጓደኛው በጃንሆይ ትዕዛዝ ከአደባባይ ራቁ ከመድረክ ወረዱ፤ ‹በሃገር ላይ ሁከት የሚሰሩ…› ስለመሆናቸው ተነግሮ አንደበታቸውን እንዲቆልፉ ተደረገ፡፡

ተመስገን፤ በጣሊያን ወረራ ጊዜ፤ ብዙ ተንገላትቷል፤ ወገኖቹ ተማርከው በውሃ ጥም ምክንያት ደም የተቀላቀለበት ውሃ ሲጠጡ አይቷል፤ በእሱ እና በወገኖቹ ላይ እየደረሰ ያለውን በደል ለጃንሆይ በሚፅፍላቸው ጊዜ፤ ጃንሆይ በስደት አገር በለንደን ሆነው ያለቅሱ እንደነበር ተፅፏል፤ ጣሊያን ድል ከሆነች በኋላ ግን፤ ሀገር የማስተዳደር አቅም ያላቸው ተብለው አንዳንድ አርበኞች ሲሾሙ እና ሲሸለሙ፤ ተመስገን ጃንሆይ ፊት ቀርቦ መሬት እንዲሰጡት እና የቡራኬው ተቋዳሽ እንዲሆን፤ በሹማምንት ግፊት ቢደረግበትም፤ ግብዣውን ሳይቀበል በመቅረቱ መንግስት ጥርስ ውስጥ ገባ፡፡

የሆነው ሆኖ፤ ‹ኒው ታይምስ ኤንድ ኢትዮጵያን ኒውስ› የሚል ጋዜጣ፤ ‹ኢትዮጵያን ከራሱ አብልጦ የሚወድ…. ስራዬ ከቶ በሕዝብ ዘንድ ይታወቅልኝ ባይ ያልሆነ… እግዚአብሔርንና ሰውን ለማገልገል የተፈጠረ… የተወደደ ባል እና አስተዋይ አባት› ብሎ የገለፀው ተመስገን ገብሬ፤ እነማን እንደሆኑ ያልታወቁ (የጃንሆይ ወዳጆች ወይም ሕዝቡን በዘበዛችሁት ብሎ ያጋለጣቸው ጠንቋዮች ወይም ሌሎች ሊሆኑ ይችላሉ) የተመረዘ ምግብ አብልተውት ሞተ፡፡

…ተመስገን ገብሬ ከርቀት ይኼ ነው፤ በቅርበት ለማወቅ ‹ሕይወቴ›ን ማንበብ ግድ ነው፡፡

እንደ ተመስገን ገብሬ ያሉ ሰዎች ጥቂቶች ናቸው፤ ተመስገን ገብሬዎች የምላቸው፤ እውነተኞችን ነው (እስካሁን ድረስ ይርጋ ዱባለዎችን ስፅፍ፤ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንሶችንና ሰለሞን ተካልኞችን ስፅፍ፤ ቴዲ አፍሮዎችን ስፅፍ፤ ራሴን ከትቼ እኔን አስገብቼ ነበር፤ በድክመታቸው ውስጥም ሆነ በብስለታቸው ውስጥ ራሴን አግኝቼው አውቃለሁና፤ በከፊልም ሆነ በጨረፍታ እነሱን የሚመስል ነገር በሕይወቴ ውስጥ አልፎ ያውቃልና፤ ስለተመስገን ገብሬዎች ስተርክ ግን፤ ራሴን ከዚህ ቅጥር አስወጣለሁ)

…እና ተመስገን ገብሬዎች፤ ለአገራቸው ደህንነት እና ለወገናቸው የተሻለ ሕይወት በብዙ ይደክማሉ፤ የድካማቸው ፍሬ ግን አይከፈላቸውም፤ ሹመት ሽልማት አይቸራቸውም፤ እንኳንስ አገር ውለታ ቆጥሮ፤ ‹አሁን እንደዚህ እንድኖር ደምና አጥንት ከከፈሉት ወገን አንዱ ነህ!› ሊለው ቀርቶ፤ በሥጋ እና በደም የሚዋለዱት እንኳን ‹ጠንቅቀው› አያውቁትም፤ ሕይወቱ በፍፁም ገድል የተሞላ መሆኑን አይመሰክሩም፡፡

ተመስገን ገብሬዎችን ተከትለው፤ እሱን ፊታውራሪ አድርገው ከኋላ የሚሰለፉ ሰዎች፤ ብዛታቸው ጥቂት ነው፤ ጥቂት ቢሆኑም ለአገራቸው ምሰሶዎች ናቸው፤ ምሰሶ እንደነበሩ የሚታወቁት ግን ዘግይቶ ነው፤ እድሜያቸው ከሄደ፤ የልጅ ልጆቻቸው ከመጡ፤ 50 እና 60ኛ የሙት ዓመታቸው ሲከበር… (የሀበሻ ጀብዱ ላይ ያነበብነው፤ የሰላሌ ኦሮሞ ተወላጅ የሆነው፤ ምኒልክ ይሙት ብሎ ለማንም ወደኋላ የማይመለሰው፤ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘንድ እንኳን የተፈራው አቢቹን ልብ ይሏል?)

ተመስገን ገብሬዎች መንገዳቸው የጨዋ ነው፤ አነጋገራቸው የጭምት ነው፤ በገድላት እና በድርሣናት ውስጥ እንደምናገኛቸው ሰማዕታት፤ ራሳቸውን ለተከበረ ነገር ያጩ ናቸው፤ ለተከታዮቻቸው ግድ አላቸው፤ የሆነ ሰው፤ የሆነ ቦታ ሆኖ፤ ለአርአያነት ሊመርጣቸው እንደሚችል ግምት አላቸው፤ ተከታዮቼ ወዴት ናችሁ ብለው ግን አይፈልጉም፤ የሚታመኑት ለሃሳባቸው ነው፡፡

ተመስገን ገብሬዎች አሟሟታቸው ሁሉ ምስጢራዊ ይሆናል- አንዳንድ ጊዜ፤ የሞቀ የደመቀ ስርዓተ ቀብር አይፈፀምላቸውም፤ ስለራሳቸው ገድል እና ስለስራቸው ድል የመዘመር አባዜ ስላልተፀናወታቸው፤ ስማቸው የተደበቀ ነው፤ በመጋረጃ የተከለለ፡፡ በተቀናቃኞቻቸው እጅ ነው የሕይወት ገመዳቸው የሚያጥረው፤ የቆሙለት እውነት ነው ጠላት የሚያፈራባቸው፡፡

…የሆነ ነገር ጀማሪዎች ናቸው፤ ‹ማንም ባልሄደበት መንገድ እንሂድ› ብለው ግን አይደለም ጉዞአቸውን የሚጀምሩት፤ እነሱ ስለፈለጉ፣ የሚያስፈልግ ስለመሰላቸው እና ልባቸው ስለፈቀደ አንድ አዲስ ሀሳብ አምጠው ይወልዳሉ፤ የወለዱትን የሃሳብ ፍሬ ግን አያዩትም…

እንደዚህ ዓይነት ሰዎች፤ ደግሜ እነግራችኋለሁ፤ በቁጥር ጥቂቶች ናቸው፤ አስፈላጊነታቸው የሚገባን ዘግይቶ ነው፤ ለመታየት በሚጓጉ እናሌላውን ዝቅ አድርገው ከፍታ ቦታ ላይ ለመቆም በሚታትሩ ሰዎች ይሸፈናሉ፤ አርበኝነታቸው ጦር ሜዳ ሄዶ ተጋድሎ ለመፈፀም ብቻ የሚዘከር አይደለም፤ አንደበታቸውም፤ ብዕራቸውም ለሃቅ የቆመ እና ለእውነት የተገራ ነው፡፡

እንዲህ ናቸው ተመስገን ገብሬዎች፡፡

## ርዕዮት ዓለሙ

# አለም አቀፍ ሽልማት ተሸለመች



በሽብርተኝነት ወንጀል ተከሳ አስራ አራት አመት ተፈርዶባት ከዚያም ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ባቀረበችው ይግባኝ የእስር ጊዜዋ ወደ አምስት አመታት የተቀነሰላት ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ ከአለም አቀፉ የሴቶች ሚዲያ ፋውንዴሽን (IWMF) ለጋዜጠኝነት ባሳየችው ቁርጠኝነት ረቡዕ ዕለት በተወካይዋ በኩል ሽልማቷን ተቀብላለች፡፡

በሽልማቱ ስነ-ስርዓት ወቅት ከቃሊቲ ማረሚያ ቤት የተላከ የእጅ ፅሁፏ የተነበበ ሲሆን ኤልያስ ወንድሙ የተባሉ በስደት ላይ ያሉ ጋዜጠኛ ርዕዮትን በመወከል ሽልማቷን ተቀብለዋል፡፡ በኤልያስ በተነበበው በዚሁ ፅሁፍ ላይ ርዕዮት ‹‹ነፃነትንና ዴሞክራሲን ለመጠየቅ አደባባይ የወጣ ህዝብ ላይ መተኮስ፣ ከገዢው ፓርቲ የተለየ አተያይ ስላላቸው ብቻ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችንና ጋዜጠኞችን ማሰር፣ የመናገር፣ የመሰብሰብና የፕሬስ ነፃነትን መከልከል፣ ሙስና እንዲሁም የአንድ ጎሳ የበላይነት›› የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ተጠቃሽ ችግሮች እንደሆኑ ገልፃለች፡፡

በመጨረሻም ‹‹የእኔ ታሪክ በነፃ አስተሳሰባቸው ምክንያት በእስር ላይ ያሉ በርካታ ኢትዮጵያውያንን ታሪክ ሊያሳያችሁ ይችላል፡፡ ›› ካለች በኋላ ‹‹እባካችሁ! ይህን ክፉ እውነታ ለመቀየር የተቻላችሁን ያህል ሞክሩ›› በማለት ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ ጥሪዋን አስተላልፋለች፡፡

ከፋውንዴሽኑ ጋር ቀድማ ባደረገችው ቃለ ምልልስ ‹‹የተሻለ ነገር ለመፍጠር አንድ ነገር ማበርከት አለብኝ ብዬ አምናለሁ፡፡ በኢትዮጵያ ኢ-ፍትሃዊነትና ጭቆና እስካለ ድረስ ይህንን በፅሁፎቼ ማጋለጥና መቃወሜን እቀጥላለሁ፡፡ አደጋ ቢኖረውም ለእውነት መቆም ግን ከመርሄ አንዱ ነው›› በማለት ገልፃ ነበር፡፡ አንድ የስራ ባልደረባዋ ከመታሰሯ በፊት በተደጋጋሚ የስልክ ማስፈራሪያ ይደርሳት እንደነበር ገልፆ ‹‹ርዕዮት በሳል የሚባሉና ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች መግለፅ የማይችሉትን ርዕሰ-ጉዳዮች ጭምር አንስታ ለመወያየት ብቁ ነበረች፡፡ ሌሎች የተንበረከኩለትን ተግዳሮቶች እስከዛሬ ድረስ ስትጋፈጥ ቆይታለች፡፡›› ሲል ተናግሯል፡፡

የአለም አቀፉ የሴቶች ሚዲያ ፋውንዴሽን የርዕዮት አለሙ ሽልማትን አስመልክቶ ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ ‹‹በእስሯ ወቅት ጓደኞቿን የምታጋልጥ ከሆነ እንደምትፈታ ቢነገራትም ፍቃደኛ አልሆነችም፡፡ በዚህም ምክንያት ለ13 ቀናት ያህል ለብቻዋ በጭለማ ቤት ውስጥ በመታሰር ተቀጥታለች፡፡ በቃሊቲ ማረሚያ ቤት በነበረችበት ወቅትም በጤናዋ ላይ እክል ገጥሟት ነበር፡፡ በሚያዚያ ወር አካባቢም ጡቶቿ ላይ በወጣ ዕጢ ምክንያት የቀዶ ጥገና አድርጋ ያለበቂ የማገገሚያ ጊዜ ወደ እስር ተመልሳለች›› ሲል ያሳለፈችውን መራራ ጊዜ አስታውሷል፡፡

በኢትዮጵያ መንግስት ላይ የፕሬስ አፈናን አስመልክቶ ተደጋጋሚ ወቀሳ ሲቀርብ ይስተዋላል፡፡ ሲፒጄ ኢትዮጵያን ከኤርትራ ቀጥሎ ብዛት ያላቸውን ጋዜጠኞችን በማሰር ከአፍሪካ በሁለተኛ ደረጃ ላይ አስቀምጧታል፡፡

## የርዕዮት መልዕክት ከቃሊቲ

በመጀመሪያ ለጥረቴና ለብርታቴ ሽልማት ላበረከተልኝ ለአለም አቀፉ የሴቶች ሚዲያ ፋውንዴሽን (IWMF) ተቋም አመራሮችና ሰራተኞች ታላቅ ምስጋና ለማቅረብ እፈልጋለሁ፡፡ ሁሌም ጠንካራ እርዳታቸውንና ማበረታቻቸው ላልተለየኝ ለዕጮኛዬ ስለሺ ሀጎስ፣ ለቤተሰቤና ለጓደኞቼም ከልብ የመነጨ አድናቆቴን እገልፃለሁ፡፡ በመቀጠልም ሀገሬ ስላለችበት ፖለቲካዊ ሁኔታና ስለመታሰሬ ምክንያት አንዳንድ ነገሮችን ለማለት እወዳለሁ፡፡

ፖለቲካዊ ንቃት ላይ ስደርስ የገዢው ፓርቲ ደጋፊ ወይም አባል መሆን በሰላም ለመኖርና ስራ ለማግኘት ቀዳሚ ተግባር መሆኑን ተረዳሁ፡፡ ማንም ቢሆን ከዚህ ማዕቀፍ ለመውጣት ቢሞክር እሱ ወይም እሷ ቅጣት ይጠብቃቸዋል፡፡ በክፉ ስራዎቹ ምክንያት ኢህአዴግን ከተቃወሙት መካከል አንዷ እኔ ነኝ፡፡

ነፃነትንና ዴሞክራሲን ለመጠየቅ አደባባይ የወጣ ህዝብ ላይ መተኮስ፣ ከገዢው ፓርቲ የተለየ አተያይ ስላላቸው ብቻ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችንና ጋዜጠኞችን ማሰር፣ የመናገር፣ የመሰብሰብና የፕሬስ ነፃነትን መከልከል፣ ሙስና እንዲሁም የአንድ ጎሳ የበላይነት ከመንግስታችን ክፉ ስራዎች መካከል ተጠቃሾች ናቸው፡፡

እነኚህን መጥፎ እውነታዎች ለመለወጥ ኃላፊነት እንደሚሰማው ጋዜጠኛ ከላይ የጠቀስኳቸውን ኢ-ፍትሃዊነትን የሚቃወሙ መጣጥፎችን አዘጋጅ ነበር፡፡

ይሄን በማደርግበት ወቅት ድፍረቴ ዋጋ እንደሚያስከፍለኝ አውቅ ነበር፡፡ ያንንም ለመቀበል ዝግጁ ነበርኩ፡፡ ምክንያቱም ጋዜጠኝነት ራሴን ለመስጠት ፍቃደኛ የሆንኩለት ሞያ ነውና፡፡

ለኢህአዴግ፤ ጋዜጠኞች የገዢው ፓርቲ የፕሮፓጋንዳ ማሽኖች ብቻ መሆን እንዳለባቸው አውቃለሁ፡፡

ለዚያም ነው የጭቁኖችን እውነት የሚገልፁ በርካታ መጣጥፎችን የፃፍኩት፡፡ በዚህ ምክንያት ከብዙ ችግሮች ጋር የተጋፈጥኩ ቢሆንም ሁልጊዜም ለመርሄና ለሙያዬ በጥንካሬ ቆሜያለሁ፡፡

በመጨረሻም የአለም አቀፉ ማህበረሰብ እውነተኛዋን ኢትዮጵያ እንዲረዳ ለመጠየቅ እወዳለሁ፡ ፡ እውነተኛይቱ ኢትዮጵያ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥርን እንደምትመለከቷት ወይም የመንግስት ባለስልጣናት ሲያወሩ እንደምትሰሙት አይደለችም፡፡

በእውነተኛዋ ኢትዮጵያ በርካታ ጭቆናዎች እየደረሱ ነው፡፡ የእኔ ታሪክ በነፃ አስተሳሰባቸው ምክንያት በእስር ላይ ያሉ በርካታ ኢትዮጵያውያንን ታሪክ ሊያሳያችሁ ይችላል፡፡

እባካችሁ! ይህን ክፉ እውነታ ለመቀየር የቻላችሁትን ያህል ሞክሩ፡፡

አመሰግናለሁ
ርዕዮት ዓለሙ

# በጠለፋ ስሌት መቋቋሙን. . .

ከ ገፅ 11 የዞረ

ፓትርያርክ ስለመምረጥ የምትማከርበት/የምትላመንበት ነው፡፡ ታዲያ ይህ መጽሐፍ በእዚህ ወቅት የህትመት ብርሃን ማየቱ አንድምታዊ ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል ማሰብ ይቻላል፡፡ ወቅቱ የቤተክህነት አስተዳደርን አስመልክቶ ብዙ የሚባልበት ነው፡፡ የሰሞኑ መጽሔቶችና ጋዜጦች አቀራረብ የሚጠቁመው ይህንኑ እውነት ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለውጥ ቢያሳይም ለረዥም ጊዜ በማንኛውም ቤተክርስቲያን አስተዳደራዊ ጉዳይ እንደማይገባ ሲናገር የነበረው ማህበረ ቅዱሳንም ስለፐትርክናው ራሱን የቻለ ልዩ እትም በማሳተም ሃሳብ ማንሸራሸር መጀመሩም የዚሁ አካል ነው፡፡ የደረጀ ‹‹460 ቀናት...› መውጣቱንም ሌሎች ትርጓሜዎች እንደሚኖሩት ብናስብም፤ ‹‹አንድም›› ብለን ከዚሁ ሁነት ጋር ማገናኘት እንችላለን ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ በእርግጥ ስለቤተክህነቱ የአስተዳደር ችግር እንድናስብ የማድረጉን ያህል መፍትሔ ከመጠቆም አንጻር ግን ብዙ የሚያስኬደን አይመስልም፡፡ ቢያንስ ግን ስለርዕሰ ጉዳዩ ለመነጋገር እድል በመፍጠር ግን ጸሐፊው ለዚህ ዓምድ አንባቢዎች በአጠቃላይና ለእኔ በግል ጠቅመውኛል፡፡ በእርግጥ ይሄ ችግር የዚህ መጽሐፍ ብቻ ሳይሆን እስካሁን ያየኋቸው የሌሎቹም ነው፡፡ የዚህ ዋና ምክንያቱ ደግሞ የቤተክህነት አስተዳደር ችግርን በተናጠል የማየት አዙሪት ነው፡፡ የ1990/1ዱ ኮሚሽን በሁለት ክፍል ያቀረበው ጠንካራ ሪፖርት እንኳን (ክፍል አንድ ሪፖርት በሐምሌ 10 ቀን 1990 ዓም (53 ገጽ) ጥቅምት 23 ቀን 1991 ክፍል 2 (31 ገጽ)) ዋናው ፍሬ ነገሩን ለመንካት ሳይደፍር ቀርቷል፡፡ የቤተክህነት መተዳደሪያ ሕግ ለአመራሩ ብቃት የማያስገኙለት ጥገናዊ ለውጦች ናቸው፡፡ በቤተክህነቱ አካባቢ ጉዳዩን ፊት ለፊት መናገር ፅዩፍ መስሎ ታየ እንጂ፤ የፈለጋቸውን በሚናገሩት በእንደአቦይ ስብሐት ዓይነቱ ፖለቲከኛ ግን ‹‹የቤተክርስቲያን አባቶች ከመንግሥት ትከሻ አልወርድ አሉ›› ዓይነት ንግግር በአደባባይ ተነግሮ ሲዘገብ ከርሟል፡፡ ንግግሩን የታዘቡት ፕ/ር መስፍን ወልደማርያምም በእኔ ትሁት አገላለጽ ‹‹የዚህ ምክንያቱ እናንተው ናችሁ›› ብለው ቢሟገቱም፡፡ እንደገባኝ የፕ/ር ሃሳብ የቤተክህነት አስተዳደርን ያልፈሰፈሰው ፖለቲካዊ አውድ (የሚያንዘረዝረው ነጻ ተቋማት ስጋት ከብቃትና መንፈሳዊ ልእልና ይልቅ ታማኝነትን መስፈርት በማድረግ የተቻለውን ያህል አመራሩን የመቆጣጠር አዝማሚያ ማሳየቱና ከውስጥ የሚነሱ ማንኛቸውንም የመስተካከል እንቅስቃሴ ታማኙን ከሚያሳጣው እንቅስቃሴ ጋር አስተሳስሮ ማየቱ) ነው፡፡ በአገሪቱ ያሉ የእምነት ተቋማት አመራሮች ስላሉበት ክስረት ደረጃ አስረጂ መጥራት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ መንግሥት እንደውትወታው ቢሆን ከሃይማኖት ጋር ያለውን ተዛምዶ በዓለም በታወቁ ሞዴሎች ደርዞ ሁለቱም በየራሳቸው ከባቢ የሚሠሩትን በመሥራት አገር ማሳደግ ይችሉ ነበር፡፡ አገሪቱና ገዢው ቡድን አሁን ያሉበት ተፈጥሮ ይሄን ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ያስመስለዋል፡፡ ለዚህ ነው ከዚያው ከቤተክህነት አካባቢ የሚንሸራሸሩ በድርጊት የሚገለጹ መፍትሄዎችን እንደቅርብ ጊዜ ዓላማ ተደርገው የሚወሰዱ ሃሳቦችን እንድንፈትሽ ግድ የሚሉን፡፡ በቀላሉ ማግኘት ከቻልኳቸው አባ ገብረመድኅን ከበደን በ2002 እና ዓምና በ2004 ዓም ያሳተሟቸው ‹‹ከሕግ ሥር የሆኑት ሁሉ ከርግማን በታች ናቸው›› ና ‹‹ሕጋዊነት የቀበሮ እምነት ሁለተኛ መጽሐፍ›› በርዕሰ ጉዳዩ ላይ የጨመቅሁት አሳብ ‹‹ጳጳሳት ፓትርያርኩን ወደሥርዓት ሊያመጡ ይችላሉ፣ ይገባቸዋልም፡፡ ያን ለማድረግ ግን ተከፋይ ደሞዝተኛ መሆን የለባቸውም›› የሚል ነው፡፡ ሐምሌ 2004 ዓም በገበያ ላይ ውሎ ቤተክህነት ውስጥ ምርቃቱ እንዳይደረግለት በመከልከሉ ምክንያት ነጻነት ተስፋዬ በ‹ዕንቁ› መጽሔት አስተያየት የሰጠበት የካህሳይ ገብረእግዚአብሔር ‹‹ብፁዓን እነማን ናቸው?›› በሚል ርዕስ ወደገበያ የገባ መጽሐፍ ያነሳው ሃሳብም ቃሉን ከመበየን ባለፈ ‹ብፁዓኑ በመንፈስ ልእልና እንዳያድጉ ያደረጓቸውን እንከኖች በመንቀስ ከእነርሱ እንዲጠበቁ የሚረዱ ሕጎችን እንዲጸድቁ መወትወት ነው፡፡›› አስተውሉ የእነዚህ ሁለት መጻሕፍት መነሻ እሳቤ የጋሽ ደረጀን ‹‹አባቶች ችግር የለባቸውም›› የሚል አስተሳሰብ የሚጻረሩና ማስረጃ ሊቆጠርላቸው የሚችሉ ናቸው፡፡ ደሞዝና ሀብት ንብረት ማፍራት የመንፈስ ልእልናቸውን እንደፈተኑ የሚያሳዩ ናቸውና፡፡ በእነዚህ መጻህፍት የተመከሩት ሀሳቦች ግን ለጳጳሳቱ ቀላል እንዳልሆነ መገመት ይቻላል፡፡ ለካህሳይ ገብረእግዚአብሄር መጽሐፍ ምርቃት አዳራሽ መከልከሉም ይሄን ሀሳባቸውን መቃወም ሳይሆን አይቀርም መባሉ ለዚህ መፍትሔ ተግባራዊነት አጠያያቂ ያደርገዋል፡፡ ፕ/ር ታደሰ ታምራት የዛሬ 15 ዓመት ከጦቢያ መጽሔት ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ ‹‹መቼም ምዕመኑ የቤተክህነት አስተዳዳሪዎች የሚራኮቱበትን ገንዘብ አልሰጥ ያለ እንደሆነ ነው ጉዱ፡፡ ደግነቱ በዓመት ሁለቴና ሶስቴ በአደባባይ ባዓላትና በንግስ ቀናት ነጭ ለብሶ በቀለም ‹ያማረ› የበዓላት አከባበር ሥርዓት ካሳየና ቁጥሩ ብዙ እንደሆነ ካስገነዘበ የሚበቃው የሚመስለው ምዕመን ይሄን ለማድረግ አለመፈለጉ በጀን፡፡›› ለዚህ ይመስላል በቤተክርስቲያኗ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ መልኩ የተፈጠረው የአስተዳደር ክስረት በቶሎ የሚቋጭ ለመሆኑ መናገር የሚከብደው፡፡

## የቀናቱ ቆይታ ትሩፋቶች

ጸሐፊው በታሪክ አጋጣሚ በተገኙበት በመንበረ ፓትርያርኩ ቅጽር ግቢ ውስጥ በቆዩባቸው 1 ኣመት ከ50 ቀናት አካባቢ የታዘቡትን በስላቅ፣ በትዝብት፣ በትችትና በአድናቆት ያስጎበኙናል፡፡ ይህ ክፍል ጸሐፊው ራሳቸውም በግልጽ የይዘቱ አካል ሲሆኑ አንዳንዴ ወገንተኝነት የሚያሳዩበት፣ ፍልስፍናቸው የሚንጸባረቅበት/የሚሞገትበት፣ ከማጣራት ሂደት ባለፈ አንዳንድ ‹ምክር› ሲሰጡ የሚታዩበትና ያልተገቡ ድርጊቶችን ያሏቸውን የተቹባቸውና ለቤተክርስቲያን አስተዳደር መሻሻል ሁሉን አሳማኝ መፍትሄ ለመጠቆም የሞከሩባቸው ናቸው፡፡ እነርሱም ‹ያልተባረከው የእርቅ ሙከራ› ስለጳጳሳቱ ስነልቦና፣ ‹ደጀጠኚው› በየእለቱ ወደቅጽሩ ስለሚመጣውና የሚስተናገደው ባለ ጉዳይ ብዛትና ሥርዓት ማጣት፤ ‹ቅዱስ ፓትሪያሪኩን እንዳየኋቸው›፣ ‹ቢሮዎቹና አንደኛው ወንበር› እና ‹ገጽታ ግንባታውና የጀርባ ምስጢር› ስለፓትሪያሪኩ ባህሪያት እና ፍላጎት፤ ‹አንደኛው ተከሳሽ› ስለአቡነሳሙኤል ባህሪይ የጠቀሱበት፤ ‹‹የሠራተኛ ቅጥር እና ምደባ›፣ ‹ካዛብላንካና ሞኖሮቪያ›፣ ‹ኮሚሽኑና ኮሚሽነሮቹ›፣ ‹አዲሱ የለውጥ አመራር እና ፍጻሜው›፤ ‹የቤተክህነት አስተዳደር ስለለውጥ ያለውን ተግዳሮት›፤ ‹በጨለማ እና በብርሃን የሚንቀሳቀሰው ጎራ› እና ‹ውክልና ያላቸውና የሌላቸው መዛግብት አቅራቢዎች› በቤተክህነቱ ንትርክና አሠራር የተፈጠሩ ቡድኖችና አካሄዳቸው የሚያትቱ ናቸው፡፡

በመጨረሻ ጸሐፊውን ለዚህ አስተያየት መነሻ የሆነንን መጽሐፍ ስላደረሱን እያመሰገንኩ፤ የቤተክህነቱ አስተዳደር ይህንን የከሰረ መንገዱን የሚያስታርቅ እርምጃ እንዲወስድ ‹እመክራለሁ›፡፡

# ኬንያን በድርበቡ...

ከ ገፅ 7 የዞረ

"እኔ ይሳካል ራዕዩ ድራፍት ቤት ነኝ። አዝገኝ እጠብቅሃለሁ ቶሎ ና!"
"እሺ ባይ!"
ስልኩ ተዘጋ። እንግዳው ነገሩ ሁሉ እንግዳ ሆነበት። "የጉድ አገር ገንፎ እያደር ይፋጃል" የሚለው ተረት ድንገት ትዝ አለው። ወድያውም ጠየቀው።
<<ኤርፖርቱ መለስ ኤርፖርት ተባለ እንዴ!?>>
<<አልሰማህም እንዴ!?>>
<<እሺ ይሁን መስቀል አደባባይ መቼ ነው መለስ አደባባይ የተባለው!?>>
<<ቆየ እኮ!>>
ግራ ገባው። ወደ ስታድየም ሲቃረቡ ግርግር ነገር አየ። <<ምንድነው?>> ብሎ ጠየቀ።
"ዛሬ እግር ኳስ ጨዋታ ነበር።" አለው። ሌላ አይነት ጨዋታ መምጣቱ ደስ አለው። <<ይገርምሀል ድሮ ቀንደኛ የስታድየም ታዳሚ ነበርኩ>> ሲል ትዝታው በአይኑ እየመጣ ነገረው። "የማን ደጋፊ ነበርክ?" ብሎ ጠይቆት መልሱንም ሳይጠብቅ "እኔ የመለስ ቡና ደጋፊ ነኝ። ዛሬ መለስ ቡና ከመለስ ጊዮርጊስ ነበር ጨዋታው፤ ስራ ባይኖረኝ አልቀርም ነበር። ይገርምሃል የመለስ ፕሪምየር ሊግ ጨዋታ ገና መጀመሩ ነው!"
እንግዳው በድጋሚ እንግዳ ስሜት ተሰማው። አይኑ እንባ አቀረረ። "ምንድነው ጉዱ!?" ሲል ጠየቀ። የታክሲ ሹፌሩ ገብቶታል። "ያው ራዕያቸውን ለማስፈፀም ግድ ነው ተብሏል" አለው።
እንግዳው ዛሬን ሆቴል አድሮ ነገ ወደ እናቱ ሀገር ሀዋሳ ያመራል። ሁሉ ነገር በመለስ ተሰይሞ አንዱን ከአንዱ ለመለየት የምንቸገርበት ደረጃ ላይ እንዳንደርስ ብቻ! ሲል በሆዱ እያሰበ።
አዲሳባ ስታድየምን ገርመም ሲያደርገው "መለስ አዲሳባ ስታድየም!" የሚል በጉልህ ተፅፎ ተመለከተ። ሰዎቹ ምን ሆነዋል...!?
"ለማንኛውም እስቲ ራስ ሆቴል አድርሰኝ!" አለው። ለማረፍ ያሰበበት ሆቴል ነው።
ዘወር እንዳሉ ደረሱ "እንኳን ወደ ራስ መለስ ሆቴል በሰላም መጡ!" ተብሎ የተፃፈ ተመለከተ። ግራ እየገባው ለባለታክሲው የተነጋገሩትን ሂሳብ ከፋሎ ወረደ።

# አኬልዳማው ፍትህ

የወ/መ/ቁ-112546
የማ/መ/ቁ-02075/04
ወንጀል- ሽብርተኝነት
የፍርድ ልክ -18 ዓመታት
እና 5 ዓመታት የሕዝባዊ መብቶች እግድ
ነሐሴ 16 ቀን 2004 ዓ.ም.



ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ይግባኝ ሰሚ ወንጀል ችሎት
አዲስ አበባ፤

ይግባኝ ባይ፡- እስክንድር ነጋ ፈንታ
መልስ ሰጪ፡- ዐቃቤ ሕግ

## በወንጀለኛ /መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 189/1 መሠረት የቀረበ ይግባኝ፤

ሀ. ይህ የይግባኝ ቅሬታ የቀረበው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በሰጠው የፍርድ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ነው፤

ለ. የቅሬታው አቀራረብ ሕጉ በሚያዘው 15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ሲሆን፤ የውሳኔው ግልባጭ ባለሁበት አ/አ ማረሚያ ቤት በኩል ሐምሌ 25 ቀን 2004 ዓ.ም. ደርሶኛል፤

ሐ. ይህ ይግባኝ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 187/1 እና 2 ሥር ያለውን የሕግ ድንጋጌ እና ጊዜ የጠበቀ ነው፤

መ. የጠቅላይ ፍ/ቤት የቀረበውን ይግባኝ መርምሮ የመወሰን ሥልጣን አለው።

የጉዳዩ ፍሬ ነገር በአጭሩ

ዐቃቤ ሕግ በ19/03/04 ዓ.ም. አሻሽሎ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ ካቀረባቸው 6 ክሶች 3ቱ ብቻ በእኔ 7ኛው ተከሳሽ ላይ የቀረቡ ናቸው። እነዚህም፡-

1ኛ. ክስ በ1996 ዓ.ም. የወጣውን የኢ/ፌ/ዲ/ሪን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32/1/ሀ፣ 38/1 እና ስለፀረ-ሽብርተኝነት የወጣውን አዋጅ 625/2001 አንቀፅ 4 እና 3/1/2፣ 4 እና 6 ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን፣ ከአሸባሪው ግንቦት 7 ከፍተኛው አመራሮች ጋር በህቡእ ግንኙነት በመፍጠር፣ ሁከትና ብጥብጥ ለመፍጠር ስብሰባ በማድረግ፣ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ መስማማት፣ የግንቦት 7 ልሣን ለሆነው ኢሣት መረጃ መሥጠት፣ ቀስቃሽ ፅሁፎችን በመፃፍና በማሰራጨት፤

2ኛ. ክስ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ ቁጥር 652/2001 አንቀጽ 7/2 የተመለከተውን በመተላለፍ የግንቦት 7 የሀገር ውስጥ ወኪል በመሆን (ከ/ፍ/ቤ አንቀፁን ወደ 652/2001 አንቀፅ 7/1 ለውጦታል።)

4ኛ. ክስ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32/1/ሀ እና 248/ለ ሥር የተመለከተውን በመተላለፍ የኤርትራ መንግስት የሽብር አጀንዳውን ለማስፈፀም እንዲመቸውና እንዲቀናጅ በመርዳት ከፍ ያለ ክህደት ወንጀል በመፈፀም የሚሉት ናቸው።

በችሎት ቀርቤ የክስ ቻርጅ የደረሰኝ ሲሆን፣ የእምነት ክህደት ተጠይቄ ወንጀሉን አልፈፀምኩም፣ ጥፋተኛም አይደለሁም በማለት ቃሌን ሰጥቻለሁ፡፡



በቀጣይነትም ዐቃቤ ሕግ የሰነድና የቪዲዮ ማስረጃዎቼ ናቸው ያለውን ያቀረበ ሲሆን፤ አንድ የሰው ምስክርም አቅርቧል። የቀረቡት ማስረጃዎች የዐቃቤ ሕግን ክስ ማስረዳት እንዳልቻሉ ሀገር የሚያውቀው ሃቅ ቢሆንም፣ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በጭፍን ጥፋተኛ ብሎኛል። ከፍተኛው ፍርድ ቤት (ከዚህ በኋላ ከ/ፍ/ቤ) ሀገራዊ እውቀትና ልምድ ገና ያልዳበረበትን የፀረ-ሽብርተኝነት ሕግ 652/2001 አንቀፅ 23 በተሳሳተ መንገድ ከመተርጐሙም ባሻገር የላባን ያህል ክብደት ያለው አንድ ማስረጃ እንኳን ሳይዝ ጥፋተኛ ለማለት እንደ ሽፋን ተጠቅሞበታል።

የይግባኝ ቅሬታው የቀረበበት ዋና ምክንያት

ጥፋተኝነቱን በተመለከተ

ከፍተኛው ፍ/ቤት ሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም. የጥፋተኝነት ብይን ሰጥቷል፡፡ የዚህ ብይን ባለ68 ገፅ ግልባጭ በ25/11/04 ደርሶኛል። በብይኑ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ስህተቶች በገፁ ቅደም ተከተል ከዚህ በታች እዘረዝራቸዋለሁ።

1. <u>በጥፋተኝነት ብይን ውስጥ ያሉ ስህተቶች</u>

በብይኑ ግልባጭ (የሰኔ 20 ቀን 2004 ዓ.ም. ግልባጭ) ገፅ 19 ላይ በ28ኛው መስመር ላይ 25ኛው የዐቃቤ ሕግ ምስክር አቶ ዘመኑ ሞላ በሰጡት ምስክርነት ‹‹…7ኛ ተከሳሽ የፋይናንስ ችግር ካለ ከአንተ 20,000 ብር፣ ከእሱም 20,000 ብር፣ ከእኔም 20,000 ብር፣ እረዳችኋለሁ። በእኛ የተጀመረው ሰላማዊ ሰልፍ ይቀጥል ብለዋል፡፡ 7ኛ ተከሳሽ ከአቶ ፋሲል ጋር በስልክ እንደሚገናኙና በፋይናንስ እንደሚረዳው ነግሮኛል፤›› ብለው መስክረዋል የተባለው ሐሰት ነው።

አቶ ዘመኑ ለዐቃቤ ሕግ ምሥክር ሆነው ሲቀርቡ የሰጡት ምሥክርነት፡-

ሀ. ባቀረብሁላቸው መስቀለኛ ጥያቄ፣ ፓርቲያቸው (መኢዴፓ) ላዘጋጀው ሰላማዊ ሰልፍ ገንዘብ እረዳችኋለሁ ብዬ ቃል እንዳልገባሁ በጠራ ቋንቋ ተናግረዋል።

ለ. ‹‹…7ኛ ተከሳሽ ከአቶ ፋሲል ጋር በስልክ እንደሚገናኙና በፋይናንስ እንደሚረዳው ነግሮኛል፤›› ብለው አቶ ዘመኑ ፈፅመው አልተናገሩም፡፡

የተከበረው ጠቅላይ ፍ/ቤት እውነታውን ከኦዲዮ እንዲያረጋግጥ እጠይቃለሁ።

በእስር ላይ የነበሩት አቶ ዘመኑ ለዐቃቤ ሕግ በምሥክርነት ቢቀርቡም፣ ለእኔም በመከላከያ ምሥክርነት ተጠርተው ቃላቸውን ሰጥተዋል። በሂደት እንደሚታየው፣ እዚያም የሰጡት ምሥክርነት እንዲሁ ተዛብቶ ተመዝግቧል።

2. <u>በጥፋተኝነት ብይን ውስጥ ያሉ ስህተቶች</u>

በብይኑ ግልባጭ ገፅ 20 ላይ (አሁንም አቶ ዘመኑ ሰጡ በተባለው ምሥክርነት) በ25ኛው መሥመር ‹‹…ወደ ሱዳን ከሄዱት 7 ሰዎች አንዱ ደወለልኝ…›› ከሚለው አንስቶ …‹‹26ኛው የዐቃቤ ሕግ ምሥክር የሆኑት አቶ አሳምነው ብርሃኑ…›› የሚለው ድረስ ያሉት 19 መሥመሮች ያለቦታቸው የገቡ ናቸው።

በእነዚህ 19 መሥመሮች የሰፈሩትን ቃላት ፈፅመው አልተናገሯቸውም። አቶ ዘመኑ የሰጧቸው የምሥክርነት ቃላት ተገልብጠው ከፋይሉ ጋር ተያይዘዋል። በእነዚህ ግልባጮች ከላይ የተጠቀሱት 19 መሥመሮች ፈፅመው እንደሌሉ ማየት ይቻላል። ሆኖም ከፋይሉ ጋር የተያያዙት እነዚህ ግልባጮች እኔን ተከሳሹን በሚጐዳ መልኩ ብዙ ስህተቶች ያለባቸው ስለሆኑ፣ እንደዋቢ ለመቆጠር የሚበቁ አይደሉም፡፡ የተከበረው ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምንም እምነት እንዳይጥልባቸው በጥብቅ አሳስባለሁ።

የዐቃቤ ሕግም ሆነ የመከላከያ ምሥክሮች በግልፅ ችሎት ቀርበው በምህላ የሚሰጧቸው የምሥክርነት ቃላት፤ ከሕግ አኳያ ከመመዘናቸው በፊት በትክክል ተመዝግበው መቅረብ እንዳለባቸው አሌ የሚባል ሐቅ አይደለም። የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግን ማህተሙን እያሳረፈ የሚሰጣቸው የእነዚህ ምስክሮች ግልባጮች ትክክለኛ መሆናቸውን የማረጋገጥ የሕግ፣ የሙያና የሞራል ግዴታ አልተወጣም። የዚህ አንድምታ ደግሞ፣ ምንም እንኳን ለውሳኔው እንደብቸኛ ምክንያት ሊቀርብ ባይችልም፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ የተዛቡ የምስክሮች ግልባጮችን መሰረት ያደረገ መሆኑ ነው።

አቶ ዘመኑ ዐቃቤ ሕግ ያቀረበብኝ ብቸኛው የሰው ምሥክር እንደመሆናቸው መጠን ቃላቸው በትክክል መቅረቡና አለመቅረቡ ሚዛን የሚደፋ ትርጉም አለው፡፡ ይህን ጥሬ ሐቅ ከማስቀመጥ ባሻገር፣ በመላ-ምቶች ዙሪያ በመዳከር (Conspiracy theories entertain በማድረግ) የፍርድ ቤቱን ውድ ጊዜ ማባከን አልፈልግም፤ አይጠቅምም፡፡ እውነቱን ፈልፍሎ የማውጣት ኃላፊነት ግን በዚህ የተከበረ ጠቅላይ ፍ/ቤት ትከሻ ላይ እንዳረፈ

ይሰማኛል፡፡

3. <u>በጥፋተኝነት ብይን ውስጥ ያሉ ስህተቶች</u>

በብይኑ ገፅ 38 ላይ በ14ኛው *መሥመር* ላይ ‹‹…ይህን ስልፍ ካሰባችሁበት አድርጉት፡፡ ግን ሌሎች ጣልቃ እንዳይገቡባችሁ፡፡ በተለዋጭ ካሉ ድርጅቶች ጋር በፋይናንስና በምንም እንዳትገናኙ፡፡ ቢቸግራችሁ እንኳን ሼር አድርገን፣ አዋጥተን ለሰላማዊ ሰልፍ ብሮሸር ለአንዳንድ ነገር እናውላለን፡፡ ከማንም ኃይል ጋር ግንኙነት እንዳታደርጉ ብርም እንዳትቀበሉ የሚል ምክር ሰጥቶናል…›› በማለት 2ኛ መከላከያ ምስክሮች አቶ ዘመኑ ሞላ ከሰጡት ሰፋ ያለ ምሥክርነት ተጨምቆ ለምዘና ተቀምጧል፡፡

ሆኖም፣ ‹‹…በተለዋጭ ካሉ ድርጅቶች ጋር በፋይናንስ በምንም እንዳትገናኙ›› ተብሎ የተመዘገበው ፍፁም ስህተት ነው፡፡ አቶ ዘመኑ ጥርት ባለ አማርኛ የመሰከሩት፣ ‹‹…ውጭ ካሉ ድርጅቶች በፋይናንስና በምንም እንዳትገናኙ ብዬ መምከሬን ነው፡፡ ውጭ ካሉት ድርጅቶች መካከል ደግሞ አንዱ ግንቦት መሆኑን ድፍን ሀገር የሚያውቀው ሐቅ ነው፡፡

የሥር ፍ/ቤት ምሥክርነቱን አድበስብሶ ለማለፍ ቢሞክርም፣ አቶ ዘመኑ የመሰከሩት በጣይቱ ሆቴል ስላደረግነው ውይይት ሲሆን፤ 2 ፍሬ ነገሮችን ለፍ/ቤቱም፣ ለዐቃቤ ሕግም፣ ለእኛ ለተከሳሾችም፣ በፍርድ ቤት ውስጥ ለነበረው ታዳሚም በግልፅ ቋንቋ አስመዝግበዋል፡፡ እነዚህም፡-

1. በመስከረም ወር መኢዴፓ የጠራውን ሰልፍ እንዲሰርዙ መምከሬን (እንደ ክሱ ከሆነ ግንቦት 7 ከመጋረጃ ጀርባ ሆኖ የሚያስተባብረው ሰልፍ ነው፡፡)

2. ውጭ ካሉ ድርጅቶች ገንዘብ እንዳይቀበሉና ምንም ዓይነት ግንኙነት እንዳይመሰርቱ መምከሬ ናቸው፡፡

የተከበረው ጠ/ፍ/ቤት የአቶ ዘመኑን ምሥክርነት ከመጋቢት 19 ቀን 2004 ዓ.ም. የችሎት ውሎ ግልባጭና ከካሴት ቁጥር 7 ያገኘዋል፡፡ (ግልባጩ መሰረታዊ ስህተቶች ያሉበት ስለሆነ ግን፣ ካሴቱ እንዲደመጥ እጠይቃለሁ፡፡)

ከፍተኛው ፍርድ ቤት የአቶ ዘመኑን ምሥክርነት በማድበስበስ፣ በማቃለልና ቃላትን በመቀናነስ ከእውነታው ለመሸሽ ከፍተኛ ጥረት ማድረጉ በግልፅ ይታያል፡፡ አስቀድሞ ተፈርዶብኛል የምለውም ለዚህ ነው፡፡

<u>4 በጥፋተኝነት ብይን ውስጥ ያሉ ስህተቶች</u>

በብይኑ ገፅ 38 ላይ በ28ኛው *መሥመር* ላይ …‹‹ተከሳሽ (እስክንድር ነጋ) በስብሰባው ላይ (በአንድነት ቢሮ) ንግግር ያደረገ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላማዊ እና ህጋዊ የፖለቲካ ትግል እና እንቅስቃሴ ብቻ ሊዳብር እንደሚገባ፣ እኛ (መኢዴፓ) ትናንሽ ፓርቲዎች ስለሆንን የጠራነውን ሰልፍ እንድናቋርጥ ተቃውሟል…›› በማለት 3ኛ መከላከያ ምሥክሬ አቶ ክንፈሚካኤል ደበበ ከሰጡት ሰፋ ያለ ምሥክርነት ለምዘና ተጨምቆ ተቀምጧል፡፡

ሆኖም፤ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ምሥክርነቱን ሸፋፍኖ ሊያልፈው ቢሞክርም፣ አቶ ክንፈሚካኤል ግን በማያሻማ ቋንቋ ‹‹…የእኛ ፓርቲ (መኢዴፓ) የጠራውን ስብሰባ (ሠልፍ) ተቃውሞታል፡፡ በዛ (ህዝባዊ) ስብሰባ (በአንድነት ጽ/ቤት) ላይ፡፡ ቪዲዮው ላይ መታየት ይችላል፣›› ብለው መስክረዋል፡፡ በካሴት ቁጥር 7 ላይ ምስክርነታቸው ሊደመጥ ይችላል፡፡

የዚህ አንድምታ ደግሞ (የሥር ፍ/ቤትን እንደ እሬት ቢመረውም)፣ የግንቦት 7 አባል ብሆን ኖሮ፣ ለሕዝብ ንግግር ለማድረግ አጋጣሚውን ሳገኝ ግንቦት 7 በጉን እያስተባበረ ያለውን ሰላማዊ ሰልፍ ልቃወምና ላሰናክል የምችልበት ቀዳዳ ሊኖር የማይችል መሆኑ ነው፡፡ ግንቦት 7 የአዲስ አበባን ሕዝብ በአዳራሽ እየሰበሰበ ለማነጋገር በየነጋታው የሚያገኘው ዕድል አይደለም፡፡ እንዲያውም፣ እንደ ልብወለዱ ውንጀላ ከሆነ፣ ይህ ብቸኛው አጋጣሚ መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ዕድሉ ሲገኝ፣ በስብሰባው ላይ የተገኙትና በክሱ የግንቦት 7 ወኪል ናቸው የተባሉት አቶ ክንፈሚካኤል ሰልፉን በመደገፍ ሌላኛው የግንቦት 7 ወኪል የተባልሁት እኔ ደግሞ ሰልፉን በመቃወም የተምታታ ሀሳብ የሚያራምድበት መድረክ እንደማይሆን ለመገመት ብዙም አያዳግትም፡፡ በዚህ ደረጃ የተዝረከረከ ድርጅት ነው ከተባለ ደግሞ፣ ክስ ይበዛበታል፡፡

ይህ የህፃናት ስብስብ እንጂ የተወሳሰበ የሽብርተኝነት ወንጀል ማቀናበር የሚችል ድርጅት አይደለም፡፡

<u>5 በጥፋተኝነት ብይን ውስጥ ያሉ ስህተቶች</u>

በብይኑ ግልባጭ ገፅ 39 ላይ በ8ኛው *መሥመር* ላይ 4ኛ መከላከያ ምሥክር አቶ ዳዊት ታደሰ የሰጡት ምሥክርነት ‹‹…ከየትኛውም ፓርቲ፣ ከብሔር፣ ከፖለቲካ፣ ከሃይማኖት፣ ወገንተኝነት የፀዳ ብለን እራሳችንም ስንሰባሰብ በዚህ መልኩ ነው የተሰበሰብነው፡፡ ፓርቲያችን የተመዘገበ አይደለም፡፡ በሃሳብ ደረጃ የነበረ ነው፣›› ማለታቸው ተመዝግቧል፡፡

አቶ ዳዊት ፓርቲ አለን ብለው አልመሰከሩም፡፡ ከየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት ጋር ወገንተኝነት የሌለው የሲቪክ ተቋም ለመመሥረት እየተነጋገርን እንደነበር ግን መስክረዋል፡፡ ይህም ከካሴት ቁጥር 7 (መጋቢት 19/2001 ዓ.ም.) በኦዲዮ ሊረጋገጥ ይችላል፡፡

<u>6 በጥፋተኝነት ብይን ውስጥ ያሉ ስህተቶች</u>

በብይኑ ግልባጭ ገፅ 55 ከ/ፍ/ቤ በአንድነት ጽ/ቤት የተደረገውን ሕዝባዊ ስብሰባ የገመገመ ሲሆን፤ በስበሰባው የተላለፈው መልዕክት ‹‹የመንግሥት ለውጥ ለማምጣት ዛሬውኑ መነሳት አለብን፤›› የሚል ነው ብሏል፡፡

ይህም አባባሉ በገፅ 41 ላይ ፍ/ቤቱ ማስረጃዎቹን ለመመዘን ከተጠቀሙበት የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ 652/2001 አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀጽ 1-6 ከተዘረዘሩት መካከል የተካተተ አይደለም፡፡

> **እንደ ከፍተኛው ፍ/ቤት ትንታኔና ድምዳሜ ከሆነ፣ የሰሜን አፍሪካ ሕዝባዊ ተቃውሞዎችን ያነሳና አርአያ ያደረገ ሁሉ ከግንቦት 7 ጋር ሳለው ግንኙነት ማስረጃ ይሆናል፡፡ በዚህ አመክንዮ ‹‹የሰሜን አፍሪካ ሕዝባዊ ተቃውሞዎች ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ይገባዋል›› ለሚለው ሃሳብና ተያያዥነት ያላቸው ትንታኔዎች ግንቦት 7 የፈጠራ ባለቤትነት አለው፡፡ ሀገር ውስጥ ያለነው 80 ሚሊዮን ኢትዮጵያዊያን የኮፒ ራይት ዕዳ አለብን ማለት ነው፡፡**

የተከበረው ጠቅላይ ፍርድ ቤት (ከዚህ በኋላ ጠ/ፍ/ቤ በሚለው ምህፃረ ቃል እጠራዋለሁ) በአፅንኦት እንደሚረዳው፤ ‹‹…የመንግሥት ለውጥ ለማምጣት ዛሬውኑ እንነሳ…›› ማለት በራሱ ወንጀል አይደለም፡፡ ሕገ መንግሥቱም ሆነ ሌሎች ንዑስ ሕጎች ስለመንግሥት ለውጥ መነጋገር፣ መመካከር፣ ማቀድ፣ ማነሳሳትና ማደራጀት አይከለክሉም፡፡ በሕግ የተጣሉት ገደቦች ሰላማዊነትና ሕጋዊነት ብቻ ናቸው፡፡

ከዚህ አኳያ፣ ፍ/ቤቱ በይፋ የተላለፈው ጥሪ ትግሉን ‹‹ወደሰላማዊና ሕጋዊ ተግባር ማሸጋገር…›› መሆኑን ተማምኗል (እንደተለመደው፤ ‹‹ሕጋዊ›› የምትለዋን ለይቶ ለመሸፋፈን መጣሩ እንደተጠበቀ ሆኖ፡፡) ሆኖም፤ በሰሜን አፍሪቃ ከተደረጉት ሕዝባዊ ንቅናቄዎች ጋር እየተጣቀሰ ሲነገር ‹‹ኢ-ሕገ መንግሥታዊ በሆነ መንገድ የመንግሥት ለውጥ እናምጣ›› የሚል ትርጉም የሚሰጠው ነው ብሎ ደምድሟል፡፡ ችግሩም ያለው እዚህ ድምዳሜ ላይ ነው፡፡

በመጀመሪያ ከጥሬ ሃቁ እንነሳ፡፡ በስብሰባው ሙሉ ሂደት ስለመንግሥት ለውጥ አንድም ጊዜ አልተነሳም፡፡ የስብሰባው መነሻና መድረሻ በሕገ መንግሥቱ የተካተቱት፣ የተዘረዘሩትና እውቅና የተሰጣቸው ተፈጥሯዊ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ናቸው፡፡

በስብሰባው ሂደት የገለፅሁት በመሠረታዊ ባህሪያቸው ተፈጥሯዊ ሆነው በሕገ መንግሥቱም እውቅና የተሰጣቸው ዴሞክራሲያዊ መብቶች፡-

1. እየተጣሱ መሆናቸው
2. መብቶቹ በአብዛኛው የአፍሪቃ ሀገራት እንኳን እየተከበሩ ባሉበት ጊዜ በሀገራችን አለመከበራቸው ታላቅ ሀገራዊ ውርደት መሆኑን፣
3. መብቶቹ ላለመከበራቸው ምክንያት የሆኑት ጥቂት የኢህአዴግ አመራር አባላት (በተለይ በዝርፊያ ላይ የተሰማሩት) እንጂ፤ ብዙሃኑ የኢህአዴግ አባላት አለመሆናቸውን፤
4. መብቶቹ ሊከበሩ የሚችሉት ተገቢውን ክብርና ዋጋ የሚሰጣቸው ሕዝብ ሲኖር ብቻ መሆኑን፤
5. መብቶቹን ለማስከበር ትግሉ በ2004 ዓ.ም. ከቃላት ወደ ሰላማዊና ሕጋዊ ተግባር መሸጋገር እንዳለበት፤
6. ሰላማዊና ሕጋዊ ትግሉ መንግሥት ከገነነባቸው የአፈና ተቋማት ችግር ሊገጥመው እንደሚችል፤
7. የአፈና ተቋማት ሕዝብን ለዘለቄታው አግተው መኖር እንደማይችሉ ከግብፅ መማር ይቻላል የሚሉት ናቸው፡፡

ከተሰብሳቢውም ከዚህ የተለየ ነገር አልተገለፀም፡፡ በአቀረብሁትም መጣጥፍም በግልፅ ተቀምጧል፡፡

ይህን ሁሉ ከ/ፍ/ቤ እጅ ካሉ የሰነድና የቪዲዮ ማስረጃዎች ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ‹‹አባይን ያላየ የሰፈሩን ምንጭ ወንዝ ይላል፤›› እንደሚባለው ካልሆነ፤ በአንድነት ጽ/ቤት የተደረገው ሕዝባዊ ስብሰባ፣ እንኳን በአፍሪቃ ደረጃ በምዕራባዊያንም ደረጃ ከመድረክም፣ ከተሰብሳቢውም Moderation የተንፀባረቀበት ነው፤ እድሜ ለኢትዮጵያዊ ጨዋነት፡፡

እርግጥ፣ የሥር ፍ/ቤት እንዳለው ሕገ መንግሥት ለማስከበር በሚደረግ ትግል የመንግሥት ለውጥ ሊያስከትል ይችላል፡፡ በአሜሪካ የWatergate ጉዳይ አንድ ጉልህ ምሳሌ ነው፡፡ ትግሉና ውጤቱ ግን፤ ፊፅሞ ኢ-ሕገመንግሥታዊ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

የሰሜን አፍሪቃ ሕዝባዊ ንቅናቄዎችም ሕገወጥ አልነበሩም፡፡ ለዚህ ቀላሉና የማያከራክረው ማስረጃ የአፍሪካ ሕብረት ለንቅናቄዎቹና ለውጤቶቹ የሰጠው እውቅና ነው፡፡ በአንፃሩ፣ ማሊ ውስጥ የተደረገውን የመንግሥት ለውጥ አውግዟል፤ እውቅና ነፍጓል፡፡ ያለፈው የአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ የተከፈተው በሰሜን አፍሪካ ሕዝባዊ ተቃውሞዎች ሰማዕት ለሆኑት የአንድ ደቂቃ የሕሊና ፀሎት በማድረግ እንደነበር ድፍን ዓለም የሚያውቀው ሐቅ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እንኳን ዜናውን አስተላልፎታል፡፡ በስብሰባው ላይ ኢትዮጵያን ወክለው የተገኙት አምባሳደር ሣህለወርቅ ዘውዴ ቆመው የአንድ ደቂቃ ፀሎት ከአደረጉት መካከል ነበሩ፡፡ ታዲያ እኔ እንደምሳሌና አርአያ ስጠቀምበት ሽብርተኛ የምሆነው በየትኛው የፍትህ ሚዛን ነው?

<u>7 በጥፋተኝነት ብይን ውስጥ ያሉ ስህተቶች</u>

በገፅ 56 ላይ ፍ/ቤቱ ማስረጃዎችን መመዘን የጀመረ ሲሆን፤ በ19ኛው *መሥመር* ላይ የአቶ ዘመኑን ምሥክርነት አስቀድሟል፡፡ በ22ኛው *መሥመር* ላይም ‹‹ለሠልፉ ወጪ ከሌላ ገንዘብ እንዳትቀበሉ፣ በጋራ እንሸፍናለን እንዳላቸው ገልፀዋል››

*ወደ ገፅ 35 ዞሯል*

# ኢህአዴግ. . . .

ከ ገፅ 3 የዞረ

በአቶ መለስ ስርዓተ ቀብር ዕለት ወይዘሮዋ እራሳቸው ‹‹የመለስ ራዕይ ካልተበረዘ እና ካልተሸራረፈ …›› ሲሉ እንደሚያስፈፅሙ የገቡለትንም ቃል ጭምር ነው። ምክንያቱም አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ስልጣን የያዙት በፓርቲው ህገ-ደንብ መሰረት ነው። ህገ-ደንብ ደግሞ የመለስ ራዕይ ውስጥ የሚካተት ነው። ከዚህ ስንነሳ የምንደርስበት እውነታ ኢህአዴግ ውስጥ መደማመጥ እየራቀ መሆኑን ነው። ሌላው ቀርቶ ‹‹የመለስ ራዕይ›› የሚል ስያሜ የተሰጠውን የኃይል ማሰባሰቢያ ባንዲራ እንኳ በህብረት ማውለብለብ እየተሳነው ነው።

የሆነ ሆኖ በግንባሩ ውስጥ የፖለቲካ ቅሬታ ያላቸው ያውም ‹‹አደገኛ›› ሰዎች ለመኖራቸው ምልክቶች መታየታቸው አጠያያቂ አይደለም። ለዚህ ዕውነታ መከራከሪያ ተደርገው ከሚቀርቡት ማሳያዎች ውስጥ አንዱ በዚህ የእምቢተኝነት እና የስርዓት አልበኝነት ተግባራቸው የፓርቲው ማዕከላዊ አመራር መሰባበሩን በተዘዋዋሪ ያሳወቁን አዜብ መስፍን የፓርቲው የስራ አስፈፃሚ አባል መሆናቸው ነው። ምን አልባትም በሀገሪቱ ፖለቲካ ላይ ምንም አይነት ተሳትፎ ያልነበራቸው፤ ወይም ‹‹የኢትዮጵያ ሰራተኞች ፓርቲ/ኢሰፓ›› የአመራር አባል ያልነበሩት የቀድሞ ፕሬዘዳንት የመንግስቱ ኃ/ማርያም ባለቤት ይህንን ስህተት ቢፈጽሙ ኖሮ ጉዳዩን ከስርዓቱ እና ከፖለቲካው ጋር በቀጥታ ማገናኘቱ አስቸጋሪ ይሆን ነበር። ነገር ግን ድርጊቱን የፈፀሙት ወ/ሮ አዜብ፣ ታግለው ለስልጣን የበቁና ገዥውን ፓርቲ ወክለው ፓርላማ የገቡ ከመሆናቸውም በላይ የገዢው ፓርቲ የስራ አስፈፃሚ አባል ናቸው። ስለዚህም የስልጣን ተዋረዱም ሆነ ውስጣዊ መረጋጋቱ በነበረበት ያለ መሆኑ በተነገረለት ፓርቲ ውስጥ የዚህን ያህል ከፓርቲያቸውና ከመንግስት ትዕዛዝ ሊያፈነግጡ የሚችሉበት አሰራርም ሆነ ደንብ አይኖርም።

በአጠቃላይ ‹‹በግንባሩ ውስጥ ልዩነት ተከስቷል›› የሚለውን ጥርጣሬ የሚያሰፋው መንግስትም ሆነ ፓርቲያቸው ሴቲቱን እንደመንግስት ለማስገደድ ሲሞክር አለመታየቱም ጭምር ነው። ሲሞን አሊሶን የተባሉ ፀሀፊ ‹‹ዴይሊ ማቭሪክ›› በተባለ ድረ-ገፅ ላይ **‹‹Grieving widow stalls smooth transition››** በሚል ርዕስ ባስነበቡት ፅሁፍ ያነጋገሯቸው አንድ ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ተንታኝ ጉዳዩን በግልፅ ቋንቋ ሲያስቀምጡት ‹‹ሴቲዩይቱ የመለስ ባለቤት ብቻ ሳትሆን ባለቤቷ ባነበሩት የከፋ አገዛዝ ሁለተኛዋ ፈላጭ ቆራጭ ናቸው።›› ብለዋል። ተንታኙ ‹‹በቅርብ የሚያውቋቸው እንደሚሉት ሴትየዋ አስቸጋሪ ባህሪ ያላቸውና ከቀድሞ ባለቤታቸው የባሰ አምባገነን›› መሆናቸውን አስረግጠው ይናገራሉ።

ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ የማታ ማታ ወ/ሮ አዜብ ምክንያቱ ባልተገለፀ ሁኔታ ቤተ-መንግስቱን መልቀቃቸው ተነግሯል። ሆኖም ላለፉት ሰላሳ አንድ ቀናት በእምቢተኝነት በመፅናታቸው የተበላሸውን የድርጅቱን ፖለቲካ መጠገን ከቶም አይቻላቸውም። የጎደፈውን ‹‹ደካማ አመራር›› ትችት ማጠብ ያዳግታል። የአመራሩን መከፋፈልም እንዲሁ መሸፋፈን አይቻልም። ጉዳዩ እንደ የፈሰሰ ውሃ ሆኖአልና።

ወ/ሮ አዜብ የተማመኑበት የፖለቲካ እና የታጠቀ ኃይል ሳይኖር ከመንግስትም ሆነ ከድርጅታቸው ፍላጎት እና ትዕዛዝ በዚህ ደረጃ ያፈነግጣሉ ብሎ መቀበሉ ይከብዳል። ምንአልባትም አዜብ የተማመኑት በታጠቀው ኃይል ሊሆን ይችላል ብሎ መገመት ይቻላል። በተለይ በቤተ-መንግስቱ ያለውን ሰራዊት። ከዚህ በመነሳት በሃሜት ኮሪደሮች ሲነገር የነበረውን ‹‹አቶ መለስን እና ቤተሰቦቻቸውን የሚጠብቀው ሰራዊት አባላት በሙሉ የአቶ መለስ የትውልድ ቦታ የሆነው የአድዋ ተወላጆች ናቸው›› የሚለውን ለማመን እንገደዳለን። ይህ እውነት ከሆነ ደግሞ ያ ኃይል ታማኝነቱ እና ተጠሪነቱ ለህገ-መንግስቱ ሳይሆን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ መሆኑ አይቀርም። እናም ይህ ሠራዊት ለቤተሰቦቻቸው ‹‹ጥላ ከለላ›› የመሆን ዝንባሌ የለውም ማለት ይከብዳል። የአዜብ ከመንግስት እና ከህግ በላይ መሆንም በዚሁ ኃይል መተማመን ያመጣው ስሜት ይመስለኛል። እዚህ ጋ የሚታየው ተጨማሪ አደጋ አዜብ በብዙ ድርድር ቤተ-መንግስቱን ቢለቁም፤ ‹‹ጋሻ›› ያደረጉት ሰራዊት አሁንም በነበረበት ግቢ ውስጥ መሆኑ ነው። ይህን ሰራዊት ሊያዘው የሚችለው ተቋም የመጨረሻ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚንስትሩ መሆኑ ግልፅ ቢሆንም ይህ ያለመፈፀሙን እያየን ነው። ከሰሞኑ ሁኔታዎች አኳያ ተነስተንም ሠራዊቱ በተሰበረ የስልጣን ተዋረድ ስር ውሏል የሚል እምነት ላይ ከደረስን ለአዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ታማኝ ይሆናል ማለቱ አስቸጋሪ ይሆናል። የዚህ ግልባጭ የሰራዊቱ ታማኝነት ለሴቲቱ እንደሆነ ይቀጥላል የሚል ነው። ይህ ደግሞ በሴቲቱና ከጀርባቸው ባለው ቡድን እና የመንግስትን ኃይል ይዣለሁ በሚለው መካከል አንዳንድ አለመግባባቶች ከተፈጠሩ በማንኛውም ሰዓት መፈንቅለ መንግስት አያደርግም ብሎ ማሰብ አይቻልም። ይህን መላምት አንዳንድ ፀሀፊዎችም ደጋግመው ይጠቅሱታል።

መቼም እየተነጋገርን ያለው በቤተ-መንግስቱ ስላለው ሰራዊት ብቻ እንዳልሆነ እንግባባለን ብዬ አስባለሁ። ምክንያቱም ያንን ሠራዊት በትውልድ መንደር የተሳሰረ ነው ብለን ካመንን፣ የትስስሩ ገመድ የት ሊደርስ እንደሚችል መገመት አያቅትምና ነው። በተጨማሪም አዜብ መስፍን የሀገሪቱ ታላቅ የቢዝነስ ተቋም የሆነው ‹‹ኤፈርት›› ኃላፊ መሆናቸው መዘንጋት የለበትም። የኤፈርትን ገቢና ወጪ ደግሞ እንኳን ኦዲተር ኢትዮጵያም እንደማታውቀው ለዓመታት ሲነገር የነበረ የአደባባይ ጉዳይ ነው። እናስ! ገንዘብ ካለ… (በነገራችን ላይ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ህውሓት ውስጥ ልዩነት የሚከሰት ከሆነ ከኤፈርት ጋ መያያዙ አይቀሬ ነው። ባለፀጋ ጄነራሎችም የልዩነቱ ዋነኛ ተዋናይ ሲሆኑ ማየታችን እንዲሁ አይቀሬ ነው)

በእርግጥ ‹‹ቡድንተኛ›› በበዛበት ስርዓት ውስጥ የመፈንቅለ መንግስት አደጋ የሚያሰጋው ከአንድ አቅጣጫ ብቻ አይደለም። ከሌላም ካልታሰበ እና ካልተጠረጠረ ቦታም የመነሳት ታሪካዊ ዳራ አለው። በዚህ ወቅትስ እነማን በአሳቻ ቦታ ምን እየሰሩ እንደሆነ ማን ያውቃል? መቼም ጠቅላይ ሚንስትሩ ያውቃሉ የሚል ቧልተኛ እንደማይኖር አምናለሁ።

እናም በደምሳሳው ከዚህ አኳያ ተነስተን ሁለት ፖለቲካዊ አሳሳቢ አደጋዎችን ልንገምት እንችላለን። የመጀመሪያው አዜብ የተማመኑበት ኃይል ከመንግስት የበረታ ጡንቻ ያለው መሆኑን ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ መንግስት ‹‹ህግ እና ስርዓት››ን በኃይል ለማስከበር ይህንን ያህል ጊዜ ሊወስድበት አይችልም ነበር። ጉዳዩን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ የጁነዲን ሳዶን ዕጣ ፈንታ ለንጽጽር በምሳሌነት ማቅረብ እንችላለን። የሆነው እንዲህ ነው፣ የኦህዴድ/ኢህአዴግ የአመራር አባልና የሲቪል ሰርቪስ ሚንስትሩ ጁነዲን ባለቤት ከሽብርተኝነት ጋር በተያያዘ በፌደራል ፖሊስ ተይዘው ይታሰራሉ፤ ጁነዲንም ይህንን ጉዳይ በመቃወም ‹‹ባለቤቴ ንፁህ ነች›› ሲሉ በጋዜጣ ላይ ያለቃቅሳሉ። በዚህ የተከፉት ጓዶቻቸውም ‹‹የፓርቲውን ገፅታ አበላሸ›› ይሉና ለግምገማ ያቀርቧቸዋል። በግምገማው ላይ በተደረገባቸው ጫናና በቀረበባቸው ውግዘት ‹‹ሂሴን ውጫለሁ›› ቢሉም ከፓርቲው አመራርነት ከመሻር አላመለጡም። እንግዲህ ንፅፅሩ ‹‹ቤተ-መንግስቱን አለቅም›› ካሉት አዜብ መስፍን ጋር ነው።

በአናቱም ከሴቲቱ እምቢታ ጀርባ ያለው ፖለቲካዊ አንድምታ ሲተነተን ‹‹የኃይለማሪያምን ሹመት አልቀበልም›› የሚል ሊሆን ይችላል። አንድ ለግንባሩ ቅርበት ያላቸው ግለሰብ ያጫወቱኝም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው። የግንባሩ ሊቀመንበር እና ምክትላቸው በተመረጡበት ስብሰባ ላይ አዜብ ከምርጫው በፊት አስተያየት አለኝ ይሉና ዕድሉ ሲሰጣቸው ‹‹አዲስ ከሚመረጡት አመራሮች መሀል አንዲት ሴት እና ነባር አባል መካተት አለባት›› የሚል ሃሳብ ያቀርባሉ። ነገር ግን ይህ ሃሳባቸው ወዲያውኑ በተቃውሞ ወድቅ ይደረግባቸዋል። የአዜብን አስተያየት ተከትሎ ለተቃውሞ እጃቸውን ያወጡት አርከበ እቁባይና ስዩም መስፍን ነበሩ፤ በተለይ አርከበ ‹‹ከሁለት ዓመት በፊት መለስ እያለ ተስማምተን ያፀደቅነው እያለ ዛሬ አንቺ ይህን ሃሳብ ከየት አመጣሽው?›› ሲሉ ክፉኛ ተቃውሞአቸዋል። ምን አልባት የአዜብ ሃሳብ ተቀባይነት ቢያገኝ ኖሮ የተጠቀሰውን መስፈርት የሚያሟሉ ብቸኛው የስራ አስፈፃሚ ሴት አባል እሳቸው በመሆናቸው ዛሬ ወይ ጠ/ሚንስትር አሊያም ምክትል ጠ/ሚንስትር ወንበር ላይ ተቀምጠው ልናያቸው እንችል ነበር። እናም የሴቲቱን እምቢተኝነት ከለጠጥነው ከዚህም ጋር ሊያያዝ ይችላል። ሁለተኛው አደጋ ያልኩት ደግሞ ይህ የሴቲቱ ጉልበተኝነት (ፍላጎትን በኃይል ማስፈፀም) በቀጣይነትም በመንግስትም ሆነ በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ ላለመግባቱ ዋስትና ያለመኖሩን ነው።

መቼም ስለ‹‹መንግስት›› ስናወራ ስለብዙ ነገር ነው የምናወራው። መንግስት በህግ ከተደራጁት ተቋማት እና በህግ ከተፈቀደለት ስራዎች ባሻገር አይን የማያያቸው፣ ጆሮ የማይሰማቸው ለጥቂቶች ብቻ የተፈቀዱ በርካታ ስራዎችንም የሚሰራ መሆኑ ግልፅ ነው። በተለይም በአምባገነን ስርአት ውስጥ እንዲህ አይነት ሚስጥራዊ አሰራር በስፋት ይታያል። ሲሰሙ የሚያጥውለውሉ፣ እራስን የሚያስቱ በመንግስት የሚፈፀሙ ምስጢሮችንም ከቶ ማን ያውቃቸዋል? ለሃያ አንድ ዓመታት በኢትዮጵያ የነበረው መንግስት በጥቂት ሰዎች ተይዞ የነበረ በመሆኑ፣ እንዲህ አይነት ‹‹ጉዱ-ጉዶች››ን የሰማቸው የለም። ሆኖም ነገሮች ቦታ ቦታቸውን ከመያዛቸው በፊት ድንገት ከ‹‹ጥቂቶቹ›› ውጭ የነበሩት የደቡቡ ሰው የመንግስት የመጨረሻው ሰው ሆነዋል። እናም ያልተፈቀደላቸውን ሚስጥሮች ይሰሙ ዘንድ የተቀመጡበት ወንበር ያስገድዳቸዋል። ለምሳሌም በ2003 ዓ.ም ዩናይትድ ኔሽን ‹‹ከኢትዮጵያ ተዘርፎ በውጭ ሀገር የተደበቀ›› ሲል ያጋለጠውን 8.2 ቢሊዮን ዶላር ባለቤቶች ሊያውቁ መቻላቸውን መገመት ይቻላል። መገመት የማይቻለው ካወቁ በኋላ ምን ያደርጉ ይሆን? የሚለውን ነው። ለነገሩ ከእርሳቸው ጀርባ ያሉ ሰዎች በስራቸው ላይ ጣልቃ ይገቡ ዘንድ የሚያስገድዳቸውም እንዲህ አይነት ሚስጥሮች ተቀብረው እንዲቀሩ ነው። በግልባጩ ደግሞ በአሁኑ ወቅት አብላጫው ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ላይ መንግስት መኖሩን ማረጋገጥ እንዲፈልግ ያስገደዱት የእዚህ አይነት ግፊቶች ናቸው። ስለዚህም ይህ ጥያቄ መልስ እስኪያገኝ ድርስ ደጋግሞ መጠየቁን ይቀጥላል ‹‹ኢትዮጵያ ሆይ መንግስትሽ ከወዴት አለ?››

ከ‹‹መለስ ራዕይ›› ጀርባ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ህይወት ማለፉን መንግስት በይፋ ከተናገረ ከሰባ ቀናት በላይ ያስቆጠረ ቢሆንም ዛሬም ድረስ መለስ በህይወት ያሉ እስኪመስል ድረስ በሀገሪቱ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ላይ

ስማቸው መነሳቱ የእለተ ተዕለት ተግባር ሆኖአል። በእርግጥ ይህ የሆነው በህይወት ያሉት የአቶ መለስ ጓደኞች ከመለስ ጋር ‹‹ፍቅር እስከ መቃብር›› የሚያስብል ግንኙነት በማሳለፋቸው አይደለም። ወይም መለስ መልካም አለቃ ስለነበሩም አይደለም። የዚህ ሁሉ ዋነኛው ምክንያት መለስ በጠንካራ መዳፋቸው ሠጥ-ለጥ አድርገው ተቆጣጥረውት የነበረውን ስልጣን ህይወታቸው ካለፈ በኋላም ‹‹በስማቸው›› እንደነበረ ለማስቀጠል ነው። ስለዚህም በመለስ ዘመን የነበረው ኢህአዴግ በመንበሩ እስከቀጠለ ድረስ ይህ ሁኔታ አይቋረጥም። ይህ መፈክር በአመራሩ ዘንድ ፓርቲውን ከመከፋፈል የሚታደግ ብቸኛ መጫወቻ ካርታ ሆኖ እስከመታየት ደርሷል።

እስከአሁን ድርስም ኢህአዴግ ‹‹የመለስን ራዕይ›› እናሳካለን በሚል መፈክር ስር በርካታ ህዝብ እና የራሱን ካድሬ ማሰባሰብ ችሎአል፡ ፡ በተጨማሪም የተበታተኑና ለመፈንዳት የተቃረቡ ሕዝባዊ ቁጣዎችን ያላንዳች ኮሽታ ማምከኑም ተሳክቶለታል። ወደፊትም በመፈክሩ ደጋፊ እያሰበሰበ፤ ተቃዋሚዎችንም እያሸማቀቀበት የመጓዝ እቅድ ይኖረዋል።

ይህም ሆኖ ‹‹የመለስ ራዕይ›› ከውስጥ እንጂ ከውጭ ለሚነሳ የፖለቲካ ልዩነት መድሀኒት የመሆን አቅም የለውም። ስለዚህም በአራቱ ድርጅቶች (ህወሓት፣ ብአዴን፣ ኦህዴድ እና ደኢህዴን) መካከል ወይም በታጠቀው ኃይል የመጠቀም ችሎታ ያለው ቡድን በኢህአዴግ ውስጥ ልዩነት ይዞ ቢወጣ የግንባሩ እድል ፈንታ የመጨረሻው ከመሆን የሚታደገው አይኖርም፡ ፡ እየታየ ያለው ሁኔታም ፓርቲው በዚህ የአንድነት መንፈስ ብዙ ሊቆይ እንደማይችል አመላካች ነው። ምንአልባትም በዚህ ወቅት ኢህአዴግ መለስ የግድ ያስፈልጉት እንደነበረ በሀዘን እያስታወሰ ይመስለኛል፡ ፡ እርሳቸው ከመድረኩ የሚወርዱት የቤት ስራቸውን ሲጨርሱ ካልሆነ አደጋ መከሰቱ አይቀሬ እንደሆነም ሁሉም ጠንቅቀው ያውቁ ነበር፡ ፡ ለዚህም ነው ከጥቂት አመታት በፊት መለስ ወደፊት በህወሓት የበላይነት የስልጣን ወሰንን ማስከበር እንደማይችል ተረድተው ግሩም ቲያትር ማዘጋጀት ጀምረው የነበረው።

አቶ መለስ የመውጫ እስትራቴጂ ማፈላለግ ከጀመሩ ጥቂት አመታት አልፈዋል። እናም እንደአማራጭ ይሆን ዘንድ ቲያትር መሰል ባህሪ ያለውን ‹‹መተካካት›› አዘጋጁ፤ ከዚህ አንፃርም ነው ዛሬ እየታየ ያለው ቲያትር አዲስ ያልሆነብን። በእርግጥ ተዋንያኑ አዲስ ናቸው- ኃይለማርያም ደሳለኝ እና ደመቀ መኮንን። አቶ መለስ ይህንን የትርጀዲ ዘውግ ያለውን ቲያትር ማዘጋጀት የጀመሩት ከድህረ ምርጫ 97 በኋላ ነው። ምክንያቱም ያንጊዜ ነው ኢትዮጵያን የምታህል ትልቅ ሀገር ሕዝቦቿን ‹‹ትምክህተኛ፣ ጠባብ፣ የደርግ ስርዓት ናፋቂ…››፤ ባንዲራዋን ደግሞ ‹‹ጨርቅ›› እያሉ ኢህአዴግን ከመሰረቱት አራቱ ፓርቲዎች ውስጥ በሚወክለው የህዝብ ቁጥር ትንሹ በሆነው ህወሓት ስም ብዙ ርቀት መጓዝ እንደማይቻል የተገለፀላቸው። በተጨማሪም በብሔር ፖለቲካ ‹‹ሳጋና ማገር›› የቆመው ‹‹ስርዓተ መንግስት›› ውስጥ የህወሓት የበላይነት ወደፊትም በዚህ መልኩ እንደተጠበቀ መቆየቱ አጠራጣሪ ከሆነ ውሎ አድሯል፡ ፡ አንድ አጥኝም አቶ መለስ በአንድ ወቅት ለህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ይህንን የሚያጠናክር ንግግር መናገራቸውን ገልጸዋል ‹‹At a meeting of the TPLF Central Committee that was convenced at the Economic Commission for Africa hail in Addis Ababa, the Prime Minister dropped a bombshell.He told the members who were hitherto in control of every policy decision not only in Tigray, but also in the rest of Ethiopia that the Mandate of TPLF was over.›› (በአፍሪካ የኢኮኖሚ ኮሚሽን አዳራሽ በተካሄደው የህውሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስደንጋጭ ነገር ተናገሩ፤ እስከ ጊዜው ድረስ በትግራይ ክልል ብቻም ሳይሆን በኢትዮጵያም በአጠቃላይ የፖሊሲ ውሳኔዎች ላይ የበላይነት ለነበራቸው የፓርቲው አባላት የህወሓት የበላይነት ማብቃቱን ገለፁ)

የማታ ማታም አቶ መለስ ከዚህ በፊት የነበሩ ልማዶችን እና አሰራሮችን በመቀመር አስተዳደራቸውን ወደ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ (በይዘት ሳይሆን በቅርፅ) ለማሸጋገር ቀን እና ሌሊት ይተጉ ዘንድ ግድ ሆነ። በውጤቱም ዛሬ በኃይለማርያም ደሳለኝ እና በደመቀ መኮንን ፊት መሪነት የሚመራውን ቲያትር አዘጋጅተው መጨረሳቸው እውነት ነው። ሆኖም ቲያትሩ ለዕይታ ከመብቃቱ በፊት ህይወታቸው በማለፉ የድርሰቱ ሰምና ወርቅ ባልገባቸው ጓዶቻቸው አዘጋጅነት ቲያትሩም ለተመልካች መቅረቡ እውነት ነው። (በነገራችን ላይ አቶ መለስ ተፈጥሮ ባትቀድማቸው ኖሮ ትያትሩ ለአቅመ-መድረክ ይብቃ የነበረው በ2007 ዓ.ም. ከሚደረገው ምርጫ በኋላ ነበር። ያን ጊዜም ግዙፉ የህወሓት እጅ በመድረኩ ላይ አይታይም። ከጀርባ ይሆን ዘንድ ነው የታሪኩ ሴራ የሚያጠነጥነው)

መለስ ህወሓትን ይዘው ከዚህ በኋላ በነበረው መንፈስ መጓዝ እንደማይችሉ በሚገባ መረዳታቸው ነው ለሃያ አንድ ዓመት ያህል በስልጣን ላይ ያቆያቸውን ስልት በአዲስ ለመቀየር የተገደዱት። ይህ ሁኔታም በሁለት ተከፍሎ ለታይ ይችላል። አሮጌው (ክፍል አንድ) እና አዲሱ (ክፍል ሁለት) ተብሎ። እናም አቶ መለስ ይህን ስልት ከየት እንደቀዱት አነፃፅረን ብናቀርበው ጉዳዩን ይበልጥ ግልፅ ያደርገዋል።

የ‹‹አልበርት ሴራውት›› መንገድ-ክፍል አንድ

ህወሓት ለ17 አመታት በዱር፣ በገደል ወጥቶ ወርዶ የታገለ በመሆኑ ሁሉን የመቆጣጠር ፍላጎቱን ለመግታት አልተቻለውም። ይህ ፍላጎቱም ቤተ-መንግስቱን፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርን፣ የመከላከያ ሚኒስትርን፣ የደህንነት ሚኒስትርን፣ የሠራዊቱን ኤታማዦር ሹም፣ ባንኩን፣ ንግዱን፣ ቀረጡን… ሁሉንም ጠቅልሎ እንዲይዝ አደረገው። ሁኔታው ሁሉ ከስድስት አስርት አመታት በፊት በርካታ የአፍሪካ ሀገራትን በቀኝ ግዛት ከያዘው የፈረንሳይ አስተዳደር የተኮረጀ መሆኑን ማየት ይቻላል፡ ፡ ፈረንሳይ በቅኝ ግዛት በያዘቻቸው ሀገራት ላይ ‹‹የቀጥታ አስተዳደር›› (Direct Rule) ፍልስፍናን በመተግበር ትታወቃለች። የሀሳቡ አመንጪም ‹‹አልበርት ሴራውት›› ይባላል። በዚህ የአስተዳደር ዘይቤ መርህ መሰረትም በሁሉም ቀኝ ተገዥ ሀገራት ከላይ ሆነው ስልጣን የሚይዙት ፈረንሳዊያን ብቻ መሆናቸውን ይደነግጋል። …. ህወሓት ለሁለት አስርት አመታት የተከተለውም ይህንኑ የአልበርት ሴራውት መንገድ ነው፤ ሌላ አይደለም።

የ‹‹ሎርድ ሉጋርድ›› መንገድ-ክፍል ሁለት

ሌላዋ ዝነኛ ቅኝ ገዢ ሀገር ታላቋ ብሪታኒያ /እንግሊዝ/ ነበረች። እንግሊዝ በቅኝ ግዛት በምታስተዳድራቸው ሀገራት ትከተል የነበረው የአስተዳደር ዘይቤ ከፈረንሳይ ይለያል። የእንግሊዞቹ ‹‹የዘወርዋራ አስተዳደር›› (Indirect Rule) የሚል ፍልስፍናን የሚከተል ሲሆን የሀሳቡ አመንጪም ‹‹ሎርድ ሉጋርድ›› የተባለ ሰው ነው። …አቶ መለስ ‹‹ከሚቀጥለው ምርጫ በኋላ ስልጣኔን እለቃለሁ›› ሲሉ የገቡት ቃል በሌላ አማርኛ ሲገለፅ የሎርድ ሉጋርድን መንገድ እከተላለሁ የሚል እንደሆነ እርግጠኛ መሆን ነበረብን፡ ፡ ልዩነቱ መለስ የአምባገነን ስርዓት መሀንዲስ ሲሆኑ፣ ሉጋርድ የቅኝ ገዥ መሀንዲስ መሆናቸው ብቻ ላይ ነው። እናም ሰውየው ተፈጥሮ ባትቀድማቸው ኖሮ ከመድረኩ መገለላቸው አይቀሬ መሆኑ ላይ ጥርጣሬ የለኝም። ስለዚህም ከሚቀጥለው ምርጫ በኋላ መለስ እና ህወሓትን ከፊት መስመር አለማየታችን እውነት ነበር። ይህ የአቶ መለስ የሂሳብ ስሌት ከምርጫ 07 በኋላ እነ ኃይለማርያምን ከፊት እንዲያስቀምጥ ተደርጎ ነው የተበጀው፡ ፡ ‹‹የመለስ ራዕይ›› ማለትም ይህ ነው፤ ሌላ አይደለም።

አቶ መለስ አንሰላስለው የደረሱበት መደምደሚያ ከሚቀጥለው ምርጫ በኋላ ህወሓት አናሳ ቁጥር ይዞ በኢህአዴግ ውስጥ የበላይ ሆኖ ለመቀጠል አለመቻሉን ብቻ ሳይሆን ይህንን ፍላጎቱን እንደከዚህ ቀደሙ በኃይል አስፈፅማለሁ ቢል ተግዳሮት የሚገጥመው ከተቃዋሚ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን ከራሱ ከኢህአዴግ ውስጥ ጭምርም እንደሆነ ነው። ስለዚህም ይህንን አደጋ ለመከላከል ህወሓት የግድ ከመድረኩ በሚታይ መልኩ ተገልሎ፣ በማይታይ መልኩ መቀጠል መቻል አለበት። ዛሬ የሆነውም ይህው ነው። በእርግጥ ይህ የፖለቲካ ጨዋታ አደባባይ የወጣው ‹‹መተካካት›› በሚል የዳቦ ስም ነው። ምናልባትም አዜብ መስፍን ከሳምንታት በፊት ለአንድ በትግሪኛ ቋንቋ ለሚዘጋጅ ሚዲያ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ላይ ‹‹የትግራይ ህዝብ፣ የህወሓት መንፈስና የመለስ ራዕይ እስካሉ ድረስ ሁሉንም እንወጣዋለን›› ያሉት ከዚህ ተነስተው ሊሆን ይችላል። (የሴቲቱ ንግግር እንደተለመደው ፕሮፓጋንዳ ‹‹የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የኢህአዴግ መንፈስ እና የአመራር አባላት እስካሉ ድረስ ሁሉንም ነገር እንወጣዋለን›› የሚል ቢሆን ኖሮ ሀሳባቸውን ለመተርጎም ወይም ለመተንተን ቀዳዳ አይኖርም ነበር)

የሆነ ሆኖ መለስ በህይወት ቢኖሩ ኖሮ ኢህአዴግ ያለስጋት በሂሳቡ ስሌት መሰረት በስልጣን መቀጠሉ ላይሳነው ይችል ነበር። ሆኖም አቶ መለስ ያለጊዜው አልፈዋል። ተከታዮቻቸውም አብረዋቸው ያላዩትን ‹‹ራዕይ-መለስ›› እንደሚያስፈፅሙ እየፎከሩ ነው፡ ፡ የሚቻላቸው ግን አይመስለኝም፡ ፡ ምክንያቱም እነ ኃይለማርያምን ከፊት በማድረግ ስርዓቱን ማስቀጠል የሚቻለው መለስ በህይወት ሲኖሩ ብቻ ነው። አሁን መለስ የሉም፡ ፡ ተተኪዎቻቸው ደግሞ ቀመሩን በሚገባ መጠቀም የቻሉ አይመስሉም፡ ፡ ወይም ለእነ ኃይለማርያም እውነተኛ ስልጣን መስጠት ይኖርባቸዋል። ነገር ግን ሶስቱም የሚቻላቸው አልሆነም፡ ፡ እናም ገና ከጅምሩም አንዳንድ ክፍተቶችን እያየን ነው። ለምሳሌም ለውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሚንስትር የሚሆነውን ሰው ከየትኛው የግንባሩ አባል ፓርቲ መመረጥ እንዳለባቸው መወሰኑ ቸግሯቸዋል፤ ሌላው ቀርቶ የፖለቲካ አቅም የሌለውን የፕሬዘዳንት ግርማ ወ/ጊዮርጊስን ወንበር መተካት ከነበረበት ጊዜው አልፏል። እነዚህ ሁኔታዎች ናቸው ኢህአዴግ ወደ ማይቀረው የመከፋፈል እጣ ፈንታው እየተገፋ ያለ ያስመስሉት።

‹‹ናዳን የገታ እሩጫ››

በረከት ስምዖን ባለፈው ዓመት ለአሳተሙት መፅሀፍ ግልገል ርዕስ ያደረጉት ‹‹ናዳን የገታ ሩጫ›› ይላል፡ ፡ እርሳቸው በዚህ ርዕስ ውስጥ ሊያስተላልፉ የፈለጉት ጉዳይ ፓርቲያቸው ‹‹በምርጫ 97 በሕዝብ ድምፅ ከስልጣን ሊባረር አፋፍ ደርሶ ከተመለሰ በኋላ ከፍተኛ የልማት ተግባራትን በመፈፀሙ ብዙሀኑን ኢትዮጵያዊ መማረክ ቻለ›› የሚል ፕሮፓጋንዳ ነው። በእርግጥ የድሉ ቁልፍ ሰው ሟቹ ጠቅላይ ሚንስትር መሆናቸውን መፃሀፉ አልሸሸገም፡ ፡ ጥያቄው ግን ከዚህኛው የናዳ ዘመንስ ድርጅቱን ማን ይታደገዋል? የሚል ነው። ኢህአዴግ ይህንን ጥያቄ በሚገባ መመለስ ከቻለ ምናልባትም ዳግም ተጠናክሮ የሚወጣበት ዕድል ሊኖረው ይችላል። ወይም አቶ መለስ ለክፉ ቀን ያቆዩት ‹‹ፓኬጅ››ን ከእነአጠቃቀሙ ማግኘት ከቻለ ‹‹ዕድሜ ማራዘሚያውን›› አገኘ ማለት ነው። በእርግጥ ይህንንም ማድረግ ችሎ በሀገሪቱ፣ በአባሎቹ እና በቅቡልነቱ ላይ ምን አይነት መአት ሊያስከትል እንደሚችል አስቀድሞ ማወቅ አይቻልም።

# የኦጋዴን ነገር...

ከገፅ 9 የዞረ

አቀፍ እርዳታ ለሁሉም ነዋሪዎች መለገስ አለመቻላቸው በፖለቲካ ስልጣን የተከፋውን ቁጥር ይበልጥ እንዲጨምር አድርጎታል፡፡

እንዲህ አይነት ችግር የመንግስት ብቻም ሳይሆን ክልሉን ነፃ አወጣለሁ በሚለውም ቡድን ላይ የሚንፀባረቅ መሆኑን ሃግማን “The political roots of the current crisis in region 5” በሚለው ፅሁፋቸው ጠቅሰዋል፡፡ ዶ/ር ሃግማን ኦብነግ እወክለዋለሁ ከሚለው ቡድን ውጭ ለሌሎቹ በአካባቢው ለሚኖሩ የጎሳ አባላት የሚያሳየው የወገንተኝነት ስሜት በጣም የወረደ መሆኑን ያትታሉ፡፡

መውጫ

ኢህአዴግ እነዚህን እና ሌሎች ተደራራቢ መሰረታዊ ምክንያቶችን መቅረፍ ባለመቻሉ የተነሳ በክልሉ ያለውን ሰላምና መረጋጋት ወታደራዊ በሆኑ እርምጃዎች ለመቅረፍ ቢሞክርም እንኳን ውጤት ማምጣት እስከአሁን ሳይቻለው ቀርቷል፡፡ ለዚህም ነው ከአሸባሪው ድርጅት ጋር ለድርድር ከመሯሯጥ ይልቅ ፖለቲካዊ መፍትሄዎች ላይ ትኩረት በመስጠት የክልሉን ነዋሪዎች መሰረታዊ ቅራኔ እና ፍላጎት ማሟላት ተገቢ ሆኖ የምናገኘው፡፡

በሶማሌ ክልል ያለው አስተዳደር ከሌሎቹ የፌደራል መንግስት አስተዳደር ስርዓት በእጅጉ የተለየና ጎሳን ማዕከል ያደረገ ክፍፍል በውስጡ ያዘለ ነው፡፡ በክልሉ ያሉ ግለሰቦች ለተቋማቱ ታማኝነታቸውን ከማሳየት ይልቅ ለጎሳቸው ያላቸው ቀናኢነት እጅግ ላቅ ያለ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለዚህ ትልቁ ምክንያት መንግስት ሊተገብረው ያሰበው ተቋማዊ አስተዳደር ምክነት ብቻ ሳይሆን የጎሳው ባህል ተግዳሮት ትልቁን ስፍራ ይወስዳል፡፡

ሁለተኛው ችግር ኢህአዴግ ሊተገብረው ያሰበው የጥቅመኝነት ፖለቲካ ያስከተለው አሉታዊ ተፅዕኖ ነው፡፡ የክልሉ ፖለቲካ በአንድ በኩል ፖለቲካዊ ይዘት ባቀፈው የጎሰኝነት ስሜት ሲወጠር በሌላ በኩል ገዢው ፓርቲ በሚፈጥረው የተሳሳተ የፖለቲካ አቅጣጫ ወደ ሌላ አዘቅት እንዲገባ አስገድዶታል፡፡ መንግስት ለእነዚህ ችግሮች ቅድሚያ ቢሰጥ የህዝቡን ልብ ከማሸነፍም በተጨማሪ የክልሉን እምቅ የተፈጥሮ ሃብት በአግባቡ ለመጠቀም አቋራጭ መንገድ ያገኝ ነበር፡፡ የሰላም ስምምነቱን ከአሸባሪው ይልቅ ቅድሚያ ከህዝቡ ጋር ማድረግ ለችግሩ ዘላቂ መፍትሄ ለማግኘት ይረዳል፡፡

# ‹‹ሽራተን...

ከገፅ 5 የዞረ

ይናገራል፡፡ ‹‹ሸራተን›› ቀኑ እስኪያሸልብ ብቻ ከአምስት መቶ በላይ ደንበኞችዋን ታስተናግዳለች፡፡

የቡሌ ዓይነቱ ብዙ ነው፡፡ ዓይነቱን የሚወስነው የሚመጣበት ምግብ ቤት ደረጃ ነው፡፡ ‹‹ራስ ስዩም›› የተባለው ቡሌ ከሁሉም የተሻለ ጣዕም እንዳለው ነው ተጠቃሚዎቹ የሚናገሩት፡፡ ‹‹ከራስ ስዩም ሆቴል›› የሚመጣው ይሄ ትርፍራፊ ምግብ በቀን ከሁለት መቶ በላይ ሰዎችን በደንበኝነት ያስተናግዳል፡፡ ከራስ ስዩም በተጨማሪ ‹‹ይርጋ ኃይሌ››፣ ‹‹ኩርቱ›› (ከኩርቱ ኮሜርሺያል የሚወጣ) ‹‹የሺ ቡና›› የሚባሉ አሉ፡፡ ‹‹የተቀመመች›› ሁለተኛ ተደራጃነት አለው፡፡ ቀዝቃዛ ቦታ አድሮ ጠዋት ከሚሸጠው ‹‹ቀዝቃዜ›› በተጨማሪ ‹‹የጥብስ፣ የቅቅል፣ የቀይወጥ›› የሚል መለያ ያላቸው ቡሌዎች አሉ፡፡ እነዚህ ሁሉ የቡሌ አይነቶች የቡሌ ተጠቃሚውን ደረጃ ሰጥተውታል፡፡ የመደብ ልዩነት የተከሰተ እስኪመስል በመካከላቸው ከፍና ዝቅ እየተደራረጉ መመለካከትም አለ፡፡

ጉድ የሚፈላው እርስ በእርስ መተያየታቸው ቀርቶ የሥርዓቱን ፈጣሪዎች መመልከት ሲጀምሩ ነው፡፡ ያኔ የገዢው መደብ ሰለባዎች መሆናቸውን ተገንዝበው በአንድ ላይ ይነሣሉ፡፡ እንደ ፈረንሳይ አብዮተኞች የገዢዎቻቸውን አንገት በጊሎቲን ካልቆረጡ የማይረኩ ይሆናሉ... ‹‹ሸራተንን›› የከበባት የቆርቆሮ ተራ ኳኳታ የገዢዎችን ፍርድ ቀን ልፋፌ መሰለኝ፡፡

# የሮማ ነጭ በሬ...

ከገፅ 33 የዞረ

የቡድን መሳሪያ በብዛት ይተኰሳል፡፡ ምድር የነደደች ይመስላል፡፡ በጦርነቱ የሰው ሕይወት ብቻ ሳይሆን አራዊትና አዕዋፍ እንኳን ሳይቀሩ እንደ ቅጠል ወድቀዋል፡፡ ተኩስ! ተኩስ! ተኩስ! ሞት! ሞት! ሞት! የጦር ሜዳ ቋንቋ! ጦርነቱ ለ12 ቀናት ቀጥሎ ይገኛል፡፡ የሰው አካል በጎራዴ ተበልቷል! አንገት ተቀንጥሶ ወድቋል! ጦርነት የሰው ሕይወት መቅሰፍት! እነሆ! ባሁኑ ሰዓት ጀግኖቹ የኢትዮጵያ አርበኞች የበላይነትን ጨብጠዋል! የጀግናው ውብነህ ተሰማ የውጊያ ዕቅድ በተግባር ውጤት አምጥቷል! ታሪክ ይናገራል! ነቃሽ ይዘናል! የሕሊና ሰዎች ነን! ታሪክ ያለፈ ሁነት ነው! የወደፊት ምናልባታዊ ክስተትን ግን ይጠቁማል! የኢትዮጵያ ቀደምት ጀግኖች ገድል በከሐዲዎች ስልታዊ እርምጃ ተቀብሮ አይቀርም፡፡ ይልቁንም ጀግንነት የዘራችን ነው! የከሐዲዎች ጉልበት ፀሐይ እንደ መታው ጤዛ ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ያብባል! ለዕውነት ዘብ ቆመናል!

ባሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ አርበኞች በውጊያ ወረዳ ውስጥ የሚገኘውን የመጠጥ ውሃ በቁጥጥራቸው ስር አድርገዋል፡፡ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በውኃ ጥም ተሰቃይቷል፡፡ ጦርነቱ በኢትዮጵያ አርበኞች የበላይነት ከፍጻሜ ተቃርቧል፡፡ የኢትዮጵያ ጀግኖች አስክሬን በክብር እየተነሳ ከዛፍ ስር ጥላ ላይ እንዲቀመጥ ለማድረግ አሁን ምድብተኞች ተንቀሳቅሰዋል፡፡ የጣሊያኖችና የባንዳዎች ሬሳ በየቦታው ተዘርሯል፡፡ ባሁኑ ሰዓት ምንም የተኩስ ድምፅ አይሰማም፡፡ የዛሬ 12 ቀን የበጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት የልዩ ልዩ አውራጃዎች አርበኞች በጥምር የከፈቱት ጦርነት በአርበኞቹ ድል አድራጊነት ተጠናቅቋል፡፡ የካቲት 4 ቀን 1930 ዓ.ም.! ኢትዮጵያ እናታችን በልጆቿ ኮራች! በዚሁ ጦርነት 12 ሺህ ያህል ከነበረው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ግማሽ ያህሉ ተደምስሷል፡፡ የተቀረው ደግሞ ተማርኳል፡፡ በርካታ መትረየሶች፤ ጠብመንጃዎችና ሌሎችም የጦር መሳሪያዎች በምርኮ ከአርበኞች እጅ ገብተዋል፡፡ የካቲት 4 ቀን 1930 ዓ.ም. አንድ! አንድ! አንድ! ይህ የበጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት የልዩ ልዩ አውራጃዎች ጥምር አርበኞች የድል ድምፅ ነው!

የእሳት ራት የሆነው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ከዕብሪቱ ተቆጥቦ የጀግኖችን ሀገር ለቅቆ ለመውጣት አሁንም ፈቃደኛ አልነበረም፡፡ በዚህም መሰረት እንደገና ተጠናክሮ በኢትዮጵያ አርበኞች ላይ አዲስ ጥቃት ለማድረስ ሰኔ 21 ቀን 1930 ዓ.ም. ‹‹ድንግል ብሶ›› ወደተባለው ቦታ በመጓዝ ላይ እያለ ጀግናው አርበኛ ውብነህ ተሰማ ጦርነት ከፈተበት፡፡ በዚህን ጊዜ መውጫና መግቢያ አጥቶ ለብዙ ቀናት በተራራ ላይ ተጎልቶ ለመቆየት እንደተገደደ ታውቋል፡፡ ይህም ብቻ አልነበረም፡፡ ጥር 12 ቀን 1929 ዓ.ም. ጀግናው አርበኛ ውብነህ ተሰማ ተከታዮቹን በማስተባበር በድንገት አደጋ በመጣል በርካታ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተዋጊዎችን ከትቢያ ጋር አዋህዷቸዋል፡፡

ውድ የኢትዮጵያ ልጅ ጀግናው ውብነህ ተሰማ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የኢትዮጵያን መሬት መርገጡ እንደተሰማ ወዲያው ተከታዮቹን አስተባብሮ ወደ ሽሬ ዘመተ፡፡ በዚህ የጦር መስመር ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ጋር በተደረገው ጦርነት ከፍተኛ ጀብዱ መፈፀሙ በታሪክ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በጊዜያዊ ድል ወደ መሀል ሀገር በመግፋቱ ከሞት የተረፉ ተከታዮቹን አስከትሎ ለአርበኝነት ቆርጦ ተነሳ፡፡ በዚህም መሰረት ‹‹ከቶማውራ›› በተባለ ስፍራ ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ጋር ከፍተኛ ጦርነት ተካሂዷል፡፡ ጦርነቱ የተካሄደው ለሁለት ቀናት ሲሆን ድሉም የአርበኞች ሊሆን በቅቷል፡፡ በዚሁ ጦርነት ከሞት የተረፉ ጥቂት የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተዋጊዎች ፈርጥጠው ወደ ጭልጋ እንደገቡ ታውቋል፡፡

የጀግናው አርበኛ የውብነህ ተሰማ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ክፉኛ ያናደደው ኢጣሊያዊው የጎንደር ገዥ ጭልጋ ላይ የነበረውን ቲኔንቴ ዴፋዚዮን ተዋጊዎችን በሙሉ በአርበኞች ላይ እንዲያዘምት አዘዘው፡፡ በትዕዛዙ መሰረት ፋሽስቱ መኰንን አንድ ሺህ አምስት መቶ ተዋጊዎችን ይዞ ወደ መሃል አርማጭሆ ገሰገሰ፡፡ ጥቅምት 19 ቀን 1929 ዓ.ም. በአርበኞች ላይ ጦርነት ከፈተ፡፡ ነገር ግን ድሉ የጀግናው ውብነህ ተሰማና የተከታዮቹ ሆኗል፡፡ ጀግኖቹ የኢትዮጵያ አርበኞች ከሞት የተረፉትንም የፋሽስት ተዋጊዎች እያሳደዱ ደምስሰዋቸዋል፡፡

አሞራው ውብነህ ተሰማ በአምስቱ የጠላት ወረራ ዓመታት አንዴም ለሕይወቱ አልሳሳም፡፡ ይልቁንም ትግሉ በጠየቀው ስፍራ ሁሉ ተገኝቷል፡፡ ጀግናው ውብነህ ተሰማ በአምስቱ የጠላት ወረራ ዓመታት በተደጋጋሚ ወደ ሱዳን በመመላለስ ለአርበኞች የጦር መሳሪያ አስገኝቷል፡፡ ጀግናው ውብነህ ተሰማ የፈረስ ስሙ ‹‹አባዘልስ›› ተብሎ እንደሚጠራ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለጀግናው ውብነህ ተሰማ በየወቅቱ ግጥሞች ተቋጥረውለታል፡፡ ይህ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ ከድል በኂላ በልዩ ልዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ተመድቦ ህብረተሰቡን በቅንነትና በታማኝነት አገልግሏል፡፡ አሞራው ውብነህ ተሰማ በየወቅቱ ልዩ ልዩ ሽልማቶችን አግኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት የአምስት ዓመት ባለአምስት ዘንባባ የአርበኝነት ሜዳይ አግኝቷል፡፡ እንዲሁም የቅዱስ ጊዮርጊስ ባለሁለት ዘንባባ ሽልማት ተሰጥቶታል፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ የክብር ሜዳሊያ ተሸልሟል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የድል ኮከብ፤ የታላቁ ምኒልክ ሜዳሊያና የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ኮርዶን ኒሻን አግኝቷል፡፡ ከታላቋ ብሪታኒያ ደግሞ የአምስት ዓመት አርበኝነት የአፍሪካ ኮከብ ሜዳሊያ ተሸልሟል፡፡ ጀግናው አርበኛ ውብነህ ተሰማ የራስነት ማዕረግ ተሰጥቶት የራስ ወርቅ ማሰሩም በታሪክ ተመልክቷል፡፡ ይህ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ በ1975 ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፡፡ ታሪኩ ግን በትውልድ ቅብብሎሽ ለዘለዓለም ይኖራል! በሕያው ሥራው ሕያው ታሪክ አስቀምጧልና! ጀግናው ውብነህ ተሰማ! ክብር! ክብር! ክብር! ለውብነህ ተሰማ!



ታዴዎስ ታንቱ

# የሮማ ነጭ በሬ ተከብቧል በበረት፤ ሲበላው ነው አሉ አሞራው ዞረበት

## ለውብነህ ተሰማ ከተገጠመው የተወሰደ

የመቃብር ፀጥታ ይስተዋላል። መርፌ መሬት ላይ ቢወድቅ እንኳን ይሰማል። በሕይወት ላይ ማን ይቀልዳል? ነፍስ መጫወቻ አይደለችም። ጥንቃቄ ተወስዷል። አርበኞች የማድፈጫ ምድብ ቦታቸውን ይዘዋል። በጥቂት ሰዓታት ምድር ቀውጢ ትሆናለች። ቢፈልጉ ሰማይ ዝቅ ምድር ከፍ ይበሉ። አድፍጠዋል። ምንም ዓይነት ምድራዊ ኃይል ይምጣ በቅጠልያ አልባሳት በዛፍ ቅርንጫፎች ውስጥ ሰምጠዋል። ከሳር ጋር ተመሳስለዋል። አምባ ጊዮርጊስ የጀግኖች መንደር መሆኗ በተግባር ይረጋገጣል።

ባሁኑ ሰዓት የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ከአስመራ ተነስቶ ዳባት ገብቷል። መረጃ እየሰበሰበ ወደ ፊት ያመራል። አርባ ካሚዮን ሙሉ መጥቷል። ወራሪ ኃይል ወደ አምባ ጊዮርጊስ አቅንቷል። ከኢትዮጵያ አርበኞች እጅ ምሱን ያገኛል። አይጥ ሞቷን ስትሻ ምን እንደምታደርግ አሳምረን አውቀናል። በአምባ ጊዮርጊስ ደም እንደ ጎርፍ ይፈስሳል። የጥይት ዶፍ ይዘንባል። የማይቀር ሁነት እንደማይቀር ይጠበቃል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተጠግቷል። የኢትዮጵያ አርበኞች የውጊያ ሥነ ልቦና ደግሞ አሻቅቧል። በልባቸው ያቅራራሉ። ቃል ድርጊት ይሆናል። ድርጊትም በቃል ይመነዘራል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አሁን በጣም ተቃርቧል። ይህ የአርበኞች የመረጃ ምንጭ ድምፅ ነው። ወራሪው ኃይል በቅርብ ርቀት ይስተዋላል። በደረሰው መረጃ የኢትዮጵያ አርበኞች በአምባ ጊዮርጊስ እንዳደፈጡ አውቋል። ከዚህ በላይ የካሚዮን ጉዞ አያዋጣም። ሁሉም ተዋጊዎች ወረዱ። በአሰራር እርምጃ ከአርበኞች ማድፈጫ እንዲደርሱ ትዕዛዝ ወርዷል። በአሰራር ወደፊት ሂድ! በኢትዮጵያ ቆራጥ አርበኞች ተኩስ የቅድሚያ ተነሳሽነት ተወስዷል። በነፍስ ወከፍ የጦር መሣሪያ ተመርቋል። ድም! ድም! ድም! ድም! የአፀፋ ተኩስ ደግሞ የደመ ነፍስ ድምታን አዘነበው። አርበኞች ከወራሪው ኃይል ዕይታ ውጭ ቀርተዋል። ጦርነቱ ጠንክሮአል። መስከረም 18 ቀን 1931 ዓ.ም መሆኑን አንዘንጋ። ወራሪው ኃይል ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል። ጦርነቱ ቀጥሏል። የኢትዮጵያ አርበኛ አጥቅቷል። ውጊያው አሁንም ተፋፍሟል። ጀግናው ውብነህ ተሰማ በአመራር እርከን ብቻ አልተወሰነም። በውጊያ አርአያነት ግምባር ቀደም ሆኗል። ውብነህ ተሰማ! ለሕይወቱ የማይሳሳ!

የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ባሁኑ ሰዓት በሽሽት እንቅስቃሴ ላይ ይስተዋላል። የኢትዮጵያ አርበኛ እያሳደደ ከትቢያ ጋር ያዋህደዋል። ጀግናው የጀግና ዘር ሀገሩን ለባዕድ ወራሪ አይሰጥም! የጀግኖች ሀገር የኩሩ ሕዝብ ምድር አትደፈርም! ይህ የኢትዮጵያ አርበኞች ድምፅ ነው! ከበጌ ምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት! ከአምባ ጊዮርጊስ የጦር ሜዳ! ባሁኑ ሰዓት ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በኩል የተኩስ ድምፅ አይሰማም። ከሞት የተረፈው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ፈርጥጧል። በርካታ የጣሊያንና የለማዳ ባንዳ ሬሣ ተዝረክርኳል። አንዳንድ ተጎምደው የወደቁ ለማዳ ባንዳዎች አርበኞች እንዲጨርሷቸው በዓይኖቻቸው ይለማመጣሉ። የኢትዮጵያ አርበኞች ግን ጊዜ አልነበራቸውም። ብዙዎቹ ከተማረኩ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ካሚዮኖች ላይ ዕቃዎችን በማራገፍ ሥራ ላይ ተጠምደዋል። ከአገልግሎት ውጭ ከሆኑት ጋር አርባ ካሚዮኖች በጀግኖቹ የኢትዮጵያ አርበኞች ተማርከዋል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ካመጣቸው ካሚዮኖች አንድም አልተመለሰም። ጥቂት አርበኞች ደግሞ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሲፈረጥጥ ያዝረከረከውን የጦር መሳሪያ ሲሰበስቡ ይታያሉ። በጣም ጥቂት አርበኞች ግን አካባቢውን ወጥረው ይዘዋል።

ጀግኖቹ የኢትዮጵያ አርበኞች በማያጠራጥር ሁኔታ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን ደምስሰዋል። ነገር ግን ከማርያም ደብር አካባቢ አዲስ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተንቀሳቀሰ። አርበኞች በውጊያ ላይ ስለቆዩ በትኩስ ጉልበት የመጣውን ኃይል ሊቋቋሙ እንደማይችሉ የውጊያ ወረዳ አዛዦች ገምተዋል። የጀግኖችን ልብ ያላወቁ ከዚህ በላይ ባያስቡ ምን ያስደንቃል? የኢትዮጵያ አርበኞች ግን ዘወትር ወኔአቸው ትኩስ ነው። አሁን ዕብሪተኛው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ወደ አርበኞች የውጊያ መስመር ተጠግቷል። ያለ የሌለ አቅሙን አስተባብሯል። የኢትዮጵያ አርበኞች በከንቱ የሚባክን ጊዜ አልነበራቸውም። ታሪክ ይናገራል። በቅድሚያ ተነሳሽነት ተኩስ ለመክፈት አላቅማሙም። ድም! ድም! ድም! ድም! ቡም! ቡም! ቡም! ቡም! የጦፈ ጦርነት ተቀስቅሷል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የአፀፋ የጥይት ዶፉን አወረደው።

የኢትዮጵያ አርበኞች ከቶም የሚበገሩ አልነበሩም። የአድዋ ጀግኖችን የደም ሕዋስ በደም ሰንቀዋል። ጀግናው አርበኛ ውብነህ ተሰማ በወርቅ ቀለም የተጻፈ ታሪክ ለትውልድ ያወርሳል። ተከታዮቹ በቁርጠኝነቱ ኮርተዋል። በተዋጊነቱ ረክተዋል።

ጦርነቱ ባሁኑ ሰዓት ተጠናክሮ ቀጥሏል። ግን የኃይል ሚዛን ወደ አርበኞች አጋድሏል። በወራሪው ኃይል ላይ ከፍተኛ ሰብዓዊ ጉዳት ይስተዋላል። አሁን አርበኞች አጥቅተዋል። ወራሪው ኃይል እንደ ልማዱ ፈርጥጧል። ድል የአርበኞች ሆኗል። ውብነህ ተሰማ ወገኖቹን አኮራ! የድል ችቦ አበራ! ይህ የኢትዮጵያ አርበኞች ድምፅ ነው! ከበጌምድርና ሰሜን ጠቅላይ ግዛት! ከአምባጊዮርጊስ ጦር ሜዳ!

አርበኛው ውብነህ ተሰማ ‹‹አሞራው›› በሚል የቅፅል ስም ጎልቶ ይታወቃል። የዛሬዎቹ ገገርዎቻችን ጎንደር ሲደርሱ ስለጀግናው ውብነህ ተሰማ ቅፅል ስም ሰምተው ከመካከላቸው አንዱን ‹‹አሞራው›› በማለት ሰይመውት ነበር። ሆኖም ግለሰቡ የትግል ጓዶቹ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ስልጣን ርካብ ከመቆናጠጣቸው ቀድሞ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።

ባሁኑ ሰዓት አሞራው ውብነህ ተሰማ የዘመቻ ዕቅድ በመንደፍ ተግባር ተጠምዷል። ጫን ያለው መጥቷል። 12 ሺህ የሚሆን የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በሙሉ አቅሙ በኢትዮጵያ አርበኞች ላይ ጦርነት ለመክፈት ተዘጋጅቷል። ይህ የአርበኞች የመረጃ ድምፅ ነው! በአርበኛው ውብነህ ተሰማ ዕቅድ መሰረት በየፊናቸው ተከታይ ያበጁ ዕውቅ አርበኞች በአንድ ግንባር ይቆማሉ። የወራሪው የፋሽስት ኢጣሊያ ሰልፈኛ በሰው ኃይል ቢያሻቅብም በአንድነት በተሰለፉ አርበኞች እንደሚደቆስ የዘመቻ ዕቅድ ትንበያ ተቀምጧል። የዕቅዱ ቅየሳ ተጠናቅቋል። አሞራው ውብነህ ተሰማ በኃላፊነት ውጊያውን ይመራል።

የኢትዮጵያ አርበኞች በተጠንቀቅ ቆመዋል። የፋሽስቶችን ደም ተጠምተዋል። ደም የለመዱ በደም ይዋኛሉ። ዕብሪተኞችንና ግፈኞችን በደም መበቀል ተገቢም አስፈላጊም ነው! ተበታትኖ ውጊያ አቅም ይፈታተናል። አንድነት ኃይል ነው! የጠገዴ፤ የወገራ፤ የጃኖራ፤ የመረባና በሌሎች የውጊያ መስመሮች የነበሩ የጦር አበጋዞች የውብነህ ተሰማን የጦርነት ዕቅድ አምነዋል። የድል ተስፋን በተስፋ እንደሚያሳይ አፅድቀዋል። በጥምር አቋም ለድል ተነስተዋል።

የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የኢትዮጵያ አርበኞችን በከፍተኛ ደረጃ ንቋል። የራሱን ልክ ያላወቀ የሰውን ልኬታ ባያውቅ ደግሞ አያስደንቅም። የናቀ ይናቃል። ተግባር በተግባር ይታያል። ዛሬ ጥር 21 ቀን 1930 ዓ.ም. ነው! የአርበኞች የመረጃ ምንጭ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን አሰላለፍ ሰልሎ ተመልሷል። አንድ አንካሳ በልመና ቋንቋ የስለላ ተግባሩን ባግባቡ ተወጥቷል። ለከበባ በአመቺ ቦታና ጊዜ ላይ እንደ ሆነ ይስተዋላል። የአርበኞች ስምሪት ሰዓቱ ደርሷል! የንቅናቄ ትዕዛዝ ወርዷል። አርበኞች በሙሉ የከበባ ምድብ ቦታቸውን ለመያዝ ተንቀሳቅሰዋል። እሳት ማንደድ በጥብቅ ተከልክሏል። መጠራራትም ሆነ በሌላ መልኩ ድምፅ ማሰማት ፈፅሞ አይፈቀድም። ጉዞ ቀጥሏል። የኢትዮጵያ አርበኞች ዳቦ በማር ሊገምጡ ተቃርበዋል። ወዮለት የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል! ተከብቧል! ዙሪያው በጀግኖቹ የኢትዮጵያ አርበኞች ታጥሯል!

ጨለማ ለብርሃን ቦታውን አስረክቧል። ነግቷል። ዛሬ ጥር 22 ቀን 1930 ዓ.ም. ነው! ማን ማንን ይገዛል? ማን ለማን ይገዛል? ከብቦ ያደረው የኢትዮጵያ አርበኞች ኃይል ተኩስ የመክፈት ቅድሚያ ተነሳሽነትን ወስዷል። ያበጠው ይፈንዳ! ድም! ድም! ድም! ድም! በአርበኞች በኩል ባሁኑ ሰዓት ተኩሱ ቀልጧል። የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ግን የአፀፋ ድምፅ አላሰማም! እንዲያውም የአርበኞች የተኩስ ድምፅ እስከዘነበበት ሰዓት ድረስ መከበቡንም እንዳላወቀ ተረጋግጧል። ገና ማለዳ ነው! አሁን ግን መልዕክት ከማዘዣ ጣቢያ ወርዷል። ‹‹ወይዘሮ ሽፍታ መጣች! በአሰራር ግቡ!›› ይህ የገናናው የፋሽስት ኢጣሊያ የምስራቅ አፍሪቃ ቅኝ ግዛት የጎንደር ዙሪያ ጦር ሜዳ ወታደራዊ ማዘዣ ጣቢያ ድምፅ ነው! አንድ! አንድ! አንድ!

ግፈኛው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የኢትዮጵያ አርበኞችን በንቀት የማየት አቋሙን አሁንም አጠናክሮ ይዞታል። የዕብሪት መንፈስ በእጅጉ ተጠናውቶታል። ብዙም አልቆየም። የአፀፋ ተኩስ ተከፈተ። ሁለቱም ወገኖች እሳት ይተፉ ገቡ። ጦርነቱ ተፋፋመ። 12 ሺህ ያህል የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በዘመኑ የዘመነ ዘመናዊ የጦር መሳሪያ እስከ አፍንጫው ታጥቋል! በተጨማሪም አስፈላጊ በሆነ ሰዓት ከሰማይ በአይሮፕላን ቦምብ ለማዝነብ ተሰልፏል። በምድርም ታንክ ማርመስመስ ለፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ከባድ ስራ አይሆንም! ደግሞ ለ‹‹ወይዘሮ ሽፍታ›› ይሄን ያህል ምን መጨነቅ ያስፈልጋል?

ጦርነቱ ቀጥሏል። ከሁለቱም በኩል

ወደ ገፅ 32 ዞሯል

# ‹‹ቃሊቲ››ን. . .

ከገፅ 36 የዞረ

እንዳለ ተሰማ፣ አለሙ አበበ፣ ደበላ ዴንሳ.... ሁሉም እዚህ ዞን ውስጥ ነበሩ፡፡ ሊፈቱ አንድ ቀን ሲቀራቸው ህይወታቸው እንዳለፈ ከተነገረው ከደህንነት ሚኒስትሩ ተስፋዬ ወ/ስላሴ በስተቀር ሌሎቹ ተፈተዋል፡፡ መፈታታቸውም ፖለቲካ መሆኑ ቀርቶ የመለስን መሀሪነት መስበኪያ ሆኗል፡፡ ግና በቃሊቲ መታሰር የሌለባቸው ንፁሃን በብዛት መኖራቸውን ምን እንለው ይሆን?

የሆነ ሆኖ እነዚያን ‹‹ምህረት-የለሽ›› እና ‹‹አስፈሪ›› እንደሆኑ የሚነገርላቸውን የደርግ ባለስልጣናት አግኝቼ ባወራቸው ብዬ ተመኘሁ፡፡ ለገሰ አስፋውን ስለሀውዜን ጭፍጭፋ እና ትግራይን ለህወሓት አስረክበው ስለመጡበት ሁኔታ ባወራቸው፣ ተስፋዬ ወልደስላሴን ደግሞ በአሉ ግርማን የት እንዳደረሱት ብጠይቃቸው፣ ለህወሓትም፣ ለሲ.አይ.ኤም፣ ለኬጂቢም፣ ለሞሳድም... ይሰሩ እንደነበረ ስለሚናፈሰው ጉዳይም አንዳንድ ነገሮችን ቢነገሩኝ ደስታዬን አልችለውም ነበር፡፡ ለፍቅረስላሴ ወግደረስም ቢሆን ብዙ ጥያቄዎች ነበሩኝ፡፡ ሙስና ‹‹ከጥሬ ስጋ እና ውስኪ›› ባላለፈበት በዛ የዋህ ዘመን ባለቤታቸው 25 ኪሎ ግራም ወርቅ ይዘው ቦንቤይ አየር ማረፊያ ተያዙ መባሉ ምን ያህል እውነት እንደሆነ እጠይቃቸው ነበር፡፡ መቼስ ‹‹አለባበስ እንደፍቅረስላሴ ወግደረስ›› የተባለላቸው የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ብዙ የሚያውቁት ምስጢር ሳይኖር አይቀርም፡፡ ‹‹ቀይ ሽብር›› እንዲቆም ስለማድረጋቸው የተነገረላቸውን፣ ሆኖም በቀይ ሽብር የተከሰሱትን ደበላ ዴንሳንም አግኝቼ ከእርሳቸው አንዳንድ ማብራሪያ ባገኝ እልል በቅምጤ ነበር፡፡ በነገራችን ላይ ደርግ የመሰረተው መንግስትም ሆነ ቢሮክራሲው በእጅጉ ውስብስብ እንደነበረ ይነገራል፡፡ ይህ የደርግ መንግስት ከኃይለስላሴም ሆነ ከመለስ መንግስት ሁሉ የበረታ ነው ይባልለት ነበር፡፡ እንዲያውም አንድ ወዳጄ ኢህአዴግ አዲስ አበባ ሲገባ የደርግ መንግስት ከጠበቀው በላይ የተደራጀ እና ጠንካራ እንደነበር መረዳቱ ምን ያህል አስደንግጦት እንደነበረ አውግቶኛል፡፡ በዚህ ሰው አባባል መሰረት በዚያን ጊዜ መንግስት መስርቶ ከማቆም ራስ ዳሽን ተራራን ከቦታው አንስቶ ባሕር መክተት ይቀላል፡፡ ይሄ ውስጥ አወቅ ወዳጄ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊም ህይወቱ ያለፈው አዲስ መንግስት ሲገነባ ነው ብሎ አርድቶኛል፡፡ ዳሩ ሃያ አንድ አመት ቢለፋም ከግብ አላደረሰውም፡፡ ስራው ከባድ ነው መሰለኝ፡፡ ያውም ከዜሮ ሲጀመር፡፡ ያውም ሁሉን የሚጠቀልል...

ለነገሩ መንግስቱ ኃይለማርያም መንግስት ለመመስረት የመለስን ያህል የለፋ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም መንጌ ኃይለስላሴን አውርዶ ሹማምንቶቻቸውን በጥይት ከመፍጀቱ ውጪ የነበረውን መንግስታዊ መዋቅርና ተቋማት አጠናክሮ ነበር ይዞ የቀጠለው፡፡ ከስም ለውጦች እና ከአንዳንድ አብዮታዊ እርምጃዎች (መሬት፣ ሀይማኖት፣ ብሄር...) በቀር፡፡ በንጉሱ እና ቤተሰባቸው ስም ተሰይመው የነበሩ ሆስፒታሎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ አካባቢዎች፣ መንግደች... ወዘተ በአብዮታዊ ስም ከመቀየር ባለፈ ያፈረሰው ነገር አልነበረም፡፡ ምንአልባትም አፄው ከስልጣን በወረዱ ጊዜ ለመንግስቱና ለጓዶቹ እንዲህ ሲሉ መከሯቸው የተባለው ምክር በልቦናቸው አድሮ ይሆናል ‹‹ሁላችሁም ልጆች ናችሁ፤ የሰራችሁት የልጅነት ስራ ነው፤ ስለሀገራችሁ የምታውቁት ነገር የለም፤ ሀገሪቷን እንዳታጠፏት!››

መለስና ኢህአዴግ ጋ ግን ይህ የለም፡፡ መንግስቱንም መማረክ አልቻሉምና የአፄውን ምክር አላስተላለፈላቸውም፡፡ እናም ከሰራዊቱ እስከ ቢሮክራሲው ስሮ ተፈንቅሎ እና ፈርሶ ነው በአዲስ የተመሰረተው፡፡ ጦር ሰራዊት፣ ባህር ኃይል፣ አየር ኃይል፣ አየር ወለድ፣ ፓራ ኮማንዶ፣ እስፓርታ... ማን የቀረ አለ? ህንፃ ኮንስትራክሽን፣ ባህር ትራንዚት፣ አውራ ጎዳና፣ የዩኒቨርስቲ መምህራን.... ይህን ሁሉ እንደአዲስ ለማቆም ሲል ኢህአዴግ እንዲህ ያለ ይመስለኛል ‹‹ኑ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር እንፍጠር፤ በብሔር ብሔረሰቦችም እንሙላት››

የሆነ ሆኖ ከታሳሪዎች እንደሰማሁት ‹‹ዞን አራት›› ለሌሎች ዞኖች የሸራተንን ያህል የቅንጦት ቦታ ነው፡፡ መጨናነቅ የለም፤ ግቢው ንፁህ ነው፤ የተሻለ ላይብረሪ እና ካፍቴሪያ አለው፡፡ ግቢው ውስጥ ዘጠኝ የተለያዩ ቤቶች ቢኖሩም በአጠቃላይ የእስረኛው ቁጥር (እኔ በነበርኩበት ግዜ) አንድ መቶ ሰላሳ አምስት ብቻ ነው፡፡ ተመሳሳይ ስፋት ያለው ዞን ሶስት ግን ከሁለት ሺ የማያንስ እስረኛ እንደሚታጎርበት ታስሮበት የነበረ አንድ እስረኛ አጫውቶኛል፡፡ ቦታው የስቃይ ቦታ መሆኑን የሚያጠናክርልህ ሰሞኑን ከአንድ ዓመት በላይ ታስረው በምህረት የተለቀቁት ስውዲናዊያን ጋዜጠኞች ‹‹የመከራ ቋት›› ሲሉ ቃሊቲን በከፍተኛ ምሬት መግለፃቸው ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ በ2002 ዓ.ም የፋሲካ በአል ዋዜማ የ‹‹ፕሪዝን ፌሎ ሽፕ›› መስራች ፓስተር ዳንኤል ቃሊቲ ብቅ ብለው ብርቱካን ሚደቅሳን ሲጠይቋት በኢቲቪ በተመለከትኩበት ዕለት ስለእስር ቤቱ የሰጡት ምስክርነት ከዚህ የተለየ ነበር፡፡ ፓስተሩ ቃል በቃል ‹‹የእስር ቤቱ ጥራት በአፍሪካ ተወዳዳሪ የለውም›› ነበር ያሉት፡፡ አስታውሳለሁ፤ በእጅጉ አዝኜ ነበር፡፡ በእርግጥ አዝኜ ብቻ ዝም አላልኩም ‹‹ፓስተር ዳንኤል ለቄሳር ወይስ ለኢየሱስ?›› በሚል ርዕስ ትዝብቴን ፍትህ ጋዜጣ ላይ አስፍሬ ነበር፡፡

በአጠቃላይ ዞን አራት ቃሊቲ ከሚገኙ ሁሉም ዞኖች የተሻለ እንደሆነ እስረኞች እያዳነቁና እያጋነኑ ሲናገሩ ሰምቻለሁ፡፡ ወደዚህ ዞን ለመቀየር ያለው መከራም እንዲሁ ከባድ እንደሆነ አስተውያለሁ፡፡ እንዲያውም አንዳንድ እስረኞች ‹‹መታሰሬን›› ችላ ብለው ወደዞን አራት በመላኬ ብቻ ምን ያህል እድለኛ እንደሆንኩ ደጋግመው ነግረውኛል፡፡ በነገራችን ላይ በዚህ ዞን የሚገኙ እስረኞች ተራ ቀማኞች ወይም እንደእኔ ተራ ጋዜጠኞች እንዳይመስሉህ፡፡ አብዛኞቹ በአንድ ወቅት ከፍተኛ የሀገሪቱ ባለስልጣን እና በተለያየ ኃላፊነት ላይ የነበሩ ሲሆን የተቀሩት ደግሞ ከበርቴዎች ናቸውና፡፡

መቼም ቃሊቲ ያለውን እስረኛ ብዛት ላስተዋለ ቦታውን እስር ቤት ከማለት ይልቅ ‹‹መንግስትና ባንዲራ›› የሌለው አነስተኛ ሀገር ማለት ይቀላል፡፡ የእስረኛውን ብዛት ሳይ ከዚህ ቀደም አንድ ወዳጄ ‹‹አሜሪካ ወይም አውሮፓ ሄዷል ብለህ ያሰብከውን ሰው ቃሊቲ ልታገኘው ትችላለህ›› ሲል የነገረኝ ትዝ አለኝ፡፡

እቃዬን ደርድሬ ስጨርስ ከአዳራሹ ወጣሁ፡፡ ግቢ ውስጥ አንድ ወጣት እና አንድ ጎልማሳ ጠረጴዛ ቴኒስ ሲጫወቱ የተወሰኑ ሰዎች ዙሪያውን ቆመው ያያሉ፤ ወይም ለመጫወት ተራ እየጠበቁ ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ አነስተኛ ጠረጴዛ ከበው ዳማ የሚጫወቱ እስረኞችም ይታዩኛል፡፡

በስተግራ በኩል ደግሞ የቴሌው ዶ/ር ተስፋዬ ብሩ እና የአዋሽ ባንኩን አቶ ለይኩን ብርሃኑን ጨምሮ ጥቂት ሰዎች ወንበር ደርድረው ተቀምጠዋል፡፡ እንዳዩኝ የሞቀ ሰላምታ ሰጡኝ፡፡ አይኔን ወደሌላው መለስኩ፡፡ ብቻውን ምድረ ግቢውን ወደሚሽከረከር ሰው፡፡ አዎን! ፀሐይዋ አናት የምትበሳ ጉልበታም ብትሆንም የቤንሻንጉል አስተዳደሪ የነበረው ግዙፉ ያረጋል አይሸሹም በእርምጃ ግቢውን በመዞር ስፖርት እየሰራ ነው፡፡ ያልተመጣጠነው ሰውነቱና እንቅስቃሴው ፈገግ ያሰኛል፡፡

በዚህ ዞን ማን የቀረ አለ? ‹‹አራጣ አበድራችኋል›› ተብለው የተከሰሱትና በቅፅል ስማቸው የሚታወቁት ሞሮኮ፣ አይ.ኤም ኤፍ.... ካፍቴሪያ ውስጥ ቁጭ ብለው ቡና ይጠጣሉ፡፡ አዛውንቱ የአያት ሪል እስቴት መስራች አቶ አያሌው ተሰማም ብቻቸውን ተቀምጠው ፀሐይ ይሞቃሉ፡፡ ከለበሱት ቱታ በላይ ጋቢ ደርበው፣ የሹራብ ባርኔጣም አጥልቀዋል፡፡ ሙቀቱን እንዴት እንደቻሉት ግራ ገብቶኛል፡፡

ይህን ጊዜም ብስል ቀይ እና እድሜያቸው ስልሳዎቹ መጨረሻ የሚጠጋ አንድ ሰው ፊት ለፊቴ መጡና ጥቂት ትክ ብለው አስተዋሉኝ፡፡ እንደዋዛም እንዲህ አሉኝ፡-

‹‹ተመስገን እንተዋወቅ፡፡ መላኩ ተፈራ እባላለሁ፡፡››

‹‹ሻለቃ መላኩ!?....›› በአግራሞት የማረጋገጫ ጥያቄዬን አቀረብኩላቸው፤ ፈገግ ብለው አረጋገጡልኝ፡፡ እርሳቸውም ፍትህ ጋዜጣን አልፎ አልፎ እንደሚያገኙ፣ የእኔን መታሰርም ከውጭ ራዲዮ መስማታቸውን ነገሩኝ፡፡ በደንብ አልሰማኋቸውም፡፡ ሻለቃውን በማግኘቴ የተፈጠረብኝ ጥልቅ ግራሞት አለቀቀኝም፡፡ ስለሰውዬው ብዙ ሰምቻለሁ፤ ብዙ አንብቤአለሁ፡፡ ታዲያ የሁሉም መደምደሚያ ምን ያህል ጨካኝ እንደሆኑ የሚገልፅ ነው፡፡ ሆኖም ከፊት ለፊቴ የቆሙትን አጠር ቀጠን ያሉትን መልከ መልካም ሰው ከተነገረላቸው ታሪክ ጋር ማዛመድ ቸገረኝ፡፡ በአእምሮዬ ውስጥም አንድ ነገር ተመላለሰብኝ፡-

‹‹ሻለቃ መላኩ የእግዜር ታናሽ ወንድም
የዛሬን ማርልኝ ሁለተኛ አልወልድም››

ይህን ያሉት በሻለቃው ጭካኔ በእጅጉ የተማረሩ የጎንደር እናቶች እንደሆኑም ሰምቻለሁ፡፡ እንዲያውም ጎንደር በኢህአዴግ መዳፍ ስር ስትወድቅ፣ ታምራት ላይኔ ይሁን በረከት ስምኦን ዘነጋሁት እንጂ ለዚህ የምሬት ግጥም ‹‹ጎንደር እንዳሻሽ ውለጂ›› የሚል የመልስ ምት በግጥም መስጠታቸውን የኢህዴንን ታሪክ የሚገልፅ መጽሐፍ ላይ አንብቤአለሁ፡፡

እናም የሻለቃው ጭካኔ ወደር እንደሌለው ነው ስሰማ ያደኩት፡፡ ስማቸው ድፍን ጎንደርን ያሸብር እንደነበር ነው የማውቀው፡፡ አብዛኞቹ የብአዴን /ኢህዴን/ መስራቾችም በረሃ የገቡት የፖለቲካ አጀንዳ ኖሯቸው ሳይሆን ከሻለቃው ጭፍጨፋ ለማምለጥ እንደሆነ ይወራል፡፡ እንዲሁም ዛሬ በአሜሪካ ሀገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን መካከል በቁጥር የሚበዙት የጎንደር ተወላጆች መሆናቸውም ከእኚሁ ሻለቃ ለመሸሽ በተደረገ ስደት ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ተደማምረው ነው መሰለኝ እስከዛሬ ድረስ በአእምሮዬ ቀርጬ የያዝኩት የሻለቃው ገፅታ በአካለ-ሥጋ ከፊት ለፊቴ ከቆመው ሰው ጋር አልገጥም አለኝ፡፡ ያውም በብዙ የሚራራቅ፡፡ ግዙፍ ሰውነት፣ እንደመዳፍ የደደረ ከርዳዳ ፀጉር፣ ሞት የሚረጩ ድፍርስ ቀያይ አይኖች፣ በጭካኔ አለት የተገነባ እንደ ድንጋይ የተቸነከረ ፊት፣ ወፋፍራም ደረቅ ከንፈሮች፣ ሠፊ አፍ... በምናቤ ስዬው የኖርኩት የሻለቃ መላኩ ገፅታ ይህ ነበር፡፡ እናም ይህ የፈጠርኩት ምስልና በግላጭ የማየው እውነተኛ ምስል ተጣረሱብኝ፤ ማመሳሰል አቃተኝ፡፡ እኚህን ቀለል ያሉ መልከ ቀና ሰው በአንድ ወቅት ‹‹መግደል ሰለቸኝ›› ብለው የሠው ልጅ ከነነፍሱ ሊማሊሞ ገደል ይጨምሩ ነበር የሚለው ታሪካቸውን አምኖ መቀበሉ ከበደኝ፡፡

(ይቀጥላል)

# አኬልዳማው ፍትህ...

ከ ገፅ 29 የዞረ

በማለት ‹‹ከሌላ›› ሳይሆን ‹‹ከውጭ›› ገንዘብ አትቀበሉ ብሎናል ብለው አቶ ዘመኑ የመሰከሩትን ለመሸፋፈን አሳፋሪ ሙከራ አድርጓል፡፡ በቀጣዩ የሐተታው አንቀፅ ‹‹ከውጭ ገንዘብ አትቀበሉ›› የሚሉት ቃላት በተከሳሽነት ቃሌ ወቅት ብቻ የተሰማ በማስመሰል አድበስብሶ አልፎታል፡፡

ለዚህ ደግሞ ግልፅ ምክንያት አለው፡፡ የግንቦት 7 አባል ሆኜ ‹‹ከውጭ ገንዘብ አትቀበሉ፣›› በማለት በሀገር ውስጥ ያሉ ፓርቲዎችን ልመክር አልችልም፤ ከ/ፍ/ቤ ይህንን ያፈጠጠ ሐቅ ማስተናገድ አልቻለም፤ አይችልምም፡፡ ይህን ቁልፍ ነጥብ እንደምንም ብሎ ወደጐን ገሸሽ ሳያደርግ ጥፋተኛ ልባል አልችልምና፡፡

ስለዚህም፣ እንደአማራጭ የተጠቀመው ስልት፣ አንድ ጊዜ ማኮሰስ ሌላ ጊዜ ደግሞ ፈፅሞ እንደሌለ ማስመሰል ሆኗል፡፡ እውነታው ግን በቃላት ጨዋታ አይድበሰበስም፤ አይሞትም፡፡

8 በጥፋተኝነት ብይን ውስጥ ያሉ ስህተቶች

በብይኑ ግልባጭ ገፅ 57 ላይ በ8ኛው መስመር ላይ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ለኮሜዲ ብቻ በሚሆን ‹‹የሎጂክ አክሮባቲክስ››፣ በመኢዴፓና በእኔ መካከል የነበረውን ውይይት የግንቦት 7 ጋዜጣ (ልሳን) ዜና ሆኖ መገኘቱን አትቷል፡፡ ዐቃቤ ሕግ ግን ጋዜጣውን በተለይ ይህን ድርጊት ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ መሆኑን አንድም ጊዜ ትንፍሽ አላለም፡፡ አገጣጣሚ ፍ/ቤቱ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ፍ/ቤቱ Proactively ወንጀለኛና ማስረጃ አገናኝቷል፡፡

ችግሩ፣ የምንኖረው በኮሜዲና በ‹‹ይሆናል›› ዓለም ሳይሆን፣ የሚዳሰሱና የሚጨበጡ ማስረጃዎች ዋጋ ባላቸው ዓለም ውስጥ መሆኑ ነው፡፡ በዚህ መለኪያ፣ የጋዜጣውን ዜናና የእኔንና የመኢዴፓን ግንኙነት የሚያገናኝ የሚዳስስና የሚጨበጥ ማስረጃ ፈፅሞ የሌለና ሊኖር የማይችል ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ከዚህ ‹‹አክሮባቲክስ›› ያተረፈው ነገር ቢኖር፣ በጭፍንና በግፍ ጥፋተኛ እንዳለኝ የሚዳስስና የሚጨበጥ ማስረጃ በራሱ ላይ ማቅረቡ ብቻ ነው፡፡

9 በጥፋተኝነት ብይን ውስጥ ያሉ ስህተቶች

በብይኑ ግልባጭ በገፅ 57 ላይ በ19ኛው መሥመር ላይ ግንቦት 7 መስከረም 11/2004 ዓ.ም. ዕትሙ፤ ‹‹ኢትዮጵያ ነክ ሰበር ዜና ታላቅ የተቃውሞ ሰልፍ በአዲስ አበባ ተጠራ፤ ሰው በነቂስ እንዲወጣ ለእያንዳንዱ ዜጋ የማስተላለፍ ግዴታ አለብን በማለት አብስሯል፤›› ይላል፡፡ ከ/ፍ/ቤ ይህንን ዜና ለእኔና ለግንቦት 7 ግንኙነት ማስረጃ ነው ብሎታል፡፡

ይህ እንግዲህ አቶ ዘመኑ፣ አቶ አበበ፣ ዶ/ር ነጋሶ፣ አቶ ሙላቱ (የ5ኛ ተከሳሽ 1ኛ መከላከያ ምስክር) ለፍ/ቤቱ በሰጡት ምስክርነት ሊሰረዝ ይገባዋል ብዬ በአንድነት ጽ/ቤትና በጣይቱ ሆቴል የተቃወምሁት ሰልፍ ነው፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት ‹‹ፍትሕ›› ይህን ይመስላል፡፡ አኬልዳማ ፍትህ!

10 በጥፋተኝነት ብይን ውስጥ ያሉ ስህተቶች

በዚሁ በገፅ 57 ላይ፣ በ21ኛው መሥመር ላይ ...‹‹ስለሆነም፣ ተከሳሽ በመከላከያ ማስረጃው ያስረዳው ጭብጥና በተከሳሽነት ቃል የሰጠው ከላይ ከተመለከቱት የዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች፣ በግልፅ ከተመለከቱት ጋር ሲገናዘብ ይህንን የግንቦት 7 ሕዝባዊ እምቢተኝነት ትግል በመተግበር የተፈፀመ መሆኑን ከማስረዳት በቀር ተከላክሏል ለማለት የሚያስችል አይደለም፤›› በማለት ፍ/ቤቱ ደምድሟል፡፡

እንደ ከፍተኛው ፍ/ቤት ትንታኔና ድምዳሜ ከሆነ፣ የሰሜን አፍሪካ ሕዝባዊ ተቃውሞዎችን ያነሳና አርአያ ያደረገ ሁሉ ከግንቦት 7 ጋር ላለው ግንኙነት ማስረጃ ይሆናል፡፡ በዚህ አመክንዮ ‹‹የሰሜን አፍሪካ ሕዝባዊ ተቃውሞዎች ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ይገባዋል›› ለሚለው ሃሳብና ተያያዥነት ያላቸው ትንታኔዎች ግንቦት 7 የፈጠራ ባለቤትነት አለው፡፡ ሀገር ውስጥ ያለነው 80 ሚሊዮን ኢትዮጵያዊያን የኮፒ ራይት ዕዳ አለብን ማለት ነው፡፡

ችግሩ ግንቦት 7ትም ሆነ ሌሎቹ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች አንዲትም ቃል ከመተንፈሳቸው በፊት እኔ ስለሰሜን አፍሪቃ ሕዝባዊ ተቃውሞች በተደጋጋሚ ስፅፍና ቃለምልልስ ስሰጥበት የነበረ ጉዳይ መሆኑ ነው፡፡ የፈጠራ ባለቤትነት የቅድሚያ ጉዳይ ስለሆነ እኔ ሀሳብ አመንጪ ግንቦት 7 አስፈፃሚ ነው የምንሆነው፡፡ ወይ ደግሞ፣ የግንቦት 7 ዋና ስትራቴጂስት ነው የምሆነው፡፡ ጥፋተኝነቴም በግንቦት 7 አባልነት ሳይሆን፣ በግንቦት 7 አመራርነት መሆን ይገባው ነበር፡፡

11 በጥፋተኝነት ብይኑ ውስጥ ያሉ ስህተቶች

በብይኑ ግልባጭ ገፅ 57 ከ26ኛው መስመር አንስቶ እስከ ገፅ 58 8ኛው መሥመር ድረስ ‹‹ነፃ ኢትዮጵያዊ ትውልድ ኮሚቴ›› በሚል ስም በመቋቋም ላይ ስለነበረውና እኔ አባል ስለነበርኩበት ኮሚቴ አትቷል፡፡

1. ኮሚቴው ‹‹የማህበራት አመሠራረትና አደረጃጀት ሕግን ይጥሳል››

2. የኮሚቴውን ምሥረታ በሚመለከት ‹‹የሀሳቡን አመንጪ በተመለከተ የሚጋጭ ነጥቦች መሥክረዋል...››

ይህ ሐተታና ድምዳሜ ደጋግሜ የማነሳውን የሥር ፍርድ ቤትን ጭፍንነት ገላጭ ነው፡፡ የቱ የማህበራት አደረጃጀት ሕግ ነው የተጣሰው? ለምን ይሸፋፈናል? ፍ/ቤቱ በሌላ ወንጀል እንዳልጠየቀ አዝኖ ይሆን? የሀሳቡን አመንጪ በተመለከተስ፣ የት ጋር ነው ከምሥክሮች የሚጋጭ ነጥቦች የተደመጠው? ለምን አይገለፁም?

በዚህ ኮሚቴ ዙሪያ ከሳሽ ምንም ዓይነት ብዥታ እንደሌለው ተጨባጭ ማስረጃ የሚሆነው (በምሥክርነት ጊዜ እንደተገለፀው) በቀሪዎቹ 6 የኮሚቴ አባላት ላይ እንኳን ክስ ሊቀርብ ቀርቶ፣ ፖሊስ ጣቢያ እንኳን ተጠርተው ቃል ያልሰጡ መሆናቸው ነው፡፡ አንዱም ለዐቃቤ ሕግ ምስክር ሆኖ አልቀረበም፡፡ በተቃራኒው፣ 2ቱ የመከላከያ ምስክር ሆነው ቀርበው ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ በላይ ምንድን ነው የሚጠበቅብኝ?

12 በጥፋተኝነት ብይን ውስጥ ያሉ ስህተቶች

በብይኑ ግልባጭ ገፅ 58 ላይ በ12ኛው መሥመር ከ/ፍ/ቤ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ያቀረብኳቸውን ፅሁፎችና ትንታኔዎች ከፀረ-ሽብርተኝነት አዋጅ አንቀጽ 23 መሠረት መዝኗል፡፡ አንቀፅ 23 አምስት ንዑስ አንቀጾችን ያቀፈ ሲሆን፣ የሥር ፍ/ቤት የትኛውን ንዑስ አንቀጽ እንዳጣቀሰ ሸፋፍኖ ለማለፍ ቢሞክርም፤ ከንዑስ 2 ‹‹በተዘዋዋሪ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት ይኖረዋል፤›› የሚለውን እንደተጠቀመበት ግልፅ ነው፡፡ የህጉ መንፈስና ዓላማ ግን፣ ተጨባጭ ማስረጃዎችን (Facts) ጋር የሚዛመድ ሲሆን የሥር ፍ/ቤት ግን የሀሳብ መመሳሰልን ለድርጅት አባልነት ማረጋገጫ መስፈርት አድርጐ ተጠቅሞበታል፡፡ ይህ ትልቅ የሕግ ስህተት ነው፡፡

ይባስ ብሎ ደግሞ፣ ከ/ፍ/ቤ ፅሁፎቹን የመዘነበት መንገድ አስገራሚም፣ አስደንጋጭም እንዲሁም በሶስተኛ ወገን ትዝብት ላይም የሚጥለው ነው፡፡ በአጭሩ እቃኛቸዋለሁ፡፡

1ኛ. ፍ/ቤት መጀመሪያ የመዘነው በአንድነት ጽ/ቤት በተደረገው ሕዝባዊ ስብሰባ ያቀረብሁትን ፅሁፍ ሲሆን፣ ‹‹ትግሉ ወደሰላማዊ ተግባር ይሸጋገር፣›› በሚል ርዕስ ስር የሚገኝ ነው፡፡ በፅሁፍ ውስጥ ‹‹ትግሉ ወደሰላማዊና ሕጋዊ ተግባር ይሸጋገር፣›› የሚለውን የከፍተኛውን ፍ/ቤት ‹‹ሠላማዊና ሕጋዊ ትግሉ ከቃል ወደተግባር መሸጋገር አለበት፤›› ብሏል በማለት የቃላትን ቅደም ተከተል በመቀያየር የፅሁፉን መንፈስና መልእክት ለመለወጥ ሙከራ አድርጓል፡፡ በእኔ ፅሁፍ የተግባሩ ይዘት ‹‹ሠላማዊና ህጋዊ›› መሆን እንዳለበት የተገለፀ ሲሆን፤ የከ/ፍ/ቤ ቋንቋ ግን የተግባሩ ይዘት ምን እንደሆነ አልተገለፀም፡፡

2ኛ. ‹‹ኢትዮጵያ ሕዝባዊ ተቃውሞና የወታደራዊ መንግሥት ጥያቄ፣›› በሚል ርዕስ ሥር እኔ የፃፍኩትና ከ/ፍ/ቤ አገኘሁት ያለው ጭብጥ የቀንና የማታ ያህል ልዩነት ያለው በመሆኑ የእኔ አስተያየትን የሚጠይቅ አይደለም፡፡ ፍ/ቤቱ በፅሁፍ ላይ የሰጠው አስደማሚ ትንታኔ የሚያረጋግጠው ነገር ቢኖር፤ በተደጋጋሚ የሚነሳውን ጭፍንነቱን ነው፡፡

3ኛ. መለስ ዜናዊና የጋዳፊ ውድቀት፤

4ኛ. የታክሲዎች ሥራ ማቆም አንድምታ፤

5ኛ. ሶሪያ፣ አሜሪካ፣ አውሮፓና ኢትዮጵያ፣

6ኛ. ሕዝቡ ሰላማዊ ለውጥ ይፈልጋል (ቃለ ምልልስ)፤

7ኛ. ሶሪያና ኢትዮጵያ፣

በሚሉት ፅሁፎችና ቃለምልልስ ዙሪያ ከ/ፍ/ቤ የሰጠው ትንታኔና ድምዳሜ፤ በመጀመሪያዎቹ 2 ፅሁፎች ዙሪያ ካለው የተለየ አይደለም፡፡

የሚጨመር ነገር ቢኖር፣ እነዚህ ፅሁፎችና ቃለምልልሶች በፀረ-ሽብርተኝነቱ አዋጅ 652/2001 አንቀጽ 23 ለግንቦት 7 አባልነት ማረጋገጫ ሚዛን የሚደፉ ከሆነ፤ ተይዘው ለሕግ የሚቀርቡ በርካታ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎች (ሀገር ውስጥ ያሉ)፣ ጋዜጠኞችና ታዋቂ ግለሰቦች ያሉ መሆናቸውን ነው፤ በእኔ ላይ ያነጣጠረ የSelective Justice ዘመቻ ከሌለ ማለት ነው፡፡ (ፈረንጆችን ጨምሮ)

በመጨረሻም፣ በገፅ 35 የ5ኛ ተከሳሽ፣ አንደኛ መከላከያ ምስክር የነበሩት አቶ ሙላቱ ጣሰው በሰጡት ምስክርነት ‹‹በወቅቱ ውይይቱን ከሚመሩት ግለሰቦች መካከል እስክንድር ነጋ የሚመለከተው አካል ሕዝባዊ፣ ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ለጊዜው መልስ አልሰጠንም፡፡ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎችም በዚህ ላይ ትብብር አላደረጉምና በዚህ ጉዳይ ላይ ብንሰራ መልካም ነው የሚል ሀሳብ ሲያቀርቡ ተከሳሽ ጊዜው ምቹ አይደለም የሚል አስተያየት እንደሰጡ አስታውሳለሁ›› በማለት ለከፍተኛው ፍ/ቤት ገልፀዋል ይላል፡፡

ሆኖም፤ አቶ ሙላቱ የሰጡት ምስክርነት ሰላማዊ ሰልፉን የተቃወመው እስክንድር ነጋ ነው በማለት ነበር፣ ከ/ፍ/ቤ የማይወዳት ነጥብ፡፡ ይህንንም፣ ከኦዲዮ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ማጠቃለያ

የቱ ጋር ነው የግንቦት 7 አባል ወይም ተባባሪ መሆኔ የተረጋገጠው? በሰው ማስረጃ ነውን? በሰነድ? ከኢ-ሜሌ የተገኘ ነገር ይኖር ይሆን? ወይስ በስልክ ጠለፋ የተገኘ ነገር አለ? የከፍተኛው ፍርድ ቤት ብይንን አንብቤ መልስ ላገኝ አልቻልኩም፡፡ የቀረቡት ማስረጃዎችማ እንዲያውም በተቃራኒ ፈፅሞ የግንቦት 7ትም ሆነ ውጭ ያሉት ሌሎች ድርጅቶች አባል ልሆን እንደማልችል አመላካቾች ናቸው፤ ያውም ከጥርጣሬ በላይ፡፡

በግፍ በሐሰት ተወንጅያለሁ፡፡ ይባስ ብሎም፣ በግፍ ጥፋተኛ ተብዬ 18 ዓመታት ተፈርዶብኛል፡፡ በመንግስት ውስጥ Check and Balance የለም ወይ?

ይግባኝ ባይ የምጠይቀው የፍትህ ልመና

የተከበረውን ጠቅላይ ፍርድ ቤት የምጠይቀው፡-

1. ንፁህ ስለሆንኩኝ፣

2. የቀረበብኝ ማስረጃ የሌለ በመሆኑ፣

3. ፍርድ ቤቶችን የሚያህሉ የተከበሩ ተቋማት የበቀል፣ የአፈናና የጭቆና መድረክ መሆን ስለሌለባቸው በነፃ እንድለቀቅ ነው፡፡

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር
እስክንድር ነጋ
የማይነበብ ፊርማ



# ‹‹ቃሊቲ››ን በጨረፍታ

## ክፍል ሶስት

*በተመስገን ደሳለኝ*

ድንግርግር አለኝ፡፡ ይህን ጊዜ ዕቃዬን ይዞልኝ የመጣው ወጣት በስሜ ጠርቶ ‹‹አይዞህ›› አለኝ፡፡ ድጋሚ መገረም ጫረብኝ፡፡ ስሜን አልነገርኩትም፡፡ የፖሊስ ኃላፊውም እንዳልነገረው አስታውሳለሁ፡፡ ታዲያ እንዴት አወቀኝ? ‹‹ታውቀኛለህ እንዴ?›› ስል ጠየኩት፡፡ እንደሚያውቀኝ ራሱን ወደላይና ታች አወዛውዞ ገለፀልኝ፡፡ እዚያ ግቢው ውስጥ በሚገኝ ሳይብረሪ ፍትህ ጋዜጣ አልፎ አልፎ እንደሚመጣ እኔንም አንገቴ ላይ በጠመጠምኩት ሻርፕ በቀላሉ ሲለየኝ እንደቻለ አጫወተኝ፡፡

ስድስት ቀናትን ስላሳለፍኩበት የ‹‹ቃሊቲ እስር ቤት›› የእስረኞች አቀባበልና አያያዝ ምን መልክ እንዳለው ጨርፌ ማሳየት ከጀመርኩ ይህ ፅሁፍ ሶስተኛው ክፍል ላይ መድረሴን ያበስራል፡፡ ከዚህ በኋላም ለአንድ ሁለት ክፍል ያህል በትርክቱ ላይ መቆየቴ አይቀሬ ነው፡፡ …እነሆም የዛሬውን ትርክት ባለፈው አስራ አምስት ቀን ካቆምኩበት እቀጥላለሁ፡፡

…ምጥጥ ያለ ፊት እና መካከለኛ ቁመት ያለው የፖሊስ ኃላፊ ባልተለመደ ሰዓት (ለስንቅ እና ለመፀዳጃ ቤት ከሚከፈትበት ጊዜ በተለየ) ጨለማ ቤቷን ከተሸጎረችበት ጓጉንቸር ነፃ አውጥቶ ወለል አደረጋት፡፡ ለስለስ ያለ ሙቀት አዘል የፀሐይ ጨረር ክፍሏን ወገግ አደራግት፡፡ ‹‹ዕቃህን ይዘህ ውጣ›› የሚለው ትዕዛዙም በጎርናና ድምፅ ተከተለ፡፡ ከተጋደምኩበት ፍራሽ ላይ ተነስቼ አስተዋልኩት፡፡ ፊቱ ላይ የሚነበብ ነገር የለም፡፡ መፈታቴ እንዳልሆነ ስሜቴ ነግሮኛል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በቆየበት ጊዜያት የዘመናት የአልጋ ቁራኞችን ‹‹አልጋህን ይዘህ ተነሳ!›› ይል ነበር፡፡ በእርግጥ ይህ ቃል እንደፖሊሱ ‹‹ትዕዛዝ›› ሳይሆን፣ ፈውስ እንደነበረ የቆየ ንባቤ ያስታውሰኛል፡፡ ህይወት አልባ መሳይ ፊት ያለው የፖሊስ ኃላፊ እቃዬን ይዤ እንድወጣ እየጠበቀኝ ነው፡፡ ፍራሽ፣ ብርድ ልብስ፣ አንሶላ፣ ጥቂት ቅያሪ ልብሶች፣ አንድ የምሳ ዕቃ… አንድ ላይ ሸክፌ ለመሸከም ተወለካከፍኩ፡፡ ስሰበስበው ተበተነ፡፡ መልሼ ሰበሰብኩት፡፡ ‹‹ተከተለኝ››፡፡ ‹‹የት ድረስ?›› ብዬ ልጠይቀው አሰብኩና ተውኩት፡፡ ተከተልኩት፡፡ ከነበርንበት ግቢ ወጥተን ሌላ ግቢ ውስጥ ገባን፤ ግቢው ከአቅሙ በላይ በሰው ጎርፍ ተጥለቅልቋል፡፡ ጫጫታው ከደራ ገበያ ጫጫታ ይበረታል፡፡ ግቢውን አቋርጠን ሌላ ግቢ ውስጥ ገባን፡፡ ኋላ ላይ እንደሰማሁት ያ ጫጫታም ግቢ ከአሰቃቂው የቃሊቲ የእስር ዞኖች ሁሉ የከፋ እንደሆነ የሚነገርለት ዝነኛው ‹‹ዞን ሶስት›› ነው፡፡ (በነገራችን ላይ ቃሊቲ ውስጡ በዘጠኝ ዞኖች የተከፋፈለ ነው፡፡ በክልል ቢከፋፍሉት ኖሮ ከስርዓቱ ርዕዮተ-አለም ጋር የተመጣጠነ ትርጓሜ ይኖረው ነበር፡፡ ታላቋን ኢትዮጵያ በዘጠኝ ቁርጥራጭ ክልሎች ከከፋፈለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ርዕዮተ ዓለም አኳያ ማለቴ ነው)

ዞን ሶስትን እንደማሳለጫ ተጠቅመን ጥቂት ከተጓዝን በኋላ በመጠኑም ቢሆን እስከአሁን ካየኋቸው ግቢዎች ሁሉ አይንን የሚማርክ ግቢ በር ላይ ደረስን፡፡ በዕውቀቱ ስዩም ‹‹አንኳኩ ይከፈትላችኋል፤ ስትገቡም ሌላ በር ይጠብቃችኋል›› እንዲል በአንዱ በር ስንገባ፣ ሌላ በር ሲጠብቀን፤ ስንተላለፍበት-ሌላ በር ስናገኝ… ስንገባ-ስንወጣ… ነው ከእዚህ አይነ-ግቡ ግቢ የደረስነው፡፡ ግቢው ስፋቱ አነስተኛ ቢሆንም ከነዋሪዎቹ (ከእስረኞቹ) አኳያ ሲታይ ተመጣጣኝ ነው፡፡ በእንክብካቤ የተያዙ አበቦችም አሉት፡፡ እንደዞን ሶስት ጫጫታ የለበትም፡፡ እየመራ ያመጣኝ የፖሊስ ኃላፊ ከግቢው በር ላይ ‹‹በስራ-ፈትነት›› የቆመ አንድ እስረኛን ‹‹አግዘው!›› አለና እቃዬን እንዲቀበለኝ አደረገ፡፡ ይህ ትዕዛዝ ያመላከተኝ ነገር የፖሊሱን ደግነት ሳይሆን ኢየሱስ መስቀል ተሸክሞ እየወደቀና እየተነሳ መጓዙ ያሰለቻቸውና ከዋና ጉዳያቸው ያዘገያቸው የሮማ ወታደሮች በመንገድ ላይ ያገኙትን ስምኦን የተባለ የ‹‹ቀሬና›› ሰውን ‹‹አግዘው›› ብለው ጉዞአቸውን እንዳፈጠኑት አይነት ትብብር ነው፡፡ ፖሊሱም ‹‹አግዘው›› ብሎ ተቻኩሎ ወደአዲሱ ማረፊያዬ በቶሎ አስገብቶኝ ሊመለስ ተጣድፏል፡፡ …ምን አጣድፎት ይሆን? የት ለመሄድ ይሆን እንዲህ የቸኮለው? የሚል ሃሳብ ሽው አለብኝ፡፡ ብቻ አግዘው የተባለው ወጣት እስረኛ እንደከተፎ ሰራተኛ እንዲያ ለሸክም አስቸገሮኝ የነበረውን ዕቃ በቀላሉ ለብቻው ጠቅልሎ ያዘው ‹‹ተው ተካፍለን እንያዝ›› ብለውም በጅ አልል አለ፡፡ ደክሞኝ ስለነበር ጥቂት አግደርድሬ ተውኩለት፡፡ ይህን ጊዜ ፖሊሱ አጠገባችን እንደቆሙ እስከአሁን ወላላስተዋልኳቸው አንድ ጠና ያሉ ሰው ዞሮ ‹‹አዲስ እስረኛ ነው፤ አልጋ ስጡት!›› አላቸውና ፊቱን አዙሮ ሄደ፡፡ የተረከቡኝ ሰውዬ ጥቂት ካስተዋሉኝ በኋላ ‹‹እስር ቤት እንኳን ደህና መጣህ ባይባልም ይህ ግቢ እዚህ ካሉት ሌሎች ዞኖች በእጅጉ የተሻለ ነው፤ እንተዋወቅ እኔ እስረኛ ብሆንም የግቢው እስረኞች ኃላፊ ነኝ፡፡ ሻምበል በጋሻው አታላይ እባላለሁ›› አሉና እጃቸውን ዘረጉልኝ፡፡

በመደነቅ አስተዋልኳቸው፡፡ ሻምበል በጋሻውን በስም እና በታሪክ በደንብ አውቃቸዋለሁ፡፡ የደርግ አባል እና የቀድሞ መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣን ነበሩ፡፡ የሚገርም ነው፡፡ መንግስቱ ኃይለማርያምም ታስሮ ቢሆን ኖሮ ዛሬ በእንዲህ አይነት ሁኔታ አገኘው ነበር፡፡ ባገኘው ብዙ የምጠይቀው ጥያቄዎች ነበሩኝ፡፡ መሪዎቻችን ከስልጣን ከወረዱ በኋላ ቢያንስ ለታሪክ እና ለተተኪው ትውልድ ትምህርት ይሆን ዘንድ ሊመልሱልን የሚገቡ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ አልታደልንም፡፡ እነሱም ለመመለስ ዕድሉን አላገኙም፡፡ መንግስቱ ኃ/ማርያም ከጥያቄም ከፍርድም አምልጦ ዚምባብዌ ከሚባል ሀገር ተደብቋል፡፡ መለስ ዜናዊም ቢሆን በተፈጥሮ ሞት ህይወቱ አልፏል፡፡ ሀገሪቷም ገና ‹‹ከሀዘኗ›› አልተላቀቀችም፡፡ ሁኔታው ሁሉ በህይወት ሳለ አካባቢውን በመበጥበጥ ለያዥ ለገናዥ አስቸጋሪ የነበረው ልጅ ህይወቱ ካለፈ በኋላ እናቱ ‹‹የሞተው ልጄ አንገቱ ረጅም ነበር›› አለች እንደተባለው አይነት ውዳሴ-ከንቱ ኢትዮጵያ ሀገሬም አምባገነን መሪዋን ‹‹ባለራዕዩ፣ ታላቁ፣ መልዐኩ፣ አዛኙ፣ ርህሩህ፣ ሰው ወዳዱ፣ ዴሞክራቱ፣ የልማት አርበኛው…›› ወዘተርፈ የሚል ማንቆለጳጳሻ ካባ ደርባ ‹‹እያለቀሰች›› ነው፡፡ እንግዲህ የሞተ ሰው አንዴ ሄዷል-አይመለስም፡፡ እኛ ወደ እርሱ እንሄዳለን እንጂ እሱ ዳግም ተመልሶ ወደኛ አይመጣም፡፡ …እናም በአፀደ-ህይወት ያለነው እንነጋገር፡፡

…አዛውንቱ በጋሻው አታላይ እየመሩ መጋዘን ወደ መሰለ ሰቀላ ቤት ይዘውኝ ገቡ፡፡ ቤቱ ሰፊ ነው፡፡ በልማት ስም ከፈረሰው የቀበሌያችን አዳራሽም ይሰፋል፡፡ በድርብርብ አልጋዎች ከመሞላቱ የተነሳ እልም ያለ ዋሻ-ባለብዙ ሸንቁሮች መስሏል፡፡ ሆኖም አልተጨናነቀም፡፡ ሻምበሉ ወደአንድ ባዶ አልጋ እየጠቆሙኝ ‹‹የላይኛው የአንተ ነው፡፡ ወደፊት አልጋ ሲለቀቅ ከስር እንቀይርልሃለን፡፡ እቃህን ከላይ መስቀል ትችላለህ፡፡ መልካም ቆይታ ይሁንልህ›› አሉና ተሰናብተውኝ ሄዱ፡፡

ድንግርግር አለኝ፡፡ ይህን ጊዜ ዕቃዬን ይዞልኝ የመጣው ወጣት በስሜ ጠርቶ ‹‹አይዞህ›› አለኝ፡፡ ድጋሚ መገረም ጫረብኝ፡፡ ስሜን አልነገርኩትም፡፡ የፖሊስ ኃላፊውም እንዳልነገረው አስታውሳለሁ፡፡ ታዲያ እንዴት አወቀኝ? ‹‹ታውቀኛለህ እንዴ?›› ስል ጠየኩት፡፡ እንደሚያውቀኝ ራሱን ወደላይና ታች አወዛውዞ ገለፀልኝ፡፡ እዚያ ግቢው ውስጥ በሚገኝ ላይብረሪ ፍትህ ጋዜጣ አልፎ አልፎ እንደሚመጣ እኔንም አንገቴ ላይ በጠመጠምኩት ሻርፕ በቀላሉ ሊለየኝ እንደቻለ አጫወተኝ፡፡ አያያዘናም ትላንትና በአሜሪካ እና በጀርመን ድምፅ ራዲዮ ቤተሰቦቼ እና የስራ ባልደረቦቼ ከታሰርኩ ጀምሮ አይተውኝ እንደማያውቁ፣ የት እንደደረስኩ ባለማወቃቸውም ስጋት ላይ መውደቃቸውን ሲናገሩ መስማቱን ጨምሮ ነገረኝ፡፡ በመጨረሻም ለስንብት ሰላምታ እጁን እየዘረጋልኝ እርሱም እዚሁ ክፍል እንደታሰረና ከምሳ በኋላ እንደምንገናኝ ቀጠሮ አስይዞኝ ሄደ፡፡ በዚህ አጋጣሚ ከመጀመሪያው የዕስር ቤት ደባሌ ጋር መተዋወቄ እንደሆነ ገባኝ፡፡ ባዶው አልጋ ላይ ፍራሼን ዘረጋሁበትና የያዙኩትን ዕቃ ደረደርኩ፡፡

እየተረኩልህ ያለሁት ግቢ ‹‹ዞን አራት›› ይባላል፡፡ የደርግ እስረኞች የታሰሩበት ነው፡፡ በእርግጥ አመቱ መጀመሪያ አካባቢ አብዛኞቹ ባለስልጣናት በምህረት ተለቀዋል፡፡ ፍሰሃ ደስታ፣ ፍቅረስላሴ ወግደረስ፣ ለገሰ አስፋው፣ ተስፋዬ ወ/ስላሴ፣

ወደ ገፅ 34 ዞሯል



addistimes2005@gmail.com